

የንግድ ህግ

ለቅድመ ስራ ስልጠና ሰልጣኞች የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል

በፌዴራል ፍትህ አካላት
ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል
የተዘጋጀ የካቲት/2001 ዓ.ም

ማውጫ

መግቢያ

1. **የንግድ ህግና ህገ-መንግስት** 6
   የንግድ ስራ ከህገ-መንግስቱና ሌሎች አዋጆች አንፃር 6
   ከፍ/ብሄር ህጉ አንፃር 8
2. **የንግድ መደብር** 9
   ስለ ንግድ መደብር በጠቅላላ 9
   የንግድ መደብር የሚቋቋምባቸው መብቶች 10
   ደንበኛ ገብያተኛ 10
   ተገቢ ያልሆነ ውድድር 11
   የአእምሮ ንብረትና ህገመንግስቱ……14
   የፊጠራ ስራ 15
   ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ 24
   የቅጅና ተዛማጅ መብቶች 26
   የንግድ ምልክት 33
   በንግድ መደብር ላይ የሚደረግ የዋስትና መያዣ 40

የመወያያ

ነጥቦች……**44**

3. **የንግድ ማህበራት** 45
   ስለ ንግድ ማህበራት በጠቅላላ 45
   የሽርካ ማህበር 48
   የሽርካ ማህበር ኣጠቃላይ ገፅታ 48
   የኣባላት መብቶችና ግዴታዎች 51
   የማህበሩ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት 52
   እሽሙር ማህበር 53
   ኣክስዬንና ሃላፊነቱ የተ.የግ.ማህበር 55
   የኣክስዬን ማህበር ምስረታ 56
   ኣጠቃላይ ይዘት 57
   የኣክስዬን ማህበር ጥቅምና ጉዳት 57
   የማህበራቱ መፍረስ 58
   ሒሳብ ማጣራት 63

የመወያያ

ነጥቦች.....66

4. **የኢንሹራንስ ውል ህግ** 67

ስለኢንሹራንስ ውል በጠቅላላ.....67

የኢንሹራንስ ውል አመሰራረት.....68

የኢንሹራንስ መሰረታዊ መርሆች.....72

የጉዳት ካሳ መሰረተ ሐሳብ 72

የኢንሹራንስ ውል ለመግባት የሚያስችል ጥቅም.....74

መዳረግ 77

መዋጮ 78

ቀራቢ ምክንያት.....79

አርቦን 83

መሸሸግና የሐሰት መግለጫ.....89

አደጋ ከኢንሹራንስ አንፃር.....91

ስለአደጋ በጠቅላላ.....91

መግለጫ የመስጠትና የማስታወቅ ግዴታ.....93

የመወያያ ነጥቦች.....96

5. **የማጓጓዣ ውል ህግ**.....98

ስለማጓጓዣ ውል በጠቅላላ.....98

የየብስ ማጓጓዣ 99

የአጓዡ ካሳ የመክፈል ሃላፊነት.....102

የሚከፈለው የጉዳት ካሳ 103

የአየር ማጓጓዣ 104

የአጓዥ ሃላፊነት.....105

የአጓዥ የተወሰነ ሃላፊነት.....107

የባህር ማጓጓዣ 109

ስለባህር ማጓጓዣ በጠቅላላ.....109

ቢል ኦፍ ሌዲንግ.....110

የአጓዥ ሃላፊነት.....113

5.4.4 **የሃላፊነት ወሰን**.....115

5.4.5 **ስለ ይርጋ** 116

የመወያያ

ነጥቦች……118

6. **የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች ህግ**.....119

ስለሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በጠቅላላ.....119

ሰነድን በቅን ልቦና መያዝ 121

የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶ ዋናገፅታዎች……122

የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መቃወምያዎች.....125

የመተላለፍያ መንገዶች……131

የንግድ ወረቀቶች.....133

የሃዋላ ወረቀት 133

የተስፋ ሰነድ 136.....

ቼክ 137

የመንገድ ቼክ 143

6.6.5 **በሰነዶች መካከል ያለ**

ልዩነትናተመሳሳይነት……..144

የመወያያ

ነጥቦች……145

7. **የመክሰር ህግ** 146

የመክሰር ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጥ 146

የመክሰር ህጉ ተፈፃሚነት.....150

የሽርካ ማህበር መክሰር……151

የኣክስዮን ማህበር መክሰር 153

የመወያያ

ነጥቦች……157

ማጠቃለያ.....158

ማጣቀሻዎች 159

መግቢያ

የሰው ልጅ ትርፍ ወደ ማምረት ከተሸጋገረበት ጥንታዊ ስልጣኔ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመነ ግሎባላይዘሽን ከግዜ ወደ ጊዜ እድገት እያሳየ የመጣው ንግድ ዓለምችን አሁን ያላትን ገፅታ እንድትይዝ ካደረጉት አበይት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ይህንን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በአንድ አከባቢ በሚኖሩ ህዝብች መካከል ከሚደረግ የዕቃ በዕቃ ልውውጥ አንስቶ የሰው ልጆች ባህር ኣቋርጠውና ረጅም ተጉዞው ከጫፍ እስከ ጫፍ የዘለቀ የንግድና ቴክኖሎጂ ምጥቀት አሁን ያለው ትውልድ የተሻለ ሂወት እንዲኖረውና የዓለም ማህበረ ሰብ በአንድ መንደር የመኖር ያክል እንዲቀራረብ ኣድርጎታል፡፡ ኢትዮጵያ ከጥንታዊቷ ግብፅ፣ ግሪክ፣ ፐርሺያ፣ ህንድና ቻይና የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስነብባሉ፡፡ ከዚህ ጥንታዊ የንግድ ግንኙነቷ አንፃር ሲታይ እምብዛም በተፈለገው ደረጃ ኣድጓል ለማለት የማያስደፍረው የኢትዮጵያ ንግድ በመጠኑም ቢሆን ግን ለዓለማችን ከተበረከተው የእድገት ትሩፋት ተካፋይ ለመሆን ግን ችሏል ፡፡ ለዚህም ነው ከ1923 የብድርና ባንክ አሰራር ህግ በ1933 የንግድ ማህበራት አዋጅና የመክሰር ህግ አዋጅ ከወጣበት ጊዜና ጎላም በ1952 ዓ.ም የንግድ ህጉ ከታወጀ በኃላ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ከዓለም ጋር ለመነገድ በርካታ ጥረቶችን ስታደርግ የምትስተዋለው፡፡ ይህ የዓመታት ጥረት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህ የንግዱ ዘርፍ በነፃ ገበያ መርህ እንዲሄድ በመደረጉ መንግስት የነደፈው ግብርና መር ኢንዱስትሪያዊ ልማት ፖሊሲና ስትራተጂን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችሉና የንግድ ግንኙነቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

የዚህ በንግድ ህግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ርእሰ ዙርያ የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል ዓላማም ሰልጣኞች በከፍተኛ ትምህርት ቆይታቸው ያገኙትን እውቀት፣ ክህሎች እና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በማስፋትና በማነፅ ይህን በመሳርያነት ተጠቅመው የሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታን በማጠናከሩ ሂደት ተገቢውን ፍትህ ለተልጋዩ ህ/ሰብ በመስጠት በመላ አገሪቱ መልካም አስተዳደርን በማሰፈን ጠንካራ የፍትህ ስርዓት እንዲገነቡ ለማስቻል ነው፡፡

የሞጁሉ አዘገጃጀትና ይዘት በተመለከተ በተዘጋጀው ስርዓተ ትምህርት መሰረት የንግድ ህገና ህገ-መንግስት፣ የንግድ መደብር (መድብል)፣ የንግድ ማህበራት፣ የኢንሹራንስ ህግ፣ የማጓጓዣ ውል ፣ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና ስለመክሰር በሚሉ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ

የተመሰረት ሆኖ በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ከህግ ኣተረጓጎምና ኣተገባበር ጋር ተያይዘው ሊነሱ የሚችሉ ጉዳዬችን በተለይ ደግሞ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት በኃላ በወጡ የተለያዩ ኣዋጆ ዙርያ ሰፋ ያለ ማብራርያ በሚሰጥ መልኩና በእያንዳንዱ ርእሰ መፀረሻ የመወያያ ነጥቦች በማንሳት ለውይይት መነሻ ሊሆን በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው።

ስለዚህ ሰልጣኞች ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት መውጣት በኃላ የህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ፖሊሲንና ስትራተጅን መሰረት በማድረግ የወጡ ከንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ኣዋጆች በሚገባ ተረድተው ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ኣገሪቱ እየተከተለችው ያለውን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት መሰረት በማድረግ ለፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበት የልማት ስትራተጂ ስኬታማነት እንዲያገለግል በሚያስችል መልኩ እንዲተገበር በማድረግ ሙያዊና ዜግነታዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል። የዚህ ሞጁል ዋና መልእክትም በእውቀት፣ ክህሎትና ዲሞክራሲ ኣስተሳሰብ የታነፀ የፍትህ ኣካላት ባለሙያ በመሆን የተገልጋዩን ህብረተሰብ የፍትህ ጥም በማርካት ህዝባዊ ኣመኔታን ለማግኘት ኣበክረን ልንሰራ ይገባል የሚል ነው።

መልካም ንባብ!!

1. የንግድ ህግና ህግ -መንግስቱ

1. 1 የንግድ ስራ ከህገ-መንግስቱና ሌሎች አዋጆች አንፃር፤

ንግድ በዓለማችን ካሉ ቀደምት ግንኙነቶች አንዱና ዋናው የእድገት መሳርያ ነው፡፡ በንግድ ህግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ላይ አንዳንድ ሃሳቦችን አንስቶ በማየቱ ሂደት ለአጠቃላይ ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ንግድ ምንድን ነው? ከሚለው ብንጀምር ንግድ ማለት “ A regularly carried out and organized production exchange of goods and services under taken with the objective of earning profit and acquiring wealth through the satisfaction of human needs.” የሚል ፍች የሚሰጠው ነው፡፡ የንግድ ስራ ሽቀጦችና አገልግሎቶች ለዋጋ ሲባል መሸጥ ማስተላለፍና መለወጥ፣ ሁሌ የሚከናወን የግብይት ሂደት ያለው፣ ለትርፍ ሲባል የሚከናወን የመሆንና እርግጠኛነት የሌለው የመክሰርና የትርፉማነት ውጤት ሊያስከትል የሚችል ባህሪ ያለው መሆኑ ከመገለጫዎቹ ባህሪያት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የንግዱን ክፍል ኢኮኖሚ በሁለት ማለትም የኢንዱስትሪና የሽቀጥ አገልግሎቶች ክፍለ ኢኮኖሚ በሚል ክፍሎ ማየት የሚቻል ቢሆንም ሁሉም ዘርፎች ለአንድ አገር ኢኮኖሚ እድገት ያላቸው አስተዋፅኦ እጅግ የላቀ ነው፡፡ የሽቀጦችና አገልግሎቶች ዘርፉን (commerce) ወስደን የተመለከትን እንደሆነ በዚህ ዙርያ ያሉ ክፍለ ኢኮኖሚዎች እንደ ባንክ፣ መጓጓዣ፣ ኢንሹራንስ፣ የማሸግ ስራና የማስታወቅያ ስራዎች ናቸው፡፡ የአገራችንን ንግድ ህግና ህገ-መንግስት ስናይ የሰው ልጆች የዕለተ ተዕለት ኑሮን ለማሻሻልና ብሎም ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ ለመራመድ የሚያስችል የኢኮኖሚ ግንኙነት እንደመሆኑ መጠን እነዚህን ግንኙነቶች በተፈለገው መንገድ ለማስኬድ የግድ በህግ መገዛትን ስለሚጠይቅ በአገራችንም በ1952 ዓ.ም የንግድ ህግ ወጥቶ እንሆ ለግማሽ ምእተ ዓመት ገደማ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 43(1) ላይ “የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ህዝብች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡” በማለት የደነገገውን መሰረት በማድረግ ለአገሪቱ የልማት እድገት ይበጃሉ ያላቸውን በርካታ ህጎች በማውጣት የንግድና የኢንቨስትመንት ስራው ከማንኛውም ግዜ በበለጠ አጠናክሮ እየሰራበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ህግ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ከመውጣቱ በፊትና ዓለም አሁን ወደ ደረሰችበት ዘመነ ግሎባላይዘሽን ከመድረሷ በፊት የወጣ በመሆኑ የራሱ የሆኑ እጥረቶች

ሊኖሩት እንደሚችሉ ለመገመት ባይከብድም ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አኳያ ሲታይ መንግስት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 51 (2)፣ 51 (9)፣ 55 (ሐ) እና 77 (6) ፣ 91 (3) እና 89(1) የተደነገጉ መንግስታዊና ሃገራዊ ግዴታዎቹን ለመወጣት በንግዱ ዘርፍ በን/ህ/ቁ 86-114 የህግ ሽፋን አግኝቶ ለዓመታት እየተሰራበት ከቆየው ህግ በተጨማሪ ከህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች አዋጆች እንደ አዋጅ ቁጥር 67/89 በማውጣትና በየጊዜው በአዋጅ ቁጥር 171/91፣ 328/95፣ 87/95፣ 95/96 እና 376/96 በማሻሻል ይህን በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ እንደ ደንብ ቁጥር 13/89 እና ሌሎች በማውጣት የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ስርዓት ባለው መንገድ እንዲመራና አገሪቱ ከዚህ ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን በማድረግ ላይ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአገራችን ያለውን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የሚመራበትን የውድድር ስርዓት ቀደም ሲል በን/ህ/ቁ 30-134 ባሉ ድንጋጌዎች የህግ ሽፋን ተሰጥቶት የነበረው ያልተገባ ውድድር (Unfair competition) ዘርዘር ባለና ከህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ኣገራዊና አህጉራዊ የእድገት ደረጃን ባገናዘበ መልኩ ዓላማው ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋነትና ማህበራዊ ደህንነት ለማስፈን እና በነጋዴዎች መካከል የሚደረጉትን ፀረ-ውድድር የሆኑ ተግባራት በመቆጣጠር ለውድድር ኣመቺነት ያለው ስርዓት መገንባት መሰረት በማድረግ ኣዋጅ ቁጥር 329/95 በማውጣት የግብይት ስርዓቱ በህግ እንዲገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

እንዲሁም በን/ህ/ቁ 127(መ)፣ 148፣ 149 የተወሰነ ሽፋን ተሰጥቷቸው የነበሩትን የፈጠራና የቅጅ ግዙፍነት የሌላቸው የንግድ መደብር መብቶች አሁን አገራችን ከደረሰችበት የእድገት ደረጃና እነዚህ መብቶች ለዜጎች ካላቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆን በመነሳት ኣዋጅ ቁጥር 123/87 የፈጠራ፣ አስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪ ንድፍ ህግን በማስፈር ለመብቱ ሰፊ የህግ ሽፋን በመስጠት ዜጎች ከዘርፉ ተጠቃሚ በማድረግ ላይና የቅጅ መብትን ደግሞ በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ኣዋጅ ቁጥር 410/97 በማውጣት ንግድ ህጉና በፍታብሄር ህጉ ከ1647 – 1674 ቁጥር ተሰጥቷቸው ከነበረው ሽፋን በእጅጉ የተሻለና ሰፊ የመብት ጥበቃ በሚሰጥ መልኩ አዲስ ህግ ወጥቶ እንዲሰራበትና ከን/ህ/ቁ 140-141 የተወሰነ ሽፋን ተሰጥቶት የነበረውን የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ሰፊ የህግ ሽፋን እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ የንግድ ህጉ በቁጥር 179 ያለውን የንግድ መደብር በዋስትና መያዝና መመዝገባ ጉዳይ አሁን ካለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፈጣንነት ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ባንኮች በዋስትና የሰጡትን ገንዘብ ቶሎ ሰብስበው ለሌላው ማበደር እንዲችሉ የምዝገባ ስርዓቱ በአዲስ ህግ እንዲገዛ ኣስፈላጊ በመሆኑ ኣዋጅ ቁጥር 98/90 ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የመክሰር ህግን መሰረት ባደረገ መልኩ በንግድ ህጉ 5ኛ መፅሐፍ ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ የባንኮችን ጉዳይ የሚመለከት ኣዋጅ ቁጥር 592/2000 እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 25/92 እንዲወጣ በማድረግ በርካታ ስራዎችን በመስራት ላየ ይገኛል፤፤ ለአንድ አገር የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት የደም ስር

የሆነው የማንገንጥ ዘርፍም ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትን መሰረት በማድረግ በርካታ ሕጎች እንደ ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 468/97 የኢትዮያ የኣቬሽን ሴኩሪቲ አዋጅ ቁጥር 432/97፣ በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የወጣ አዋጅ ቁጥር 31/88 በማውጣት በህገ-መንግስቱ በግልፅ የሰፈሩትን የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ላይ ይገኛል።

1.2 ከፍ/ብሄር ህግ አንፃር፤

ህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 41(1) "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደርያው የመረጠውን ስራ የመስራት መበት አለው።" በማለት የዜጎችን መብት በግልፅ የሚደነግግ በመሆኑና አንቀፅ 41(2) የህንን በሚያጠናክር መልኩ "ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደርያውን፣ ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው" በማለት የሚደነግግ በመሆኑ አንድ ኢትዮጵያዊ/ት በንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ በመሰማራት ነግደው የመኖር መብት ህገ-መንስታዊ መብታቸው መሆኑን በግልፅ ያስረዳል። ይህ ህገ-መንግስታዊ መብት ከፍ/ብሄር ህጋችን አንፃር ሲታይም ፍ/ህ/ቁ 16 የመስራት ነፃነትን መሰረት በማድረግ በፍ/ህ/ቁ 16(1) ላይ "ማንም ሰው ሁሉ የሞያ፣ ስራውን ወይም የእረፍት ግዜዎቹን በሚመለከተው ረገድ መልካም ነው ብሎ በገዛ ኣሳቡ የመረጠውን ስራ ለማካሄድ ነፃነት ኣለው።" ሲል በፍ/ብ/ህ/ቁ 16)2) ላይ ደግሞ "ይህንን ነፃነቱን ሊቀንሱበት የሚችሉት ምክንያቶች የሌለውን ሰው መብት፣ መልካም ባህልና ህጎችን የማክበር ግዴታዎች ብቻ ናቸው" በማለት ስለሚደነግግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትና ፍ/ብሄር ህግ መካከል አንድነት ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ሆኖም ግን በንግድ የመተዳደር ህገ መንግስታዊ መብት ከፍታብሄር ህጉ አንፃር ሲታይ በሁለት መንገዶች ማለትም በፈቃደኛነትና(voluntary restrain) በግድ (compulsory restrain) መብቱ ሊገደብ የሚችልበት ሁኔታ አለ ። በፈቃደኝነት መብትን ለመገደብ የሚቻለው ልክ በፍ/ብ/ቁ 16(3) ላይ እንደተደነገገው "ማንኛውም ሰው ሁሉ ይህን የመስራት ነፃነቱን በመቀነስ አንድ የተወሰነ ስራ ብቻ ለማካሄድ ወይም አንድ ስራ ላለመስራት የገባው የውል ግዴታ ሁሉ ተገቢ ጥቅም መኖሩን ካላረጋገጠ በስተቀር ሊፀናበት አይችልም" የሚለውን መሰረት በማድረግ ነው ።ይሄውም አንድ ሰው በህገ-መንግስቱ የተረጋገጠለትን በንግድ የመተዳደር መብቱን በፈቃዱ ሊተው የሚቻለው በን/ህ/ቁ 158 መሰረት የንግድ መደብር በሚሸጥበት ጊዜ ከሸጠበት ቀን አንስቶ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ተመሳሳይ የስራ ዓይነትና በተሸጠው የንግድ ቤት አከባቢ ለገዢው ጉዳት የሚያደርስ የውድድር ስራ መስራትን ስለሚከለክልና ይህን ከተላለፈ በን/ህ/ቁ 131 ተጠያቂ ሲለሚሆን በመብቱ ለመገልገል በን/ህ/ቁ 22 ያለውን ግዴታ ማክበር ስለሚጠበቅበት በህገ-መንግስቱ የተጠበቀለት መብቱን በራሱ ፈቃድ (voluntary restrain) በስምምነት እንዲተዉ የሚገደዱበት ሁኔታ ይኖራል።

ማንኛውም ሰው በፈለገው የንግድ መስክ ተሰማርቶ ንግድን ለማካሄድ እንደሚችል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 41(1) (2) በግልፅ ቢደነግግም በህገ-መንግስቱም ሆነ በሌሎች ህጎች እንደሚታየው እነዚህ መብቶች ያለገደብ የተሰጡ አይደሉም፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል አንዳንድ መብቶች ሊገደቡ እንደሚችሉ ሁሉ በፈለጉት መስክ በንግድ የመተዳደር መብትም አስገዳጅ ገደቦች (compulsory restraints) ያለቡት ለመሆኑ ከ/ን/ህ/ቁ 11-26 ባሉ ድንጋጌዎች ገደቦች ተበጅተውለታል፡፡ ለምሳሌ አንድ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወይም 18 ዓመት ያልሞላው ሰው ፍ/ብ/ህ/ቁ 288 በሚደነግገው መሰረት ካልሆነ በስተቀር የንግድ ስራን ማካሄድ አይችልም፡፡ ስለዚህ በንግድ የመተዳደር መብት ህገ-መንግስታዊ መብት ነው ቢባልም ያለ ህጋዊ ገደብ የተሰጠ መብት ላለመሆኑ ን/ህ/ቁ 27ን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 652 እና 461(ሐ) ጋር በማዛመድ ካየነው ይህ መብት ከህገ- የመነጨ ገደቦች ያለቡት ለመሆኑ መገንዘብ እንችላለን፡፡

የንግድ ህግ፣ የፍታብሄር ህግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ያላቸውን ግንኙነት እስካሁን ባየነው መልኩ የሚገለፅ ሆኖ የንግድ ህጉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትን መሰረት በማድረግ ከወጣው የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ አንፃር ሲታይ ያለው ገፅታስ ምን ይመስላል? ብለን የተመለከትን እንደሆነ እንደሚታወቀው አገራችን የምትከተለው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ መሰረት ተደርጎ የሚወሰደው የሰው ጉልበትና ጥሬ ሃበት የሚተዳደረው በሸቀጦች ወይም በአገለግሎት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በከተሞች አከባቢ በሚከናወን የአነስተኛ ጥቃቅን ተቋሞችና ለካፒታል ቆጣቢ መካከለኛና ታላላቅ ተቋሞች ትኩረት በሚሰጥ የከተማ ልማት ስትራተጅም ጭምር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን ያለው የንግድ ህግ ሲመረመር አገራችን እየተከተለችው ያለውን ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተቀረፀና ይህን ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት የማረጋገጥ ጉዞ በሚያግዝ መልኩ የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ በማጎልበት ሂደት ለሚከሰቱ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ኣለመግባባቶች ለመፍታት በእጅጉ የሚቸገርና በርካታ ህጎች በተሟላ መልኩ ይዟል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ንግድ ህግ ሲነሳ ቀደም ሲል በኮድ መልክ የወጣውን የ1952 ዓ.ም የንግድ ህግን ብቻ ሳይሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትን መሰረት በማድረግ ከንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በርካታ ሕጎችንም ጭምር ስለሆነ አነዚህን በሚገባ ተገንዝበን በስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ አገራችን ለተያያዘችው ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማረጋገጡ ሂደት ውጤታማነት እንዲያገላግሉ አበክረን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

2. <u>የንግድ መደብር (መድብል)</u>

2.1. ስለንግድ መደብር በጠቅላላ

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ "የንግድ መደብር (Business) ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም ከተለመደው አባባል ወጣ ባለ መልኩ ነው። ን/ህ/ቁ 124 "የንግድ መደበር (መድብል) የሚባለው አንድ ግዙፍነት የሌለው በን/ህ/ቁ 5 ለተጠቀሱት የንግድ ስራዎች ዓይነት ለሆነው ላንድ ስራ ማካሄጃ የተዘጋጁ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ሁሉ ናቸው።" በማለት ትርጉም መስጠቱ የትርጉሙ ግዙፍነት የሌለው አባባል እንደመልካም ስም፣ የቅጅ መብት፣ የፓተንት መብትን የሚያመላክት ሲሆን ግዙፍነት ያላቸው የሚለው አባባል ደግሞ እንደ ወንበርና ጠረጴዛ የመሳሰሉትን ተንቀሳቃሽ ግዙፍነት ያላቸውን የሚያካትት ነው። የአማርኛው ቅጅ የንግድ መደብር ሲል እንደ ሱቅ፣ ንግድ የሚካሄድበትን ስፍራና መጋዘንን ያመለክታል። ከዚህ አባባል ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች ቋሚ የመነገጃ ስፍራ እንደ ሱቅና መጋዘን የሌላቸው ሰዎች የንግድ መደብር (Business) የላቸውም ሊባሉ ይችላሉን? የሚል እና ህጉ የሚንቀሳቀሱ ሲል ግዙፍነት የሌላቸውን ንብረቶች ነው ወይስ ግዙፍነት ያላቸውን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችንም ያጠቃልላል? የሚሉ ናቸው። በነዚህ ጥያቄዎች ዙርያ የአዘጋጁ አስተያየት የንግድ መደበር (Business) ነው ወይም አይደለም ብሎ ለማለት ጉዳዩ መታየት ያለበት በንብረቶቹ ስብሰብነት ሳይሆን የተሰበሰቡት ለንግድ ስራ ነው ወይስ አይደለም ከሚል መነሻ መሆን ይኖርበታል የሚል ነው። ስለዚህ ግዙፍነት ያለው ይሁን የሌለው የሚንቀሳቀስ ንብረት በን/ህ/ቁ 5 ያሉትን የንግድ ስራዎች ለማከናወን እስከ ተገለገልንበት ድረስ የንግድ መደብር (Business) ተብሎ መወሰድ ይኖርበታል።

2.2. የንግድ መደብር የሚቋቋመባቸው ነገሮች (Elements of Business)

ቀደም ሲል እንዳየነው የንግድ መደብር ግዙፍነት ያለው ወይም ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሊሆን ይችላል። ግዙፍነት ከሌላቸው መብቶች ጥቂቶቹን ወስደን የተመለከትን እንደሆነ የንግድ መደብር የሚባለው እንደ ደንበኛ የሆኑ ገብያተኞች (good will)፣ የንግድ ስም(trade name)፣ የሚነገድበት የተለየ የንግድ የማስታወቅያ ሰሌዳ፣ የንግድ ስራ የሚከናወንባቸው ቤቶች የማከራየት መብት፣ የቅጅ መብት፣ ፓተንትና የንግድ ምልክት መብትና ሌሎች መብቶችን ያካተተ ሊሆን ይችላል።

2.2.1. ደንበኛ ገብያተኛ (Good will)

የደንበኛ ገብያተኛ (good will) ትርጉም ፡-

Lord Eldon የተባሉ ተመራማሪ "The good will …is nothing more than the probability that the old customer will resort to old place. በማለት የተረጎሙት ሲሆን

Lord Machanghten

> *Good will the very sap and life of the business, with out which the business would, yield little or no profit. It is the whole advantage what ever if may be of reputation and connection of*

firm. This may have been built up by years of honest work or gained by lavish expenditure of money.

በማለት ተርጉመውታል፡፡ ከነዚህ ትርጓሜዎች መገንዘብ የሚቻለው የአንድ ንግድ መደብር ደንበኛ ገብያተኛ (good will) ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሆኖ በን/ህ/ቁ 130 እንደተገለፀው ደንበኛ ገብያተኛ ለማግኘት በነጋዴውና በሰዎስተኛ ወገን መካከል በተፈጠረ መልካም ግኑኝነት የሚመሰረት ነው፡፡ ለዚህም አንድ ፀሃፊ "good 'will is the result of good' operation of the business organization and is extent depends up on good operation, good handling of customers, quality production, trust and confidence of third parties on the given business organization or trader." በማለት ገልፀውታል፡፡ ስለዚህ ደንበኛ ገብያተኛ (good will) እንደሁሉም የሚንቀሳቀሱ ግዙፍነት የሌላቸው መብቶች የህግ ጥበቃ የተሰጠው በመሆኑ መብቱ በሚጣስበት ጊዜ በዚህ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ወገን በፍ/ብሄር ከውል ውጭ በሆነ ሃላፊነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 2057፣ 2059 በወንጀል ደግሞ በወንጀል ህግ ቁጥር 719 በመክሰስ መብትን ማስከበር የሚያስችል የህግ ጥበቃ የተሰጠው መብት ነው፡፡

2.2.2. ተገቢ ያልሆነ ውድድር (Unfair competition)

- የንግድ አሰራር ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንፃር ስንመለከተው ኣዋጅ ቁጥር 329/95 አገራችን ከምትከተለው ኣጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖ'ሊሲና ስትራተጂ ጋር በተጣጠመ መልኩና የህገ-መንግስቱን አንቀፅ 89(2) "መንግስት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል እድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት" የሚለውን መሰረት በማድረግ የወጣ ሲሆን ለዚህም በኣዋጁ መግቢያ ላይ የተጠቀሱትን
    - የንግዱ ስራ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖ'ሊሲ መሰረት ተገቢውን ኣሰራር ተከትሎ መካሄድ ስላለበት፤
    - ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋነትንና ማህበራዊ ደህንነትን ለማስፈን እና በነጋዴው መካከል የሚደረጉትን ፀረ-ውድድር የሆነ ተግባራት በመቆጣጠር ለውድድር ኣመቺነት ያለው ስርዓት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤
    - መሰረታዊ የሆነ የአንዳንድ የንግድ ዕቃዎች አገልግሎቶች ላይ እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ዋጋውን መቆጣጠርና ስርጭቱንም ስርዓት በማስያዝ ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሰራር ለመዘርጋት ኣልሞ የወጣ ኣዋጅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የዚህ አዋጅ ይዘት የነጋዴውን ማህበረሰብ ጥቅምንና የሌላውን የሸማች ማህበረሰብ ጥቅሞች አጣጥሞና ስርዓት ባለው መንገድ ጤናማ የኢኮኖሚ ውድድር በአገሪቱ እንዲሰፍን ሁኔታዎችን በማመቻቸት አገራችን እየተከተለችው ላለው የሰላም የልማትና የዲሞክራሲያዊ

ስርዓት ግንባታ የንግዱ ዘርፍ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በማስቻል ህዝብ በየደረጃው የልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ እንዲወጣ የተደረገ ህግ መሆኑን ለመገንዘብ ኣያዳግትም፡፡

ተገቢ ያልሆነ ውድድር በንግድ ህጉ ከቁጥር 130-134 ባሉ ድንጋጌዎች ፍ/ብ/ህ/ቁ 2057 ሽፋን ተሰጥቶት የቆዳ ቢሆንም አሁን አገራችን እየተከተለችው ካለው ገበያ ተኮር የልማት ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣምና የነፃ ገበያ መርህን መሰረት ያደረገ የገበያ ውድድርን የሚመራ የንግድ አሰራር አዋጅ ቁጥር 329/95 ከወጣ ወዲህ ተገቢ ያልሆነ ውድድር በዋናነት መገዛት ያለበት በዚህ አዋጅ ነው፡፡
ወደ አዋጁ ዝርዝር ይዘት ከመግባታችን በፊት ተገቢ ያልሆነ ውድድር ማለት ምን ማለት እንደሆነና ድርጊቱ የሚገለፅባቸውን መንገዶች ስንመለከት አንድ Haines የተባለ ፀሃፊ

> *Unfair competition is use or simulation by one person of names, symbols or devices of a business rival in such a manner as is calculated to deceive and cause the public to trade with the first, when they intend to and would otherwise have traded with the second.*

በማለት የተረጎመው ሲሆን የተገቢ ያልሆነ ውድድር መገለጫዎች ደግሞ፡-

- ሐሰተኛና አሳሳች ወሬዎችን ከዋጋ፣ ምርት፣ ባህሪና የተመረተበት ቦታና አመራረት ማሰራጨት፡፡
- የማስተዋወቅ ስራን ተጠቅሞ የሸቀጦች የተሳሳተ መረጃ ማሰራጨት፡፡
- የተጭበረበረ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም፣ የምርት መግለጫ (Product labeling) እና ማሸግያዎችን(packing) መጠቀም፡፡
- የተሳሳተ (የተጭበረበረ) ደረሰኝ ማቅረብ፣ ሚስጢር መበተን ለምሳሌ እንደ ሳይንሳዊ፣ ቴክኒካዊ አመራረት፣ የንግድ መረጃ ማቅረብ ያሉ መግለጫዎች ያሉት ነው፡፡

በንግድ ህጉ ያሉ ድንጋጌዎች በግልፅ በአዋጅ ቁጥር 329/95 የተሻሩ ባለመሆናቸው በስራ ላይ ልናውላቸው የምንችል መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአዋጁ ዓላማ በአንቀፅ 3 ላይ ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆነ የንግድ ስራዎች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ለማድረግ እና በንግድ ፅቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦትና ስርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጅቶችን በመከላለልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ በመሆኑ በርካታ ከአደረጃጀትና አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚችሉ ድንጋጌዎች ያሉት ቢሆንም አንዳንድ የአዋጁን አንቀፆች ስንዳሰስ የአዋጁ አንቀፅ 6(1) በድብቅ መስማማትን ስለማያካትት የራሱ የሆነ ውሱንነት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህም የአዋጁ አንቀፅ 6(2) በተወሰነ ደረጃ

- ዋጋን በጋራ የመወሰን ስምምነት፣
- የገበያ ዋጋን ለመወሰን በሽርክና ለመጫረት የሚደረግ ስምምነት፣
- ገበያን ወይም ደንበኞችን መመደብ የመከፋፈል ስምምነት፣
- የምርትና ሽያጭ ኮታ ምደባ ስምምነት፣
- ላለመሸጥ፣ አገልግሎት ላለመስጠትና ላለመደራደር በህብረት አቋም መያዝን እንደ ህገ-ወጥ ድርጊት ስለሚወሰድ ድብቅ አሰራርን በተሰነ ደረጃ ያካተተ ቢሆንም ይህ አድራጎት በድብቅ ሲደረግ ነው ወይስ በግልፅ በአደባባይ እንደዚህ ብሎ መቅረብን ነው እንደ ህገ-ወጥ ድርጊት የሚወሰደው? ለሚለው ህጉ እምብዛም ግልፅ መልስ የሚሰጥ አይደለም፡፡

ገበያን በበላይነት አለአግባብ ስለመጠቀም የሚደነግገው አንቀፅ 11 ገበያ በበላይነት አለአግባብ መጠቀም ምን ማለት እንደሆነ በትርጉም ክፍሉ ባለመተርጎሙ በአፈፃፀም ላይ ችግር የሚፈጥርና ለትርጉም የተጋለጠ መሆኑ እንደተጠበቀ የአዋጁ አንቀፅ 11(2) (ሀ) እና 11(2) (ቀ) ግራ የሚጋቡ የሚችሉ ናቸው፤፤ አንቀፅ 11(2) (ሀ)

“በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተገቢ ያልሆነና እጅግ የናረ ወይም የወረደ የመሸጫ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ መጠበቅ ወይም አቅርቦትን መገደብ ወይም ሌላውን ከንግድ ስራ ለማገድና ላለማስገባት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ስራ መስራት” ሲል አንቀፅ 11(2) (ቀ) ደግሞ ‘ተገቢ ውድድር እንዳይኖር ለማድረግየማምረቻ ወጪን በማይሸፍን ዋጋ መሸጥ፤፤” ይላል፡፡

የነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት ገበያን በበላይነት አለአግባብ ስለመጠቀም (abuse of dominance) ሳይሆን የሚናገሩት አንዱ ሌላውን ስለመዋጥ (Predatory pricing) የሚናገሩ በመሆናቸው ግልፅነት ይጎድላቸዋል፡፡

ሌላው የአዋጁ ይዘት ችግር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው ያላግባብ ከመወዳደር ውጭ ስለሆነ ሁኔታ የሚደነግገው ነው፡፡

አንቀፅ 10(2) (ሸ)

> በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱትን ዕቃዎች ለማጥፋት ወይም ለመጉዳት ወይም በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ያለውን ማንኛውንም የንግድ ክፍል ለመገደብ ወይም በምኖፖል ለመያዝ በማሰብ የነዚህ ዓይነት እቃዎች በተሰሩበት አገር ዋና ገበያዎች ከሚሸጡበት የገበያ ዋጋ ወይም የጅምላ ዋጋ ባነሰ ዋጋ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት፡፡

የሚለው የህጉ ሃይለ ቃልና ይዘት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስለመወዳደር (Unfair competition) ዙርያ የሚያጠነጥን ሳይሆን ምርትን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ስለማስገባት (damping) ላይ በመሆኑ ለአፈፃፀም የሚያስቸግር ይዘት ያለው ድንጋጌ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 20 እና 21 ስለዕቃዎች ዋጋ ማመላከትና ስለ የንግድ ዕቃዎች መግለጫ (Labels of goods) የሚደነግጉ በመሆናቸው ይዘታቸው ያላግባብ ከመወዳደር ጋር የሚሄድ ብቻ ኣይደለም፡፡ የአዋጁ ይዘት ሁለት ገፅታዎች እንዲኖሩትና ከውድድር ጋር ተያያዥነት ያላቸውና ከውድድር ጋር ተያያዝነት የሌላቸው (non-competition issues) ለመለየት በሚያስችግር መልኩ የተቀረፀ በመሆኑ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙርያ ክርክር ሲነሳ መንስኤውንና የክርክሩን ይዘት ለይቶ በማውጣት ህጉ 'commercial competition issue' ላይ ብቻ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ከነዚህ እጥረቶች በመለስ ሌላው እንደ ጥንቻሬ የሚታየው ግን በአዋጁ የተደነገጉትን ህጎች መጣስ ሁለት ዓይነት እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ መሆኑ ነው፤፤

1. አስተዳደራዊ እርምጃ በአንቀፅ 25 መሰረት
   - ኣቤቱታ የቀረበበትን ድርጊት እንዲታገድ፣ እንዲስተካከል ወይም ጨርሶ እንዲቋረጥ ማድረግ፡-
   - የንግድ ፍቃዱን ማገድ ወይም ጨርሶ መሰረዝ
   - የተጎጂውን የመወዳደር አቅም በነበረበት ለመመለስ የሚያስችል ተገቢ እርምጃ መውሰድ
   - የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ዕቃዎች በሆኑ ጊዜ ዕቃዎቹ እንዲያዙና እንዲሸጡ በማድረግ ከሽያጭ በተገኘው ገቢ ላይ ለሽያጩ ሂደት የወጣውን ወጪ ተቀናሽ ሆኖ ቀሪው ለባለቤቱ እንዲመለስለት ማድረግ ሲሆኑ ይህም በሚሆንበት ጊዜ ባለቤቱ ወለድ ወይም ሌሎች ክፍያዎችን መጠየቅ የማይችልበት አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ይቻላል፡፡
2. በአዋጁ አንቀፅ 27 በተደነገገው መሰረት የቅጣት ኣወሳሰን ስርዓትን ተከትሎ በአንቀፅ 26 መሰረት የቅጣት ውሳኔ መስጠት ሲሆን በዚህም መሰረት የሚሰጠው ቅጣት
   - በአማራጭ የአጥፊውን ጠቅላላ ንብረት ዋጋ እስከ አስር በመቶ ወይም የአጥፊውን ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ እስከ አስራ አምስት በመቶ ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጫ፣
   - በተከለከለው ማንኛውም ተግባር ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የማንኛውም ግለሰብ ተባባሪነት መኖር ከተረጋገጠ ጥፋት ባደረገው ሰው ላይ ከብር 5,000.00 (አምስት ሺ) እስከ 50,000.00 (ሃምሳ ሺ) ብር ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ያልተገባ ውድድር ግለሰብንም ሆነ የአገር ኢኮኖሚ ልማት ፀር በመሆኑ ይህንን ህግ በስራ ላይ በምናውልበት ጊዜ የግለሰብ ኪስ በማደለብ የአገሪቱን ልማት ከሚገድል ስግብግ ነጋዴ ህዝቡንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሚታደግና ልማታዊ ባለሃብቱን በሚያጠናክር መንገድ መሆን እንዳለበት ልንገነዘብ ይገባል፡፡

2.2. 3 የአእምሮ ንብረትና ህግ መንግስቱ

የአእምሮ ንብረት ከድሮ ጀምሮ ሮማውያን የግለሰብ መብት (personal right) እና ግዙፍ መብት (real right) በሚል ከሚመድቧቸው የንብረት መብቶች በተጨማሪ ለየት ያለ መብት ሲሆን ስያሜውን በተመለከተ የተለያዩ ፀሓፍት የተለያየ አጠራር ሲጠቀሙ ይስተዋላል:: ለዚህም አንዳንዶቹ ግዙፍነት የሌለው መብት (incorporeal right) ሌሎቹ ደግሞ የአእምሮ ንብረት (intellectual property) በማለት ይጠሩታል:: ይህ አጠራር ምንነቱን የሚቀይር ባለመሆኑ በይዘቱ አንድ ነው :: የአእምሮ ንብረት መብት ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሲሆን አገሮች ይህን የንብረት መብት ከሚከተሉት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲ በመነሳት በህግ-መንግስታቸውና ከዚያ በታች ባሉ ህጐቻቸው ጥበቃ በመሰጠት በልማት መሳርያነት ሲገለገሉበት የሚገኝ የንብረት መብት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት ለአእምሮ ንብረት የተሰጠው የህግ ማእቀፍ ስንመለከት በአንቀፅ 51(19) ላይ "የፈጠራና የድርሰት መብቶችን ይፈቅዳል፣ ይጠብቃል" ሲል መንግስት ለአእምሮ ንብረት መብት መከበር የሚኖረውን ሃላፊነት መሰረት በማድረግ ሲደነግግ በአንቀፅ77(5) ላይ ደግሞ "የፈጠራና የኪነጥበብ መብቶችን ያስጠብቃል" በማለት ይደነግግል፡፡ ከነዚህ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በአገራችን ኪነ ጥበብ፣ ድርሰትና የቴክኖሎጂ እድገት ከፍ እንዲል በማድረግ ዜጐች በአገሪቱ ማሕበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥና እድገት ላይ ያላቸውን ሚና ከወትሮው በተሻለ መንገድ እንዲጫወቱ በማስቻል በሰፊው የልማት ተሳታፊና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የማድረግ ዓላማ ያለው መሆኑ ነው፡፡

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የህግ-መንግስት ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የአእምሮ ንብረት መብት በፈጠራ (patent) እና በኪነ-ጥበብ ስራ ወይም ድርሰት (copy right) ብቻ የታጠረ የንብረት መብት ነውን? የሚል ሲሆን የአእምሮ ንብረት መብት ከፈጠራ መብት (patent) እና የድርሰትና ወይም የኪነ ጥበብ ንብረት መብት(copy right) በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ንድፍ (Industrial design)፣ የንግድ ምልክትና (Trade marks)፣ የእፅዋት አዳቃዮች መብት(plant breeders right) እና ሌሎች በርካታ መብቶችን የሚያካትት በመሆኑ የህግ-መንግስቱ ህጋዊ ሽፋን ጠበብ ያለ ነው ብሎ መረዳት የሚቻል ቢሆንም የነዚህ መብቶች ጥበቃ ከህግ-መንግስቱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመነጨ ሌሎች ህጐች የህግ ሽፋንና የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብቶች ጥበቃ የተደረገላቸው በመሆኑ የዜጐች መብቶች ለአደጋ የተጋለጡበት ሁኔታ በአገሪቱ የፍትህ ስርዓት የለም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ መንግስትም በህግ-መንግስቱ አንቀፅ 89(1) መሰረት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሃገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበት መንገድ የመቀየስ ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ ይህን ህገ-መንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ አዋጆችን አውጥቶ ከማንኛውም ግዜ በበለጠ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ የሚሰጥ አሰራርና አደረጃጀት ዘርግቶ ለዘላቂ ልማት ስትራቴጂ ስኬትና በዚ መስክ ሊገኝ የሚችለውን እድገት ለማስመዝገብ ከፍተኛ ስራ

በመስራት ላይ ነው፡፡ ይህ መብት በተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት በተሰጣቸው የንግድ መደብሮች ሊያገዝ የሚችል መብት ስለመሆኑ በንግድ ህጉና ሌሎች አዋጆች ተደንግጎ የምናገኘው ነው፤፤ በመሆኑም የአእምሮ ንብረት መብት መረጋገጥና አለመረጋገጥ በአንድ አገር ማህበረ-ኢኮኖሚና ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያለው ፋይዳን መሰረት በማድረግ የህግ ሽፋን የሚሰጠው የንብረት መብት እንደመሆኑ መጠን በፍትህ አካላት ዘንድም በየጊዜው የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች በአግባቡ ለማስተናገድ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 13(1) የተጣለባቸውን ህገ-መንግስቱን የማክበር እና የማስከበር ግዴታቸውን ሊወጡ የሚያስችል ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

2.2.4 የፈጠራ ስራ (patent)

ቀደም ሲል በን/ህ/ቁ 127(መ) የህግ ሽፋን ተሰጥቶት የነበራው የፈጠራ ስራ አሁን ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በወጣው አዋጅም እውቅና የተሰጠው ነው፤፤ የአእምሮ ንብረት ጥበቃ ስርዓት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማስቻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 123/1987 በአንቀፅ 2(5) ላይ "ፓተንት ማለት የፈጣ ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን የፈጠራ ስራውን ከአንድ ምርት ወይም የምርት ሂደት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡" በማለት ሲተረጉመው በአንቀፅ 2(3) ላይ ደግሞ " ፈጠራ ማለት በቴክኖሎጂ መሰክ ለአንድ የተወሰነ ችግር ተግባራዊ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የፈጠራ ሰራተኛ ሃሳብ ነው " በማለት የፈጠራን ምንነት ይገልፃል፡፡

እውቁ Wikipedia, the free encyclopedia በድረ ገፁ ላይ የፈጠራ ስራን (patent) እምብዛም በአዋጁ ከተሰጠው ትርጉም ባልተለየ መልኩ እንዲህ ሲል ተረጉሞታል፡፡

> *The term patent usually refers to a right granted to any one who invents or discovers process, machine, article of manufacture, or composition of matters, or any new and useful improvement there of.*

ከነዚህ የተቀራረቡ ትርጓሜዎች መረዳት የሚቻለው የፈጠራ መብት (patent right) የሚመነጨው አንድ ሰው በአእምሮው ከሚፈጥረው አዲስና ጠቃሚ ምርት ወይም ግኝትና አዲስ ባይሆንም በሌላ ሰው ፈጠራ ተሰርቶ በስራ ላይ የቆየን ነገር በማሻሻል የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችለው ተጨማሪ የፈጠራ ስራ በማከልና በማሻሻል እንደሆነ ነው፡፡ የአዋጁ ተፈፃሚነት ለንግድ መደብርም እንደሆነ ከአዋጁ አንቀፅ 2(7) " ሰው' ማለት የተፈጥሮ ሰውወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው" ከሚለው መረዳት ስለሚቻል የፈጠራ ስራ እንደ አንድ የንግድ መደብር ግዙፍነት የሌለው መብት በዚህ ዕሁፍ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፤፤ በመርህ ደረጃ የፈጠራ መብት አዲስ በመፍጠር ወይም ያለውን በማሻሻል ሊገኝ የሚችል የአእምሮ ንብረት መብት እንደሆነ መግንዘብ ቢቻልም የአገራችንን ህግ በምናይበት ጊዜ ግን የዚህ ዓይነት መብት የሚሰጠው በአዋጁ አንቀፅ 40(1) መሰረት

ለአገልግሎት ሞዴል (ለአነስተኛ የፈጠራ ስራ) ካልሆነ በስተቀር በፓተንት መብትነት አንድን ቀደም ሲል የነበረን የፈጠራ ስራ አሻሽሎ በመስራት የአእምሮ ንብረት መብት ማግኘት እንደሚቻል የሚደነግግ አይደለም፡፡ የዚህ ዓይነት ልዩነት በብዙ አገሮች ህግም ያለ ነው:: ለምሳሌ በአሜሪካ የፓተንት ህግ አንድን ሰው ፈጠራ አሻሽሎ መስራት እንደ መብት ጥሰት ተወስዶ የፍ/ብሄር ተጠያቂነትን የሚስከትል ሲሆን በአውስትራልያ ህግ ተጨማሪ የፈጠራ ስራ መስራት ማለትም አሻሽሎ ማውጣት የተፈቀደ ነው::

በአገራችን የፈጠራ ስራን ለማስጠበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 123/87 አላማዎችን ስንመለከት የፈጠራ ስራ አእምራዊ ንብረት መብት የአንድን ሰው በፈጠራው ስራ መገልገልን (Use or practice) መብት የሚጐናፀፍ በመሆኑ በዋና አላማነት ይዞት የሚነሳው ሌሎችን ያለ ባለመብቱ ፈቃድ እንዳይገለገሉበት መከልከል (excluding others) ነው:: ከዚህ በተጨማሪ

1. ለአገር ውስጥ ፈጣሪዎች (local inventors) ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የአገሪቱን የቴክኖሎጂ እድገት በማፋጠን የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲንና ስትራቴጂን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ስራን የመስራት ዓላማ ያለው ነው ፡፡
2. ከአገር ውስጥ የቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች በተጨማሪ ከውጪው ዓለም የቴክሎጂ ሽግግር እንዲኖር የሚያስችል ምቹ ሁኔታን በመፍጠር አገሪቱ ከዚህ ተጠቃሚ እንድትሆን በማድረግ ዘርፉ ለሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ልማትና መልካም አስተዳደር ስኬት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት የማስቻል አላማን በመያዝ የወጣ ህግ ለመሆኑ ከአዋጁ መግብያና ከዝርዝር ህጐቹ መረዳት እንችላለን፡፡ በመሆኑም የአገር ውስጥ ፈጠራን በዋና የልማት መሳርያነት በመጠቀም ከውጪው ዓለም መውሰድ ያለብንን ልምድ መበውሰድ ጠንካራ፣ ዘላቂና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚን መገንባት መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ እድገት ማረጋገጥን እንደግብ የያዘ ነው፡፡ የፓተንት መብት መጠበቅ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን ስናይ አገሮች የፓተንት መብት እንዲጠበቅ የሚያደርጉባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን ወሰደን ያየን እንደሆነ:-
    - ለኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ ከዚህ ተጠቃሚ ለመሆን፤
    - መብቱ በመጠበቁ ሰዎች ፈጠራቸውን እንዲያወጡና ህዝቡ ከዚህ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል፤
    - ተመራማሪዎች ወደ ውድድር እንዲገቡና ኩባንያዎች ከዚህ የፈጠራ ስራ ውድድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻልና በቀላል ዋጋ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ፤
    - ኩባንያዎች የፈጠራ ስራውን ገዝተው ማምረት ሲጀምሩ በሌላ የሚፈበረክ ከሆነ አደጋ ላይ ሊጥላቸውና ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ ሊከታቸው ስለሚችል

የፓተንት ህግ ከሌለ ደፍረው የፈጠራ ስራን ሊገዙ ስለማይችሉ የህጉ መኖር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: ስለዚህ በአንድ አገር የፈጠራ ህግ ሲወጣ የራሱ አላማዎችና ምክንያቶች ያሉት እንደመሆኑ መጠን በኛ አገርም ከፍ ብለው የተገለፁት አላማዎች ያሉት ነው::

2.2.4.1 ጥበቃ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸው የፈጠራ ስራዎች

የፈጠራ ስራ መብት (patent right) የሚሰጠው እንዴት ላለ ፈጠራ ነው? የሚለውን ስንመለከት ይህ መብት ለሁሉም እንደማይሰጥ አዋጁ በአንቀፅ 3 ላይ በዝርዝርና ለይቶ የሚያሳይ መልኩ የደነገገውን ወስደን ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ አንድ የፈጠራ ስራ የህግ ጥበቃ እንዲያገኝ ከተፈለገ ቀጥሎ ያሉትን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል::

1. *አዲስነት (Novelty) - አንድ የፈጠራ ስራ አዲስ ነው የሚባለው በቀደምት ጥበብ ያልተሸፈነ ሲሆን ነው፡፡ ቀደምት ጥበብ ማለት የፈጠራ ስራውን በተመለከተ ማመልከቻ ከገባበት ወይም እንደአግባቡ ከቀዳሚው ቀን በፊት በየትኛውም የአለም ክፍል በተጨባጭ በሚታይ ህትመት ወይም በቃል ወይም ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የተገለፀ ነገርን ያጠቃልላል (አንቀፅ 3(2))*
2. *ፈጠራዊ ብቃት (Inventive Step) - አንድ የፈጠራ ስራ ፈጠራዊ ብቃት አለው የሚባለው ከሚመለከታቸው ጋር አግባብነት ካለው ቀደምት ጥበብ አንፃር ሲታይ በመስኩ ተራ እውቀት ላለው ሰው ግልፅ ያልሆነ እንደሆነ ነው፡፡ (አንቀፅ 3(4))*
3. *ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት(Industrial Applicability) - አንድ የፈጠራ ስራ ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት አለው የሚባለው በዕዳ ጥበብ፣ በግብርና፣ በማህበራዊ አገልግሎቶችና ሌላ ማናቸውም መስክ ሊሰራ ወይም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ነው (አንቀፅ 3(5))*

በመሆኑም አንድ የፈጠራ ስራ የህግ ጥበቃ አግኝቶ ፈጣሪ ነኝ የሚለው ሰውም በመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ስራው እነዚህን ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን ህጋዊ መስፈርቶች (legal requirements) ማሟላት የግድ ይላል፡፡

የፈጠራ ስራ ጥበቃ የማይደርግላቸው ስራዎች በአዋጁ አንቀፅ 4 ላይ ተዘርዝረው ያሉት ሲሆኑ እነሱም፤

- የህዝቡን ሰላም ወይም ስነ-ምግባር የሚፃረሩ ፈጠራዎች፤
- የእፅዋት ወይም የእንስሳት ዓይነቶች ወይም የእፅዋት ወይም የእንስሳት ውጤቶችን ለማስገኘት በስነ-ህይወት ዘርፍ የሚከናወኑ ስራዎች፤
- ጨዋታዎችን ለማካሄድ ወይም የንግድና የኢንዱስትሪ ስራዎችን ለማከናወን የተዘጋጁ ስልቶች፣ ደንቦች፣ ዜዴዎች እንዲሁም የኮምፒዩተር ፕሮግራም፤

- ግኝቶች፣ ሳይንሳዊ ቲዎሪዎች (theories) እና የቅመራ ዘዴዎች፣ (mathematical methods)
- ሰውን ወይም እንስሳትን በቀዶ ጥገና ወይም በቴራፒ ህክምና ዘዴዎች ለማከም እንዲሁም የሰዎችን ወይም እንስሳትን በሽታ ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎች የፈጠራ መብት ጥበቃ የማይሰጣቸው ክንዋኔዎች ተደርገው ነው የሚወሰዱት፡፡ ይህ ማለት ግን የሰዎችን ወይም የእስሳትን በሽታ ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎችን በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያገለግሉ ውጤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ (አንቀፅ 4(2) ስለዚህ ህጉ ለፈጠራ ስራ የህግ ጥበቃ ለመስጠትም ላለመስጠትም በመለክያነት የሚገለገለው የፈጠራ ስራው የህዝብን ጥቅም ያስጠብቃል ወይስ አያስጠብቅም? በግል የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት ሊያዝ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን መስፈርቶች የሚጠቀም ነው::

2.2.4.2 የፈጠራ ስራ መብትና ይዘት

የፓተንቱ ይዘት ባለቤቱ በፈጠራው ላይ ያለውን ብቸኛ መብት የሚያረጋግጥና ሌሎች በደንብ ቁጥር 12/89 አንቀፅ 14 እና ቀጥሎ ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት ዝርዝር ነጥቦችን የያዘ መሆን አለበት፡፡ (የአዋጁ አንቀፅ 15) አንድን የፈጠራ ስራ የስራ የፓተንት ባለ መብት የተሰጠውን ፈጠራ ለመፈብረክ ወይም በሱ ለመገልገል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ለመጠቀም መብት ይኖረዋል፡፡ ሶስተኛ ወገኖችን የባለ ፓተንቱ ፈቃድ ሳያገኙ ፓተንት በተሰጠው ፈጠራ ለመፈብረክ አይችሉም፡፡ ሶስተኛ ወገኖች ተጠያቂ ሊሆኑ የማይችሉት የፓተንት መብት (patent right) ለፈጣሪው የተሰጠው ከሆነ ብቻ ነው፡፡ (አንቀፅ 22(1) እና 23) ይህ ሰው ያለእርሱ ፈቃድ ፓተንቱን የሚፃረር ወይም መብቱን ሊነካ የሚችል ድርጊትን በሚፈፅም ማናቸውም ሰው ላይ በፍ/ቤት ክስ የመመስረት መብት አለው:: መብቱ ያልተረጋገጠለት ሰው የኔ ፈጠራ ስራ ነው በሚል ብቻ ግን በሶስተኛ ወገኖች ላይ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ የፈጠራው ባለቤት የፓተንት መብት የማግኘትና በሶስተኛ ወገኖች ሊመጣ ከሚችል መጣስ ህጋዊ ጥበቃ እንደሚደረግለት ሁሉ ግዴታም ያለበት ነው:: ይሄውም ባለፓተንቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጠራውን ስራ ላይ የማዋል ወይም በርሱ ፈቃድ ሌሎች ሰዎች ፈጠራውን ስራ ላይ እንዲያውሉ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ (አንቀፅ 27)
የፓተንት መብት የሚሰጠው እንዴት ነው? የሚለውን አንስተን ስናይ በመርህ ድረጃ መብቱ የሚሰጠው ለፈጠራ ሰራተኛው ሲሆን የፈጠራ ስራው በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በጋራ ሆነው አንድን የፈጠራ ስራ ካከናወኑ የጋራ የፓተንት መብት ይኖራቸዋል፡፡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ተመሳሳይ የፈጠራ ስራ ስርቻለሁ በማለት በሚቀርቡበት ጊዜ የፈጠራው ባለቤት የሚሆነው አስቀድሞ ማመልከቻ ያስገባው ነው:: (አንቀፅ 11(1)) ይሄውም ህጉ (first to file rule and right of priority) በመርህ ደረጃ የሚከተል ነው:: ፓተንት የሚሰጠውም

በአዋጁ አንቀፅ 14 መሰረት ኮሚሽኑ ፓተንት ስለመስጠቱ በኦፊሴል ጋዜጣ በማሳወቅ ፣ የፓተንቱን ሰርትፍኬትና የፓተንቱን ቅጂ ለአመልካቹ በመስጠት፣ በመመዝገብና ክፍያ ለሚያስፈፅም አካል የፓተንቱን ቅጂ በመስጠት ነው:: የፓተንቱ ይዘትም ባለፓተንቱ በፈጠራው ላይ ያለውን ብቸኛ መብት የሚያረጋግጥና በደንቡ መሰረት ሌሎች ነገሮችን ያካተተ ይሆናል::(አንቀፅ 15) በኢትዮጵያ የፓተንት መብት የሚሰጠው ለተፈጥሮና የህግ ሰው ሲሆን በአሜሪካ አገር የዚህ ዓይነት መብት የሚሰጠው ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው:: በኛ አገር የፈቃድ አሰጣጥ ስነ-ስርዓቱ ምን ይመስላል? የሚለውን ስንመለከት ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር አንድ ሰው ተቀጥሮ በሚሰራበት ግዜ ለሚገኘው የፈጠራ ስራ የፓተንት መብቱ የሚሰጠው ለቀጣሪው ነው:: የቅጥሩ ሁኔታ ከፈጠራ ስራው ግንኙነት የሌላው ወይም ከቅጥር ወይም የአገልግሎት ውል ጋር ግንኙነት በሌለው መንገድና የቀጣሪው ወይም የአሰሪውን ሃብት፣ መረጃ፣ ማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ ማተሪያል ወይም መሳርያ ሳይጠቀም የፈጠራ ስራውን ያከናወነው ከሆነ ግን የፓተንት መብቱ የሚሰጠው ለፈጣሪው ወይም ለተቀጣሪው ወይም ለአገልግሎት ሰጪው ነው፡፡ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው የቀጣሪውን መሳርያ በመጠቀምና የተቀጣሪው የግል አስተዋፅኦ ታክሎበት ለሚገኝ የፈጠራ ስራ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለው በስተቀር እኩል ድርሻን መሰረት በማድረግ የሁለቱ ማለትም የቀጣሪውና የተቀጣሪው የጋራ ንብረት ይሆንና የፓተንት መብቱ በጋራ ይሰጣል፡፡ (አንቀፅ 7) ስለዚህ የፈጠራ ስራ ባለቤትነት ይዘቱ የፈጠራውን ብቸኛ ባለመብትነት የሚያረጋግጥ ሰነድ ሲሆን የዚህም ውጤት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው በማድረግ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት ጥበቃ እንዲያገኝ ማስቻል ነው፡፡ የፈጠራ ስራ ባለቤትነት መብት (patent right) የሚሰጠው አንድም ለፈጣሪው ለራሱ ወይም ይህን ስራ እንዲያከናውን የተቀጠረ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በሆነበት ግዜ ደግሞ ፓተንቱ የሚሰጠው ለቀጣሪው መሆኑንና ተቃራኒ ስምምነት ከሌለና ለፈጠራ ስራው የሁለቱም አስተዋፅኦ ካለበት ደግሞ ፓተንቱ የሚሰጠው ለሁለቱም በጋራ ባለቤትነት እንዲያገግል በሚያስችል መንገድ ይሆናል፡፡

2.2.4.3 የባለፓተንት መብት ገደቦች

የፓተንት መብት የአእምሮ ንብረት መብት እንደመሆኑ መጠን የፈጠራ ስራው ባለቤት በዚህ መብቱ ብቸኛ ባለቤት በመሆን ሶስተኛ ወገኖች ያለሱ ፈቃድ በዚህ የፈጠራ ስራ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የመከልከል ውጤት ያለው መብት (negative right) ነው:: ሆኖም ግን ይህ መብት በህግ ገደብ (limitation) የማይደረግበት የንብረት መብት (monopoly right) ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 25 ላይ የተወሰኑ ገደቦች ተጥሎበታል:: እነዚህም፡-

ሀ. ንግድ ነክ ባልሆኑ ተግባሮች ያለፈጣሪው ፈቃድ ቢገለገሉበት በህግ አያስጠይቅም፡፡

ለ. ፓተንት የተሰጠበት ፈጠራ ለሳይንሳዊ ምርምርና ሙከራዎች ዓላማ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ማድረግ የተፈቀደ ነው ፡፡

ሐ. በባለፓተንቱ ወይም በሱ ፈቃድ ኢትዮጵያ ውስጥ በገበያ ላይ ከዋሉ ፓተንት የተሰጣቸው ሸቀጦች ጋር በተያያዘ መልክ የሚከናወኑ ድርጊቶች ናቸው::

እንዲሁም በአንቀፅ 25(2) ላይ

የህዝብን ጥቅም በተለይም የብሄራዊ ደህንነት፣ የምግብና የጤና ወይም የሌሎች ብሄራዊ የኢኮኖሚ ዋና ዘርፎች የልማት ፍላጐት ለመጠቀም ኮሚሽኑ ያለባለፓተንቱ ፈቃድ የመንግስት ድርጅት ወይም ኮሚሽኑ የሚሰይመው ሶስተኛ ወገን ለባለፓተንቱ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ፈጠራውን አንዲጠቀም ሊወሰን ይችላል፡፡ የካሳ ክፍያውን በሚመለከት ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ላይ ወደ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባልበት ይችላል::

ሲል ይደነግጋል፡፡ የነዚህ ድንጋጌዎች አላማ በህገ-መንግስቱ እውቅና የተሰጠውን የፈጠራ ጥበቃ በመርህ ደረጃ የባለቤትነት መብቱ የፈጣሪው ሰው የራሱ ወይም ከአንድ በላይ በሚሆኑበት ግዜ የጋራ እንደሆነ በመቀበል ለህዝብ ጥቅምና አገር ደህንነት ሲባል ግን በዚህ የአእምሮ ንብረት መብት ላይ ገደብ (Limitation) ሊጣልበት እንደሚችልና ይህም በሚሆንበት ግዜ ባለፓተንቱ ካሳ የማግኘት መብት እንዳለው ማረጋገጥ ነው፡፡

2.2.4.4 የፓተንት መቋረጥ፣ መተውና መሰረዝ

የፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ግዜ ጥበቃ ለማግኘት የቀረበው ማመልከቻ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ለአስራ አምስት ዓመታት ቢሆንም በተለያየ ምክንያት የመብቱ መቋረጥ፣ መተው፣ መሰረዝ ሊከሰት ይችላል፡፡ የፓተንት መብት ሊቋረጥ የሚችለው ባለመብቱ ፓተንቱን የተወ መሆኑን ለኮሚሽኑ በፅሑፍ ሲያሳውቅና የመብት ማቆያ ክፍያ በተወሰነው የግዜ ገደብ ውስጥ ያልተፈፀመ ሲሆን ነው፡፡ይሄውም የመብቱ መቋረጥ ሊከሰት የሚችለው በፍላጐትና ግዴታን በአግባቡ ባለመፈፀም ምክንያት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ የፓተንት መብት መተው ሊከሰት የሚችለው ደግሞ በፍላጐት ላይ ተመስርቶ የሚመጣ ሲሆን የክንውኑ ስነ-ስርዓትም ባለፓተንቱ መብቱን መተውን ለኮሚሽኑ ሲያሳውቅና ኮሚሽኑ ይህን የመተው ሁኔታ በመመዝገብ አትሞ ሲያወጣው ነው፡፡ ባለፓተንቱ መብቱን ትቻለሁ ያለበት ጊዜ መብቱ ለሌላ ሶስተኛ ወገን በውል ከተሰጠ በኃላ ከሆነ የሚኖረው ስነ-ስርዓት የመተው ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኘው ሌላው ተዋዋይ ወገን ስምምነቱን ሲሰጥ ብቻ ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት መብቱ በውል የተላለፈለት ሰው ጥቅም (third party interest) ለመጠበቅ እንደሆነ መገመት ቢቻልም ይሁንታ በማይሰጥበት ጊዜ ስለሚኖረው ስነ-ስርዓት

ህጉ በግልፅ የሚለው ነገር የለም፡፡ ከአጠቃላይ የድንጋጌው ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ግን ይህ መብት ፀንቶ ለሚቆይበት ግዜ በውል የፓተንት መብት የተላለፈለት ሰው በፓተንቱ እየተገለገለበት ሊቆይ እንደሚችል ነው፡፡ የፓተንት መብትን መሰረዝ የሚመለከትም ቀጥለው የምናያቸው መስፈርቶች በሙሉ ወይም በከፊል ከተሟሉ ፍ/ቤት ፓተንቱን ሊሰርዘው ይችላል፡፡ (አንቀፅ 34፣35 እና 36) ይሄውም

ሀ. ፓተንት የተጠየቀበት ነገር በአዋጁ ቁጥር 123/89 አንቀፅ 3 እና 4 መሰረት ፓተንት ሊሰጥበት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፡፡

ለ. ፈጣሪው በሚበቃ መጠን ግልፅና ሙሉ በሆነ መልክ ባለመግለፁ በመስኩ ለሰለጠነ ሰው በተግባር ለመተርጐም የማያስችል ሲሆን ነው ፡፡

ፓተንቱ ሲሰረዝ የዚህ የፓተንት መብት መሰረዝ ህጋዊ ውጤትም ወደ ኃላ ተመልሶ በሚሰራ ውጤት (retroactive effect) ይኖረዋል፡፡ ለዚህም ነው አንቀፅ 37(2) "በከፊል ወይም በሙሉ የተሰረዘ ፓተንት ዋጋ ቢስ ሆኖ የሚቆጠረው ፓተንቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይሆናል" ሲል የሚደነግገው፡፡

ስለዚህ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ የፓተንት መብት ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ፈጠራ ስራ ባለቤቶች የሚሰጥ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት ሆኖ ህገ-መንግስታዊና ከዚያ በታች ባሉ አዋጆችና ደንቦች ጥበቃ የተደረገለትና ወደ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችል ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ነው፡፡ የፓተንት መብት ጥበቃ የሚያገኘው ለ15 ዓመት ሆኖ የዚህ መብት ዋናው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም ሶስተኛ ወገኖች ያለባለፓተንቱ ፈቃድ እንዳይገለገልበት መከልከል ነው፡፡ ፓተንት ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ቢሆንም በአንድ ወቅት ተፈጥሮ ለ15 ዓመት ህጋዊ ውጤት ኖሮት ማንነቱን ሊያጣ ወይም ቀሪ ሊሆን የሚችል ወይም በመሃል እክል ገጥሞት ሊሰረዝ ወይም ሊቋረጥ ወይም በነፃ ፈቃድ ሊተው የሚችል የአእምሮ ንብረት መብትም ነው፡፡

2.2.4.5 የአስጋቢ ፓተንት (patent of introduction)

የአስገቢ ፓተንት የሚሰጠው ለማን ነው? የአስገቢ ፓተንት የሚሰጠው በውጭ አገር የፓተንት ፈቃድ ለተሰጠውና የጥበቃ ጊዜው ላላለፈበት እንዲሁም በኢትዮጵያ ፓተንት ላልተሰጠው የፈጠራ ስራ መግለጫ ለሰጠና ሙሉ ሓላፊነት ለሚወስድ ማንኛውም የአስገቢ ፓተንት ሊሰጠው ይችላል:: (አንቀፅ 18) የአስገቢ ፓተንት መመዘኛዎችም ለፈጠራ ፓተንት ከሚጠይቁት መመዘኛዎች ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የአስገቢ ፓተንት መሰረቱ የውጭ ፓተንት እንደመሆኑ መጠን የአስገቢ ፓተንት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት ሰው የውጭውን ፓተንት ቁጥር፣ ቀንና ምንጭ ወይም ዝርዝር መረጃውን የማያውቅ ከሆነ የሚገኝበትን ምንጭ መጠቆም ይኖርበታል፡፡ (አንቀፅ 19(1) (2)

የአዋጁ አንቀፅ 11(2) የእንካ ለእንካ መርህ (principle of reprocity) እንደተጠበቀ ሆኖ የአስገቢ ፓተንት አመልካች በአንቀፅ 11(2) የተጠቀሰው አንድ ዓመት ግዜ ከማለቁ በፊት

የውጭው ፓተንት ባለቤት ማመልከቻ ካላቀረበ ወይም የአስገቢ ፓተንት ባለቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 21 ማለትም የአስገቢው ፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ግዜ መሰረት ፈጠራው ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ካልቻለ ወይም ዓመታዊውን ክፍያ መፈፀም ካልቻለ የአስገቢ ፓተንቱ ዋጋ ቢስ ወይም ህጋዊ ውጤት የሌለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ (አንቀፅ 20(1)) ይሄም በሚመለከተው አካል ጠያቂነት የአስገቢ ፓተንት መብቱ በአዋጁ አንቀፅ 36 መሰረት በፍ/ቤት የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

የአስገቢ ፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆየው የአስገቢ ፓተንት ከተሰጠ ከሶስት ዓመት በኃላ በየዓመቱ በስራ ላይ የዋለ መሆኑ የማረጋገጥ ግዴታና ዓመታዊ ክፍያ የመክፈል ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስገቢ ፓተንቱ ፀንቶ የሚቆየው እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡ (አንቀፅ 21) የዚህ ዓይነት የፓተንት መብት መፍቀድ አላማው የውጭ ፓተንት የተሰጠን ፈጠራ ስራ በኢትዮጵያ እንዲገባ በመፍቀድ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖርና ከዚህ ዘርፍ ልናገኝ የምንችለውን ጥቅም አሟጠ በመጠቀም ለልማት በማዋል በዘርፉ የአሰራር፣ አደረጃጀትና የሰው ሃይል ብቃት እንዲጨምር ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ወሳኙ የአገር ውስጥ እድገት ቢሆንም ለውጭውም ቢሆን ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አሁን ዓለማችን ከደረሰችበት የግሎባላይዘሽን እድገት አኳያ ሲታይ በእጅጉ አስፈላጊና ተገቢም ነው ፡፡

2.2.4.6 የአገልግሎት ሞዴል (Utility model)

በአዋጅ ቁጥር 123/87 እና ደንብ ቁጥር 12/89 ለአነስተኛ የፈጠራ ሰዎች የሚሰጣቸው ጥበቃ የአገልግሎት ሞዴል ሰርትፍኬት እንደሆነ ከአዋጁ አንቀፅ 38 እና ከደንቡ አንቀፅ 39 መረዳት የሚቻል ሲሆን እንደ ፓተንት መብት ሁሉ የአገልግሎት ሞዴል በህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው የፈጠራ ስራዎችን ያካተተ ነው፡፡

በአገልግሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ጥበቃ የሚደረግላቸው የአዲስነትና የኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አነስተኛ ፈጠራዎች በአገልግሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ጥበቃ ይደረግላቸዋል መመዘኛዎቹም፡፡

አዲስነት - አንድ አነስተኛ የፈጠራ ስራ አዲስ ነው የሚባለው ማመልከቻው በተመዘገበበትቀን ኢትዮጵያ ውስጥ በታተሙ ፅሑፎች ላይ ቀደም ሲል ያልተገለፀ ወይም ለህዝብ ያልቀረበ ወይም በይፋ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፈጠራ ስራው ማመልከቻ ከመመዝገቡ ከ6 ወራት በፊት መገለፁና ጥቅም ላይ መዋሉ አዲስነቱ አያስቀረውም (አንቀፅ 39(1) (2))

ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት - አንድ የፈጠራ ስራ ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት አለው የሚባለው በዕደ ጥበብ፣ በግብርናና በማህበራዊ አገልግሎቶችና ሌላ በማናቸውም መስክ ሊሰራ ወይም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ነው፡፡ (አንቀፅ 3(5))

የአገልግሎት መዴል ጥበቃ የሚሰጠው ለ5 ዓመት ሲሆን አነስተኛ የፈጠራ ስራው በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ የዋለ ከሆነ ለተጨማሪ 5 ዓመት ይታደሳል፡፡ (አንቀፅ 44(1)) አነስተኛ የፈጠራ ስራን መብት የሚያስጠብቀው የአገልግሎት ሞዴል ከፓተንት ጋር ሲነፃፀር ቀላል፣ ውድ ያልሆነና ፈጣን የፈጠራ ስራ ማስጠበቅያ መንገድ በመሆኑ ብዙዎች ሊገለገሉበት የሚችል የፈጠራ ስራ ማስጠበቅያ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በአገልግሎት ሞዴል ጥበቃ የሚደረግላቸው የአነስተኛ የፈጠራ ስራዎች የመኖራቸው ያህል ጥበቃ የማይደረግላቸውም አሉ፡፡ እነዚህም፡-

- ፓተንት የተሰጠበት ወይም የህዝብ ንብረት የሆነን ነገር የቀድሞ ይዘት፣ ጠባይ ወይም ተግባር ቀይሮ በአጠቃቀሙ ወይም በታለመለት ተግባር መሻሻልን የሚያስከትል ካልሆነ በቀር በቅርፅ፣ በመጠን ወይም በማተሪያል መልክ የሚደረግ ለውጥ የአገልግሎት ሞዴል ጥበቃ አይደረግለትም፡፡ (አንቀፅ 40(1))
- የታወቁ ንጥረ ነገሮችን ጥንቅር ተመሳሳይ ተግባር ባላቸው ሌሎች የታወቁ ንጥረ ነገሮች የመተካትና ይህም በሚገኘው ጥቅም ወይም አሰራር ላይ ምንም ዓይነት መሻሻል የማያስገኝ ሲሆን፡፡ (አንቀፅ 40(2))
- ለህዝብ ሰላምና ስነ-ምግባር ተፃራሪ የሆኑ አነስተኛ ፈጠራዎች ከሆኑ የአነስተኛ የፈጠራ ስራ መብት ማስጠበቅያ የሆነው የአገልግሎት ሞዴል ሰርተፍኬት አይስጥም፣ የሚደረግላቸው ጥበቃም አይኖርም፡፡ (አንቀፅ 40(3))

ስለዚህ የአገልግሎት ሞዴል ሰርተፊኬት ለአነስተኛ የፈጠራ ስራዎች መብት ማስጠበቅያ ተብሎ የሚሰጥ የፈጠራ መብት ሲሆን ጥበቃ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸው የአነስተኛ ፈጠራ ስራዎች በህግ ተለይተዋል:: ይህ መብት ፀንቶ የሚቆየው ለአምስት ዓመት ሲሆን የፈጠራ ስራው በአገር ውስጥ በስራ ላይ የዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ለተጨማሪ አምስት ዓመት ሊታደስ ይችላል:: የጥሰት መፍትሔን (remedies) በሚመለከት በአሜሪካን አገር የፍ/ብሄር ተጠያቂነትን ብቻ የሚያስከትል ሲሆን በፈረሳይና አውስትራሊያ የወንጅል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው:: በኛ አገር ህግም የፍታብሄር ተጠያቂነት ከውል ውጭ ባለ ሃላፊነት በአንቀፅ 2027 ff በወንጀል ደግሞ በወ/ህ/ቁ 721 የሚያስጠይቅ ነው::

2.2.5 ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ (Industrial Designs)

የኢንዱስትሪ ንድፍ ማለት ምን ማለት ነው? የኢንዱስትሪ ንድፍ ማለት የመስመሮች ወይም የቀለሞች ቅንጅት ወይም ከመስመሮችና ከቀለሞች ጋር የተያያዘ ወይም ያልተያያዘ ባለሶስት ገፅታ ቅርፅ ሲሆን ቅንጅቱ ወይም ቅርፁ ለኢንዱስትሪ ወይም ለዕደ ጥበብ ውጤቶች ልዩ መልክ የሚሰጥና በኢንዱስትሪ ወይም ዕደ-ጥበብ ለሚመረት ምርት እንደ ንድፍ የሚያገለግል ነው፡፡ ሲል በአንቀፅ 2(2) ላይ ሲተረጉመው እውቁ Wikipedia free encyclopedia በህጋችን ከተሰጠው ትርጉም እምብዛም ባልተለየ መልኩ:-

Industrial design rights are Intellectual property rights that protect the visual design of objects that are not purely utilitarian. An Industrial design consists of creation of shapes, configurations or composition of patterns or color or combination of patterns and color in three-dimensional form containing aesthetic value.

የሚል ትርጉም ሰጥቶታል::

2.2.5.1 ጥበቃ የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው ንድፎች

በኢንዱስትሪ ንድፍ የንብረት ባለቤትነት መብት እንደሌሎች የአእምሮ ንብረቶች የህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው የኢንዱስትሪ ንድፎች ያሉት ሲሆን ጥበቃ የሚደረግላቸውን የተመለከትን እንደሆነ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ያሟሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል::

የኢንዱስትሪ አዲስነት - አንድ የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስ ነው የሚባለው የንድፉ ዋና ዋና ባህርያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየና ከምዝገባ ቀን ወይም እንደ አግባቡ ከቀዳሚው ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን ነው፡፡ በንድፎቹ መካከል ያሉ የተለዩ ገፅታዎች ልዩነት በጥቃቅን ዝርዝሮች ከሆነ ተመሳሳይ ናቸው ተብለው ይወሰዳሉ፡፡ (አንቀፅ 46(2) (ሀ))

ተግባራዊ ተፈፃሚነት - አንድ የኢንዱስትሪ ንድፍ ተግባራዊ ተፈፃሚነት አለው የሚባለው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምርቶችን በተደጋጋሚ ለማውጣት በሞዴልነት ለማገልገል የሚችል ሲሆን ነው፡፡ (አንቀፅ 46(2) (ለ))

የኢንዱስትሪ ንድፍ ህጋዊ ጥበቃ የማይደረግላቸው ንድፎችን ስንመለከት ደግሞ

- እውቅና ስለማይኖረው ጥበቃ ሊደረግለት አይችልም፡፡ (አንቀፅ 46(3))
- ቴክኒካዊ ውጤቶችን ለማግኘት ብቻ ለሚውሉ ማናቸውም ነገሮች በዚህ አዋጅ ለኢንዱስትሪያዊ ንድፎች የሚሰጠው ጥበቃ አይሰጣቸውም፡፡ (አንቀፅ 46(4))

ለህዝብ ሰላም ወይም ስነ-ምግባር ተፃራሪ የሆነ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ከሆነ አይመዘገብም፡፡ ካልተመዘገበ ደግሞ ህጋዊ ሰተርፍኬት ባለቤት በንድፉ ለመሰራት ወይም ለመልገል ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኃን ለመጠቀም ብቸኛ መብት እንዲኖረው ማስቻል ነው፡፡ (አንቀፅ 49) ይህን መብት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የኢንዱስትሪ ንድፉን ያቀፈ ምርት ናሙና ወይም የንድፉን ስእላዊ አምሳያና ንድፉ ሊያገለግል የታቀደውን የምርት ዓይነት መያዝ ይኖርበታል:: ከማመልከቻው ጋር የተመደበውን ክፍያ ይከፍላል:: ከዚህ በኋላ የቀረበው ንድፍ ተመርምሮ ተቀባይነት ካገኘ የኢዱስትሪ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ይሄውም የኢንዱስትሪ ንድፍ መብት እንዴት ይረጋገጣል? የኢንዱስትሪ ንድፍ መብት የሚረጋገጠው በምዝገባ ሲሆን የምዝገባው ይዘትም

- የንድፍ ስራው የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መሆኑን
- የኢንዱስትሪ ንድፉን ቀዳሚነት
- የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ሰራተኛ ማንነትና ባለቤቱ በኢንዱስትሪዊ ንድፉ ያለውን ብቸኛ መብት ይይዛል::

በመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ምዝገባ ወሳኝ ነው:: ኮሚሽኑ የቀረበለት ማመልከቻን በማስመልከት በሚሰጠው ውሳኔ አመልካቹ ካልተስማማው የውሳኔው ቅጂ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ60 ቀን ውስጥ ይግባኙን ወደ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል:: ስለዚህ በአገራች ሆነ በሌሎች አገሮች የኢንዱስትሪ ንድፍ ህግ ለፈጠራ ስራ ጥበቃ የሚሰጥ ቢሆንም ለሁሉም የኢንዱስትሪ ንድፎች ሁሉ ልዩነት በሌለው መንገድ (indiscriminately) ጥበቃ የሚሰጥ ህግ ግን አይደለም::

2.2.5.2 መብቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

የአንዱስትሪ ንድፍ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት እንደሌሎቹ የአእምሮ ንብረት መብቶች ፀንቶ የሚቆይበት ግዜ ያለው ነው:: አገሮች እንደየ ፍትሕ ስርዓታቸው የተለያየ መብቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ አላቸው:: ለምሳሌ በካናዳ 10 ዓመት፣ በጃፓን 15 ዓመት፣ በአሜሪካ 14 ዓመት በእንግሊዝ የተመዘገበና ያልተመዘገበ የሚል አሰራር ስለሚከተሉ የተመዘገበ ከሆነ 25 ዓመት ያልተመዘገበ ከሆነ ደግሞ ለ15 ዓመት ፀንቶ ይቆያል:: በኢትዮጵያም የምዝገባ ማመልከቻው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ለ5 ዓመት ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን ይህ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ እየዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ደግሞ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መብት ለተጨማሪ ሁለት አምስት ዓመታት ሊራዘም ይችላል፡፡ (አንቀፅ 50(1)) ይህም የይራዘምልኝ ማመልከቻ የማብቅያ ግዜው ከመድረሱ በፊት ዘጠና ቀን አስቀድሞ በማመልከት ሊከናወን ይገባል ካልሆነ አይታደስም ፡፡ (አንቀፅ 50(2))

ስለዚህ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የባለቤት መብት የሚሰጠው ለንድፍ ፈጣሪ ሲሆን ጥበቃ የሚሰጣቸው ንድፎች ለአገር ልማት ከሚያበረክቱት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንፃር እየታዩ ሲሆን በይዘታቸውና አላማቸው የህዝቡን ሁለንተናዊ እድገት ወደ ኃላ የሚጐትቱ የኢንዱስትሪ ንድፎች የማይመዘገቡና ከሶስተኛ ወገኖች ጥሰት ለመከላከል ማንኛውም ዓይነት የህግ ጥበቃ የማይደረግላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 123/1987 ድንጋጌዎችና ደንብ ቁጥር 12/89 አንቀፅ 40 እና ቀጥለው ያሉ ድንጋጌዎች ልንረዳው የምንችል እውነታ ነው፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪ ንድፍ ህግ እንደሌሎች የአእምሮ ንብረቶች ስርዓት ባለው መንገድ እየተመራ ለአገር ልማት እንዲውል የማድረግ ህዝባዊ አላማን መሰረት ያደረገ ነው ፡፡

2.2.6 የቅጅና ተዛማጅ መብቶች (Copy Right and Neighboring Rights)

የቅጅና ተዛማጅ መብቶችን በማስመልከት የወጣው አዋጅ ቁጥር 410/96 በአንቀፅ 2(8) ላይ "የቅጅ መብት ማለት ከአንድ ስራ የሚመነጭ የኢኮኖሚ መብት ሲሆን አግባብነት ባለው ጊዜ የሞራል መብቶችን ይጨምራል" በማለት ሲተረጉመው ተዛማጅ መብት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ደግሞ በአንቀፅ 2(14) ላይ " ተዛማጅ መብት ማለት ከዋኝ፣ የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲሰር፣ የብሮድካስቲንግ ድርጅት በስራው ላይ ያለው መብት ነው" በማለት ተርጉሞታል፡፡ እውቁ Wikipedia free encyclopedia በበኩሉ

> *Generally it is "the right to copy", but also gives the copy right holder the right to be credited for the work, to determine who may adapt the work to other forms, who may perform the work, who may financially benefit from it, and others.*

በማለት የቅጂ መብት ለአእምሮ ንብረት ባለቤት የሚያስገኘውን መብት ሰፋ ባለመልኩ ተርጉሞት እናገኛለን፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋለ ያለብን ነገር የቅጂ መብት ሽፋን የሚሰጠው ሃሳብን (ideas) እና መረጃን (information) ሳይሆን የህግ ጥበቃ የሚሰጠው የቅጂውን መብት መሰረት በማድረግ ስለሆነ ጥበቃው ለሃሳቡና ለመረጃው ሳይሆን ለአፃፃፍ ቅርፅ (forms) ወይም አገባብ (manner) መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የቅጅ መብት ተኩረት የሚያደርገውና ሽፋን የሚሰጠው ለሀሳቡ አገላለፅ እንጂ ሀሳቡ እንዳይጣስ ማድረግ አይደለም:: *Copy right usually protects the expression of an idea not the idea itself. Thus, copy right does not prohibit a reader from freely using and describing that concept to others, it is only the particular expression of that process as originally described that is covered by copy right.*

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች አዋጅ አላማ በአገራችን ያለውን የስነ-ፅሁፍ፣ የኪነ ጥበብ እና ሌሎች ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች የህግ ጥበቃ እንዲያገኙ በማድረግ የአገራችንን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኒኖሎጂያዊ እድገት በማፋጠን አገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል ነው፡፡ ይህን አብይ አላማ መሰረት በማድረግ አዋጁ ከአሁን ቀደም በፍታብሄር ህጉ ከቁጥር 1647- 1674 ባሉ ህጎች ለቅጅ መብት ተሰጥቶ የነበረን የጥበቃ ሽፋን በማስፋት አዳዲስ መሰረተ ሃሳቦችና መብቶች እንዲካተት ያደረገ ነው:: የማስተላለፍያ መንገዶቹ (transferability) እንዲሰፋ በማድረግ ተገቢ የሆነ ጥበቃ እንዲያገኙና ዋስትና አግኝተው ባለሙያዎቹ በልበ ሙሉነት እንዲሰሩ የማስቻል አላማን በመያዝ የወጣና በስራ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ከማንኛውም ግዜ በላይ በአደረጃጀትና አሰራር ተጠናክሮ በመሄድ ላይ ያለ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ ያገኘ የኢኮኖሚም ዘርፍ ነው፡፡ በቅጂ መብት ሽፋን የሚሰጣቸውን የአእምሮ ንብረቶች በማስመልከት Wikipedia ላይ ያየን እንደሆነ ፣

> *copy right may apply to a wide range of creative, intellectual, or artistic forms or "works" . . . can include, poems, theses,*

plays, other literacy works, moves, dances, musical composition, audio recordings, drawings, sculptures, photographs, software, radio and television broadcasts, and industrial designs, graphic designs.

በማለት የቅጅ መብት ጥበቃ የሚያገኙ ስራዎችን በመዘርዘር ሲያሰፍር በአገራችን የወጣው አዋጅ ቁጥር 410/96 ከዚህ ጋር በተቀራረበ መልኩ ጥበቃ ስለሚደረግላቸው የቅጅ መብት ማስገኛ ስራዎች በአንቀፅ 4(1) (ሀ) (ለ) ላይ የሚከለት ፈጠራ ስራ ጥበቃ ይደረግላቸዋል በሚል ስር፤

- ትርጉም፣ የማመሳሰል ስራ፣ ቅንብርና ሌላ የስራውን ዓይነት የሚቀይር ወይም የሚያሻሽል ስራ ወይም
- በይዘት፣ በቅንብር፣ ወይም በአመራረጥ የተነሳ ኦርጅናል የሆነና በሚነበብ መሳርያ ወይም በሌላ መልክ ያለ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የቅኔ ስብስብ ወይም ዳታቤዝን የመሳሰለ የስብስብ ስራ።

በማለት የሽፋን አድማሱን ሲገልፅ የህግ ጥበቃ ለማግኘት ስለሚኖረው መስፈርት በማስመልከት ደግሞ በአንቀፅ 6(1) ላይ ማንኛውም የስራ አመንጪ የስራው አላማና ጥራት ከግምት ስውጥ ሳይገባ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት ሊያገኝ የሚችለው ስራው ወጥ ወይም ኦርጅናል ከሆነ፣ ከተቀረፀ ወይም ግዙፍነት ካገኘ ስራውን በማውጣት ምክንያት ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ እንደሚያገኝ ሲደነግግ ስራው የፎቶ ግራፍ ስራ በሚሆንበት ግዜ ደግሞ ከፍ ብለው ከተገለፁት መስፈርቶ በተጨማሪ ስራው የአንድ ስብስብ አካል ሲሆን ወይም በመፅሓፍ መልክ ሲታተሙ ወይም የስራ አመንጪውን ወይም ወኪሉን ስምና አድራሻ ሲይዙ እንደሆነ በአንቀፅ 6(2) (ሀ) (ለ) ላይ በግልፅ ሰፍሯል። ስለሆነም በአገራችን የአንድን ስራ ቅጂ መብት ለማግኘት የተጠቀመበት የአፃፃፍ ወይም የፎቶ አነሳስ ወይም የዘገባ ስርጭት ቅርፅ (form) ወይም አግባብ (manner) ኦርጅናል መሆንንና ስራዎቹ የፎቶና የብሮድካስቲን በሚሆኑበት ግዜ ደግሞ ኦጅናል ከመሆን በተጨማሪ በህጉ አንቀፅ 6(2) እና (3) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሚሟላት እንዳላባቸው ህጉ ያስገድዳል።

2.2.6.1 የቅጅና ተዛማጅ ስራዎች መብቶች

የቅጅ መብት ባለቤት ብቸኛ መብቶች (exclusive rights)

- ቅጂዎችን ማባዛት ወይም እንደገና ማባዛትና መሸጥ፤
- ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ከአገር ማውጣት፤
- የመጀመርያውን ስራ የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፤
- ስራውን ለህዝብ ማቅረብ፤
- መብቱን ለሌሎች የማስተላለፍ፤

- ስራውን በሬድዮና ቴሌቪዝን ማስተላለፍ ናቸው::

የቅጅና ተዛማጅ ስራ መብት የኢኮኖሚና የሞራል መብቶች በሚል ለሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን በአንቀፅ 19 ላይ ያለው ስለ ቅጂ ማሰራጨት መብትና በአንቀፅ 9 ላይ በግል አገልግሎት ስራ ስለማባዛት ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የቅጂ ስራ የአእምሮ ንብረት ባለቤት የሚኖሩት የኢኮኖሚ መብቶችን በማስመልከት ህጉ በአንቀፅ 7 ላይ ማንኛውም የስራ አመንጪ ወይም የአንድ ስራ ባለቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል በማለት ስራን የማባዛት፣ የመተርጎም፣ የማመሳሰል፣ የማቀናበር፣ ወይም ወደ ሌላ ዓይነት የመቀየር፣ በሽያጭ ወይም በኪራይ ኦርጅናል ስራን ወይም ቅጅውን የማከፋፈል፣ ኦሪጂናል ወይም ቅጂውን ከውጭ አገር የማስገባት፣ ኦርጅናል ወይም ቅጅውን ለህዝብ የማሳየት፣ ስራን በይፋ የማከናወን፣ ስራን ብሮድካስት የማድረግ ወይም በሌላ መንገድ የማሰራጨት መብቶች ይኖሩታል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆና ህጉ ለዚህ አጠቃላይ የቅጂ የኢኮኖሚ መብት ጥበቃ ሲሰጥ ለሁለም ክንዋኔዎች እንዳልሆነ በአንቀፅ 7(2) ላይ የሚደነግግ ሲሆን በ7(3) ላይ ደግሞ ዋናው አመንጪ ወይም ወራሾች ስለሚኖራቸው ኢኮኖሚያዊ መብት በደንብ እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡ አንድ የቅጂ ወይም ተዛማጅ ስራ ባለቤት የሚኖሩት የኢኮኖሚ መብቶች ከፍ ብለው የተዘረዘሩት ሲሆኑ ባለቤቱ በነዚህ መብቶች ሊሰራባቸው የሚችለው ወይም መብቱ ፀንቶ የሚቆየው እስከመቼ ነው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን ስናይ የተለያዩ አገሮች የተለያየ የጊዜ ሰሌዳን ይጠቀማሉ ለምሳሌ በአሜሪካ መብቱ ፀንቶ የሚቆየው ከ50-70 ዓመት ሲሆን በየ 28 ዓመቱ መታደስን ይጠይቃል:: ከዚያ በኋላ የህዝብ ንብረት (public domain) ይሆናል :: በጣልያን ከሞተ በኋላ ለ6 ዓመት፣በፈረንሳይ ለ14 ዓመትና በስፔን ለ80 ዓመት መብቱ ፀንቶ የሚቆይበት ህግ አላቸው:: ወደኛ አገር ህግ ስንመጣ አዋጁ በአንቀፅ 20 ላይ:-

20(1) " ኢኮኖሚ መብቶች የስራ አመንጪው በሂወት በቆየበት ዘመንና ከሞተ በኃላ ለወራሾቹ እስከ ሃምሳ ዓመት ፀንተው ይቆያሉ፡፡"

20(2) " በጋራ የስራ አምንጪዎች የተሰራ ስራን በሚመለከት ጉዳይ የሃምሳ ዓመቱ ግዜ መቆጠር የሚጀምረው የመጨሻው የስራ አመንጪው ከሞተበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡"

20(3) " የስራው አመንጪ ከሞተ በኃላ የታተመ ስራ የሃምሳ ዓመት የጥበቃ ግዜ መቆጠር የሚጀምረው ስራው ከታተመበት ግዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡"

20(4) " አንድ ከኦዲዮቪዥዋል ስራ ውጪ የሆነ ሰብስብ ስራ አኮኖምያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ስራው ከተሰራበት ወይም መጀመርያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመርያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነ አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመት ይሆናል፡፡"

20(5) " ስራው የአመንጪውን ሰም ካልያዘ ወይም በብእር ስም የታተመ ከሆነ የስራው አመንጪ የኢኮኖሚ መብት ፀንቶ የሚቆየው ስራው ከተሰራበት ወይም መጀመርያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመርያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻው አንዱ ጀምሮ ለ50 ዓመታት ይሆናል።"

20(6) " በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (5) ከተመለከተው ግዜ በፊት የስራው አመንጪ ማንነት ከታወቀ ወይም የማያጠራጥር ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) እንደሁኔታው ተፈፃሚ ይሆናል።"

20(7) "በፎቶ ግራፍ ስራ ላይ ያለ የኢኮኖሚ መብቶች ፀንተው የሚቆዩት ስራው ከተሰራበት ግዜ ጀምሮ ለሃያ አምስት ዓመት ይሆናል።"

20(7) "በኦዲዮቪዥዋል ስራ ላይ ያለ ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ስራው ከተሰራበት ወይም ለህዝብ ከተሰራጨበት ግዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመታት ይሆናል።"

ከዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው የኢኮኖሚ መብቶች ግዜው መቁጠር የሚጀምረው ሞትን ወይም የመጨረሻ ህትመትን ወይም ከሞት በኃላ ለሚወጣ ህትመት ህትመቱ ለመጀመርያ ግዜ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ መሆኑን ነው።።

የቅጅና ተዛማጅ ስራዎች የኢኮኖሚ መብት እንደ ማንኛውም መብት ከባለቤቱ ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችል መብት ነው።። የሚተላለፈውም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በማስተላለፍ ወይም ፈቃድ በመስጠት ሲሆን ውሉ መመስረት ያለበትም በፅሁፍ ነው።። ይሄውም መብት በሚተላለፍበት ግዜ ፈቃድ የሰጠው ወይም የመብቱ ባለቤት የሚጠቀምባቸውን ቁሳዊ ነገሮች አያጠቃልልም።። የመብት ማስተላለፊያው ሰነድ መብቱ የሚተላለፍበትን ጊዜ በግልፅ ካልያዘ የመብቱ ይተላለፍልኝ ጥያቄ መቅረብ የሚችለው በ10 ዓመት ግዜ ውስጥ ነው:: የፈቃድ ይተላለፍልኝ ጥቄያው ደግሞ በ5 ዓመት ግዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል።። በሌላ አነጋገር የተጠቀሰው ግዜ ካለፈ በኃላ የይተላለፍልኝ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም ማለት ነው።። (አንቀፅ 23 እና 24) በዚህ መንገድ መብቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይገለገልበት ከቀረና በቅጅና ተዛማጅ መብት ባለቤት መብት ላይ ጉዳት ያደርስ እንደሆነ የስራው አመንጪ የመብቱን መተላለፍ ወይም ፈቃድ መስጠትን ሊሽረው ይችላል።።(አንቀፅ 25)

የስራው አመንጪ የኢኮኖሚ መብቶች ባለቤት ቢሆንም ባይሆንም የሞራል መብቶች አሉት።። እነዚህም:-

- **ወቅታዊ ሁኔታን በብሮድካስት አማካይነት ለመዘገብ ባጋጣሚ ወይም በድንገት ከተካተተ ስራ ውጪ የስራ አመንጪነቱ እንዲታወቅ የመጠየቅ መብት አለው ።። (አንቀፅ 8(1) (ሀ))**

- ሳይታወቅ የመቆየት ወይም የብእር ስም የመጠቀምና ክብሩንና መልካም ስሙን የሚያጐድፍ የስራ መዛባት፣ መቆራረጥ ወይም በሌላ መልክ መቀየርን የመቃወም መብት ይኖረዋል፡፡ (አንቀፅ 8(1) (ለ)(ሐ))
- ስራን የማሳተም ሞራላዊ መብት ይኖረዋል፡፡ አንቀፅ 8(1) (መ))

አንድ የቅጅና ተዛማጅ ስራዎች ባለቤት በአንቀፅ 8 ላይ የተዘረዘሩትን የሞራል መብቶች ለወራሾች ወይም የስጦታ ተቀባዮች ካልሆነ በቀር በሂወት እያለ እነዚህን መብቶች ወደ ሌላ ሶስተኛ ወገኖች ሊያስተላልፋቸው የሚችል መብቶች አይደሉም፡፡ (አንቀፅ 8(2)) የሞራል መብት የሚወረስ ወይም በስጦታ የሚሰጥ ቢሆንም የስራው አመንጪ በሂወት ባለበትና መብቱ ፀንቶ ባለበት ግዜም ሆነ ወራሾች ወይም የስጦታ ተቀባዮቹ በመብቱ የተጠቃሚነት መብታቸውን ትተነዋል ብለው ለማመልከት ይችላሉ፡፡ የሞራል መብቶች ፀንተው የሚቆዩበት የኢኮኖሚ መብቶች ፀንተው ከሚቆዩበት ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አንቀፅ 8(3) (4))

አንድን የቅጂ መብት የተሰጠበትን ንብረት ፍትሓዊ በሆነ መንገድ መገልገልን (fair use) በማስመልከት የተለያዩ አገሮች የተለያየ አሰራርን የሚከተሉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የሚሰሩበት መለክያን ወስደን ስናይ፣-

- የተጠቀመበት አላማና ባህሪው (purpose & characteristic)
- የቅጂ መብቱ ተፈጥሮ (nature)
- ከስራው የቱን ያህል ነው የተወሰደው (what amount or portion of the whole work was taken)
- በቅጂ መብቱ ላይ በገበያ የሚኖረው ዘላቂ ውጤት (the effect of the use upon the potential market for the value of the copyrighted work) የሚሉ ናቸው::

በካናዳ ለግል አገልግሎት አባዝቶ መጠቀም ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደ ሲሆን በአውስትራሊያ አባዝቶ መጠቀም የሚፈቀደው ለምርምር፣ ለጥናት፣ ተችቶ ለመፃፍ ፣ ለዜና ሪፖርትና የህግ ምክር አገልግሎት ለመስጠት ሲሆን ብቻ ነው:: በአሜሪካ ህግ 10 ቅጂ ማባዛት ለንግድ ስራ እንደተባዛ ይቆጠራል ከሚል በቀር ከዚያ በታች ማባዛት የተፈቀደ ስለመሆኑ በግልፅ የሚለው የለም:: የኢትዮጵያ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ህግም በአንቀፅ 9(1) ላይ አንድ ቅጂ (a single copy) ለግል አገልግሎት ሲባል ማባዛት የሚፈቅድ ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ህግ አለም አቀፍ መመዘኛ (International standards) ያሟላና ለስራ አመንጭነት መብት ጥበቃ የሚሰጥ ህገ-መንግስታዊ እውቅና የተሰጠው መብት ሆኖ እንደ ሌሎቹ የአእምሮ ንብረት መብቶች ሊተላለፍ የሚችልና የራሱ የሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ያለው የኢኮኖሚና የሞራል መብት የሚያስገኝ ንብረት ነው፡፡

2.2.6.2 የመብት ጥሰት መፍትሔዎች (Remedies)

የቅጅና ተዛማች መብቶች ለማስጠበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 401/96 ሶስት ዓይነት መፍትሔዎችን የሚሰጥ ሲሆን እነሱም የፍ/ብሔር መፍትሔ፤ የደንበር ላይ እርምጃና የወንጀል ቅጣት ናቸው፡፡

የፍ/ብሄር መፍትሔ

የፍታብሔር መፍትሔን በተመለከተ ስልጣኑ የተሰጠው ለመደበኛ ፍ/ቤት ሰለሆን ፍ/ቤት የመብት ጥሰት ያለመሆኑን ከማረጋገጡ በፊትና ካረጋገጠ በኃላ ሊወሰድ ከሚችለው እርምጃ ዓንፃር በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: ይሄውም ከመረጋገጡ በፊት ሊወሰድ የሚችለው በጊዚያዊነት የእግድ ትእዛዝ (interim injunction) መስጠት ሲሆን የመብት ጥስት መኖሩ ከተረጋገጠ ግን

- ባለመብቱ ያወጣውን ወጭና ለደረሰበት ጉዳት ቁሳዊና ሞራላዊ ካሳ እንዲከፈለው ይወሰናል::
- ያለ ባለመብቱ ፈቃድ እንዳይባዛ ወይም ከአገር ውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተባለን ነገር ያስገባ ወይም ያሰራጨ ካለ እንዲወረስ ያዛል ::
- ከቅጅ መብት ጋር የተያያዙ የሂሳብ መግለጫዎች ሰነዶች፤ የንግድ ስራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወረቀቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና እሽጉች እንዲያዙ ትእዛዝ ይሰጣል::
- አመልካች ከካሳው በተጨማሪ ያለአግባብ በልፅጓል ሲል የከሰሰ እንደሆነ ፈቃድ ቢሰጠው ሊከፍል ይችል የነበረውን ያህል እንዲከፍለው ይወስናል ::
- ባለቤቱ ከተጠርጣሪው የተገኘውን ትርፍ ብቻ እንዲከፈለው በጠየቀ ጊዜ እንዲከፍለው መወሰን፡፡ ተከሳሹ የተጠየቀው ትርፍ በሌላ ገበያ የተገኘ ሂሳብ ነው የሚል ከሆነ የማስረዳት ሸክም በተከሳሹ ላይ ይወድቃል፡፡
- ይሄውም ለባለመብቱ የሚከፈለው ካሳ ለደረሰበት ጉዳትና በመጣሱ ሌላው ወገን ያገኘውን ትርፍ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡
- የቅጅ መብት በመጣሱ ምክንያት የሚከፈል ሞራል ካሳ ከ 100.000 ብር ያላነሳ ሆኖ የደረሰውን ጉዳት መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡
- ሆኖም ግን መብት የጣሰው ሰው ድርጊቱን የፈጸመው ባለማወቅ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ ፍ/ቤቱ ያገኘውን ትርፍ ብቻ እንዲመልስ ሊወሰን ይችላል፡፡
- ቅጅዎችን ወይንም ጥቅሎቹን በቅጅ ባለመብቱ ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ከንግድ እንቅስቃሴ ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዲወገዱ ወይም በሌላ ተገቢ አኳኋን እንዲጣሉ ለማዘዝ ይችላል፡፡ ይህ ቅጅዎችን በቅን ልቦና በያዘ 3ኛ ወገን ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ (አንቀፅ34)

የደንበር ላይ እርምጃ

- በቅጅ ባለመብቱ በሚቀርብለት ማመልከቻ የጉምርክ ባለስልጣን ቅጅዎችን በቁጥጥር ስር ያደርጋል::
- ይህን እርምጃ መውሰዱ ለአመልካቹ ወይም የዕቃው ባለቤት ወድያውኑ ያሳውቃል::
- አመልካቹ በ10 ቀናት ውስጥ ህጋዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ካልቻለ እቃውን ለመያዝ የተወሰደው እርምጃ ይነሳል ::
- አመልካች ያቀረበው ማመልከቻ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሲሆን በመያዙ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል::
- በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሰረት የጉምሩክ ባለስልጣን መብት የጣሰን ዕቃ መውረስ ይችላል:: (አንቀፅ35)

የወንጀል ሃላፊነት

- የወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ሆን ብሎ የቅጅ መብትን የጣሰ ሰው ከ 5 ዓመት ባላነሰ እና ከ10 ዓመት ባልበለጠ ፅኑ እስራት ይቀጣል::
- የወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በከፍተኛ ቸልተኝነት በዚህ አዋጅ ጥበቃ የተደረገላቸው የቅጅ መብቶችን የጣሰ ከሆነ ከ 1ዓመት በማያንስና ከ 5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሰራት ይቀጣል::
- አግባብነት ባለው ግዜ ወንጀሉን ለመፈጸም ያገለገሉ ዕቃዎችን መሳሪያዎችን መብት የጣሱ ዕቃዎችን መያዝ፣ መውረስና ማውደምን ይጨምራል:: (አንቀጽ36)

ስለዚህ የኢትዮጵያ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ህግ አለም አቀፍ መመዘኛ (International standards) ያሟላና ለስራ አመንጭነት መብት ጥበቃ የሚሰጥ ህገ-መንግስታዊ እውቅና የተሰጠው መብት ሆኖ እንደ ሌሎቹ የአእምሮ ንብረት መብቶች ሊተላለፍ የሚችልና የራሱ የሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ያለውና የኢኮኖሚና የሞራል መብት የሚያስገኝ ስራ ነው:: የመብቱ ተጠቃሚዎች የፍታብሄር መፍትሄ የሚያገኝ መሆናቸው በተጨማሪ የመብቱ ጥሰት የወንጀል ተግባርን ያካተተ ከሆነ በወንጀል ተጠያቂ የማስደረግን መብት የሚያጐናፅፍ ነው::

2.2.7 የንግድ ምልክት (Trade Mark)

የንግድ ምልክት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 በአንቀፅ 2(12) ላይ:-

> *የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው:: ምልክቱ ቃላቶችን፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣*

ቀለሞችን ወይም የፅቃዎችን ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርፅ ወይም የእነዚህኑ ቅንጅት ሊይዝ ይችላል፡፡ በማለት ሲተረጉመው ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ Wikipedia the free encyclopedia

Trade mark is a distinctive sign or indicator of some kind which is used by an individual, business organization or other legal entity to identify uniquely the source of its products and/or services to consumers, and to distinguish its products or services from those of other entities.

ሲል የንግድ ምልክት ምንነትን ይገልፃል፡፡ ስለሆነም የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ምርት ወይ አገልግሎት ወይም ምንጭ (origin) **በማስመዝገብ እንደ ብቸኛ መለያ** (exclusive sign) **ተወስዶ ሰዎች አንድን ምርት ወይም አገልግሎት ከሌላው ምርትና አገልግሎት ለመለየት የሚያገለግል ምልክት ሆኖ ማሳከር** (confusion) **የማስወገድ አላማ ያለው ነው፡፡**

የንግድ ምልክት ህጋዊነት የሚመሰረተው ወይም ጥበቃ የሚያገኘው በምዝገባ እንደሆነ ከአዋጁ አንቀፅ 4፣ 5፣ 15 **እና** 16 *መረዳት* **የሚቻል ሲሆን** Wikipedia **ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ የንግድ ምልክቶች የሚባሉ እንዴት ያሉ ምልክቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ልክ በአንቀፅ** 2(12) **እንደተዘረዘረው፡-**

''A trade mark is a type of intellectual property, and typically comprises a name, word, phrase, logo, symbol, image or combination of these elements.''

በማለት የንግድ ምልክቶች ምን ዓይነት ሊሆኑ እንደሚችሉ መዘርዘሩ ህጋችን የቱን ያህል አለማቀፋዊ መመዘኛዎችን (international standards) **ያሟላ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡**

የንግድ ምልክት አላማም ፅቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች መልካም ስም እና ዝና ለማስጠበቅና በተመሳሳይ ፅቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል መሳከር (confusion) **በማስወገድ የንግድ ስራ የነፃ ገበያ ስርዓትን መርህ ተከትሎ እንዲሄድና የሸማቾችን ምርጫ ማስጠበቅም ነው:: ብሄራዊ ጥቅም በተለይም የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂን እውን የማድረግ አላማም ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ጤናማ፣ ነፃ ውድድርና በእውቀት ላይ የተመሰረተ የግብይት ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ህጉ በሚያዘውና ግልፅ በሆነ የንግድ ምልክት ላይ ተመስርቶ ማምረትና አገልግሎት መስጠት ለአንድ ህብረተሰብ እድገት ቁልፍ መሳርያ ነው፡፡ በመሆኑም በነፃ ገበያ መርህ መሰረት ጤናማ የምርትና አገልግሎት ውድድር በማካሄድ ህብረሰተቡ ሰፊ አማራጭ አግኝቶ ለከፈለው ዋጋ የሚመጥን እቃ ወይም አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ የአዋጅ ቁጥር** 329/95 **የንግድ አሰራር መርህን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡**

2.2.7.1 የንግድ ምልክት ምዝገባ

ለምዝገባ ብቁ መሆን የሚቻለው፤-

- የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በግልፅ ለመለየት የሚያስችል መሆን ለመመዝገብና ህጋዊ ጥበቃ ለማግኘት አንዱ መስፈርት ነው፡፡ (አንቀፅ 5(1))
- አንድ የንግድ ምልክት በጥቁርና ነጭ ወይም በከለር ቀለም ሊመዘገብ ይችላል:: በጥቁርና ነጭ ቀለም የተመዘገበ የንግድ ምልክት በማናቸውም የቀለሞች ቅንጅት ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን የንግድ ምልክቱ የተመዘገበው በከለር ቀለም ከሆነ ጥበቃ የሚደረግለት በተመዘገበው የከለር ቀለም ቅንጅት ብቻ ይሆናል፡፡ (አንቀፅ 5(2))
- አንድ ሊመዘገብ የሚችል የንግድ ምልክት የምልክቱ ልዩ ባህሪ የሚቀንስ ወይም የሌላ ሰውን መብት የሚጥስ እስካልሆነ ድረስ ጥበቃ ሊደረግላቸው የማይችሉ ክፍሎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ (አንቀፅ 5(3))

ለምዝገባ ብቁ ስለማይሆኑ የንግድ ምልክቶች በማስመልከት አዋጁ በአንቀፅ 6 ላይ የዘረዘራቸውን ስንመለከት ደግሞ:-

- በአንቀፅ 5 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የማያሟላ ሲሆን ምልክቱ በንግድ ምልክትነት አይመዘገብም፣
- ድምፅ ወይም ሽታን የያዘ የንግድ ምልክት አይመዘገብም፣
- ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግልቶች ለመለየት የማያስችል ከሆነ የንግድ ምልክቱ አይመዘገብም፣
- የህዝቡን ሰላምና ስነ-ምግባር የሚፃረር ሲሆን እንደዚሁ አይመዘገብም ፣
- የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ዓይነቶች፣ ጥራት፣ ብዛት፣ ጠቀሜታ፣ ዋጋ ወይም የመነጨበትን ቦታ፣ የተመረተበት ወይም የሚቀርብበትን ግዜ ወይም ባህሪ ብቻ የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣
- የንግድ ምልክቱ የሚመለከታቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በሚመለከት ወይም በኢኮኖሚያዊ ወይም የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተለመዱና በጋራ መግባቢያ ቋንቋነት የሚያገለግሉ ምልክቶች ወይም መለያዎች ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት ሲሆን፡፡
- ከዕቃው ተፈጥራዊ ሁኔታ የመነጨ ወይም የአንድን ዕቃ ቴክኒካዊ ውጤት ለማግኘት አስፈላጊ የሆነን ወይም ዕቃው ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚጨምርን ቅርፅ ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት::
- የዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ የመነጨበት ቦታ ወይም ዓይነትና ባህሪ በተለመከተ ህዝቡን ወይም የንግዱን ማህበረሰብ ሊያሳሳት የሚችል የንግድ ምልክት ሲሆን፡፡
- ከአሁን ቀደም በተዘጋጀ አፊሴላዊ ምልክት የተመዘገበ የማንኛውም ሀገር መንግሰት፣ በይነ-መንግስታዊ ድርጅት ወይም በአለም አቀፍ ስምምነት የተቋቋመ ድርጅት፣

ወታደራዊ ምልክት፣ ሰንደቅ አላማ፣ ሌላ አርማ፣ ስም፣ ምህፃረ ቃል፣ የስም አህፅሮት መሰረት ያደረገ የንግድ ምልክት ሲሆን፡፡

- የአመልካቹ የቤተዘመድ ስብ ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት
- ያለ ግለሰቡ ፈቃድ የአንድን በህይወት ያለ ግለሰብ ሙሉ ስም የያዘ የንግድ ምልክት ሲሆን በህግ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ አመልካች እንዲመዘገብለት የሚያቀርበው ምልክት የሶስተኛ ወገን መብት የሚነካ በሚሆንበት ግዜ አይመዘገብም:: ከዚህ አኳያ ህጉ የሶስተኛ ወገኖችን መብት በመጠበቅ የንግድ ምልክት እንዳይደረግ የሚከለክልባቸው ሁኔታዎች በአንቀፅ 7 ላይ የተዘረዘሩ ሲሆን እነሱም፤
- ቀደም ሲል ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሲሆንና ማሳከርን (confusion) የሚፈጥር ሲሆን፤
- የንግድ ምልክቱ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆነ የሌላ ሰው እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ፤
- በባለቤቱ በፅሁፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚደረግለትን የሌላ ሰው የስነ-ፅሁፍ ወይም ኪነ-ጥበባዊ መብት ወይም የሌላ ሰውን የፎቶግራፍ ወይም የዲዛይን መብት የያዘ ነው ተብሎ ሲታመን የንግድ ምልክቱ አይመዘግብም፡፡ ያለመመዝገብ ህጋዊ ውጤት እንደሚታወቀው የህግ ጥበቃ አለማግኘትና ከህግ ጋር በሚፃረርበት ግዜ ደግሞ ለፍ/ብሄርና ወንጀል ተጠያቂነት የሚዳርግ ነው፡፡

2.2.7.2 ምዝገባ የሚያስገኘው መብት

- ባስመዘገበው የንግድ ምልክት የመጠቀም ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀበት የመፍቀድ መብትን ያስገኛል፡፡
- ሌሎች ወገኖች የንግድ ምልክቱን በሚያሳስት መንገድ እንዳይጠቀሙና ህዝቡን እንዳያሳስቱ የማድረግ መብትን ያጐናፅፋል፡፡
- ሌሎች ሰዎች የባለቤቱን ጥቅምን በሚጐዳ አኳኃን እንዳይገለገሉበት የማድረግ መብት ይሰጣል፡፡
- ሌሎች መሰል ድርጅቶች ተመሳሳይ ምልክት ተጠቅመው ማሳከር በመፍጠር መብቱ እንዳይጐዱ ለማገድ የሚያስችል መብት ያስገኝለታል::
- የንግድ ምልክት ማሳከር (confusion) ተፈጥሯል ባለበት ግዜ ክስ የመመስረት መብት ይኖረዋል፡፡ (አንቀፅ 26)

የአንድ የንግድ ምልክት መመዝገብ ከፍ ብለን ያየናቸውን መብቶች የሚያስገኝ ቢሆንም መብቶቹ ያለገደብ የተሰጡ አይደሉም፡፡ በመሆኑም አንቀፅ 27 በምዝገባ የተገኙ መብት ገደብን በማስመልከት የንግድ ምልክቱን በመያዝ በእቃዎቹ ምንጭ ዓይነት ለውጥ ሳይደረግባቸው በማንኛውም አገር በመሸጥ ላይ ባሉ ሶስተኛ ወገኖች ላይ የንግድ ምልክቱ

ባለቤት የመከልከል መብት አይኖረውም፡፡ እንዲሁም ሶስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና ዕቃቸውን ወይም አገልግሎታቸውን ምንጭ በማያሳስት መንገድ ለማስተዋወቅ ወይም ለመረጃ አላማ እንዳይገለገሉበት የንግድ ምልክት ባለቤቱ መከልከል አይችልም፡፡ ይህ ማለት ግን ሶስተኛ ወገኖች በነዚህ ገደቦች ሽፋን በባለመብቱ ላይ ጉዳት እዲያደርሱ ህጉ ፈቅዷል ማለት አይደለም፡፡

የንግድ ምልክት በምዝገባ መብቶችን ሲያስገኝ ገደቦች ያሉበት እንደመሆኑ ሁሉ የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ፈራሽ የሚሆንባቸው ሁኔታዎችና የምዝገባው ፈራሽነት ውጤት ምን እንደሆነም በህጉ ሽፋን ተሰጥቶታል፡፡ ምዝገባው ፈራሽ የሚሆነው በአዋጁ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሳያሟሉ የቀሩ እንደሆነ ምዝገባው ፈራሽ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ምዝገባው በከፊል ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ ከሆነ ባልተመዘገቡት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ የንግድ ምልክቱ በከፊል ፈራሽ ይሆናል፡፡ (አንቀፅ 36) የምዝገባው ፈራሽነት ውጤትም ውሳኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው የንግድ ምልክቱ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ይህም ማለት የምዝገባው ፈራሽነት ወደ ኃላ ተመልሶ ውጤት (retroactive effect) ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ የሶስተኛ ወገኖች መብትን ለመጠበቅ የንግድ ምልክቱ ፈራሽ ስለመሆኑ በአእምሮ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በማውጣት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ በዚህ መንገድ ፈራሽ የሆነ የንግድ ምልክት ባለቤት በፈቃድ ውል ምልክቱን የሰጠው አካል ይህን የንግድ ምልክት እንዲከፍል ያደረገው ገንዘብ ቢኖርም ይመለስልኝ ብሎ መጠየቅ ግን አይችልም፡፡ ስለዚህ የንግድ ምልክት ፈራሽ መሆን ሁለት ውጤቶች ያሉት ሲሆን እነሱም ወደ ኃላ ተመልሶ የመስራትና ለምዝገባው ሲባል የተከፈለ ገንዘብ ካለም የማይመለስ መሆኑ ናቸው፡፡ (አንቀፅ 37) ከፍ ብለን የተመለከትናቸው የምዝገባ ውጤቶች ወይም መብቶች፣ ገደቦቻቸው፤ ፈራሽነትና ውጤቱን ሲሆን የንግድ ምልክት ምዝገባ ሊታደስ፣ ሊተውና በጥቅም ላይ ባለመዋሉ ምክንያት ስለሚሰረዝበትና በዚህ መብት የመጠቀም በሙሉ ወይም በከፊል መብት በመስጠት ወይም ፈቃድ በመስጠት ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ስርዓትም በህጉ (በአንቀፅ 20፣ 25፣ 34፣ 35፣ 28) ላይ በዝርዝር ተደንግገው የምናገኛቸው ናቸው፡፡ የንግድ ምልክት እንደሌሎች የአእምሮ ንብረቶች የራሱ የሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ያለው ሲሆን አንቀፅ 24 ይህን በማስመልከት "በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ 35 እስከ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ምልክት ምዝገባ ፀንቶ የሚቆየው የምዝገባው መመልከቻ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለሰባት ዓመታት ይሆናል " ሲል የሚደነግግ ሲሆን አንቀፅ 35 ጥቅም ላይ ያልዋሉ የንግድ ምክቶች ስለሚሰረዙበት ሁኔታ የሚደነግግ ህግ እንደመሆኑ መጠን አንድ የተመዘገበ የንግድ ምልክት በስራ ላይ ባልዋለበት ግዜ የግድ ፀንቶ የሚቆይበት 7 ዓመት መጠበቅ ሳያስፈልግ ሊሰረዝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በአንቀፅ 36 እንደዚሁ አንድ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ፈራሽ ስለሚሆንበት ሁኔታ የሚደነግግ በመሆኑ በዚህም ሁኔታ ፀንቶ የሚቆይበትን 7 ዓመት መጠበቅ አስፈላጊ ያለመሆኑን ይገልፃል፡፡ አንቀፅ 37 ስለፈራሽነት ውጤት የሚደነግግ

በመሆኑ የንግድ ምልክቱ ፀንቶ ባይቀጥልም በመፍረሱ ምክንያት የሚኖረው ውጤት ወደ ኃላ ተመልሶ እንዳልተመዘገበ እንደሚቆጠርና በምዝገባው ምክንያት የተከፈለው ገንዘብ የማይመለስ ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ የአንቀፅ 24 ሐሳብ ፀንቶ የሚቆየው ለሰባት ዓመታት ቢሆንም በመሃል ግን የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ሊሰረዝ፣ ፈራሽ ሊሆንና የፈራሽነት ውጤት ሊኖው እንደሚችል የሚደነግግ ነው።

የንግድ ምልክት ምዝገባን በማስመልከት መዝጋቢው ፅ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በይግባይ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት መሄድ ይችላል:: ስለዚህ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት በሶስተኛ ወገኖች ለሚደርስ ጥሰት የፍታብሄር መፍትሄ (civil remedies) እና የወንጀል ቅጣት (criminal sanctions) በማስከተል የፍታብሄርና የወንጀል ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ ህግ ከፍተኛ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ የሚያደርግለት መብት ነው።(አንቀፅ 17፣ 40 እና 41)

እስከ አሁን ያየናቸውን አጠር ባለ መንገድ ለማስቀመጥ የንግድ ምልክት እንደሁሉም የአእምሮ ንብረቶች ከምዝገባ በኃላ የሚገኝ የግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሆኖ በሂደት ሊሰረዝ፣ ፈራሽ ሊሆን፣ ሊተውና ሊታደስ የሚችል መብትና ግዴታ ያለበት በመጨረሻም ከ7 ዓመት በኃላ ካልታደሰ መብቱ ቀሪ የሚሆንና ህግ የፍታብሄርና የወንጀል ጥሰት እንዳይገጥመው በፍትህ ስርዓቱ ከፍተኛ የሆነ ጥበቃ ተሰጥቶት የአገር ኢኮኖሚ ጤናማ በሆነ የግብይት ስርዓት ላይ እንዲመሰረትና የሸማቶችን መብት ከማሳከር (confusion) ነፃ በሆነ መንገድ በነፃ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ የፅቃ ወይም የአገልግሎት ምርጫ እንዲካሄድ የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ለኢኮኖሚ ልማቱ ስኬት የግብይት ስርዓቱ የነፃ ገበያ መርህን ተከትሎ እንዲሄድ የማድረግ አለማና ግብ ያለው ነው::

2.2.7.3 የመብት ጥሰት መፍትሄዎች (Remedies)

የንግድ ምልክትን መሰረት በማድረግ ክርክር በሚነሳበት ጊዜ ፍ/ቤት እና የጉምሩክ ባለስልጣን ጊዜያዊ መፍትሄዎች ሊሰጡ እንደሚችሉና ዘላቂ መፍትሄም በፍ/ቤት ሊሰጥ እንደሚችል ይኸውም የፍ/ብሄር እና የወንጀል መፍትሔ ብሎ ማስተናገድ እንደሚቻል አዋጁ በግልፅ ይደነግጋል።

የፍ/ብሄር መፍትሔ

በዚህ አዋጅ መሰረት በጊዜያዊ የፍ/ብሄር መፍትሔነት የሚወሰዱት ጊዜያዊ እርምጃዎች ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ የሚሰጥ ጊዜያዊ እግድ (interim injunction) ሲሆን ይኸውም አዋጁ በአንቀፅ 39(4) (ሀ)ላይ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ155 (1) ከተደነገገው በተሻለና ግልፅ በሆነ መንገድ እግድ ለመስጠት አደጋ ላይ የወደቀው ጥቅም በካሳ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ አደጋው የማይቀር መሆኑ ሲረጋገጥ፣ የክሱን ጥንካሬና ውሳኔ መስጠት በእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በመመርመር እግድን መስጠት እንደሚቻል የሚደነግግ በመሆኑ በፍ/ቤት ስልጣን ላይ ልዓም ያበጀ ነው።

የሁለቱ ተከራከሪዎች አቋም ተመሳሳይ በሚሆንበት ጊዜም ፍ/ቤት ጠለቅ ያለ ምርመራ (deep investigation) ማካሄድ እንዳለበት አዋጁ በአንቀፅ 39 (4) (ሐ) ላይ ግዴታ የሚጥል በመሆኑ በዚሁ አዋጅ የሚሰጥ እግድ ስለተጠየቀ ብቻ የሚሰጥ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የንግድ ምልክት ክርክር በሚኖርበት ጊዜ ሌላው ሊወሰድ የሚችል መፍትሔ ንብረቱ ዋስትና ተደርጐለት ለ10 ቀናት በጉምሩክ ተይዞ እንዲቆይ ማድረግ ሲሆን ከሳሽ ወይም መብቱ ተጣሰ በማለት አቤቱታውን ለጉምሩክ ባለስልጣን ያመለከተ ሰው በዚያ 10 ቀን ውስጥ ከፍ/ቤት ትዕዛዝ ካላመጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ገቢ ሆኖ ንብረቱ ለሌላው ወገን ይመለስለታል:: (አንቀፅ 42(1)) የዚህ ህግ ፋይዳም ባለመብቱ የእፎይታ ጊዜ(breathing time) አግኝቶ ጉዳዮን ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብና መመዘኛዎቹን አሟልቶ ከተገኘ ከፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ በማውጣት በመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ጊዜ መስጠት ነው፡፡ ሌላው በአዋጁ ያለ ጊዜያዊ መፍትሔ ፍ/ቤት ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ ምክንያት አንደኛው ወገን መብቱ ተጥሷል በማለት ያመለከተ እንደሆነ በአንቀፅ 39(1) (ለ) እና 39(5) መሰረት ለክርክር መነሻ የሆነው ንብረት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161(1) (ሀ) እና በወ/ሰ/ሰ/ህ/ቁ32 መሰረት እንዲበረብርና እንዲያዝ እንዲሁም እንዲታሰር ወይም እንዲታቀብ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለፍ/ቤቱ ስልጣን የሚሰጥ በመሆኑ አንድ የንግድ ምልክት ባለቤት መብቱ እንዲሁ እንዳይጣስ የህግ ከለላ የሚሰጠውና በዘላቂነትም በፍ/ቤት ውሳኔ መብቱን እንዲያስከብር የሚያስችል ነው፡፡ እስካሁን ያየናቸው አንድ የንግድ ምልክት ባለቤት መብቱ ተጥሷል ባለበት ጊዜ ስለሚያቀርበው ክስና ጊዜያዊ መፍትሔ:: ቀጥለን ስለሚኖሩት ዘላቂ መፍትሔዎች (Final Remedies) እናያለን፡፡

አንዱ መፍትሔ በፍ/ ቤት ክሶ ለደረሰበት ጉዳት ካሳ እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው የንግድ ምልክት ባለቤቱን መብት መጣሱ ከታወቀ በዚያ ጊዜ ውስጥ ያገኘውን ትርፍ(Account of Profit) እንዲመለስ ማድረግ ሲሆን የዚህ ዓይነቱ መፍትሔ በአፈፃፀም ላይ አንድ ህገ ወጥ ስራን የሚሰራ ሰው የንግድ ሒሳብ ደብተር ይይዛል ተብሎ ስለማይገመት ስሌቱ ለማወቅ አስቸጋሪ የሆነ የመፍትሔ አገባብ ነው፡፡ ገንዘባዊ ጥቅም ካላቸው መፍትሔ በተጨማሪ ፍ/ቤት የእንዲታወቅ ፍርድ (declaratory judgment) በመስጠት የንግድ ምልክት መብት በሶስተኛ ወገኖች እንዳይጣስ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አዋጁ በፍ/ብሄር መፍትሔነት ያስቀመጣቸው እግድ (injunction) እና ካሳ (compensation) ሲሆኑ በአንቀፅ 40(2) ያለው የካሳ አከፋፈል ስርዓት በፍ/ብ/ህ/ቁ 2091 ከተደነገገው ጉዳት ካሳ = የጉዳት መጠን ከሚለው መርህ ማፈንገጥ (deviation) የሚስተዋልበት ነው፡፡ ይኸውም የንግድ ምልክት መጣስን ተከትሎ የሚመጣ የካሳ አከፋፈል ስርዓት መሰረቱ ጉዳት (damage) መሆኑ ቀርቶ መብት ጥሷል የተባለው ሰው መጣሱ ከተረጋገጠ በዚያ ንግድ ምልክት ጥሶ በመነገድ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ በሙሉ እንዲከፍል በማድረግ ወይም ፈቃድ ተሰጥቶት ቢነግድ ይከፈል ከነበረው ኪራይ(royalty) የሚበልጥ እንዲከፍል በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ስሌቱ “Compensation equals to damage” መሆኑ ቀርቶ የዚህ አዋጅ መርህ ለየት ባለ መንገድ

ስለቱ “Compensation equal to net Profit or royalty +” ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ምልክት አዋጅ ቁጥር 501/98 የሚከተለው የካሳ አከፋፈል ክልሰ ሓሳብ (theory) ያለአግባብ መበልፀግን the theory of unlawful enrichment ክልስ ሐሳብ ሲሆን የፍ/ብሄር ህጉ የሚከተለው የጉዳት ካሳ አከፋፈል the theory of damages ክልስ ሓሳብን የተከተለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ በአንቀፅ 40(1) ላይ ልክ በፍ/ብሄር ህጉ አንቀፅ 2121 ላይ እንደተደነገገው ዘላቂ እግድ (permanent injunction) ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ “ ተከሳሹ የመብት መጣስን ድርጊት እንዲያቆም ሊወሰን ይችላል በማለት ስለሚደነግግ ለባለ መብቱ ከፍተኛ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ የሚሰጥ ነው፡፡

የፍ/ብሄር መፍትሔን በማስመልከት ስለሚኖሩ ጥሰቶችና መፍትሄዎቻቸው እንደተገለፀው ሆኖ የንግድ ምልክት ባለቤቱን መልካም ስምና ዝናን (reputation of honor) እንዲመለሰልት ፍ/ቤት ፍ/ብ/ህ/ቁ 2120 እና ን/ህ/ቁ/134(2) (ሀ) በሚያዙት መሰረት በማስታወቂያ እንዲወጣና ህዝቡ እንዲያውቀው እንዲደረግ ለማዘዝ ስለሚችል የንግድ ምልክቱ ባለቤት በዚህ ራሱን መልሶ ወደ ገበያው በማስገባት ለበለጠ ጥቅም ሊሰራ የሚያስችለውን ሁኔታ እንዲመቻችለት ያደርጋል፡፡

የወንጀል ሃላፊነት

በመጨረሻም አዋጁ የንግድ ምልክት ጥሰትን መሰረት በማድረግ የፍ/ብሄር መፍትሄዎች እንደሚደነገግ ሁሉ በአንቀፅ 41 ላይ ወንጀልን በማስመልከት የንግድ ምልክት መብት ጥሏልተብሎ የተጠረጠረው ሰው ድርጊቱ መፈፀሙ ሲረጋገጥ በወ/ህ/ቁ 720 መሰረት ሆነ ብሎ የጣሰ ከሆነ ከ5 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡ አንዲሁም ወንጀሉን ለመፈፀም ያገለገሉ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎችና መብት የተጣሰባቸውን ዕቃዎች መያዝ፣ መውረስና እና ማስወገድን ያጠቃልላል ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ የሚያሳየው የንግድ ምልክት መጣስ የቱን ያህል እንደሚያስቀጣ ብቻ ሳይሆን ህጉ ህዝቡ በህጋዊ የንግድ ምልክት ባልተጠቀሙ ግለሰቦች እንዳይታለልና ያልሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት በመግዛት ሊደርስበት ከሚችል ጉዳት ለመጠበቅ የቱን ያህል ክብደት እንደሰጠ ነው። ከዚህ ህግ በስተጀርባ ያለው ህዝባዊ ፖሊስ ስግብግብ ነጋዴዎችን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ በማድረግ ህ/ሰቡን የነፃና ፍትሐዊ ግብይት ስርዓት ተጠቃሚ ማድረግም ጭምር ነው። ስለዚህ የአእመሮ ግዙፍነት የሌላቸው የሚንቀሳቀስ ንብረቶቸ መብት የንግድ መደብር መብቶችም ስለሆኑ በንግድ ህጉ ከተሰጣቸው የህግ ሽፋን በላይ በነዚህ አዋጆች ጥበቃ የተደረገላቸው በመሆኑ በዚህ ርእሰ ጉዳይ የሚነሱ አለመግባባቶች በንግድ ህጉና ሌሎች አዋጆች መፍትሄ ሊያገኙ ይገባለ፡፡

2.3 በንግድ መደበር ላይ የሚደረግ የዋስትና መያዣ

የንግድ ህጉ በንግድ መደብር ያለን መብት በመያዣ ዋስትና ማስያዝ እንደሚቻል በን/ህ/ቁ 179 እና ቀጥሎ ባሉ ድንጋጌዎች የሚፈቅድ መሆኑ ከእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል ።።የዚህ ዓይነት መያዣ ምዝገባን በማስመልከት በነጋሪት ጋዜጣ እንደሚወጣ በን/ህ/ቁ 1175 ላይ ተደንግጎ ለዓመታት ህጉ በነጋሪት ሳይወጣ መቆየቱ ካለው እውነታ ለመረዳት የሚቻል ሐቅ ነው።። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ከወጣ በኋላ ግን በንግድ ተቋማት ዙርያ የሚታየውን ክፍተት ለሞምላትና ለኦኮኖሚው እንቅስቃሴ አመች ሁኔታ ለመፍጠር የንግድ ተቋሞቻቸውን በባንክ በዋስትና ካስያዙ ባለዕዳዎች ላይ ጥሩ የንግድ አሰራር ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ኣዋጅ ቁጥር 98/90 ወጥቶ በስራ ላይ ከዋለ እንሆ አሰርት ዓመታትን አስቆጥሯል።። በዚህም መሰረት በኣዋጁ አንቀፅ 2(1) ላይ ለንግድ ተቋሞ ማለት በ1952 ዓ.ም በወጣው የንግድ ሕግ የተመለከተው የንግድ መደብር ነው" በማለት ፍችው የሚሰጥ ሲሆን በአንቀፅ 2(5) ላይ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ኣካል ነው ይላል።።

አንድን የንግድ ተቋም በመያዣነት ለማስመዝገብ የንግድ ፍቃድ ለመስጠት በህግ ስልጣን ከተሰጠው የንግድ ፍቃድ መኖርን የሚጠይቅ ሲሆን ለመመዝገብ በኣዋጁን ኣንቀፅ 5 እና 6 መስፈርቶችንና መሟላት ያለባቸውን ነገሮች እንዲሟሉ ህጉ ያስገድዳል።። በዋስትና መያዣነት በን/ህ/ቁ 175(1) (ሰ) እና 178(1) (ሠ) መሰረት የተሰጠን ንብረት ገንዘብ ጠያቂው መለያ ምልክት (identification mark) ሊያደርግባቸው ይችላል።። በኣዋጁ አንቀፅ 13 መሰረት ን/ህ/ቁ 189 ቢኖርም የመያዣ ዋስትና መያዣ ያለው ገንዘብ ጠያቂ ባንክ የሚፈልገው ገንዘብ ሳይከፍል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቅያ ለባለ ዕዳው በመስጠት ንብረቱን በሓራጅ የመሸጥና ንብረቱን ወደ ገዢ የማስተላለፍ ወይም በመጀመርያው የሓራጅ ሽያጭ ገዥ ከጠፋ ንብረቱን በዋስትና በሰጠው መጠን የባለቤቱን መብት በስሙ እንዲዛወር ያደርጋል።። ይህ ኣዋጅ ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ስትከተለው ከነበረው የመያዣ ንብረት በፍ/ቤት ኣሸጠ ዕዳን መክፈል (Judicial foreclosure) ወደ ገንዘብ ጠያቂው በዋስትና የያዘውን የንግድ ተቋም በራሱ ኣሸጠ ገንዘቡን ገቢ ወደሚያደርግበት (power of sale foreclosure) እንዲሸጋገር ያደረገ አሰራር ነው።።

ይህ ኣዋጅ ወደኋላ ተመልሶ ስለሚኖረው ውጤትም በአንቀፅ 14 ላይ ከኣሁን ቀደም በን/ህ/ቁ 1175(2) መሰረት ተመዝግበው የነበሩትን የንግድ ተቋም መያዣዎች ከ30 ቀን ላላነሰ ጊዜ ማስጠንቀቅያ በመስጠት ልክ በኣዋጁ አንቀፅ 13 ከተገለፀው ባልተለየ መልኩ ለባንክ መብት የሚሰጥ ነው።። ባንክ በዋስትና መያዣ የያዘውን ንበረት በሓራጅ በሚሸጥበት ጊዜ እንደኣግባብነታቸው ፍ/ብ/ሰ/ሰ/ሕ/ቁ 394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ሂደቱን መምራት እንደሚጠበቅበት የኣዋጁ አንቀፅ 16 የሚደነግግ በመሆኑ የባለእዳዎች መብት የሚያስጠብቅ ስለመሆኑ ግልፅ ነው።። አንድ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ግልፅ መሆን ያለበት

ጉዳይ በኢትዮጵያ የንግድ ተቋም በዋስትና መያዣነት የመስጠትና የምዝገባ ስርዓት ውሉ የሚደረገው ከባንክ ጋር በሚሆንበት ጊዜ የኣዋጅ ቁጥር 98/90 ድንጋጌዎችን መከተል የግድ የሚል መሆኑና ውሉ የሚደረገው ከባንክ ውጭ ከሆነ ሰው ጋር በሚሆንበት ግዜ ግን የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ማስተናገድ ስለሚኖርብን የፍትህ ስርዓቱ ሁለት የንግድ ተቋም የዋስትና መያዝን ምዝገባን አሰራር የሚከተል መሆኑ ነው፡፡ በዋስትና የተያዘን ንብረት አሸጦ ለእዳ መክፈያነት ማዋል(foreclosure) ምን ማለት እንደሆነ ስንመለከት፤-

> *Foreclosure is defined as to shut out, to bar, to destroy an equity of redemption, a termination of all rights of the mortgagor or his guarantee in the property covered by the mortgage… the term is also loosely applied to any of the various methods, statutory or otherwise known in different jurisdictions, of enforcing payment of the debt scurried by a mortgage by taking and selling the mortgaged estate. የሚል ትርጉም ያለው ነው፤፤*

የመያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ዓይነቶችም ጥብቅ መያዣን ለዕዳ መክፈያ ማዋል(Strict foreclosure) ይህ ዓይነት የመያዣ ዕዳ መክፈያነት ማዋል በፍርድ መያዣ ተቀባዩ በመያዝነት የያዘውን የንብረት ባለቤትነት ወደ እሱ እንዲዛወርለት አመልክቶ ዕዳ ከፋዩ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የመፈፀምያ ጊዜ ውስጥ ዕዳው ሳይከፍል ቢቀር መያዣ ተቀባዩ (ገንዘብ ጠያቂው) በመያዣነት ባስያዘው ንብረት ላይ ለመጨረሻ ግዜ የባለቤትነት መብቱ የሚያጣበት የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ዓይነት ነው፡፡ ጥብቅ የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ያለው ጠንካራ ጎን አሰራሩ መያዣ ተቀባዩን(ባለሃብቱን) በመያዣነት የያዘውን ንብረት ለዕዳ መክፈያነት ንብረቱን እንዲወስድ የሚፈቅድ አሰራር ስለሆነ ባለ ሃብቱን ንብረቱን ሲሸጥ የሚያወጣውን ወጪ የሚቀንስ ከመሆኑም ባሻገር በፍርድ ሂደት የሚጠፋውን ረጅም ግዜና ክፍያ እንዲቀንስለት የሚያደርግ አሰራር ስለሆነ ከባለ ሃብቱ ጥቅም አኳያ ስታይ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ አሰራር ካለው ደካማ ጎን አንፃር ሲታይ ደግሞ በመያዣነት የተያዘውን ንብረት የዕዳው መክፈያ ግዜ በማለቁ ብቻ የአንድን ሰው ሃብት ዕዳውን ባለመክፈሉ መያዣ ሰጪውን ካለው ዕዳ በላይ የሚያወጣውን ንብረት እንዲያጣ በአንፃሩ መያዣ ተቀባዩን ማግኘት ከሚገባው ሃብት በላይ እንዲያካብት የሚያደርግ አሰራር በመሆኑ ከባለ ዕዳው መብት በእጅጉ የሚጎዳ አሰራር ነው፡፡ የዚህ ዓይነት አሰራር በመጥፋት ላይ ያለ የመያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል አሰራር ነው፡፡

በፍርድ ቤት ውሳኔ መያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል (Judicial Foreclosure) የዚህ ዓይነት የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ፍርድ ቤት በመያዣ የተያዘውን ንብረት ተሸጦ ለዕዳ መክፈያነት እንዲውል የሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት ንብረቱ ተሸጦ ዋጋው በዕዳ ከሚጠየቀው የገንዘብ መጠን በላይ በሆነ ግዜ ለዕዳ መክፈያነት ከዋለው ገንዘብ ውጭ ያለውን ቀሪ ገንዘብ

በባለ ዕዳው እንዲመለስ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚሰጥበት የሚያገኘ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል አሰራርን የሚከተል የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ዓይነት ነው፡፡ ይህ ዓይነት አሰራር በአገራችን የፍታብሄር ህግ ቁጥር 2851 እና 3060ን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 65/89 ከመውጣቱ በፊት ፍ/ብ/ሰ/ሰ/ህ/ቁ.394-449 ባሉ ድንጋጌዎች ሲሰራበት የቆየ የመያዣ ንብረትን ለዕዳ መክፈያነት የማዋል ዓይነት አሰራር ነው፡፡
በፍርድ ቤት ውሳኔ መያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ያለው ጠንካራ ጎን መያዣን ለዕዳ መክፈያነት በሚሸጥበት ግዜ ሂደቱ በፍርድ ቤት ክትትል እና ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ስለሚፈፀም ለእዳ መክፈያነት የተያዘው ንብረት ተሸጦ በዕዳ ከሚጠየቀው ገንዘብ በላይ ባወጣ ግዜ ቀሪው ገንዘብ ለመያዣ ሰጪው(ለባለ ዕዳው) እንዲመለስለት የሚፈቅድ አሰራር ስለሆነ ከባለዕዳው መብት አኳያ ሲታይ ጠቃሚ አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር በፍርድ ቤት የማለፍን ግዴታ ያለበት በመሆኑ በፍርድ ቤት ለማለፍ የሚጠይቀውን የገንዘብ ወጪ ሆነ የግዜ ብክነት ስለሚያስከትል ባለሃብቱ በወቅቱ ከባለ ዕዳ የሚጠይቀውን ሃብት እንዲያገኝ የማያስችል ነው፡፡

መያዣ ተቀባዩ በመያዣነት የያዘውን ንብረት ከፍርድ ቤት ውጭ ሸጦ ለዕዳ መክፈያነት የሚያውልበት አሰራር (Power of sale foreclosure) የሚባለ ሲሆን ይህ ዓይነት የመያዣነት ለዕዳ መክፈያ ማዋል መያዣ ተቀባዩ ለመያዣ ሰጪው (ባለ ዕዳው) ዕዳ የመክፈያው ግዜ ማለፍን እና እንዲከፍለው ማስጠንቀቅያ በመስጠት በማስጠንቀቅያ በተገለፀ ግዜ ውስጥ ዕዳ ከፋዩ ዕዳውን ሳይከፍል ሲቀር በመያዣነት የተያዘውን ንብረት ሸጦ ለዕዳ መክፈያነት የሚያውልበት አሰራርን የተከተለ የመያዣ ንብረት ለዕዳ መክፈያነት የማዋል ዓይነት ነው፡፡ ይህ ዓይነት አሰራር ባንኮች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት እየተተገበረ ያለ አሰራር ነው፡፡
መያዣ ተቀባይ በመያዣነት የያዘውን ንብረት ከፍርድ ቤት ውጭ ሸጦ ለዕዳ መክፍያነት ማዋል ያለው ጠንካራ ጎን በፍርድ ቤት ለማለፍ የሚጠየቀውን ገንዘብና ግዜ የሚቆጥብ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን ይህ አሰራር ከባለ ዕዳው የንበረት ባለ መብትነት አንፃር ስታይ በህግ በተቋቋመ ሌላ ሶስተኛ ወገን የሚመራና ዕልባት የሚያገኝ ባለመሆኑ በተለይ በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በተለያዩ ምክንያቶች ዕዳው ሳይሸፍን በቀረ ግዜ ባለዕዳውን በከፍተኛ ደረጃ ቀሪው ዕዳ በመያዝነት ካስያዘው ንብረት ውጭ ባለ ሃብቱ እንዳይገባ ለመከልከል ክስን ወደ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሽያጭ ሂደቱ ለማሰናከል እንዲጥር የሚጋብዝ አሰራር ስለሆነ የዚህ ዓይነት ድክመት የሚታይበት አሰራር ነው፡፡ እነዚህ የመያዣን ለዕዳ መክፈያ ማዋል ዓይነቶች ካለባቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አንፃር ስታዩ እንደሌላው አሰራር ሁሉ የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ያላቸው ሲሆኑ ኢትዮጵያ እየተከተለችው ያለ የፎርክሎዥርና አሰራር ከፍርድ ቤት ውጭ በመያዣበት የተያዘውን ንብረት ሸጦ ለዕዳ መክፈያነት የማዋል አሰራር ላለፉት 40 ዓመታት ስትከተለው የቆየችውን ክስን አጣርቶ

የባለ ሃብትነትን እና የባለዕዳነትን መብትና ግዴታ በውሳኔ ከመስጠት ባሻገር የአፈፃፀም ስነ-ስርዓት ሰፋ ባለመልኩ በህግ በመያዣነት የተያዥነት የተያዘውን ንብረት ለፍርድ መስፈፀምያ የሚውልበት አሰራር በህግ በማሻሻል ሲሆን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በቀዳሚነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 65/89 ሆነ ይህንን አዋጅ በመሻር የወጣው አዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/97 በመደንገግ ነው፡፡ የዚህን አሰራር አስፈላጊነትና ወቅታዊነት በሚከተለው ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መግብያ ላይ ያለ ሲሆን ይሄውም፡፡ በባንኮች በዋስትና የተያዙ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲሸጡ በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰንና ውሳኔውንም ለማስፈፀም የሚወስደው ጊዜ በጣም ረጅም በመሆኑ፡- በቁጠባ ሂሳብ መልክ ህዝብ የሰበሰቡትንና ከተለያዩ ምንጮች ያገኙትን ገንዘብ በማበደር የሚገኘው የወለድ ገቢ የሚተዳደሩ ባንኮች ስራ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በማሳደሩ፡- ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴው አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ባንኮች ለተያየዩ የንግድና የልማት እንቅስቃሴ የሚሰጣቸው ብድሮችን በተቀላጠፈ መንገድ ለመሰብሰብ እንዲችሉና ለወደፊቱ ጥሩ የንግድ አሰራር ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ለባንክ ብድር በመያዣ የተሰጠ የሚያንቀሳቅሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ሽያጭ በሚመለከት በስራ ላይ ያሉትን ሕጎች ማሻሻልና አዲስ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፡፡ በአዋጅ መግብያ ላይ እንደተገለፀው ባንኮች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የነበረውን የብድር አሰባሰብ አሰራር ተከትለው ይሰሩ ቢባሉ ውጤቱ አገሪቱ እየተከተለችው ያለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራተጂ የሚጎዳ በመሆኑ ይህን ሁለት ዓይነተ አሰራር መከተሏ አግባብነት ያለው ነው፤፤ ስለሆነም ኢትዮጵያ በፍ/ቤት የመሸጥንና በባንክ የማሸጥን ስርዓት በመከተል የምዝገባው ስርዓትና መዝገቡን ሁለት እንዲሆን የተደረገ አሰራር የምትከተል መሆኗ ልንገነዘብ ይገባል፡፡

የመወያያ ነጥቦች

1.ደንበኛ ገብያተኛ (good will) ምንድን ነው? የደንበኛ ገብያተኛ የገንዘብ ጥቅም (Value) የሚወሰነው ምንድን ነው?

2.አቶ ዘመኩን የተባለ የፒኮክ ጫማ መሸጫ መደበር ከፍቶ ላለፉት 5 ዓመታት ሲነግድ ከቆየበት መደብሩ አጠገብ ወ/ሮ ሂወት ተመሳሳይ የፒኮክ ጫማ መሸጫ መደብር ብትከፍት አቶ ዘመድኩን በተገቢ ያልሆነ ውድድር ክስ ሊመስርትባት ይችላልን? ለምን?

3.የቀበሌ 20 ነዋሪዎች ኣግኣዚ የእቁብ ማህበር ቢመሰርቱና በተመሳሳይ ሁኔታ የቀበሌ 19 ነዋሪዎች ኣግኣዚ የእቁብ ማግበር ቢመሰርቱ የቀበሌ 20 ነዋሪዎች በቀበሌ 19 ነዋሪዎች ላይ የያልተገባ ውድድር ክስ መመስረት ይችላሉን ? ለምን?

4.አቶ በቀለ የተባለ እውቅ የመንደሩ ነጋዴ በመንደሩ ሌላ ኣቶ በቀለ የሚባል ነጋዴ መኖሩን ቢሰማ ባለተገቢ ውድድር ክስ ማቅረብ ይችላልን? ለምን?

5.በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 41(1) (2) እና ን/ህ/ቁ 158 መካከል መጣረስ ኣለን? ይህን የንግድ ህግ ድንጋጌ የህገ-መንግስቱን ይዘት ስለሚፃረር በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 9(1) መሰረት መሻር ያለበት ድንጋጌ ነው ብሎ መከራከር ይቻላልን? ለምን?

6.ከንግድ ምልክት ጀርባ ያሉ ፖሊሲዎች ምንና ምን ናቸው?

7.በአንድ ግዙፍነት ያለው የሚንቀሳቀስ ንብረት የንግድ ምልክት፣ የፓተንትና የቅጅ መብቶች መቀላቀል ሊከሰት ይችላልን? እንዴት?

8.የንግድ ምልክት ምዝገባ የሚያሰኛቸው መብቶች ምንድን ናቸው?

9. ንግድ ምልክት ጥሰት መፍትሄዎች (Remedies) ምንድን ናቸው?

10.የንግድ ምልክት ጥምች ምንድን ናቸው?

3. የንግድ ማህበራት

3.1. ስለንግድ ማህበራት በጠቅላላ

የንግድ ማህበራት እድገት ከኣገሮች የኢኮኖሚ እድገት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው፡፡ የትሳሰሩ ሰንሰለት የሚጀምረው በግለሰብ ደረጃ ንግድን ከማካሄድ ሲሆን በተደራጀ መልክ እስከ ማስኬድ የሚዘልቅ ነው፡፡ ይህ የተለያየ ደረጃዎችን እያለፈ አሁን ወዳለንበት ድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎች (Transnational corporations) እንደ ኣሸን የፈለበት ዘመነ ግለባላይዘሽን የደረሰው የንግድ ማህበራት አደረጃጀት ግዙፍነትና እነዚህን ለማስተዳደር የወጣው ህግ ስንመለከት ወደ አገራችን ለመጀመርያ ግዜ 1884 ዓ.ም የገባውን “Franco - Ethiopian Rail way company” ብንወስድ እስከተጠቀሰው ጊዜ ኢትዮጵያ ኩባንያ የሚባል ሆነ የንግድ ማህበራት ህግ እንዳልነበራት ከታሪክ ፀሃፍት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ኩባንያ በ1905 የተከፈተው አብሲንያ ባንክ ሲሆን ይህም ራሱን ችሎ ሳይሆን የግብፅ ብሄራዊ ባንክ ቅርንጫፍ በመሆኑ የተከፈተ ነበር፡፡ ለመጀመርያ በኢትዮጵያ የተከፈተው ኢትዮጵያ ባንክ (Bank of Ethiopia) በ1931 ዓ.ም ሲሆን ቀጥሎ የኢትዮጵያ እርሻና ንግድ ልማት ኩባንያ በጥቂት የግዢ መደብ መሰራችነት ሊቋቋም ችሏል፡፡ በአገራችን የንግድ ማህበራት ህግ ለመጀመርያ ጊዜ የወጣውም በ1933 ዓ.ም ነበር ፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በኣገራችን የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ በተለይ ደግሞ በተደራጀ መልኩ በንግድ ማህበር መቋቋም ከጀመረ ቅርብ እንደሆነና ከነበረው ንጉሳዊ ኣገዛዝ በኃላም የደርግ መንግስት ይከተለው በነበረ የእዝ ኢኮኖሚ ምክንያት የነበሩት ኩባንያዎች በመንግስት ተወርሰው በመቆየታቸው ሂደቱን ዘገምታዊ እንዲሆን እንዳደረገው ነው፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ ባለው ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ በመፈጠሩ ተደራጅቶ የንግድ ስራ የመስራት መብት እንደገና ሊያንሰራራ ችሏል፡፡ በተደራጀ መንገድ የንግድ ስራን የማከናወን መብት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትና ይህን መሰረት በማድረግ ከወጡት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ኣንፃር ስንመለከተውም

የንግድ ማህበር ሰዎች በግላቸው ከመነገድ ይልቅ ለኣንድ የኢኮኖሚያዊ ዓላማ በመደራጀት በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት የሚያስችላቸው የገንዘብ አቅምንና የገበያ ማስፋፋትን መሰረት በማድረግ በተሻለ የንግድ ስራ የተሻለ ገቢ ለማግኘት አቅደው የሚመሰርቱት ናቸው፡፡ ይህ የመደራጀት መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 31 ላይ “ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት ኣለው፡፡ ሆኖም ኣግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በህገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ

ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከለ ይሆናል፡፡" በማለት ስለተደነገገ "ማንኛውም ሰው" የሚለው የህገ-መንግስቱ ሃይለ ቃል የሚያመለክተው የተፈጥሮ ሰውንና በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው የንግድ ማህበራት መደራጀትን ሲገልፅ "ለማንኛውም ዓላማ" የሚለው ደግሞ ለንግድ ስራም ጭምር በንግድ ማህበር የመደራጀትን መብት የሚፈቅድ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ በንግድ ማህበራት የመደራጀት መብት በህገ-መንግስቱ 41(2) "ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደርያውን ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው" ከሚለው ህገ-መንግስታዊ መብት አንፃር ያየነው እንደሆነም ዜጎች አዋጪ ነው ባሉት የንግድ ማህበር መርጠው እንደመተዳደርያ ስራቸው ሊወስዱት የሚያስችል ህገ-መንግስታዊ መብት ያላቸው መሆኑን እንድንረዳ የሚያስችለን ነው፡፡

በአንድ አገር የኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት የንግድ ማህበራት አገራችን እየተከተለችው ላለው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ስኬታማነት የሚጫወቱት ሚናም በእጅጉ ከፍተኛ ነው፡፡ ዜጎች በተናጠል ቢሰሩዋቸው የማዋእለ ንዋይ፣ የማስተዳደር ዓቅማቸውን የሚፈታተኑ የንግድ ስራዎች ከሌሎች ተመሳሳይ ዓላማና የወደፊት በዘርፉ ተስማርተው በመስራት የመበልፀግ ራእይ ካላቸው ሰዎች ጋር ተደራጅተው በተለያየ የኢኮኖሚ ዘርፍ በመስራት ራሳቸውን ጠቅመው በአገራዊ ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ማረጋገጥ ሂደት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ስለሆነ በስፋት ልንሰራበት የሚያስችለን የአደረጃጀት ስርዓት ነው፡፡ አገራችን ከእዝ ክፍለ ኢኮኖሚ ተላቃ ወደ ነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲና እስትራቴጂ ትግበራ ከገባች ወዲህ በንግድ ህጉ ባሉ ድንጋጌዎችና የገበያ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በወጡ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና የባንክና ኢንሹራንስ አሰራሮች ታግዘው እግጅ በርከታ አክስዮን ማህበራትና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት ተመስርተው የአገሪቱን ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ሂደት ላይ የመሆናቸው ሚስጢር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ ለውጥ ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ በንግድ ማህበራት ተደራጅቶ መስራት በህገ-መንግስቱና ከዚያ በታች ባሉ የአገራችን ህጎች ጥበቃ የተሰጠው መብት በመሆኑ እየተከተልን ያለውን ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ፈጣንና ዘለቂ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ እውን በማድረጉ ሂደት በመስርያነት ልንጠቀምባቸውና ስርዓት ባለው መልኩ ሊመሩ እንደሚገባ በውል ልንገነዘብ ይገባል፡፡

በአገራችን ያለውን የንግድ ማህበራት አመዳደብ (classification) ሌሎች አገሮች እየተከተሉት ካለ አመዳደብ አንፃር ስናየው አገሮች እስካሁን እየተከተሉት ያለው አሰራር አንድን ማህበር የንግድ ማህበር ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመለየት ሁለት አካሄዶችን የሚከተል ነው፡፡ ይሄውም አንዳንዶቹ በተቋቋሙበት ዓላማ (objective) መሰረት ለንግድ ስራ የተቋቋመ ከሆነ የንግድ ማህበር ነው ብለው ሂደቱ በንግድ ህግ እንዲገዛ ሲደረግ ከዚህ ውጭ የሆነ ስራ ለመስራት የተደራጀ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ለንግድ ስራ ያልተደራጀ ማህበር (non-commercial organization) ብለው በመፈረጅ በሌሎች የአገሪቱ ህጎች እንዲገዛ

የሚያደርግ አሰራርን የሚከተሉ ናቸው፡፡ ለዚህ በምሳሌነት ልትጠቀስ የምትችል ቤልጂም ስትሆን ሌሎች አገሮች እንደ አሜሪካ ባለ አገሮች ደግሞ የንግድ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ወይም ፎርም መሰረት በማድረግ የሚለዩበት አሰራር እንጂ ለንግድ የተቋቋመ (commercial) ወይም ለንግድ ያልተቋቋመ (non-commercial) የሚል ክፍፍል የማያደርጉ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያን የንግድ ማህበራት አመዳደብ እንዴት እንደሚለይ ስንመለከት ህጋችን የንግድ ማህበራትን ለንግድ የተቋቋመ (commercial) እና ለንግድ ያልተቋቋመ (non-commercial) በሚል ምድብ የሚከፍል አካሄድን የሚከተል ነው፡፡ ይህ የፌረንሳይ የንግድ ማህበራትን አመዳደብ የሚከተለው ህጋችን በን/ህ/ቁ 10 ላይ አንድ የንግድ ማህበር ለአንድ የተለያዩ የሚታወቅ የንግድ ስራ የተደራጀ ከሆነ የንግድ ማህበር ተብሎ እንደሚወሰድና የተደራጀው በኣክስዮን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ በን/ህ/ቁ 5 የተዘረዘሩትን ስራዎች አካሄደ አላካሄደ የንግድ ማህበር ተደርጎ የሚወሰትበትን አሰራር የሚከተል ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ማህበር የንግድ ማህበር ነው ብሎ ለመፈረጅ የተደራጀበት ዓላማ በን/ህ/ቁ 5 ያሉትን ተግባራት ለማከናወን ከሆነ ከተቋቋመበት ዓላማ (objective) ተነስተን የንግድ ማህበር ነው ስንለው በሌላ በኩል ግን የተቋቋመበት ዓላማ በን/ህ/ቁ 5 ያሉትን የንግድ ተግባራት ለመፈፀም ባይሆንም የተከተለው ፎርም (form) በኣክስዮን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር እስከሆነ ድረስ ማህበሩ የንግድ ማህበር ነው ተብሎ እንደሚወሰድ የሚደነግግ ህግ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለበት የሽርካ ማህበር የንግድ ማህበር ለመባል በን/ህ/ቁ 5 ካሉት ዝርዝር ተግባራት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅበት ሲሆን የንግድ ህጉ እንደምንመው የሚወሰደው የፌረንሳይ ህግ ግን ከዚህ ለየት ባለ መልኩ የተቋቋመበት ዓላማን መሰረት ሳያደርግ ሁሌ ልክ በኛ አገር ን/ህ/ቁ 10(2) ለኣክስዮንና ሃላፊነቱ ለተወሰነ የግል ማህበር የተሰጠው የህግ ሽፋን ለሁለት ዓይነት ሃላፊነት ላለበት ሽርካ ማህበር (General and Limited) የህግ ሽፋን የሚሰጥ ነው፡፡ ከፈረንሳይ ኣካሄድ ለየት ባለ መልኩና ከኢትዮጵያ ን/ህ/ቁ 10(1) ኣካሄድ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሚደነግግ የጀርመን ህግ ሲሆን በተለይ ደግሞ ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለበትን ማህበር በተመለከተ የአገራችን ንግድ ህግ የጀርመን ህግን አካሄድ የሚከተል ነው፡፡

በአገሮች የንግድ አሰራር እንደዚህ ያለ አመዳደብ መከተል የሚያስፈልግበት ምክንያት የንግድ ማህበሩን ከሌላው ማህበር በመለየት የንግድ ሂደቱን ስርዓት ባለው መንገድ ለመምራትና ሂደቱ አገሪቱ ለነደፈችው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራተጂ ስኬት በመሳርያነት እንዲያገለግልና የሶስተኛ ወገኖችን መብት በማስጠበቁ ሂደት የራሱ የሆነ የቁጥጥርና ድጋፍ ስርዓት እንዲኖረው ለማስቻል ነው፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ኢትዮጲያም ሆነች ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ቤልጂም ለሰወስተኛ ወገን የማሳወቅ (publicity) ኣሰራርንና የንግድ ምዝገባ (Commercial registry) ኣሰራርን ተከትሎ እንዲሄድ የሚያደርግ ኣሰራር በመከተል

ስርዓት ባለው መንገድ እንዲመራ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ አንድ ሰው በንግድ መዝገብ ከተመዘገበ ነጋዴ ነው ተብሎ የመገመት መብት ያለው መሆኑን ን/ህ/ቁ 117(1) ሲደነግግ ይህን ሳያደርግ የንግድ ስራ ሲያከናውን ቢገኝ ግን ን/ህ/ቁ 115 የወንጀልና የፍ/ብሄር ሃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የሚደነግግ ህግን ተከትሎ በወንጀል ሃላፊነት ወ/ህ/ቁ 434 እና አዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀፅ 46 ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል፡፡ የፍ/ብሄር ሃላፊነትን በሚመለከትም ን/ህ/ቁ 118(1) መሰረት በማድረግ በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብ የንግድ ስራ ሲያከናውን የተገኘ ሰው ለስራው ስራ እንደ ነጋዴ ተወስዶ ሃላፊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በሌላ አነጋገር በሶስተኛ ወገን ላይ ያደረሰው ጉዳት ካለ ከውል ውጭ በሆነ ሃላፊነት ተጠያቂ በማድረግ ለደረሰው ጉዳት መክፈል ያለበትን ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ነጋዴ በመሆኑ ለመንግስት መክፈል ያለበትን ግብር ላለመክፈል ሳይመዘገብና ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ እየሰራ ቢገኝ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ያለበትን ግብር ገቢ እንዲያደርግ ማስገደድ ይቻላል፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊወሰድ የሚችለው አስተዳደራዊ እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀፅ 21(2) መሰረት ንግዱን እንዲዘጋ ማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ የንግድ ማህበራት አጠቃላይ ገፅታን ስንመለከት የራሳቸው የሆነ ህጋዊ አደረጃጀትና ተልእኮ ያላቸው ሆነው ህጋዊ ሰውነት ለማግኘትና ወደ ገበያው ለመግባት የምዝገባ፣ ፈቃድና ማስታወቅ ስራዎችን የሚጠይቁ ጠንካራ የአገር ኢኮኖሚ በመገንባት ሂደት የተበታተነን መዋእለ ንዋይ አሰባስቦ በተደራጀ መልክ የልማት ስራን ለማከናወን የሚያስችሉ መሳሪያዎች ሲሆኑ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ተደራጅቶ የንግድ ስራ የማከናወን መብት በህገ-መንግስቱና ከዚያ በታች ባሉ ህጎች የተረጋገጠ መብት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

3.2 ሽርካ ማህበር

3.2.1 የሽርካ ማህበር አጠቃላይ ገፅታ

“የሽርካ ማህበር ውል ማለት ሁለት ወይም ብዙ ሰዎች መዋጮ አዋጥተው በአንድነት እና በህብረት የኢኮኖሚ ተግባር ያለው ስራ ለመስራትና ከሚገኘው ትርፍም ሆነ ከሚመጣው ዕዳ ተካፋይ ለመሆን የሚስማሙበት ውል ነው፡፡” በማለት ን/ህ/ቁ 211 ተርጉም የሰጠው ሲሆን በማነፃፀርያነት ያገለግለን ዘንድ አንድ Professor M.C.Kuchhal የተባሉ ህንዳዊ የዘርፉ ተመራማሪ የሰጡትን ትርጉም የወሰድን እንደሆነ “partnership is the relation between persons who have agreed to share the profit of a business carried on by all or any of them acting for all” (P.295) በማለት ተርጉመውታል፡፡ ከነዚህ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጋራ የሆኑ ሓሳቦች (common elements) ያለዋቸውና የተለያዩበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ነው፡፡

በን/ህ/ቁ 211 መሰረት አንድ የሽርካ ማህበር ለማቋቋም

- ውል መኖር አለበት፣
- መዋጮ ማዋጣት፣

- በአንደነት እና በህብረት የኢኮኖሚ ተግባር መስራት፣
- ትርፍም ሆነ ዕዳ ለመከፈል መስማማትን የሚጠይቅ ሲሆን ፕሮፌሰር M.C.Kuchhal በሰጡት ትርጉም ደግሞ
    - There must be a contract,
    - Between one or more persons,
    - With the objective of sharing profits,
    - The business must be carried on by all or any of them caring for all.

የሚሉ ሃሳቦችን ይዟል፡፡ እነዚህን ስናነፃፅር የዘርፉ ተመራማሪ ለሽርካ ማህበር በተሰጡት ትርጉም ላይ ስለመዋጨና ዕዳ በሚኖርበት ጊዜ ስለሚኖረው አከፋፈል የሚለው ነገር የለም፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የታወቀ ነው ከሚል ወይስ በሌላ ምክንያት? ክርክር ሊያስረሳ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ የአዘጋጁ አስተያየት ግን መብትና ግዴታ ተነጣጠለው የማይሄዱ በመሆናቸው መዋጮ ማዋጣትም ሆነ ዕዳ ሲኖር የመክፈል ግዴታ በህንድ ህግም አለ የሚል ነው፤፤

በአገራችን የንግድ ማህበራት ህግ ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ካለው የሽርካ ማህበር በስተቀር በሌሎቹ የሽርካ ማህበራት የተለያዩ የሽርካ ማህበር አባላት ያሉ ስለመሆኑ የሚገልፅ ድንጋጌ የለም፡፡ M.C.Kuchhal በዓፋት መፅሐፍ ላይ እንደሚታየው ግን የተለያዩ የሽርካ ማህበር አባላት እንዳሉ ሲሆን እነርሱም

1. ተሳታፊ (active or actual) የሽርካ ማህበር አባል የዚህ ዓይነት አባል በሽርካ ማህበሩ የዕለተ ዕለት እንቅስቃሴ ተካፋይ የሚሆንና አባል ስለመሆኑ ለህዝብ በማስታወቅያ የወጣና ከማህበሩ በሚሰናበትበት ጊዜም ከስንብቱ በኃላ ለሚመጣ የሽርካ ማህበሩ ዕዳ ተጠያቂ ላለመሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ከሽርካ ማህበሩ መውጣቱን ለህዝብ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት የሽርካ ማህበር አባልነት ነው፡፡
2. ስዉር (Sleeping or dormant partner) የሚባል ገንዘቡን ብቻ ወደ ሽርካ ማህበሩ በማስገባት ከተገኘው ትርፍም ሆነ ኪሳራ ከድርሻው ዝቅ ያለ ገንዘብ እየተከፈለው ግን ደግሞ አባልነቱን ለህዝብ ሳያሳውቅ የሽርካ ማህበር አባል ሆኖ የሚቀጥል ነው፡፡
3. ዝምተኛ (Silent partners) የዚህ ዓይነት አባል ከሽርካ ማህበሩ አባላት ጋር በሚያደርገው ስምምነት በሽርካ ማህበሩ አስተዳደራዊ ስራ ሳይሳተፍ ግን ደግሞ በዕለተ ዕለት የንግድ ማህበሩ ስራዎች እየተሳተፈ የተገኘ ትርፍና ኪሳራ ከሌሎች አባላት ጋር የሚከፈልና ለሶስተኛ ወገኖች ለሚነሳ የይከፈለኝ ጥያቄ ሃላፊነት የሚወስድ የሽርካ ማህበር አባል ነው፡፡
4. ለትርፍ ብቻ አባል የሆነ (partner in profit only) የዚህ ዓይነት አባል በሚገኘው ትርፍ የተወሰነውን መጠን ከሌላው የሽርካ ማህበሩ አባል ለመውሰድ የተስማማና ሽርካ ማህበሩ ለሚያጋጥመው ኪሳራ ተጠያቂ ያልሆነ ግን ደግሞ በህንድ የንግድ ማህበራት ህግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የሽርካ ማህበር (Limited partnership) ባለመኖሩ

ሶስትኛ ወገኖች ለሚያነሱት የመብት ጥያቄ ግን ሃላፊነት የሚወስድ የሽርካ ማህበር አባል ነው።

5. ንኡስ የሽርካ አባል (sub partner) የሽርካ ማህበሩ አባል ከሌላ የውጭ ሰው ጋር ከሚገኘው ትርፍ ላይ ለመከፈል ብቻ የሚስማማበትና በሽርካ ማህበሩ ላይ ምንም ዓይነት መብትም ሆነ ሃላፊነት የሌለው ዓይነት አባል ነው።
6. በአባል ሳይሆን አባል የመሰለ (partner by estoppels or holding out) የዚህ ዓይነት ሽርካ በማህበሩ የሽርካነት ግንኙነት ሳይኖረው ለሶስተኛ ወገኖች በማህበሩ ሽርክና አለኝ ብሎ በመናገሩ፣ በመፃፉ ወይም በድርጊት ከሳየና በሶስተኛ ወገኖች ላይ በማህበሩ ምክንያት ጉዳት ከደረሰባቸው እንደ ሌሎቹ የሽርካ ማህበሩ አባላት ተጠያቂ የሚሆን ዓይነት አባል ነው።

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በኢትዮጵያ ያለው የሽሪኮች ዓይነት በህንድ ካለው የሽርካ ዓይነት ያነሰ ለመሆኑ ግልፅ ቢሆንም እዚህ ላይ ሊያነጋግር የሚችለው ነጥብ ከላይ በተገለፀው መንገድ ሽርኮች በመሆናቸው ሃላፊነት አለባቸው የሚል ክርክር ቢነሳ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳቱን ማስተናገድ ያለባቸው በንግድ ህጉ መሰረት ወይስ በሌላ የፍ/ብሄር ህግ የሚል ሲሆን እዚህ ላይ እንደመፍትሄ ሐሳብ መውሰድ ያለበት በንግድ ህጉ ባልተሸፈኑ ግንኙነቶች መገዛት ያለባቸው እንደሌላው ውል ወይም ከውል ውጭ ሃላፊነት መሆን አለበት የሚል ነው።

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት ሶስት ዓይነት የሽርካ ማህበራት ያሉ ሲሆን የነዚህን ማህበራት አጠቃላይ ገፅታ አጠር ባለ መልኩ ስንመለከት፤-

1. ተራ የሽርካ ማህበር (ን/ህ/ቁ 227-270)
   - በጥቂት አባላት የሚመሰረት ሽርካ ማህበር ነው።
   - የንግድ ማህበር ላይሆን ይችላል።
   - በን/ህ/ቁ 5 የተዘረዘሩትን ተግባራት ላያከናውን ይችላል።
   - በስራ ላይ የመዋለ ኣጋጣሚ ዝቅተኛ ነው።
   - የአባላቱ ሃላፊነት ያልተወሰነ ነው።
   - የአባላቱ ጥቅም በነፃ አይተላለፍም።
2. ህብረት ሽርካ ማህበር (ን/ህ/ቁ 280-295)
   - ብዙውን ግዜ በጥቂት አባላት የሚመሰረት ነው
   - የአባላቱ ጥቅም በነፃ አይተላለፍም
   - አባላቱ ያላቸው ሃላፊነት ያልተወሰነ ነው
   - ሽርካ ማህበሩ የሚመራው በአብዛኛዎቹ የተራ ሽርካ ማህበር ህጎች ነው።
3. ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለበት ሽርካ ማህበር (ን/ህ/ቁ 296-303)
   - አንድ ወይም ሁለት የማህበሩ አባላት ሃላፊነታቸው የተሰወነ ከመሆኑ ውጭ ልክ እንደ ህብረት ሽርካ ማህበር ዓይነት ማህበር ነው።

- የኣባላቱ ጥም በነፃ ኣይተላለፍም

የነዚህ የሸርካ ማህበራት ምንነት በሚከተሉት መመዘኛዎች (criteria's) ሲታይም የሚከተሉትን ጭብጦች ይዞ እናገኘዋለን፡፡

ተ.ቁ	የንግድ ማህበሩ ዓይነት	ሃላፊነት	የኣባላቱ ጥቅም መተላለፍ	የኣባላቱ ቁጥር	ህጋዊ ሰውነት	መነሻ ካፒታል
1	ተራ ሸርካ ማህበር	ያልተወሰነ ሃላፊነት ን/ህ/ቁ 255	በነፃ ኣይተላለፍም ን/ህ/ቁ 250	> 2 <6 ን/ህ/ቁ 211(1)	ህጋዊ ሰውነት አለው ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 210(2)	15,000 ብር
2	ህብረት ሸርካ ማህበር	ያልተወሰነ ሃላፊነት ያለው ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 294	በነፃ ኣይተላለፍም ን/ህ/ቁ 282(1)	> 2 <6 ን/ህ/ቁ 211(1)	ህጋዊ ሰውነት አለው ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 286	15,000 ብር
3	ሀሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለው የሸርካ ማህበር	ያልተወሰነና የተወሰነ ሃላፊነት ያላቸው ኣባላት ያለበት ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 300-301	በነፃ ኣይተላለፍም ን/ህ/ቁ 274(2)	> 2 <6 ን/ህ/ቁ 211(1)	ህጋዊ ሰውነት አለው ን/ህ/ቁ 286/303	15,000 ብር

በሸርካ ማህበር መሰረቱ ውል ነው ሲባል በሸርካ ማህበርና ሌሎች ውሎች መካከል ልዩነት የለም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፤፤ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን የወሰድን እንደሆን

- ❖ የሸርካ ማህበር እንደ ሌሎች ውሎች ባለ እዳ (debtor) እና ባለሃብት (creditor) የሚፈጥር ወይም የአንዱ መብት ሌላው ግዴታ የሚሆንበት ኣካሄድን መሰረት የሚያደርግ አለመሆኑና ሁሉም የሸርካ ማህበሩ ኣባላት ተመሳሳይ ኣቋም (equal footing) ያላቸው መሆኑ ከሌሎች ውሎች የሚለየው ባህሪው ነው፡፡
- ❖ ሌሎች ውሎች ተቋምን (institution) የመመስረት ባህሪ የሌላቸው ሲሆን የሸርካ ማህበር ስምምነት ግን ተቋምን ሊፈጥር የሚችል ነው፡፡
- ❖ ሌሎች ውሎች ውልን የማፍረስ ውጤት ሲኖራቸው ሸርካ ማህበር ግን ሸርካ ማህበሩን ለመመስረት የተደረሰው ስምምነት ከመፍረሱ በተጨማሪ ማህበሩም እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የሸርካ ማህበራት እንደ ሌሎቹ የንግድ ማህበራት ሰዎች በግል ማከናወን ያልቻሉትን የንግድ እንቅስቃሴ በሸርክና ተደራጅተው እውቀታቸውንና

ጥሪታቸውን በማቀናጀት ለራሳቸውና ለህብረተሰቡ ጠቃሚ በሆነ በኢኮኖሚው ዘርፍ በመስራት በልማት አጋርነት ሊሰማሩባቸው የሚችሉ የስራ መስኮች ናቸው።

3.2.2 የሽርካ ማህበር አባላት መብቶችና ግዴታዎች

- ❖ ማህበሩን ለነሱ ተስማሚ በሆነ መንገድ የመመስረት
- ❖ ንብረቱንና ጥቅሙን እንደፈለጉ በጋራ ስምምነት ማስተዳደር
- ❖ በማህበሩ ጉዳይ ላይ ያልተገደበ መብት ያላቸው መሆኑ
- ❖ የትርፍ ክፍፍል ስርዓት የመወሰን (ን/ህ/ቁ 252)
- ❖ ኪሳራ ሲኖርም ይህንን የመጋራት መብትና ጥቅም ይኖራቸውል።
- ✓ በህብረት ሽርካ ማህበር የሃብት ክፍፍልና የዕዳ መጋራትን በማስመልከት የሚለው የለም (ን/ህ/ቁ 284(7)
- ▪ ከሽርካ ማህበሩ ጋር ያለመወዳደር (ን/ህ/ቁ 244፣292)
- ▪ የሽርካ ማህበሩን ንብረት ለሽርካ ማህበሩ አገለግሎት እንዲውል የማድረግ (245)
- ▪ ባለሃብቶች ከሽርካ ማህበሩ የሚጠይቁትን ዕዳ የመክፈል (ን/ህ/ቁ 255፣280፣294 እና 296)
- ▪ የሽርካ ማሕበር አባላት ፈቃድ ሳታገኝ የማህበሩን ጥቅም ወደሌላ ያለማስተላለፍ (ን/ህ/ቁ 282)

3. 2 .3 ስለሽርካ ማህበር መፍረስና ሒሳብ ማጣራት

የማህበር መፍረስ ማለት ማህበሩ ህልውናው የሚያጣበት (Organization comes to an end) ሲሆን ይህ መፍረስ በዋናነት ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸውን የንግድ ማህበራት የሚመለከት በመሆኑ ፈረሰ ማለት የንግድ ስራን ከመስራት አቆ ወይም ታመመ እንጂ ሞተ ማለት እንደሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል። በመሆኑም የንግድ ማህበሩ ከፈረሰ በኃላ ሒሳብ የማጣራት ስራ ይካሄዳል። ይሄውም ሂሳብ አጣሪዎች (Liquidators) ድርሻ ሲሆን አጣሪዎች ስራቸውን አከናውነው እስኪጨርሱ ድረስ የንግድ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆን እንደተጠበቀ ይቆያል። ይህን ህልውናውን የሚያጣው አጣሪዎቹ የማጣራቱን ስራ ጨርሰው የተገኘው የንግድ ማህበር ገንዘብ ለባለ እዳዎች የሚከፈለው ተከፍሎ ካለቀና ቀረ ካለም በአባላቱ መካከል ተከፋፍሎና ሂደቱ ካለቀ በኋላ ነው። የንግድ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያገኘው በምዝገባና በማሳወቅ እስከሆነ ድረስ ህልውናውም ማጣት ያለበትም በንግድ መዝገብ የነበረን የማህበሩ ስም እንዲሰረዝ በማድረግና ሶስተኛ ወገኖች ህልውናውን ያጣ መሆኑን እንዲያውቁት በማስታወቅያ እንዲገለፅ በማደረግ ነው።

የማህበሩ መሰረዝ ሊከሰት የሚችለው በሶስት ምክንያቶች ሲሆን እነሱም በህግ፣ በስምምነትና በፍርድ ቤት ናቸው። አንድ የንግድ ማህበር በህግ ሊፈርስ የሚችለው የተቋቋመበትን

ዓላማ ያሳካ ወይም ማሳካት የተሳነው እንደሆነ ነው፡፡ ሌላው የንግድ ማህበር በህግ እንዲፈርስ የሚደረግበት ሁኔታ ማህበሩ ሲመሰረት የተወሰነው የግዜ ገደብ በመድረሱ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የማህበሩ አባላት የመፍረሻ ጊዜው ከመድረሱ በፊት በስምምነት ጊዜውን ማራዘምና በንግድ መዝገቡ ማሻሻያ እንዳያደርጉ ይከለከላሉ ማለት አይደለም፡፡ የአንድ ንግድ ማህበር አባላት የመፍረሻ ጊዜው ከመድረሱ በፊት አስቀድመው ማህበሩ እንዲፈርስ ከተስማሙ የስምምነታቸው ቅጂ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብና ለሶስተኛ ወገኖች በማሳወቅ የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስም ሆነ የማጣራቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኃላ እንዲሰረዝ ለማድረግ ይችላሉ፡፡

አንድ የንግድ ማህበር በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሊወሰንበት የሚችለው የንግድ ማህበሩን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የጤና መታወክ ወይም በአባላቱ መካከል ሊያሰራ የማይችል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት መፈጠሩን ከተረዳ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይሄውም ለመፍረሱ በቂ ምክንያት (good cause) መኖሩ ሲረጋገጥ የሚፈፀም ነው፡፡ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰዱ የሚችሉትም ለምሳሌ የማህበሩ አባላት በተፈጠረው አለመግባባት ውሳኔ ማሳለፍ የማይችሉ ሲሆን ወይም ማህበሩን በምግባረ ብልሹነት ማስተዳደር ከተጀመረ ለመፍረሱ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል፡፡ ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ሽርካ ማህበር መሰረቱ ውል ሆኖ በውሉ መሰረት መቀጠል ሲሳነው ወይም ዓላማውን አሳክቶ ወይም ቀደም ሲል በተገለፀ በርካታ ምክንያቶች ሊፈርስ ብሎም ሂሳቡ ከተጣራ በኃላ ሊሰረዝ የሚችል የንግድ ማህበር ነው፡፡

3.3 የእሽሙር ማህበር

እሽሙር ማህበር በን/ህ/ቁ 271 መሰረት ሰዎች ሌሎች ፎርማሊታዎች እንዲያሟሉ ሳይጠበቅባቸው ለአንድ ዓላማና ግብ በመስማማት ብቻ ሊመስርቱት የሚችል የንግድ ማህበር ሲሆን የሚቋቋመው ለንግድ ወይም ለንግድ ላልሆነ ስራ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌሎች አገሮች የህግ ማእቀፍ ለእሽሙር ማህበር የሚሰጠው ቦታ እንደ ኢትዮጵያ የንግድ ህግ የንግድ ማህበር ነው በሚል ሳይሆን በን/ህ/ቁ 271 ላይ እንደተገለፀው “…. ማህበርተኞቹ እንደፈቃዳቸው የውላቸውን ሁኔታዎች ወስነው ያቋቋሙት ማህበር” ተደርጎ ነው የሚታየው፡፡ ለምሳሌ በጀርመን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣልያን እሽሙር ማህበር እንደ ሰዎች ሰብሰብ እንጂ እንደ አንድ የንግድ ማህበር የሚታይበት ሁኔታ በህጋቸው የለም፡፡ እሽሙር ማህበር ከኢትዮጵያ ህግ አኳያ ሲታይ የተለየ ወይም አጠቃላይ ስራ ለመስራት ሊቋቋም የሚችል ሲሆን ከጊዜ አንፃርም ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ ሊቋቋም የሚችል የንግድ ማህበር ነው፡፡ ከኢትዮጵያ የእሽሙር ማህበር ህግ ጋር የሚመሳሰለው የቤልጅም ህግ ሲሆን በዚች አገር ከ1873 ዓ.ም ጀምሮ እሽሙር ማህበርን እንደ ንግድ ማህበር እውቅና የሚሰጥ ህግ አለ፡፡ የእሽሙር ማህበር ምስረታ በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ ህግ የለም ይህም ማለት ውሉ በፍ/ህ/ቁ 1681 መሰረት በቃል፣ በተለመዱ ምልክቶች ሊመሰረት ይችላል

ማለት ነው፡፡ ውሉ በፅሁፍ የማይደረግ በመሆኑ በሰዎቹ መካከል ክደት ቢፈጠር መብትን ለማስጠበቅ ከፍተኛ የማስረዳት ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ ችግር መኖሩ እንደተጠበቀ ሌላው ግራ የሚያጋባው ነገር ቢኖር ግን በን/ ህ/ቁ/ 275(4) ላይ “የስራ አስኪያጁ ስልጣን በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ ይወስናል ይህን ስልጣን የሚወስነው ቃል ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች መቃወምያ ሊሆን አይችልም” ሲል የሚደነግግ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ብቻም አይደለም ን/ህ/ቁ 276(2) እንደዚሁ “ስራ አስኪያጅ ያልሆኑ ማህበርተኞች ለማህበሩ ዕዳዎች ተካፋይ የሚሆኑት በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ በተወሰነው መጠን ብቻ ነው” ይላል፡፡ ይህን ከን/ህ/ቁ 214 ጋር በማገናዘብ ስናየው የእሽሙር ማህበር ምስረታ በፅሁፍ የመሆን ጉዳይ የምርጫ ጉዳይ ነው ሊባል ይችላልን? የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ የሚያረገን ሲሆን ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ምስረታው በማህበር መመስረቻ ፅሁፍ (memorandum of association) ነው ከተባለ ይህ በንግድ መዝገብ ሊመዘገብና ለሶስተኛ ወገኖች የማሳወቅ ግዴታን ሊያስከትል አይችልምን? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው፡፡ እንደ አዘጋጁ አስተያየት ከሆነ ዛሬ ስለ እሽሙር ማህበር መመስረቻ ፅሁፍ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች ከአርቃቂው ቅደም ተከተልና ወጥነት አለመኖር የመነጨ እንጂ የእሽሙር ማህበር ግንኙነት በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ ሁኔታ ስላለ አይደለም የሚል ነው፡፡ ለዚህም እንደመነሻ ሊወሰድ የሚችለው ከኢትዩጲያ ንግድ ህግ ተመሳሳይነት ያለው የቤልጅም ህግ ስለእሽሙር ማህበር ምስረታ ፎርም ሆነ ለሶስተኛ ወገኖች ስለማስተዋወቅ የሚለው ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ሌላው እሽሙር ማህበር እንደሌሎቹ የንግድ ማህበራት ህጋዊ ሰውነት የሌለውና በማህበር ስም ንብረት ለመያዝም ሆነ ለመክሰስም ለመከሰሰም የማይችል አባላቱ በን/ህ/ቁ 273 መሰረት ባወጡት መጠን የግል ንብረታቸው የግል እንደሆነ ተደርጎ የመውሰድ አካሄድን የሚከተል ነው፡፡ የእሽሙር ማህበር ህልውና ለሶስተኛ ወገኖች የተጋለጠ ከሆነ ማህበሩ እሽሙር ማህበር መሆኑ ይቀርና በን/ህ/ቁ 272(4) መሰረት እንደ ሽርካ ማህበር ተወስዶ ሶስተኛ ወገኖች መብታቸውን ለማስጠበቅ በማህበሩ ላይ ክስ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡ የእሽሙር ማህበር አስተዳዳሪ እንዳልተጋለጠ ወኪል (Undisclosed agent) በስሙ ስለሚሰራ ለማንኛውም የመብት ጥያቄ በግሉ ሃላፊ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረበለትን ዕዳ ከከፈለ በኋላ ከማህበርተኞቹ ገንዘቡን እንዲመልሱለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት እሽሙር ማህበር

- አብዛኛው ጊዜ በጥቂት ሰዎች የሚመሰረት
- በአብዛኛው ለተወሰነ ዓላማና ጊዜ የሚመሰረት
- ህጋዊ ሰውነት የሌለው (ን/ህ/ቁ 210(2)፣ 232(2)
- የአባላቱ ጥቅም በነፃ ሊተላለፍ የማይችል(ን/ህ/ቁ 274(2)
- ማህበሩ ለሶስተኛ ወገኖች በጋህድ የማይታይ
- የአባላቱ ሃላፊነት የሚወሰነው በመመሰረቻ ፅሁፍ መሰረት ሆኖ የተወሰነ ሃላፊነት ያላቸው ናቸው፡፡ (ን/ህ/ቁ 276 (2))

- የአባላቱ ብዛት ከሁለት የበለጠ ከስድስት ያነሰ መሆን ያለበት(ን/ህ/ቁ 211(2)
- የመነሻ ካፒታል 15,000 ብር የሆነ የንግድ ማህበር ነው።

በኢትዮጵያ እሽሙር ማህበር ላይ የመክሰር ፍርድ የማይሰጥበት ምክንያት ህጋዊ ሰውነት የሚሰጠው (separate legal personality) ስለሌለው ነው። በአንድ አንድ እንደ ጀርመንና አሜሪካ ባሉ አገሮች ግን የሽርካ ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሚይሰጣቸው ባይሆንም በእንደዚህ ያሉ የንግድ ማህበራት ላይ ግን የመክሰር ፍርድ ሲሰጥባቸው ይስተዋላል። በእንግሊዝ ህግ ደግሞ ሽርካ ማህበር ህጋዊ ሰውነት የማይሰጠው በመሆኑ የመክሰር ፍርድ ኣይሰጥበትም። በፈረንሳይ ህግ ደግሞ በሽርካ ማህበር ላይ የመክሰር ፍርድ የሚሰጠው የኣባላቱን መክሰር ሳይጨምር ነው።

በኢትዮጵያ ያለው አሰራር አንድ ከእሽሙር ማህበር በስተቀር ያለ የንግድ ማህበር የሚጠበቅበትን ዕዳ መክፈል ካልቻለ በን/ህ/ቁ 1156 መሰረት የመክሰር ውሳኔ የሚሰጠው በን/ህ/ቁ 1158(1) (2) ማስጠንቀቅያ ከተሰጠው በኋላ ኣባላቱ ዕዳውን ካልከፈሉ አብረው ከንግድ ማህበሩ ጋር የመክሰር ውሳኔ ይሰጥባቸዋል።

3.4 ኣክስዮንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ኣክስዮን ማህበር ግለ ሰቦች በግላቸው ሊያቋቁሙትና ተወዳዳሪ ሆነው ለመውጣት የመዋእለ ንዋይ እጥረታቸውን ለማስወገድ እየተጠቀሙበት ያለ ዘመናዊ የንግድ ማህበር ነው። የዚህ ዓይነት ንግድ ማህበር የገንዘብ እጥረትን ለመቅረፍ ወይም በተደራጀ መንገድ ወደ ገበያ ለመግባት በማሰብ የሚመሰረት ብቻ ሳይሆን በአገልግሎት ላይ ያልዋለ ገንዘብ ያላቸው ባለፀጎች የኣክስዮን ዕጣ በመግዛት ገንዘቡ ትርፍ እንዲያስገኝላቸው የሚጠቀሙበትም ጭምር ነው።

የኣክስዮን ማህበርም ሆነ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የራሳቸው በጎ ገፅታዎች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አንዱ የኣባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ (limited liability) መሆን ነው። (ን/ህ/ቁ 304 እና 510 (1) ይህ በአንግሎ አሜሪካን ካለው አሰራር ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለተኛው ጠንካራ ጎድናቸው የኣክስዮን ማህበሩ ኣባላት በሙሉ ቢሞቱም ኩባንያው ግን የማይሞት መሆኑ ነው። ይህ ማለትም ሌሎች ተወላጆች ኣክስዮኑን በመውረስ ሊቀጥሉበት ይችላሉ። ለምሳሌ በሁለተኛ ዓለም ጦርነት ግዜ የኩባንያው ባለኣክስዮኖች ለጠቅላላ ስብሰባ እንደተቀመጡ በሃይድሮጅን ቦንብ ኣልቀዋል ኩባንያው ግን ኣባላቱ በቦምብ በማለቃቸው ምክንያት ህጋዊ ሰውነቱን ኣላጣም። ይህ ኣክስዮን ማህበር ባህሪ ከሽርካ ማህበር የሚለየውና የጥንካሬው መገለጫ ነው። ሌላው ኣክስዮን ማህበር ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቅ በመሆኑ ግዙፍ ኢንተርፕራይዞች እንዲኖሩና ለዚህም ህዝብ በገቢ ማስገኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲሳተፍ የሚያደርግ መሆኑ ነው። በመጨረሻም ኣክስዮን ማህበር የኣባላቱን ማንነት ታሳቢ የማያደርግ መሆኑ ናቸው። ኣክስዮን ማህበር የራሱ ጠንካራ ያለው እንደመሆኑ

መጠን የራሱ ድክመት ያለው ነው ለዚህም ይመስላል Avatar sigh “Corporate entities works like boomerang and hits a man who tries to use it” በማለት የሚገልፁት፡፡ እንደ ኣክስዮን ማህበር ደካማ ጎድኖች የሚወስዱት ጉዳዮችም፤-

- ኣክስዮን ማህበር ለመመስረት የሚጠይቀው ስነ-ስርዓት ውስብስብና አስቸጋሪ መሆኑ (Formation formalities and procedure are cumbersome)
- ለምስረታው የተለያዩ ባለሙያዎች እንደ የመመስረቻ ፅሁፉንና ደንቡን የሚያረቅ የህግ ባለሙያ፣ በዓይነት የተደረገውን መዋጮ ለመገመት የሂሳብ ወይም የምህንድስና ባለሙያን መጠቀም ስለሚጠይቅ ወጪ እንዲጨምር የሚያደርግ መሆኑ (Incorporation requires expenditure)
- የኩባንያው ንብረት እንደ ኩባንያው ንብረት እንጂ እንደ ኣባሉ ንብረት ስለማይታይ በመዋጮ የተዋጣው ንብረትና የዚህ ንብረት አስተዳደር የተነጣጠለ መሆኑ (Separation of fund and management)
- የኣክስዮን ማህበር የሚቋቋመው ለኣባለቱ ትርፍ ለማስገኘት ቢሆንም የማህበሩን ዘላቂ ጥቅም፣ ለብሄራዊ ኢኮኖሚ ኣስተዋፅኦ የማድረግ፣ ለሰራተኞች ህልውና ሃላፊነት የመውሰድ፣ በሚመረተው ምርትና ደንበኞች መካከል ያለውን ጤናማ ግንኙነት የማስጠበቅ ሃላፊነት (Social responsibility) ያለበት መሆኑ በቀላሉ የሚጠቀሙበት እንዳይሆን የሚያደርገው ምሆኑ ናቸው፡፡

3.4.1 የኣክስዬን ማህበር ምስረታ

1. በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ በፈረሙ ሰዎች (persons who sign on a memorandum of association)
2. በፕሮስፔክተስ ላይ በሚፈርሙ ሰዎች (Persons who sign on a prospectus)
3. በዓይነት መዋጮ ባደረጉ ሰዎች (Persons making contribution in kind)
4. ልዩ ፅጣ ባላቸው ሰዎች (Persons allocated with special shares of profit)
5. ለኣክስዬን ማህበሩ መመስረት መነሻ እቅድ ባዘጋጁ ሰዎች (Persons who initiate plans for the formation of company or making possible the formation) ሊመሰረት ይችላል፤፤ የመስራቾች መብትና ግዴታም፤-

- ልዩ የኣክስዬን ትርፍ
- የኣክስዬን ማህበሩ ኣባል የመሆን
- በዓይነት መዋጮ የማዋጣት
- ለማስተዋወቅ የወጣ ወጪ እንዲመለስላቸው ከማህበሩ የመጠየቅ መበት
- የማህበሩ ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የመሾም መብቶች ያሉዋቸው ሲሆን በግዴታነትም

- ለኩባንያው ጥቅም በቅን ልቦና የመስራት
- በማስተዋወቅ ሂደት የተገኘ ጥቅም አለመሸሸግ

- የኣክስዮኑን ዋጋ ከፍ አድርጎ የተገኘ ጥቅምን ኣለመሸሸግ ሲሆኑ እነዚህን ጥሰው በሚገኙበት ጊዜ በጋራና በነጠላ ለሶስተኛ ወገኖች ጉዳት ሃላፊ ናቸው፡፡ የወንጀል ሃላፊነትን በተመለከተ እንደየ ሁኔታው በወ/ህ/ቁ 692፣ 695፣ 696 መታየት ያለበት ሲሆን የፍ/ብሄር ሃላፊነት በተመለከተ ፍ/ህ/ቁ 2028 እና ቀጣይ ህጎቸ የሚታይ ይሆናል፤፤ ክስ የማቅረብያ ይርጋ ግዜው በን/ህ/ቁ 309 (2) መሰረት ክሱ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

የሃላፊነቱ የወሰነ የግል ማህበር በባህሪው የሸርካ ማህበርና ኣክስዬን ማህበር ቅይጥ ሆኖ እርስ በርስ ትውውቅ ባላቸውና የኣባለ ማንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚመሰረት የንግድ ማህበር ነው፡፡ የማህበሩ እጣዎች ለውጭ ሰው የማይሸጥ ሲሆን ከምስረታ በኋላም የማህበሩ ኣባላት ፈቃዳቸውን ሳይሰጡ ድርሻውን ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት በኣባላቱ መካከል ሊሆን ብቻ ነው፡፡ ኣክስዬን ማህበርም ሆነ ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ከምስረታ በኋላ ማህበሩ ስም ሊኖረው ይገባል፡፡ የሚሰጠው ስያሜ የህዝብ ፖሊሲን መፃረር፣ የሶስተኛ ወገኖች መብትን የሚነካ መሆን የለበትም (ን/ህ/ቁ 133(2) () እና 134) እንዲሁም በንግድ ማህበሩ ስም ፊት "ኣክስዬን ማህበር (አ/ማ) ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚል መጨመር አለበት (ን/ህ/ቁ 305 እና 514(2))

3.4.2 የኣክስዬን ማህበርና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ኣጠቃላይ ይዘት

1. **ኣክስዬን ማህበር**
   - ከሌሎቹ የሸርካ ማህበር የተለየ መሆኑ፡፡
   - የኣባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 508)
   - የኣባላቱ ቁጥር ብዙ ላይሆን ይችላል ይሄውም ለምስረታው ≥ 5 ኣባላት ሊኖሩት ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 307(1)
   - ህጋዊ ሰውነት ኣለው፡፡ (ን/ህ/ቁ 214(2))
   - የኣባልነት መብት በነፃነት ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል
   - ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ በሚጠይቁ የንግድ ስራዎች ለመሰማራት የሚመሰረት ነው፡፡

2. **ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር**
   - ❖ የኣክስዬን ማህበርና ሸርካ ማህበር ቅይጥ ነው፡፡
   - ❖ የኣባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 510)
   - ❖ የተወሰነ ቁጥር የሚያዝና የኣባላቱ ጥቅም ወደ ሶስተኛ ወገን በነፃነት የማይተላለፍ በመሆኑ የሸርካ ማህበር ባህርያት ያሉት ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 523 (2))
   - ❖ ህጋዊ ሰውነት ያለው ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 214 (2))

❖ የመነሻ ካፒታሉ 15,000 ብር ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 512)

3.4.3 ኩባንያዎቹ ጥቅምና ጉዳት -

- ጠንካራ የገንዘብ አቅም (financial strength)
- የተወሰነ ሃላፊነት (limited liability)
- የመስፋፋት እድል (Scope of expansion)
- ውጤታማና ንቁ አስተዳደር (efficient and bold management)
- የተበተነ አደጋ (diffused risk) ጥቅሞች ያሉዋቸው ሲሆን ከጉዳት አንፃርም
- ➢ በቀላሉ የማይመሰረት መሆን (difficulty of formation)
- ➢ የንብረቱ ባለቤት ያለመሆን (Lack of owner's personal Interest)
- ➢ የውሳኔ መዘግየት (delay indecision making)
- ➢ በጥቂቶች እጅ የወደቀና ተንኮል የተላበሰ አስተዳደር (Oligarchic fraudulent management)
- ➢ የግብር ክፍያው ከፍተኛ መሆን(high taxation)
- ➢ ሚስጢር አለመጠበቅ (Lack of secrecy) ናቸው፡፡

3.4.4 የማህበራቱ መፍረስ

1. **በህግ ምፍረስ (dissolution by law)**

እነዚህ ማህበራት በህግ ሊፈርሱ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካት ሲሳናቸው ወይም መፈፀም ሲያቅታቸው (failure of purpose or impossibility of performance) ፣ ከማህበሩ ካፒታል ሶስት አራተኛው ሲጠፋ (loss of three quarter of the capital) እና የመክሰር ክስ ሲቀርብ (institution of bankruptcy proceedings) ናቸው፡፡ (ን/ህ/ቁ 331(4)፣ 517 (ሐ)) ሌላው አክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተመሰረተበት ዓላማ አሳክቶ ወይም ሳይሳካ ግዜው ሲደርስ የሚከናወን መፍረስ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 217(ሀ)፣ 495(1)

አንድ አክስዬን ማህበር የተቋቋመበትን ዓላማ በማሳካቱ ምክንያት

በህግ በሚፈርስበት ሁኔታ ዙርያ አንድ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 58/92 ሆርን ኢንተርናሽናል ባንክ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ጋር የነበረን የፍ/ቤት ጉዳይ ወስደን ስንመለከት ሆርን ኢንተርናሽናል ባንክ ፈቃዱ የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 84/1986 መሰረት ሆኖ ብሄራዊ ባንክ የንግድ ፈቃዱን የተሳሳተ መረጃ በመስጠት የተቋቋመ ነው በሚል ምክንያት በመሰረዙ ምክንያት ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት በሆርን ኢንተርናሽናል ከሳሽነት የቀረበ ሲሆን በፍርድ ቤት ትእዛዝ ባንኩ እንዲፈርስ ተደርጓል ፍ/ቤቱ አክስዬን ማህበሩን ለማፍረስ የተጠቀመበት የህግ ድንጋጌ ን/ህ/ቁ 495(1) (ለ) ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት "ማህበሩ የተቋቋመበት ስራ ሲያልቅ" የሚል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ፍ/ቤቱ ሆርን ኢንተርናሽናል

ባንክ እንዲፈርስ ለሰጠው ውሳኔ በምክንያትነት የገለፀው ህግ በአግባቡ እንዳልሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ግን የዚህ ዓይነት ክፍተት ሊመጣ የቻለው በአገራችን የምስረታ (formation) ችግር ያለበት አክስዬንም ሆነ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተመሰረተ በኋላ በህግ ስለሚፈርስበት ሁኔታ በንግድ ህጉ ያልተሸፈነ በመሆኑ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡

1.2 የማህበሩ ዕድሜ ማለቅ (Expiration of the company)

ን/ህ/ቁ 217(3) ማህበሩ በህግ ወይም በስምምነት የሚፈርስበት ምክንያት በሚል ርእሰ ስር ማህበርተኞቹ ማህበሩ እንዲቀጥል ካልተስማሙ በቀር ማህበሩ የተቋቋመበት ዘመን ሲፈፀም ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ አንድ አክስዬን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር ሊፈርስ ከሚችልባቸው ምክንያቶች አንዱ በመመስረቻ ፅሁፍ ላይ ለተወሰነ ግዜ የተቋቋመ ማህበር ከሆነ የጊዜው መድረስ በራሱ በህግ ያገኘውን ህጋዊ ሰውነቱን እንደሚያጣ የሚገልፅ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ አባላቱ ማህበሩ ዘመኑ ሊያልቅ ሲቃረብ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ (extra-ordinary meeting) በመጥራት የማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ (memorandum of association) በ2/3 ድምፅ እንዲሻሻል ከወሰኑ በማሻሻል ሊቀጥሉ እንደሚችሉ በህግ የተፈቀደ መሆኑ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 217(3)፣ 495(1) (ሀ)፣ 425(1)፣ 423 እና የማህበሩ ዓይነት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚሆንበት ጊዜ በን/ህ/ቁ 536(2) መሰረት መሻሻልን የሚጠይቅ ነው፡፡

1.3 የማህበሩ ካፒታል ሶስት አራተኛ መጉደል (loss of three quarter of the capital) ለማህበሩ በህግ መፍረስ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ማህበር ስራውን ለማከናወን የግድ ገንዘብ ያስፈልገዋል ይህ ገንዘብ በሶስት ዓይነት መንገድ የሚገለፅ የማህበሩ ካፒታል ሊሆን ይችላል ይሄውም፡-

- በማህበሩ መመስረቻ መሰረት ፅሁ (አክስዬን) እንዲወጣ በመደረግ የሚገኝ የማህበሩ ካፒታል (nominal capital or authorized capital) የሚባለው ዓይነት ካፒታል፣
- ሌላው በማህበሩ የወጡ አክስዬኖች ዋጋ (issued or subscribed capital) የሚባለው ሲሆን፣
- ሶስተኛው ለአክስዬኖች የተከፈለው ገንዘብ መጠን (paid up capital) ወይም አክስዬኑ ያልተከፈለ ዋጋ (un paid capital) የሚባል ሲሆን በዋናነት አንድ አክስዬን ማህበር ስራዎቹን በሚያካናውንበት ጊዜ ሶስተኛ ወገኖች ዋስትና ተሰምቷቸው ያለ ስጋት ከኩባንያው ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ የሚያስችላቸው የማህበሩ ካፒታል ስለሆነ አክስዬን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ን/ህ/ቁ 80 እና 517 (መ) እና (ሰ) መሰረት ካፒታላቸውን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ስለ ካፒታል መጥፋት ስናስብ መሰረታችን የሚሆነው የአክስዬን ዋጋ በሙሉ ስለተከፈለበት አክስዬን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ

የተወሰነ የግል ማህበር ካፒታል እንጂ ቀደም ሲል ስለገለፅናቸው የማህበሩ ካፒታል ሁለት ሶስተኛ መጥፋት አለመሆኑን ከን/ህ/ቁ 495(1) (ሸ) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ በአንድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሶስት አራተኛው ካፒታል መጥፋትን መሰረት በማድረግ ሊፈርስ የሚችለው በን/ህ/ቁ 543(1) መሰረት በማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማህበሩ እንዲፈርስ ሃሳብ ሲቀርብ መሆኑና የዚህ ዓይነት መፍረስ ሊከሰት የሚችለው የማህበሩ ሶስት አራተኛ ካፒታል በመጥፋቱ ምክንያት አንድ አክስዬን ማህበር እንዲፈርስ የሚደረገው በን/ህ/ቁ 495(2) የአባላቱ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ (Extraordinary meeting) በመጥራት መሆኑና ይህም የሚደረግበት ምክንያት አባላቱ የማህበሩን ካፒታል ከፍ እንዲል በማድረግ ሊታደጉት ይችሉ እንደሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ን/ህ/ቁ 495(3) እንደሚደነግገው በአንድ ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ጠያቂነት ማህበሩ በፍ/ቤት እንዲፈርስ ይደርጋል፡፡

1.3 ኩባንያው በመክሰሩ ምክንያት ክስ ሲቀርብበት የሚኖር መፍረስ (bankruptcy proceeding)

አክስዬን ማህበርና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሁሌ ነጋዴ ናቸው ተብለው ሲለሚታሰቡ ለመክሰር ህግ በእጅጉ የቀረቡ የንግድ ማህበራት ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ን/ህ/ቁ 968 (1) በን/ህ/ቁ 5 መሰረት ነጋዴ በሆኑና በን/ህ/ቁ 10(1) ከአሸሙር ማህበር በስተቀር የመክሰር ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ሲል የሚደነግገው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ማስተዋልን የሚጠይቅ ነገር ን/ህ/ቁ 969 "ማንኛውንም ከንግድ የተያያዘውን ዕዳውን መክፈል ያቋረጠና መክሰሩ በፍርድ ቤት የተወሰነ ነጋዴ ሁሉ ሆኖ የሚቆጠር ነው" በማለት ስለሚደነግግ የመክሰር ህግ የሚመለከተው በን/ህ/ቁ 5 ነጋዴ ለሚባሉ ብቻ ነው የሚል ትርጓሜ በመስጠት ሌሎች የንግድ ማህበራትን አይመለከትም ብሎ መወሰድ የለሌበት መሆኑ ነው፡፡ ለምን ቢባል ን/ህ/ቁ 5 ከ10 ጋር አጣምረን ካየነው ከአሸሙር ማህበር በስተቀር ሁሉም የንግድ ማህበራት ነጋዴ ናቸው ተብለው ስለሚታሰቡ አክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርም የመክሰር ህግ በነሱም ላይ ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ አንድ አክስዬን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዕዳውን መክፈል ካልቻለ በ15 ቀን ውስጥ ስልጣን ወዳለው ሬጂስትራር ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡ (ን/ህ/ቁ 974) የዚህ ማህበራት በመክሰር ምክንያት በፍ/ቤት ውሳኔ መስጠቱን እንደምክንያት በመውሰድ በህግ እንደፈረሱ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ን/ህ/ቁ 495(1) ይዘት በመመልከት ልንገነዘብ የምንችል ሲሆን ይህ የሚደረግበት ምክንያትም አንድ ከሰሯል የተባለ የንግድ ማህበር በአባላቱ ውሳኔ ይቀጥል የሚባል ከሆነ የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ዋስትና እንዲያጡ

የሚያደርግ በመሆኑ መክሰር እንደ አንድ የንግድ ማህበር በህግ የሚፈርስበት ምክንያት በመውሰድ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስትና መስጠት ተገቢ በመሆኑ ነው።

በንግድ ህጉ አንድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመክሰር ምክንያት ሊፈርስ ስለሚችልበት ሁኔታ በተለየና ግልፅ በሆነ መንገድ የሚለው ነገር የለም። ሆኖም ግን ን/ህ/ቁ 542 ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሌሎች የንግድ ማህበራት በሚፈርሱባቸው ምክንያቶች ሊፈርስ እንደሚችል የሚደነግግ በሆኑና ሌሎች የንገድ ማህበራት በመክሰር ምክንያት ሊፈርሱ እንደሚችሉ ደግሞ ን/ህ/ቁ 968(1) ስለሚደነገግ የዚህ ዓይነት ማህበርም በመክሰር ምክንያት ሊፈርስ እንደሚችል ግልፅ ሊሆን ይገባል። የንግድ ማህበር ይፈርስልኝ ጥያቄ የሚቀርበውም በን/ህ/ቁ 975 መሰረት፡-

- ነጋዴው መክሰሩን ለማሳወቅ ማመልከቻ ሲያቀርብ
- አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ሲያመለክቱ
- ህግ ኣስከባሪው ሲጠይቅ
- ፍ/ቤት ራሱ ሲፈቅድ ናቸው።

ስለዚህ የአንድ የንግድ ማህበር መፍረስ ከህግ ሊመነጭ የሚችለው የተቋቋመበት ዓላማ ማሳካት ሲሳነው፣ ዓላማውን ያሳካ ቢሆንም የተቋቋመው ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑና ጊዜው ሲደርስ ኣባላቱ የመመስረቻ ፅሁፋቸውን በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሁለት ሶስተኛ ድምፅ በማግኘት እንዲታደስ ለማድረግ የሚያስችል ውሳኔ መስጠት ሳይችሉ የቀሩ እንደሆነ ወይም በመክስር(bankruptcy) ምክንያት ወይም ን/ህ/ቁ 495(1) የተዘረዘሩ ሌሎች ምክንያቶች ነው።

2. በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስ (Dissolution by the court)

አንድ ኣክስዬን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኣባላቱ ወይም አንድ አባል በቀረበ የይፍረስልን ጥያቄ ሊፈርስ ይችላል። (ን/ህ/ቁ 218(1)) ኣባል የሚባለውም በን/ህ/ቁ 331 ወይም 521 መሰረት መዋጮ ያደረገ ሰው ነው። ማህበሩ እንዲፈርስ የሚደረገው ግን እንዲሁ የማህበሩ ኣባል ስላመለከተ ብቻ ሳይሆን በን/ህ/ቁ 218 መሰረት ትክክልኛ ምክንያት (good cause) መኖርንም ጭምር የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም እዚህ ላይ እንደመከራከርያ ሊነሱ የሚችሉት ሃሳቦች ን/ህ/ቁ 218(2) በሁሉም የንግድ ማህበራት ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደነገገ በመሆኑ በኣክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርም ተፈፃሚ መሆን ኣለበት። በፍርድ ቤት ውሳኔ የመፍረስ ጉዳይ ለሽርካ ማህበር ብቻ የተሰጠ የማፍረሻ መንገድ ኣይደለም። በሁሉም የንግድ ማህበራት ተፈፃሚነት ማግኘት ያለበት ነው የሚሉ መከራከሪያዎችን በማንሳት ን/ህ/ቁ 495(1) እና 542(1) ጠቅሶ መከራከር ይቻላል። ሌላው መከራከርያ ሊሆን የሚችለውም ን/ህ/ቁ 218(2) ያለቀለት ዝርዝር (exhaustive list) ኣይደለም በማለት የሚቀርብ መከራከርያ ነው። በዚህ ርእሰ ጉዳይ የፍርድ ቤት ኣቋም ምን ይመስላል ብሎ ለማየት ዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያ ከብሄራዊ ባንክ ጋር የተከራከሩበትን

ፍ/መ/ቁ 812/88 ወስደን ስናይ መሰራቾች ነን የሚሉት ከብሄራዊ ባንክ ጋር የተፈጠረው ከፍተኛ አለመግባባት ምክንያት በማድረግ ማህበሩ እንዲፈርስ አቤቲታቸውን ወደ ፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያና ብሄራዊ ባንክ መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት መፈጠሩን ሳያጣራ በሌሎች ፍሬ-ነገሮች እንደ ጠቅላላ ጉባኤ አለማካሄድ፣ አዲተሮች ያለመሾም፣ ከአባላቱ በመዋጮ የተሰበሰበ የማህበሩ ገንዘብ ዕዳው ለመሸፈን የማይችል መሆኑን እንደ ትክክልኛ ምክንያት (good cause) በመውሰድ ዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያ እንዲፈርስ ወስኗል። ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ መረዳት የሚቻለው በን/ህ/ቁ 218(2) የተዘረዘሩት ትክክልኛ ምክንያቶች አንድ የንግድ ማህበር በፍ/ቤት ውሳኔ ለማፍረስ ብቸኛ ምክንያቶች አለመሆነቸውን ነው።

ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን በፍ/ቤት በማፍረስ ዙርያ ያሉትን የፍ/ቤቶች አካሄድ ስንመለከት እንደዚሁ የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት አቶ ጣሂር ሃጂና አቶ አብዱል መሊክ የመሰረቱት "Engineering and mechanical work shop Garage private limited company" በመካከላችን አለመግባባት ስለተፈጠረ ማህበሩ ይፍረስልን በማለት ባስከፈቱት ፍ/መ/ቁ 2869/87 ላይ ማህበሩ እንዲፈርስ የወሰነ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በአባላቱና አልፋ የጉዞ ወኪል መካከል የነበረውን የማህበሩ ይፍረስልን ክርክር በፍ/መ/ቁ 97/90 ማህበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ ለመስጠት ምክንያት አድርጎ የወሰደው በመካከላቸው ጠንካራ ጠብ የመፈጠሩ ምክንያት ነው። ይህም የሚያሳየው ን/ህ/ቁ 218(2) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደመሆኑ መጠን ለሁሉም የንግድ ማህበራት ተፈፃሚ መሆን አለበት የሚል አረዳድ በፍ/ቤቶች አካባቢ መኖሩን ነው።

3. የአባላት ቁጥር ባለመሟላት ምክንያት የማህበር መፍረስ (Reduction of the number of members below the legal requirement)

ኩባንያውን ለመመስረት በህግ የታወቀው ቁጥር ባለመሟላቱ ምክንያት አንድ ኩባንያ ሊፈርስ ይችላል። ለዚህም ን/ህ/ቁ 311 የአባላቱ ቁጥር ከ5 በታች ከሆነ ማህበሩ እንደሚፈርስ ይደነግጋል። ስለ አክስዬን ማህበር መፍረስ የሚደነግገው ን/ህ/ቁ 495(1) የሚመለሰውም ወደ ን/ህ/ቁ 311 ነው። ስለዚህ አንድ ኩባንያ በን/ህ/ቁ 525 እና 532 (1) ማማላት የሚገባውን አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል። የሃላፊነቱ የተወሰነ ግል ማህበር አባላት ቁጥርን ለመወሰን የተደነገገው ን/ህ/ቁ 511 የአባላቱ ቁጥር ከሁለት በታች ከሆነ ማህበሩ እንደሚፈርስ ይደነግጋል። ሌላው አንድ እንደዚህ ያለ የንግድ ማህበር እንዲፈርስ ምክንያት የሚሆነው የዕጣዎቹ በአንድ ሰው ባለቤትነት ስር መካማችት ሲኖር በን/ህ/ቁ 278(ሰ) መሰረት የሚደረግ መፍረስ ነው። ለዚህም የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት በኢትዮጵያ መድን ድርጅትና ረዲ አለም አቀፍና አባላቱ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መካከል የነበረውን ክርክር በፍ/መ/ቁ 70/89 የአባላቱ ቁጥር ህግ ከሚጠይቀው መስፈርት

በታች በመሆኑ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የአባላት ቁጥር ለንግድ ማህበሩ ህልውና የቱን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ነው፤፤

4. በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የአክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መፍረስ (Voluntary dissolution of share and private limited company)

በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የንግድ ማህበር መፍረስ የሚከሰተው ን/ህ/ቁ 217(ለ) በሚደነገገው መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን ነው፡፡ ይህ ህግ ጠቅለላ ድንጋጌ በሚል ስር የሚገኝ በመሆኑ ለአክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ለዚህም ነው ን/ህ/ቁጥር 495(1) (ሀ) "በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲቀጥል ካልተወሰነ በቀር..." የሚለውን አባባል የሚጠቀመው፡፡ በአክስዬን ማህበር ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚጠራው የአባላቱን የአክስዬን ብዛት ከግምት ሳያስገባ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 424) እንደዚህም ምልአተ ጉባኤውን በተመለከተ ን/ህ/ቁ 425(3) የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለማሳለፍ በመጀመርያው ጥሪ ከባለአክስዬኖች ግማሽ፣ በሁለተኛው ጥሪ አንድ ሶስተኛ፣ በሶስተኛው ጥሪ እጅግ ቢያንስ አንድ አስረኛው ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ ስብሰባው ይቀጥላል ሲል የሚደነግገው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንድ አክስዬን ማህበር ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ በአባላቱ ፈቃድ እንደሚፈርስ ግን በግልፅ የሚለው ነገር የለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያትም በህግ ሁኔታዎች በማስቀመጥ የማህበሩ አባላት ፍላጎትን ከመገደብ ይልቅ በራሳቸው ነፃ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ የማህበር መፍረስን እንድ አካሄድ የመረጠ ይመስላል፡፡

በሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዙርያ ያለውን በፈቃድ ላይ የተመሰረተ መፍረስን ሰናይ ን/ህ/ቁ 217 (ለ) ማንኛውም የንግድ ማህበር በአባላቱ ፈቃድ ሊፈርስ እንደሚችል ቢደነግግም የዚህ ዓይነት ማህበርን የማፍረስ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ የሚደነግገው የህጉ ማእቀፍ ሃላፊነቱ የግል ማህበር በምን መንገድ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ መፍረስን ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚችል የሚለው ነገር የለም፡፡ ን/ህ/ቁ 532(1) እና 535 ቢሆንም ለዚህ መልስ የሚሰጡ አይደሉም፡፡

3.4.5 የሂሳብ ማጣራት (liquidation)

የአክስዬን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እስካሁን እያየናቸው በመጠን ምክንያቶች ሊፈርሱ ይችላሉ፡፡ የፈረሰ ማህበር ሂሳብ መጣራት ደግሞ ከፍተኛ የህግ እውቅና የተሰጠው ነው፡፡ በአገራችን ከን/ህ/ቁ 497-509 ባሉ ድንጋጌዎች የአክስዬን ማህበር ንብረት ማጣራትን በሚመለከት የሚደነግግ ሲሆን ስለ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ማጣራት ከመፍረስ ቀጥሎ የሚመጣ አማራጭ የሌለው መንገድ (indispensable element) ሆኖ ሳለ ስለመፍረስ ብቻ ደንግጎ ስለ ማጣራት በዝምታ ማለፉ ምክንያታዊ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሽርካና አክስዬን ማህበር

ቅይጥ እንደመሆኑ መጠንና በሽርካና አክስዬን ማህበር የማጣራት ሂደት ተመሳሳይነት ያለው ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የአንዳቸውን የማጣራት ሂደት ህግ ተከትለን እንዳናጣራ የሚከለክል ህግ ባለመኖረሩ በዚህ መንገድ ሂሰሳቡን ማጣራት ይቻላል ። ስለ ማጣራት ስናነሳ የአጣሪዎችን ጉዳይ ማንሳታችን የግድ ሰለሆነ አጣሪዎችን በተመለከተ በሚቀጥለው መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል።

1. የአጣሪዎች ህጋዊነት (Legal status of liquidators)

አጣሪ ሁለት (dual) ማንነት ያለው ነው። አንደኛው ኩባንያውን በመወከል የሚይዘው አቋም (position) ሲሆን ሌለኛው ደግሞ አበዳሪዎችን በመወከል የሚኖረው አቋም (position) ነው። የኩባንያው ወኪል በመሆን በን/ህ/ቁ 500(1) መሰረት ንብረት መሸጥ የሚችል ሲሆን ስራውን የሚያከናውነውም ልክ እንደ ኩባንያው አስተዳዳሪ በመሆን እንደሆነና የሚኖረው ግዴታም ሆነ ሃላፊነት የሚገዛው በን/ህ/ቁ 499(1) መሰረት ነው።

2. የአጣሪዎች ሹመት(Appointment of Liquidators)

አጣሪ የሚሸምበት ዋናው ምክንያት ፍትሃዊ የንብረት አስተዳደርና ክፍፍል በአባዳሪዎች (Creditors) እና በን/ህ/ቁ 496 መሰረት የሚሾመው በመመስረቻ ፅሁፍ ወይም ኩባንያው ለማፍረስ በተካሄደው ጠቅላላ ድንገተኛ ጉባኤ ነው። ከሁለቱ ባንዱ መንገድ ካልተሾመ በፍርድ ቤት ሊሾም ይችላል። ን/ህ/ቁ 496(1) አጣሪ ስለሚሾምባቸው መንገዶች ቢደነግግም የመመስረቻ ፅሁፍን በማስመልከት የተደነገጉት ን/ህ/ቁ 313 እና 516 በመመስረቻ ፅሁፍ አጣሪ ስለሚሸምበት የሚሉት ነገር የላቸውም። ይህም ብቻ አይደለም አጣሪ የሚሆን እንዴት ያለ ሰው እንደሆነና የተፈጥሮ ሰው አጣሪ ስለሚሆንበት ሁኔታም ሆን እንዳይሆን የሚከለከልበት ግልፅ የሆነ ድንጋጌ የለም። በነዚህ ሓሳቦች ዙርያ አንድ Lawrence church የተባለ ፀሃፊ፤ በዚህ ፀሓፊ አባባል አጣሪ መሆን ያለበት የተፈጥሮ ሰው ነው ለምን ቢባል ን/ህ/ቁ 347(4) የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር የተፈጥሮ ሰው መሆን አለበት በማለት ስለሚደነግግ የተፈጥሮ ሰው በመሆኑ በህግ የወጣን ነገር በመጣስ በህግ ሰውነት የተሰጠውን ተቋም አጣሪ (liquidator) አድርጎ መሾም አይቻልም የሚል ነው። የአጣሪ መሾም ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? ያልን እንደሆነ ን/ህ/ቁ 499(2) ዳሬክተሮቹ በስራ ላይ እንደሚቆዩ የሚደነግግ በመሆኑ አጣሪዎች ስራቸውን በአግባቡ እንዳያከናውኑ ሊገቷቸው የሚችሉ መሆናቸውና ን/ህ/ቁ 498(2) ዳሬክተሩ ማህበሩን ሊወክል ስለሚችልበት ሁኔታ ስለሚደነግግና ን/ህ/ቁ 497(2) ዳሬክተሮቹ በማጣራቱ ወቅት አንዳንድ ስራዎች እየሰሩ በማህበሩ ስለመቆዩበት ሁኔታ የሚጠቁመው ነገር በመኖሩ አጣሪዎች በተገቢው መንገድ ስልጣናቸውን መሰረት በማድረግ እንዳይሰሩ ሊገድባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ የሚያሳይ ነው። ሆኖመ ግን አጣሪዎቹ ይህን ተቋቁመው ንብረቱን የማጣራትና ለጉዳዩ እልባት የመሰጠት

ሃላፊነትና የንግድ ህጉ በሚሰጣቸው መብት ተጠቃሚ የመሆን መብትን የሚያሰገኝላቸው ነው።።

3. የኣጣሪዎች ክፍያ (Remuneration of liquidators)

የሂሳብ ኣጣሪ የኩባንያውን ኣባላትን ሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች (creditors) ለመርዳት ሲል ወደ ስራው የሚገባ ሰው ኣይደለም። የንግድ ህጉ ስለ ሂሳብ ኣጣሪ ክፍያ የሚለው ነገር ባይኖርም ይህን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ኣስተያየቶችን መስጠት ይቻላል። ኣንደኛው ህግ ኣውጪው የሂሳብ ኣጣሪውን ክፍያ የመወሰን ጉዳይ ለኧሚዎች ስለተወው እነርሱ መወሰን ይችላሉ የሚል ሲሆን ሌላው የዳሬክተሮችና ስራ ኣስኪያጆች ክፍያ በኣባላቱ የሚወሰን እስከሆነና የሂሳብ ኣጣሪው ሃላፊነት በን/ህ/ቁ 499 መሰረት የዳሬክተሮችና ስራ ኣስኪያጆች ካላቸው ሃላፊነት ጋር እኩል እስከሆነ ድረስ ክፍያውም መወሰን ያለበት በማህበሩ ኣባላት ነው ብሎ በህጉ የሚታየውን ክፍተት መሙላት ይቻላል የሚል ነው።

4. የሂሳብ ኣጣሪውን ስለመሻር (removal of a liquidator)

የሂሳብ ኣጣሪን መሻር በማስመልከት ን/ህ/ቁ 496(3) "ሂሳብ ኣጣሪዎችን የማህበሩ መፍረስ የመወሰነው ጉባኤ ሊሽራቸው ይችላል። ሂሳብ ኣጣሪዎቹን በቂ በሆኑ ምክንያቶች ማህበርተኞች ወይም ተቆጣጣሪዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ በ/ን/ህ/ቁ 493(2) መሰረት ፍርድ ቤት ሊሽራቸው ይችላል።" በማለት ስለሚደነግግ የሂሳብ ኣጣሪዎች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤና በፍርድ ቤት ውሳኔ ከስልጣናቸው ሊነሱ ይችላሉ።

5. የሂሳብ ኣጣሪዎች ኣጠቃላይ ስልጣን

የሂሳብ ኣጣሪዎች የኩባንያው ወኪሎች እንደመሆናቸው መጠን የሚኖራቸው ስልጣንም መታየት ያለበት ኣንድ ወኪል ከሚኖረው ስልጣን ኣንፃር ነው። በዚህም መሰረት ኣጣሪዎች ፍ/ብ/ህ/ቁ 2189 እንደሚደነግገው ወካዩ በሰጠው ስልጣን መሰረትና ለወካዩ ጥቅም መስራት ይጠበቅበታል። ይሁንና ሂሳብ ኣጣሪ የኩባንያው ወኪል በመሆኑ ስለሚኖረው ስልጣን ለማየት ከፍ ብሎ የተገለፀውን ኣነሳን እንጂ ን/ህ/ቁ 500(1) የሂሳብ ኣጣሪ ስልጣን በማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ሊገደብ እንደሚችል ስለሚደነግግ የሂሳብ ኣጣሪ ስልጣን እንዲሁ ያለገደብ (un limitedly) የተተወ ኣይደለም። ኣንድ ሂሳብ ኣጣሪ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ እንደ ኣንድ የመልካም ቤተሰብ ኣባት (*bonus pater familias*) በከፍተኛ ቅን ልቦና **(utmost good faith)** መስራት ይጠበቅበታል። ኣጣሪዎች የኩባንያውን ንብረትና የሂሳብ ደብተር የመያዝና የገንዘብ ጠያቂዎችን የመጥራትና ዕዳውን የማጣራት ማስረጃ የመመርመር፣ ዕዳውን የመክፈልና የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት የማስጠበቅ፣ ከዕዳ መክፈያ የቀረውን ትርፍ ሃብት በኣባላቱ መካከል እንዲከፈል የማድረግ፣ በን/ህ/ቁ 226 መሰረት ማህበሩ ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ የማድረግ ስራዎችን ይሰራሉ። ለዚህም ን/ህ/ቁ 499(2)፣ 500፣ 504(1)፣ 502(3)፣ 1110፣ 1056፣ 1066፣ 1068፣ 508(2)፣ 505፣ 495፣ 542፣ 217፣ 218 መሰረት በማድረግ ያሉትን የስራ ድርሻዎች፣ ሃላፊነቶችና ስልጣን መገንዘብ ይቻላል።

ስለዚህ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ የንግድ ማህበራት መሰረታቸው ውል ቢሆንም የራሳቸው የተለየ ባህሪ ያላቸውና በንግድ ህጉ ድንጋጌዎች የሚገዙ ናቸው፡፡ እንደሁለም ውሎች ተመስርተው ለረዥም ጊዜም ሆነ ላጭር ጊዜ በሂወት ከቆዩ በኃላ ቀሪ የሚሆኑና ለዚህም የራሳቸው ስርዓት ያላቸው መሆናቸውን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ካልተመዘገበ፣ የማስታወቅ ስራ ካልሰራና ፈቃድ ከሌለው የንግድ ማህበር ጋር የተደረገ ውል ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው?
2. አበበች ጎበና ህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ከAction Aid Ethiopia ጋር በመተባበር ገቢው ለጎዳና ተዳዳሪዎች ማሳደጊያ የሚውል “ወገን ለወገን” ማተሚያ ቤት ቢከፍት በን/ህ/ቁ 210 ትርጉም የንግድ ማህበር ሊባል ይችላልን?
3. የእጅ ኢደጥበበኛ ማን ነው? አንድን ሰው እደ ጥበበኛ ብሎ ለመፈረጅ ያሉት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?
4. በሽርካና የጋራ ባለሃብትነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
5. አክስዬን (ዕጣ) መብት በአላባ ወይም በዋስትና ለሌላ ሰው ሊሰጥ የሚችል መብት ነውን?
6. የአክስዬን ዓይነቶችና ባህርያት ምንድን ናቸው?

7. በኣክስዬንና የግዴታ ወረቀቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
8. ገንዘብ ጠያቂዎች በኣክስዬን ማህበር ዳሬክተሮች ስራ ኣስኪያጆች የግል ንብረት ላይ እጃቸውን ሊዘረጉ የሚችሉት መቼና እንዴት ነው?
9. በንግድ ማህበር መፍረስና ሂሳብ መጣራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
10. በመለወጥ (Conversion) ላይ ባለ ኩባንያ የገንዘብ ጠያቂዎች መብት ምንድን ነው?

4. የኢንሹራንስ ውል ሕግ

4.1. ስለኢንሹራንስ ውል በጠቅላላ (Insurance in General)

ኢንሹራንስ እንደ ግንኙነት በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል በሚደረስ ስምምነት ላይ የሚመሰረት ሆኖ ትርጉሙንና ባህሪውን በምንመለከትበት ጊዜም የኢትዮጵያ ንግድ ህግ በቁጥር 654(1) ላይ የኢንሹራንስን ምንነት በሚከተለው መንገድ፡-

"A contract where by a person called the insurer undertake against payment of one or more premiums to pay a person called the beneficiary a sum of money where a specified risk materializes" በማለት ፍቺ ሲሰጥ የዘርፉ ተመራማሪ የሆኑ E.R.Hardy Ivamy የተባሉ እንግሊዛዊ የዘርፉ ተመራማሪ ደግሞ፡-

> *Insurance or as it is sometimes called assurance, In the widest sense of the term may be defined, as a contract where by a*

person called the insurer undertakes in return for the agreed consideration called the premiums to pay to the another person called the assured on the happening of the specified event.

በማለት የኢንሹራንስን ምንነት ይገልፃሉ፡፡ ከነዚህ ሁለት ትርጓሜች መገንዘብ የሚቻለው ልዩነት ን/ህ/ቁ 654(1) የኢንሹራንስ ካሳ አከፋፈል (mode of indemnification) የኢንሹራንስ ሽፋን የተገባለት አደጋ ሲደርስ የኢንሹራንስ ውል ሰጪው (insurer) ኢንሹራንስ ውል ተቀባዩ (insured) በጥሬ ገንዘብ ካሳ እንደሚከፈል ሲደነግግ በእውቁ ተመራማሪ professor Ivamy በሰጡት ፍች ላይ ግን" A sum of money or its equivalent" በማለት አማራጭ የካሳ አከፋፈልን የሚፈቅድ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ በኢንሹራንስ ትርጉም ዙርያ ሊነሳ የሚችለው ነጥብ አንድ የኢንሹራንስ ውል ተቀባይ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ካሳ እንዲከፈለው በሚጠይቅበት ግዜ የን/ህ/ቁ 654(1) የካሳ አከፋፈሉ ስርዓት በጥሬ ገንዘብ ስለሚል በሌላ መንገድ ካሳውን አልቀበልም ብሎ በመከራከርያ ሊያነሳው ይችላልን? የሚል ሲሆን እንደ አዘጋጁ አስተያየት ከሆነ ካሳ ተከፋዩ በጥሬ ገንዘብ ካልሆነ አልቀበልም ብሎ መከራከር አይችልም የሚል ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለው ን/ህ/ቁ 654(1) ካሳ በጥሬ ገንዘብ እንደሚከፈል ቢደነግግም

1. የኢንሹራንስ ውል ዓላማ የመድን ሽፋን የተገባለት ንብረት አደጋ የደረሰበት መሆኑ ሲረጋገጥ ባለንብረቱን ወይም ህጋዊ ወራሾቹን አደጋው ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መመለስ እስከሆነ ድረስ ይህ ደግሞ በጥሬ ገንዘብ ካልሆነ በሌላ መንገድ መፈፀም አይቻልም ብሎ መደምደም የማይቻል በመሆኑ የዚህ ዓይነት መከራከርያ ተቀባይነት ማግኘት የለበትም የሚልና፡-
2. በኛገራችን ያለውን አሰራር በምንመለከትበት ግዜ ለምሳሌ በናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) ለንግድ ተሽከርካሪ እንዲያገለግል የተዘጋጀው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ክፍል 1 አንቀፅ 2 ላይ፡-

"The company may at its option pay **in cash** the amount of loss or damage or may **repair**, **reinstate** or **replace** the motor vehicle or any part there of ……" በማለት የውል ቃሉን አሰፍሮ የምናገኘውና እስካሁን ባለ የመንግስትም ሆነ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች እየተከተሉት ያለ አሰራር ይሄው በመሆኑና የባለንብረቱን ጥቅም እንዲቀር የሚያደርግ ባለመሆኑ መብቱ ተጣሰ ብሎ ለመክሰስ የሚያስችል ምክንያት የሌለው በመሆኑ መከራከርያው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል ነው፡፡የኢንሹራንስን ባህሪ በምንመለከትበት ግዜ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አስቀድሞ በኩባንያዎች ተዘጋጅቶ የሚቆይና የኢንሹራንስ ሽፋን የሚጠይቀው ግለሰብ ወይም ድርጅት የማመልከቻ ፎርሙን ሞልቶ ካቀረበ በኃላ በኢንሹራንስ ኩባንያው የስምምነት ቃሉ ተሞልቶ ከቀረበ በኃላ ካስፈለገህ ተቀብለው ካልፈለግክ ደግሞ ተወው (take it or leave it) ፖሊሲን

የሚከተል የውል ዓይነት በመሆኑ የኢንሹራንስ ሽፋን ጠያቂው የመደራደር መብት ዝቅተኛ የሆነበት ልዩ የውል ዓይነት ነው።

4.2. የኢንሹራንስ ውል አመሰራረት (Formation)

አንድ የኢንሹራንስ ውል ሕግ ፊት ዋጋ ያለው ሆኖ የማስገደድ ሃይል እንዲኖረው ከተፈለገ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1678 ያሉትን መመዘኛዎች ኣማልቶ መገኘት ይጠበቅበታል። ይህም ማለት በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ላይ መመስረት ይኖርበታል በመሆኑም የኢንሹራንስ የነፃ ፈቃድ መርህን *(consensus ad idem)* የሚከተል ነው። በነፃ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ስምምነት ኣለ ብሎ ለማለት በጥያቄ ኣቅራቢው (offeror) የቀረበውን የውል ቃል ውሉን ተቀብየዋለሁ የሚለው ወገን (acceptor) የቀረበለትን የውል ቃል ያለምንም ሁኔታ (unconditionally) እንዳለ መቀበል ይጠበቅበታል። ሌላ ቃል በመጨመር መልስ ከሰጠ ግን መቀበል ወይም መስማማት መሆኑ ይቀርና ኣፀፋዊ መጠይቅ (counter offer) ስለሚሆን በነዚህ ወገኖች መካከል የኢንሹራንስ ውል ኣለ ብሎ መውሰድ ኣይቻልም። በመጠየቅና መቀበል ሂደት ኣንደኛው ወገን የቀረበለትን ጥያቄ መሰረት ያደረገ መልስ በወቅቱ ሳይሰጥ ቢቀር የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚለውን መሰረት ኣድርገን በምናይበት ግዜ በኣሜሪካን ኣገር ኣብዛኛዎቹ ፍ/ቤቶች የተከሰተው መዘግየት ኣሳማኝ ምክንያት የሌላው መዘግየት (Unreasonable delay) ነው ብለው ባመኑበት ግዜ በኩባንያው ላይ የሚከተሉትን የሃላፊነት መርሆች መሰረት በማድረግ ተጠያቂ የሚያደርጉበት ኣሰራርን ይከተላሉ። መርሆቹም

1. የማመልከቻ ፍርም ከሰጠውና ሞልቶ ከመለሰለት በኃላ በተገቢው ግዜ መቀበሉን ካላስታወቀው ፎርሙን በመስጠቱ ብቻ በውስጠ ታዋቂነት የውሉን ቃል እንደተቀበለ ተቆጥሮ ይህን በመጣስ (breach of implied agreement) መሰረት በማድረግ ተጠያቂ የሚሆንበት መርህን ተከትለው የሚወሱኑበት ኣካሄድ፣
2. ማመልከቻ ተሞልቶ በሚቀርብበት ግዜ ለማስተማመኛ ተብሎ የተያዘ ገንዘብ (retention payment) ከነበርና ኩባንያው በወቅቱ መቀበሉን ሳይገልፅ የዘገየ እንደሆነ ኩባንያው ስምምነቱን እንደሰጠ ተቆጥሮ ተጠያቂ (liable) የሚሆንበት የኣወሳሰን መርህን ፣
3. የማመልከቻ ፎርም ተሞልቶ የቀረበለት የኢንሹራንስ ኩባንያ ሳይዘገይ መልስ መስጠት ይኖርበታል። ይህን ግዴታውን በኣግባቡ ካልተወጣ ከውል ውጭ (tort) ሃላፊነት ኣለበት የሚል መርህን ተከትለው ተጠያቂ የሚያደርጉበት ኣካሄድን ይከተላሉ። ከዚህ በመነሳት የኣገራችን ንግድ ህግ በዚህ ጭብጥ ዙርያ ያለው ኣቋም ምንድን ነው? ብለን ስንመለከት ኣንድ የማመልከቻ ፎርም ተሞልቶ የቀረበለት የኢንሹራንስ ኩባንያ መቀበሉን ሆነ ያለመቀበሉን በመግለፅ ሂደት ላይ በመዘግየቱ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግግ ኣይደለም ይህም ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ህግ "ዝም ማለት መቀበል ማለት ኣይደለም" *(non-consent it quit tacit)* የሚለውን መርህ **(maxim)** የሚከተል ነው።

በመሆኑም ነው የኛ አገር ህግ ኢንሹራንስ ገቢውን በማሃል ሊከሰት ከሚችለው የኢንሹራንስ ሽፋን ያለማግኘት ለመከላከል ***(cover note or provisional guarantee)*** ኣሰራርን በን/ህ/ቁ 657 (1) ላይ ደንግጎ የምናገኘው፡፡

የኢንሹራንስ ውል ልዩ ውል ቢሆንም እንደሌሎቹ ውሎች የመጠየቅና መመለስ (offer and acceptance) ችሎታ ያላቸው መሆን (competent parties) የውሉ መሰረት የሆነ ንብረት ወይ ሂወት (subject matter of insurance) የውል ፎርም እና የሚታወቅ አደጋ (certain peril) መግለፅን የሚጠይቅ የውል ዓይነት ነው፡፡ የኢንሹራንስ ውል ለመግባት ሁለት ሰነዶችን መጠቀም ይጠይቃል እነህም በኢንሹራንስ ሽፋን ጠያቂው (offeror) የሚሞላ ቅፅ (Proposal form) እና የመድን ሽፋን ሰጪ (acceptor company) የውሉን ቃል በማተት የኢንሹራንስ ኩባንያ ስራ ኣስኪያጅ የሚፈርምበትና የኩባንያው ማህተም የሚያርፍበት ፖሊሲ ናቸው፡፡ የነዚህ ሰነዶች ይዘት አጠር ባለመልኩ የተመለከትን እንደሆነ በማመልከቻ ፎርሙ (insurance proposal) ላይ እንደ የሚጠየቀው ኢንሹራንስ ሽፋን የተለያየ ቢሆኑም ሀሉም ዓይነቶች በይዘትነት ኣካተውት የምናገኘው ይዘት ደግሞ ኣላቸው፡፡

1. የኢንሹራንስ ሽፋን ተቀባዩ ማንነት የሚገልፅ (description of the proposed assured)
2. የኣደጋው መግለጫ (description of the risk)
3. የኢንሹራንስ ሽፋን የተጠየቀበት አደጋ እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች (description of circumstances affecting the risk)
4. የኢንሹራንስ ሽፋን የተጠየቀበት አደጋ እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች (Previous history of the offeror) ዋናው ይዘቱ ሆኖ ግን ደግሞ በኢንሹራንስ ሽፋን በተጠየቀበት ንብረት ወይም ሂወት ሁኔታ ላይ እንዲያተኩር ተደርገዉ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

4.2.1 የኢንሹራንስ ፖሊሲ ይዘት (contents of the policy)

የኢንሹራንስ ፖሊሲ በኩባንያዎች የሚዘጋጅ የውል ሰነድ ነው፡፡ የዚህ ሰነድ ይዘትም ከዚህ በታች በተገለፀው መልኩ ተዘጋጅቶ የሚቆይ ሰነድ ሆኖ ይዘቱም፡-

1. የኢንሹራንስ ዓይነትና ባህርያት የሚገልፅ መግቢያ (preamble clause)
2. የኢንሹራንስ ሽፋን ከመቼ እስከ መቼ እንደሚቆይና የኢንሹራንስ ሽፋን ሰጪው ካሳ የሚከፍልባቸው ሁኔታዎች (operative clause)
3. የኢንሹራንስ ኩባንያው ስራስኪያጅ የሚፈርምበትና የኩባንያው ማህተም የሚያርፍበት (signature clause) የያዘ ሲሆን ፖሊሲው በዋናነት የውሉን ሁኔታዎች (conditions) የያዘው የፖሊሲው operative clause ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት የምናገኘው ክፍል የያዘ ነው፡፡

ከኢንሹራንስ ኣመሰራረት ጋር ተያይዞ በህግና በተግባር መካከል ያለው ሁኔታ መሰረት በማድረግ በኣገራችን ያለው የፎርም ሁኔታ ምን ይመስላል? ብለን ስንመለከት ለኣንድ ህግ ፊት ዋጋ ያለው የኢንሹራንስ ውል (valid contract of insurance) ፈቃድ፣ ችሎታ ያላቸው መሆንና ህጋዊ መሆን ኣስፈላጊ የመሆኑን ያክል የኢንሹራንስ ውል ፎርም ህግ በሚያዘው መሰረት መፈፀሙ ለውሉ ዋጋ ያለው መሆን (validity) ወሳኝ ነው፡፡ በኣገራችን የኢንሹራንስ ፎርም ምን መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህ/ቁ 1725(1) በግልፅ በፅሑፍ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ ሲደነግግ በንግድ ህጉ እምብዛም ግልፅ ባልሆነ መንገድ (not vividly) በን/ህ/ቁ 657(1) የኢንሹራንስ ውል በኢንሹራንስ ፖሊሲ መደገፍ እንዳለበት በን/ህ/ቁ 667(3) የኢንሹራንስ ውል በኢንሹራንስ ፖሊሲ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑና ፖሊሲው የውሉን ዝርዝር ይዘት መያዝ ያለበት ስለመሆኑና በን/ህ/ቁ 659(1) በበኩሉ ውሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ የኢንሹራንስ ውልን ፎርም በማስመልከት የሚደነግጉ ህጎች መገንዘብ የሚቻለው የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በኣገራችን ፍ/ብ/ህ/ቁ 1727(1) መሰረት ውሉ በተዋዋይ ወገኖች መፈረም ያለበት ስለመሆኑና ፍ/ብ/ህ/ቁ 1728(1) ውሉ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ እንዳለበት በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የኢንሹራንስ ውልን ኣመሰራረት በተመለከተ በኣገራችን ያለው ኣካሄድ ግን በእጅጉ ከህጉ ያፈነገጠ ነው የሚመስለው፡፡ በተግባር እየተሰራበት ያለው ኣካሄድ የኢንሹራንስ ሽፋን ጠያቂው ማመልከቻውን (Proposal) ሞልቶ ያቀርብና ከኩባንያው ጋር ከተነጋገሩ በኃላ ስምምነት ላይ ከደረሱ ኩባንያው የኢንሹራንስ ፖሊሲውን በሞምላት የስራ ኣስክያጁን ፊርማና የኩባንያው ማህተም ኣርፎበት ውል ነው ተብሎ ለኣመልካቹ ተሰጥቶት ውል እንደተመሰረተ የሚወሰድበትን ኣካሄድ የሚከተል ነው፡፡ ይህም ማለት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1727(1)፣ 1728(1) መሰረት የኢንሹራንስ ውሉ፡-

- በፅሁፍ መሆን እንዳለበት
- የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ በኣንድ ሰነድ መኖር
- በምስክሮች መረጋገጥ የሚጠይቅ ሲሆን

በን/ህ/ቁ 657፣ 658፣ 659 መሰረት ደግሞ

- ማመልከቻውን የመሙላት
- ውሉን ፖሊሲ በሚባል ሰነድ ማዘጋጀት
- የፖሊሲው መፈረም የሚጠይቅ ፎርማሊቲ ያለው ነው፡፡

የፍታብሄር ህጉንና የኢንሹራንስ ህጎችን ፎርምን በማስመልከት ያላቸውን ይዘት ስንመለከት የተወሰነ ልዩነት እንዳላቸው ማስተዋል የሚቻል ቢሆንም የንግድ ህጉ የፍታብሄር ህጉ ኣጋዥ መሆን peter win ship በዓፉት መፅሃፍ ላይ የሰፈረውን፣

> *“.....a recent theory which is still wide spread maintains that the commercial law is autonomous. I thought it preferable, however, and more in conformity with the permanent place of civil law in the future*

law of Ethiopia, in the theory of obligation, and in regulation of contracts, to maintain the classic principle of the priority of civil law. Commercial law is thus a law supplementing their civil code. This principle I have incorporated in article 1 of the commercial code…

በማለት የወሰድን እንደሆነ የኢንሹራንስ ፎርምን በማስመልከት በፍታብሄር ህጉና ንግድ ህጉ የተወሰነ ልዩነት (apparent contradiction) ያለ ቢሆንም ልዩነቱ መፈታት ያለበት የገለፁትን ገዢው የፍታብሄር ህጎቹ ናቸው በሚል የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ ተዘጋጅቶ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ፈርመውበት በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ አለበት የሚለውን በስራ ላይ እንዲውል በማድረግ እንደሆነ የህጉ አርቃቂ ሃሳብ ቢሆንም በተግባር ከፎርም ጋር በተያያዘ ሁኔታ በፍ/ቤቶች የተለያየ አቋም ሲያዝበት የቆየው የኢንሹራንስ ፎርም ተሟልቷል አልተማላም ክረክር የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት በርካታ ጉዳዮችን ፍ/ብ/ህ/ቁ 1725(ለ)፣ 1727(1) እና 1728(1) በሚያዘው መሰረት የተገባ ውል ባለመሆኑ በኩባንያውና በኢንሹራንስ ውልን ተቀባይ መካከል ውል የለም በማለት ሲወሰን እንደቆየ በፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት

1. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. መልከ ኣክስዬን ማህበር - መ/ቁ 49788
2. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. ኦሮሚያ የውሃ፣ መኣድንና ኢነርጂ ቢሮ - መ/ቁ 24051
3. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. ሳትኮን ሃ.የተ.የግ.ማህበር - መ/ቁ 30269
4. " " " V. ጥሩወርቅ መኮነን - መ/ቁ 04649
5. " " " V. ፈጣን የኮንስትራክሽ ድርጅት - መ/ቁ 39988
6. ብሄራዊ የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ኩባንያ ሀ. አለማዬህ - መ/ቁ 45444

ከሰጣቸው ውሳኔዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከዚህ በተለየ መንገድ የኢንሹራንስ ውል ፎርም መታየት ያለበት ከንግድ ህጉ አንፃር ነው በመሆኑም የንግድ ህጉ የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ የሚደረግ ስለመሆኑ በግልፅ የሚለው ነገር እስከሌለ ድረስ ወደ ፍ/ብሄር ህጉ መሄድ ሳያስፈልግ *" The special derogates over the general "* የሚለውን መርህ ተከትለን መሄድ አለብን በሚል ምክንያትና የንግድ ህጉ ለኢንሹራንስ ጉዳይ ልዩ በመሆኑ ውል አለ ተብሎ ነው መወሰድ ያለበት በማለት በስር ፍ/ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ሲሽር ይታያል፡፡ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ ሳሊኒሌከስ አሸሙር ማህበር ከአዋሽ ኢንሹራንስ ጋር በሚከራከርበት ሰ.መ.ቁ . 23703 ፍ/ብሄር ህጉ በ1725 ላይ የሚደነግገው ለብዙ ዘመን የሚቆዩ ውሎች ስለሆነና የኢንሹራንስ ውል ግን ለአንድ ዓመት ብቻ የሚደረግ ውል በመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡ የሰበር ችሎት ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 454/2005 በሚያዘው መሰረት ታትሞ ያልወጣ በመሆኑ አስገዳጅነት አለው ባይባልም እንደሌሎቹ ውሳኔዎች ለትችት ግን

የተጋለጠ ነው፤፤ ለምን ቢባል እንደ አዘጋጁ ግንዛቤ ከሆነ " ለብዙ ዘመን የሚቆዩ ውሎች" የሚለውን የድንጋጌውን ርእስ ብቻ ወስዶ የኢንሹራንስ ውል ለአንድ አመት ብቻ የሚደረግ ውል ነው በሎ ማሰብ በራሱ የሂወት ኢንሹራንስን ከህጉ ሽፋን የሚያገል ነው፤፤ በሌላ በኩልም ፍ/ብ/ህ/ቁ 1725 ብዙ ዘመን የሚል ቃል በርእስነት መጠቀሙ በ1725(ለ) የተደነገገውን የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ መሆን አለበት የሚለውን የህጉን ሃይለ ቃል መሻር አልነበረበትም፤፤ በመሆኑም የሰበር ውሳኔም ቢሆን በስር ፍ/ቤቶች ከሚታየው የአተረጓጎም ችግር እምብዛም ችግሩን በሚፈታ መንገድ የተሰጠ ውሳኔ ነው የሚሰኝ እይደለም፤፤ ስለዚህ የኢንሹራንስ ፎርምን በማስመልከት በፍ/ብሔር ህጉና የንግድ ህጉ ያሉት ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/2005 የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ ለአመታት የቆየውን አወዛጋቢ ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ ያደረገ ነው በሎ ለማለት የሚያደፍር አይደለም፡፡

የኢንሹራንስ መሰረታዊ መርሆች (Basic Principles of Insurance)

የጉዳት ካሳ ፅንሰ ሓሳብ (The concept of Indemnity)

የኢንሹራንስ ውል ዋስትና የተሰጣቸው አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ሃላፊነት የሚወስድበት ውል አይደለም፡፡ የኢንሹራንስ ዋስትና በተሰጣቸው አደጋዎች ምክንያት የሚደርሰን የገንዘብ ጉዳትና ለመተካት የሚዳረግ ውል ነው፡፡ በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት በሞተር ኢንሹራንስ ፖሊሲ ዋስትና ስለተሰጠው መኪና የኢንሹራንስ ስፋን የሚደረግለት መኪናው አደጋ እንዳይደርስበት መከላከል ሳይሆን በአደጋ ምክንያት የሚደርስ የገንዘብ ጉዳትን ለመካስ ነው፡፡ በመሆኑም በሞተር ፖሊሲው ዋስትና የተሰጠው ነገር መኪናው ሳይሆን የኢንሹራንስ ገቢው የገንዘብ ጥቅም ነው፡፡ የኢንሹራንስ ዋስትና የተሰጠው ነገር ምናልባትም ንብረት ሆኖ የራስና ከእቃው ተለይቶ የማይታይ ዋጋ ቢኖረውም በኢንሹራንስ ውል የውል ጉዳይ (subject matter of Insurance contract) የሚሆነው ማለትም የተዋዋዮች ግዴታ የሚመሰረትበት ነገር ኢንሹራንስ ገቢው በንብረቱ ላይ ያለው የገንዘብ ጥቅም ኢንሹራንስ ገቢው ኢንሹራን ለመግባት የሚያስችል ሕጋዊ መብት ይሰጠዋል፡፡ የኢንሹራንስ ውል በሕግ ድጋፍ እንዲያገኝ ለማድረግ ውሉ ኢንሹራንስ ለመግባት በሚያስችል ጥቅም መደገፍ አለበት፡፡ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ከሌለ የኢንሹራንስ ውል ሊኖር አይችልም በሌላ አነጋገር ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም አለመኖር ውሉን ከመሰረቱ ያፈርሰዋል፡፡

የካሳ መርህ የሚመነጨው የኢንሹራንስ ውሎች የካሳ ውሎች ብቻ ናቸው ከሚለው ህግ ነው፡፡ ይህን ማለት ጉዳቱ መካስ ያበለት ኢንሹራንስ ገቢው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ከነበረበት የገንዘብ አቋም በማያሳንስ ወይም በማያስበልጥ መንገድ ነው፡፡ የመርሁ ግብ ኢንሹራንስ ገቢው ጉዳት ከደረሰበት በኋላ በተቻለ መጠን ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደነበረበት የገንዘብ አቋም መመለስ ነው፡፡ የዚህ መርህ ውጤትም ኢንሹራንስ ገቢው ከጉዳቱ ትርፍ እንዳያገኝ

ወይም ማናቸውንም ጥቅም እንዳያገኝ መከልከል ነው፡፡ የመርሁ ዋነኛ ሓሳብም ካሳ ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ነው፡፡ ማነስም መብዛትም የለበትም፡፡ ካሳው ከጉዳቱ የሚበልጥ ከሆነ ኢንሹራንስ ገቢው ትርፍ ማግኘቱ ሲሆን ይህ ደግሞ ስለ ኢንሹራንስ የመግባት ጥቅም በሚገልፀው ክፍል ውስጥ ከተጠቀሰው ኢንሹራንስ ዓላማ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ በሌላ በኩል ካሳው ያነሰ ከሆነ ኢንሹራንስ ገቢው አልተካሰም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የካሳ መርሆዎች ሚዛኑ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይሞክራል፡፡ ከደረሰው ጉዳት ትርፍ ማግኘት የሚቻል ቢሆን ኢንሹራንስ ገቢው ሆነ ብሎ ጉዳቱን እንዲያመጣ ይገፋፋል፡፡ እንዲሁም ኢንሹራንስ ገቢው ንብረቱን ለመጠበቅና አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከል ግዴለሽ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡ በመሆኑም የዚህ መርህ አስፈላጊነት ከሕዝብ ጥቅም ይመነጫል፡፡ ሆነ ተብለው የሚመጡ ጉዳቶች የአገር ሃብት ያባክናሉ በመሆኑም የህዝብ ጥቅምና የህዝብ ፖሊሲ የኢንሹራንስ ውሎች ካሳ እና ካሳ ብቻ የሚሰጠው እንዲሆኑ ያስገድዳሉ፡፡

ኢንሹራንስ ከጋራ ግንዘብ ጉዳቶችን መካፈል በሚለው መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የጋራ ግንዘቡ ማለትም የአረቦን መዋጮ የሚወስነው ቀደም ብለው በደረሱ ጉዳቶች ላይ በመመስረት እንደመሆኑ ከጋራ ግንዘቡ የሚከፈለው ክፍያ ኢንሹራንስ ገቢው ትርፍ ወይም ጥቅም ሳያገኝ በደረሰበት ጉዳት ልክ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የካሳ መርህ ተግባራዊ የማይሆን ከሆነ የኢንሹራንስ ዘርፍ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥርና ለሃብት ብክነት የሚዳርግ ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ የኢንሹራንስ ውል መሰረቱ ካሳ መክፈል በሚሆንበት ግዜ የሚከተለው ዓላማ አደጋ ያገጠመውን ባለንብረት አደጋ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት የኢኮኖሚ ሁኔታ መመለስ ሲሆን የካሳው መጠንም ከደረሰበት ጉዳት መብለጥ የሌለበት መሆኑን ን/ህ/ቁ 678 መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሌ የጉዳት ካሳው መጠን ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል መሆን አለበት ማለት አይደለም ምክንያቱም ኢንሹራንስ ሽፋን በከፊል በመግዛት ባለንብረቱ ቀሪውን ራሱ በንብረቱ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ወደነበረበት የመመለስ አሰራር (self insuring) በጉዳት ካሳ መርህ የሚከለከል ባለመሆኑ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የሚኖረው የካሳ አከፋፈል መሰረት ተደርጎ የሚወሰደው የጉዳቱ መጠን ሳይሆን የኢንሹራንስ ሽፋኑ መጠን ነው፡፡

4.3.2. ኢንሹራንስ ሊገባባት የሚችል ጥቅም (Insurable interest)

የኢንሹራንስ ውል ኢንሹራንስ ሊገባበት የሚችል ጥቅም መኖርን እንደ አንድ ህጋዊ መስፈርት የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህም ነው አንድ Patterson የተባሉ የዘርፉ ተመራማሪ “An insurable interest in its broadest sense is a relation between the insured and the event will cause substantial loss or injury of the some kind to the insured.” በማለት የሚገልፁት፡፡ ይህን ዘርዘር ባለ መልኩ ስናይ አንድ ሰው ኢንሹራንስ ሊገባበት

የሚችል ጥቅም ኣለው የሚባለው መቼ ነው? የመለውን ያነሳን እንደሆነ Professor Vance በዓፉት መፅሃፍ ላይ በሚመለከተው መልኩ ኣንድ ሰው ኢንሹራንስ ሊገባበት የሚችል ጥቅም ኣለው የሚባለው፡-

- *When the insured possesses a legal title to the property insured, whether vested or contingent, defensible or indefensible.*
- *When he has an equitable title, of whatever character and in whatever manner acquired.*
- *When he possesses a qualified property or possessor right in the subject of the insurance, such as that of bailee.*
- *When he has mere possession or right of possession.*
- *When he has neither possession of the property, nor any other legal interest in it, but stands in such elation with respect to it that he may suffer, from its destruction, loss of legal right dependent up on its continued existence.* ሲኖር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይህ የኢንሹራንስ መርህ በኣገራችን ን/ህ/ቁ 675 እና 693 ተደንግጎ የምናገኘው ሲሆን መርሁ ህዝባዊ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ የዜጎች ጥቅምን የማስጠበቅ ዓላማ ያለው ነው፡፡ ኣንድ ሰው የኢንሹራንስ ሽፋን ሊሰጠው የሚያስችል ጥቅም ኣላው ብሎ ለማለት ከሂውት ኢንሹራንስ ውጭ ባሉ ሌሎች የኢንሹራንስ ዓይነቶች የኢንሹራንስ ሽፋን የሚሰጠው ነገር በግንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ የካሳ መሰረተ ሃሳብ ውጤት ከሆኑ ነገሮች ኣንዱ ኢንሹራንስ ገቢው የሚጠይቀው ካሳ የደረሰበትን ኪሳራ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ኪሳራ እንዲደርሰበት ከተስፈለገ በወደመው ወይም በተጎዳው ንብረት ላይ ጥቅም ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ ኢንሹንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅምን የሚደግፉ ዋና ዋና ሁኔታዎች የሚከተሉ ናቸው፡፡

ሀ. ዋስትና ሊሰጠው የሚቻል ንብረት፣ መብት፣ ጥቅም ፣ ሕይወት፣ ሃላፊነት መኖር

ለ. ይህ ንብረት መብት ሕይወት ወዘተረፈ የኢንሹራንስ ዋስትና የሚሰጠው ነገር (subject mater of Insurance) መሆን ኣለበት፣

ሐ. ኢንሹራንስ ገቢው የኢንሹራንስ ዋስትና ከሚሰጠው ነገር ጋር ሕጋዊ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማሳየት ማለትም ንብረቱ መብቱ ጥቅሙ ሕይወቱ ሲጠበቅ ተጠቃሚ መሆን ከነዚህ ነገሮች መጉዳት እና ከሃላፊነቱ መፈጠር ደግሞ የሚጎዳ መሆኑን ማሳየት

መ. የኢንሹራንስ ዋስትና በተሰጠው ነገር እና በኢንሹራንስ ገቢው መካከል በሕግ ተቀባይነት ያለው ግንኙነት መኖር ኣለበት

4.3.2.1ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም አፈጣጠር ወይም አነሳስ

❖ **ከባለቤትነት የሚነሳ ጥቅም**

የንብረት ባለቤትነት ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም መኖሩን ለማረጋገጥ የተለመደውና ግልፅ የሆነው ምሳሌ ነው፡፡ ለምሳሌ የአንድ ህንፃ ባለቤት ህንፃው በእሳት ቢጋይ ወይም በሌላ አደጋ ቢጎዳ የገንዘብ ኪሣራ ይደርስበታል፡፡ በመሆኑም ሕጉ ለባንብረቱ ኢንሹራንስ የመግባት እና ኪሳውን የማግኘት መብት ይሰጠዋል፡፡ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ከጋራ ባለቤትነትም ይገኛል፡፡

❖ **ፍፁም ከሆነ ባለቤትነትም ባሻገር ከፊል ባለቤትነት**

ከፊል ባለቤትነት ባለበት ጊዜ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችለው ጥቅም ይኖራል፡፡ በርካታ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችሉ ጥቅሞች በአንድ ንብረት ላይ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ባለቤትና መያዣ ያዥ በአንድ ንብረት ላይ ጥቅም ይኖራቸዋል፡፡ መያዣ ያዡ ማለትም ገንዘቡን ያበደረው ሰው መያዣ የተያዘው ንብረት እንዲጠበቅ ስለሚፈልግ በዚህ ንብረት ላይ ኢንሹራንስ ለማግኘት የሚያስችል ጥቅም አለው፡፡ ነገር ግን ጥቅሙ ባበደረው ገንዘብ ልክ የተወሰነ ብቻ ነው፡፡ በመያዣ የተሰጠው ንብረት ባለቤት ጥቅም ግን የንብረቱ ሙሉ ዋጋ ነው፡፡ እነዚህ የተለያዩ ጥቅሞች በተለያዩ ፖሊሲዎች ዋስትና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ የተለያዩ ከአንድ በላይ ጥቅሞች በአንድ ንብረት ላይ ባለበት ጊዜ ለሁሉም ባለጥቅሞች ፖሊሲ የሚሰጠው የእያንዳንዱን ሰው መብትና ጥቅም በመከተል ነው፡፡ ባንክ ወይም ሌላ የልማት ድርጅት በአንድ ንብረት ላይ ለብድር ዋስትና ምክንያት ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ይኖረዋል፡፡ እናም የኢንሹራንስ ፖሊሲዎቹ ለባንኩ እና ለባለንብረቱ ጥቅም ሊሰጥ ይቻላል፡፡ የካሳ ክፍያ በሚፈፀምበት ጊዜ ሁለቱም መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡

❖ **ከሕግ የሚመነጭ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም**

አደራ አስቀማጭ በራስ ቸልተኝነት በይዞታው ስር ባሉ ንብረቶች ለሚደርስበት ጉዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም በይዞታው ሥር ባሉ ንብረቶች ኢንሹራን ለመግባት የሚያስችል ጥቅም አለው ለምሳሌ (ባለመጋዘን፣ ባለላውንደሪ ወ.ዘ.ተ) ለእሳት አደጋ የሚሰጥ ፖሊሲ እንደሚያስገነዝበው ዋስትናው ሽፋን የሚሰጠው ለኢንሹራንስ ገቢው ንብረቶች ብቻ ሳይሆን በአደራ ወይም በኮሚሽን ለሚጠብቀው ንብረት ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ በመኪና ንግድ ላይ የተሰማራ (Motor trader)፣ ባለጋራዥ በእጁ ላሉ ለጥገና በገቡ የደንበኞች መኪኖች እንደ ንብረት ጠባቂ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም አለው፡፡

❖ **ከውል የሚመነጭ ኢንሹራንስ ለመግባት በሚያስችል ጥቅም**

የአንድ ህንፃ፣ ባለቤት ህንፃውን ሲያከራይ የኪራዩ ዋጋ ህንፃው በእሳት ቢጋይ እንኳን ሊከፈል ይገባል ብሎ ተስማምቷል፡፡ ስለሆነም ተከራዩ በኪራይ ከፍያ ምክንያት የሚደርስበትን ኪሳራ ዋስትና ሊገባበት ይችላል፡፡ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ለመከራየት በሚደረግ ውል ተቋራጩ በመሳሪያው ላይ ለሚደርስ ጉዳት እንዲሁም በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት አለበት የሚል ስምምነት ካለ ተቋራጩ ከውል የመነጨ

ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ስላለው ተስማሚ ዋስትና በራሱ ስም እንዲሁም ከንብረቱ ባለቤት ጋር በጋራ ዋስትና ሊያገኝ ይችላል፡፡ ህንፃ ድልድይ ግድብ ወዘተ ለመገንባት በባለቤቱ ወይም በአሰሪው እና በተቋራጩ መካከል በሚደረግ ውል ውስጥ ተቋራጩ (Contractors' all risk insurance) የሚል የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለሚሰራው ስራ በላዩ ላይ ላሉ እቃዎች የኢንሹራንስ ውለ ሊገባ ይችላል፡፡

❖ **ከሕግ ኃላፊነት የሚመነጭ ኢንሹራንስ ለመግዛት የሚያስችል ጥቅም**

አሰሪዎች በሰራተኞቻቸው ላይ ለሚደርስ የስራ ላይ ጉዳት ማለትም ኪሳራ በመነጨና በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ካሳ ለመክፈል ሕጋዊ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህ ኃላፊነት የሚመነጨው ከኢትዮጵያ የፍትሕብሔር ሕግ ነው፡፡ ይህ የሕግ ኃላፊነት በሚመጣበት ጊዜ የገንዘብ ኪሳራ ይደርሳል፡፡ እናም ይህ ትክክለኛ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅምን ይመሰርታል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የመኪና ባለቤት የሆነ ሰው ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም የሚኖረው በመኪናው ላይ ለሚደርስ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በሌላ ሶስተኛ ሰው አካል ወይም ንብረት ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ሳቢያ ለሚመጣበት የሕግ ኃላፊነት ጭምር ነው፡፡ አንዳንድ የሞተር ፖሊሲዎች ለምሳሌ የግል ተሽከርካሪ ፖሊሲ የሶስተኛ ወገኖች ኃላፊነትም የሚመለከተው ኢንሹራንስ ካሣ የሚከሰው ኢንሹራንስ የገባውን ባለቤት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ተገቢውን መንጃ ፈቃድ የያዙና መኪናውን ለማሽከርከር በኢንሹራንስ ገቢው የተፈቀደላቸውን ሰዎች ጭምር ነው፡፡ በባለቤትነት ኢንሹራንስ የገባው ሰው ሌላ ሰው ላመጣው የሕግ ግዴታ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም የለውም ቢሆንም የካሣ ክፍያው ሲያመቻች እንደተወካይ ይገመታል፡፡ ስለዚህ የዚህ መርህ ዋና መልእክት አንድ ሰው ኢንሹራንስ ሊገባበት የሚችል ጥቅም ከሌለው ጉዳት ቢደርስበት የሚያጣው ጥቅም ስለማይኖር የኢንሹራንስ ውል ሊገባበትም ሆነ የጉዳት ካሳ ሊጠይቅበት ስለማይችል የኢንሹራንስ ውል ለመግባት በውሉ ጉዳይ (subject matter of insurance) ጥቅም ያለው መሆንን የግድ ይላል፡፡

4.3.3. *መዳረግ* (subrogation)

መዳረግ (subrogation) የጉዳት ካሳ መክፈል (indemnity) ሌላው ገፅታ (corollary) ሲሆን ኢንሹራንስ ሽፋን ሰጪ በኢንሹራንስ ተቀባይ እግር ተተክቶ በመብቱ የሚሰራበት መርህ ነው፡፡ የመዳረግ ትርጉም፤-

> *A legal fiction admitted or established by the law, incase exclusively determined by virtue of which an obligation, extinguished with regard to the original creditor by payment which the has received from third person or form the debtor, himself, but with funds that a third person furnished to that effect, in regard as subsisting in favor of this third person who has paid, the rights and actions of the ancient creditor. (Artur and Rau. P.187)*

መዳረግ የሚኖረው መቼ ነው? የሚለውን ስናይ ድግሞ፤-

“Subrogation takes place, in the full sense of the word, when one person, on paying the debt of another is entitled to stand in the shoe of the creditor, and to enforce against the debtor every right which the original creditor could have enforced against him.” (John H. MunKman. P.77) የሚለውን እናገኛለን የዚህ መርህ ህጋዊ አስፈላጊነት የሚመሰርትባቸው ምክንያቶችም፡-

1. የኢንሹራንስ ሽፋን ተቀባይ ሁለት ግዜ የጉዳት ካሳ በመውሰድ ያለአግባብ መበልፀግ የለበትም የሚል አቋም መያዙ፡-
2. ካሳ የመክፈል ጫና ማረፍ ያለበት ጉዳት ባደረሰው ሰው ላይ መሆን አለበት የሚል ህዝባዊ ፖሊሲን መሰረት የሚያረግ መሆኑ፡-
3. በመዳረግ ምክንያት ኩባንያዎች ገቢ ስለሚያገኙ አርቡን በሚወሰኑበት ግዜ ክፍያውን ዝቅ እንዲል በማድረግ እንዲደፋፈሩ ማስቻል ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ የመዳረግ ስነ-ስርዓት የሚመራው በን/ህ/ቁ 683(2) መሰረት ሲሆን የዚህ መብት መሰረቱ ህግ ነው፡፡ ከዚህ መርህ ጋር ተያይዞ ትኩረት ማግኘት ያለበት ጉዳይ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከረው የመዳረግ መበት ከጉዳት ካሳ መክፈል (indemnity) ጋር በእጅጉ ግንኙነት ያለው እንደመሆኑ መጠን ይህ መርህ በሂወት የኢንሹራንስ ውል ላይ ተፈፃሚ የማይሆን መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም በመከንያትነት የሚወሰደው የሂወት ኢንሹራንስ ለተወሰነ ግዜ ከሚደረግ የሂወት ኢንሹራንስ በስተቀር (except term life insurance) የተቀሩት የሂወት ኢንሹራንስ ውሎች የመዋዕለ ንዋይ ቁጠባ (saving or investment) በመሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ መዳረግ ማለት አንድ ሰው ሕጋዊ ግዴታ ኖሮበት ሌላውን ከካስ በኃላ በተካሰው ሰው መብቶች እንዲጠቀም የሚያደርገው መብት ነው፡፡ በአንድ የእንግሊዝ ሃገር የፍርድ ቤት ጉዳይ ላይ እንደተገለፀው ለአንድ ሰው ካሳ የከፈለ ኢንሹራንስ ሰጭ ኢንሹራንስ ገቢው ከሌላ ከማንኛውም ምንጭ ያገኘውን ክፍያ የማስመለስ መብት አለው፡፡ በመሆኑም ይህ መርህ ኢንሹራንስ ሰጭው ኢንሹራንስ ገቢው ከኢንሹራንስ ሁኔታ ጋር

በተገናኘ ማንኛውንም ትርፍ እንዲያስመልስ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ኢንሹራንስ ሰጭዎች በኢንሹራንስ ገቢው ስም በመሆን ሊኖሩት የሚችሉትንና ጉዳቱን ሊቀንሱ የሚችሉትን መብቶች እንዲጠቀምባቸው ያደርጋል፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ጉዳይ ኢንሹራንስ ገቢው ከኢንሹራንስ ሰጭው ከሌላ ወገን ካሳ እንዳይቀበል ኣልተከለከለም፡፡ እየተባለ ያለው ኢንሹራንስ ገቢው ከሌላ ወገን ካሳ መቀበል ቢችል ገንዘቡ የራሱ ሳይሆን ካሳ ለከፈሉት ኢንሹራንስ ሰጭዎች በአደራ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ የመዳረግ ግብ ከካሳ መርህ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ በመሆኑም በኢንሹራንስ ሰጭው የተካሰ ኢንሹራንስ ገቢ ከሌላ ምንጭ ተጨማሪ ካሳ እንዳያገኝ ይከለከለላል፡፡ እዚህ እየያየን ያለነው ኢንሹራንስ ሰጭዎች የከፈሉትን ከኢንሹራንስ ገቢው ውጭ ከሆኑ ሌሎች ወገኖች የሚያስመልሱበት መንገዶች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው መዳረግ የካሳ መርህ ደጋፊ ነው የተባለው፡፡ የመዳረግ መብት የካሳ መርህ ደጋፊ እንደመሆኑ ከላይ እንደተገለፀው ለሂወትና ለኣካል ጉዳት ኢንሹራንሶች ተፈፃሚነት ኣይኖረውም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የካሳ ኢንሹራንሶች ኣይደሉምና፡፡ ኢንሹራንስ ሰጭው ግዴታ ሳይኖርበት ለኢንሹራንስ ገቢው ክፍያ የፈፀመ እንደሆነ ኢንሹራንስ ገቢው ከሌላ ምንጭ ገንዘብ ቢያገኝም ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መበት ኣይኖረውም፡፡ ይህም የሆነው ያለግዴታ ክፍያ እንደ ካሳ ስለማይቆጠርና የመዳረግ መብትም የካሳ መርህን ለመደገፍ የመነጨ በመሆኑ ነው፡፡

4.3.4. መዋጮ (Contribution)

የመዋጮ መርህ የካሳ መርህ ደጋፊ ሲሆን ኢንሹራንስ ገቢው ለተመሳሳይ ጉዳት ከኣንድ በላይ ኢንሹራንስ ሰጭዎች የተሰጡ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ሲኖሩ የካሳውን ኣከፋፈል ለመወሰን የታቀደ ነው፡፡ ኣቋሙ ላይ ስለ መዳረግ መብት ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ማለትም ኢንሹራንስ ገቢው ከኣንድ በላይ የገንዘብ ምንጭ ያለው በመሆኑ ከሁሉም ምንጮች ክፍያ እንዲያገኝ ከተፈቀደለት ትርፍ የሚያገኝበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ የመዋጮ መርህ የካሳ ክፍያ ጥያቄውን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በኢንሹራንስ ሰጭዎች በማከፋፈል ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም መዋጮ ኣንድ ኢንሹራንስ ሰጭ ሌሎች ኢንሹራንስ ሰጭዎች እኩል ላይሆን ቢችልም የካሳውን ክፍያ እንዲካፈሉ ሊያደርግ የሚችልበት መብት ነው ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ የዚህ መርህ መሰረታዊ ነጥብ ኣንድ ኢንሹራንስ ሰጭ ሙሉ የካሳ ክፍያ ቢፈፅም በተመሳሳይ ኣደጋ ኢንሹራንስ ከሰጡት ድርጅቶች ተመጣጣኝ ክፍያ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ ሙሉ የካሳ ክፍያ ያልተከፈለ እንደሆነ ኢንሹራንስ ገቢው ከሌሎች ኢንሹራንስ ሰጭዎች መጠየቅ ያለበት ሲሆን የመዋጮ መርህ ጠቅላላው የካሳ ከፍያ ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ እንዲከፋፈል ያደርጋል፡፡ የመዋጮ መርህ ሌላው የካሳ መርህ ሲሆን ኢንሹራንስ ገቢው ለተመሳሳይ ጉዳት ከኣንድ በላይ ኢንሹራንስ ሰጪዎች የተሰጠው የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ሲኖሩ የካሳውን ኣከፋፈል ለመወሰን የታቀደ ነው፡፡ የዚህ ዓላማም የኢንሹራንስ ገቢው የጥቅም ምንጭ ኣንድ ሆኖ ሳለ ከተለያዩ የኢንሹራንስ ሰጪዎች ካሳ በመውሰድ ትርፍ እንዳያገኝ ለመከላከል ነው፡፡ በመሆኑም ኣንድ

ኢንሹራንስ ሰጪ የካሳ ክፍያውን በሙሉ በመክፈሉ ወይም በከፊል በመክፈሉ ብቻ ከሌሎች የኢንሹራንስ ሰጪዎች በድርሻቸው እንዲከፍሉ ሊጠይቅ የሚያስችለውን መብት ያስገኝለታል፡፡

የመዋጮ መርህ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ከተፈለገ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላትን ይጠይቃል፡፡

- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፖሊሲዎች መኖር አለባቸው ፡፡
- ፖሊሲዎቹ ለተመሳሳይ ንብረት ዋስትና የሰጡ መሆን አለባቸው፡፡
- አደጋው በሁሉም ፖሊሲዎች የሚገኝ መሆን አለበት፡፡
- በስም የተጠቀሰው ኢንሹራንስ ገቢ ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ፖሊሲዎች በተመሳሳይ ጊዜ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ የመዋጮ ዋናው ዓላማ ኢንሹራንስ ገቢው ከዚህ የንግድ ዘርፍ አትራፊ እንዳይሆን በመከላከል ኢንሹራንስ ሰጪዎች በግዴታቸው መጠን ሃላፊ እንዲሆኑ በማድረግ የኢኮኖሚ ዘርፉን ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል ነው፤፤

4.3.5 ቀራቢ ምክንያት (proximate cause)

4.3.5.1 የመርሁ አስፈላጊነት

የኢንሸሹራንስ ውል ዓላማ ለማንኛውም ጉዳት ሳይሆን ኢንሹራንስ በተሰጠው አደጋ ለሚመጡ ጉዳዮች ካሳ መክፈል ነው፡፡ የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጣቸው አደጋዎች ፖሊሲው ላይ በግልፅ የተመለከቱ ሲሆን የኢንሹራንስ ሰጭው ሓላፊነት የሚመጣው ጉዳቱ ዋስትና በተሰጠው አደጋ መንስኤነት ሲመጣ ብቻ ነው፡፡ ጉዳቱ ዋስትና በተሰጠው ወይም ባልተሰጠው ወይም በተገለለ አደጋ ምክንያት ሊመጣ እንደሚችል ግልፅ ነው፡፡ **ለምሳሌ** ዕቃዎች ቢቃጠሉ የጉዳቱ ምክንያት እሳት በመሆኑና በቃጠሎ ፖሊሲ የተሸፈነ በመሆኑ ካሳው ተከፋይ ይሆናል፡፡ የዕቃዎቹ መሰረቅ ስርቆት በቃጠሎ ዋስትና የማይሸፈን በመሆኑ ካሳው ተከፋይ አይሆንም፡፡ ዕቃዎቹ በአመፀኞቹ ቢቃጠሉ የጉዳቱ ምክንያት አመፅ ስለሆነና ይህም በቋሚው የቃጠሎ ፖሊሲ የተገለለ በመሆኑ ካሳው ተከፋይ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ጉዳቱ የሚያስከፍል መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የጉዳቱን መክንያት መወሰን ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳት ሲደርስ በፖሊሲው መሸፈን አለመሸፈን ለማረጋገጥ የጉዳቱን ምክንያት ወይም ምክንያቶች መወሰን አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው Aristotle “true knowledge is the knowledge of proximate cause” በማለት የሚገልፀው፤፤ ጉዳቱ የአንድ ምክንያት ውጤት ብቻ ሲሆን ኢንሹራንስ ገቢው ሃላፊነቱን ለመቀበል የሚያደርገው ውሳኔ ቀለል ያለ ነው፡፡ ማድረግ የሚኖርበት ጉዳቱን ያደረሰው አደጋ በፖሊሲው መገለፁን መመልከት ብቻ ነው፡፡ የተገለፀ ከሆነ ሃላፊነትን ይቀበላል ካልሆነ አይቀበልም፡፡ በሌላ በኩል ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ጉዳቱን ሊያመጡ የሚችሉባቸው

ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ በነዚህ ሁኔታዎችም ቢሆን ሁሉም አደጋዎች የተሸፈኑ ከሆነ ወይም ሁሉም ያልተጠቀሱ ወይም የተገለሉ ከሆኑ ሃላፊነት የመቀበሉ ውሳኔ ግልፅ ነው፡፡ የተሸፈኑ ከሆነ መቀበል ያልተሸፈኑ ወይም የተገለሉ ከሆነ አለመቀበል ነው፡፡ ሆኖም ሁኔታው ዋስትና የተሰጠውን፣ ያልተሰጠውን ወይም የተገለለውን አደጋ ያካተተ ሲሆን በያንዳንዱ አደጋ ምክንያት የመጣውን ጉዳት መለየት አስፈላጊ ይሆናል ፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ አደጋ በራሱ ብቻ ላመጣው ጉዳት ቀራቢ ምክንያት ይሆናል፡፡ ሆኖም ምክንያትና ውጤቱን በግልፅ መለያየት ያልተቻለ ሲሆን ጉዳቱን ለማምጣት ወሳኝ የሆነው ምክንያት መለየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

4.3.5.2 የቀራቢ ምክንያት ትርጓሜ

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ቀራቢ ምክንያትን በማስመልከት የተደነገጉት ን/ህ/ቁ 663 እና 665 ስለ ቀራቢ ምክንያት ምንነት የሚሰጡት ትርጉም የለም ፤፤ ይህም ብቻ አይደለም ህጎቹ በራሳቸው ግልፅነት የሚጎድላቸው መሆናቸው ራሱ በአተረጓጎም ላይ ችግር የሚፈጥሩ እንዲሆኑ አድረጓቸዋል፤፤ ሆኖም ግን በዘርፉ ሃብታም ልምድ ካላቸው የእነ እንግሊዝ ተመራማሪዎች professor Ivamy እና Raul Colinvoux መፃህፍት መረዳት እንደሚቻለው ጉዳቱ በአንድ አደጋ ምክንያት ብቻ ከመጣ በሃላፊነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ችግር አይኖርም፡፡ ሆኖም በተጨባጭ ጉዳቱ በአንድ ላይ ወይም ተከታትለው የመጡ ሁለትና ከሁለት በላይ ምክንያቶች ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ ጉዳቱን ያመጣውን በጣም ጠቃሚውን፣ ውጤታማውንና ወሳኙን መለየት አሰፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህ ምክንያት ቀራቢ ምክንያት ሲባል ሌሎች ምክንያቶች ሩቅ ምክንያቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ የቀረበ ምክንያት መርህ ውጤት ከተረጋገጠና ምክንያቱ ከታወቀ ከዚህ ውጭ መሄድ አያስፈልግም በማለት የሚነገረውም በምክንያትና ውጤት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ “ሕጉ በምክንያቶች ምክንያት ላይ አያገባውም”፡፡ **ለምሳሌ** አንድ ሰው መንገድ ሲያቀቅርጥ በመኪና ቢገጭ የአደጋው የቅርብ ምክንያት በመኪናው መገጨቱ እንደሆነ ማወቁ አያስቸግርም፡፡ የአደጋውን ምክንያት ለመፈለግ መኪና መንገዱን ለምን እንዳቋረጠ ለማወቅ ጥረት ማደረግ አያስፈልግም፡፡ ወይም ደግሞ ሰውየው ባለበት ቢቆይ ኖሮ አደጋው አይደርስም ነበር ሊባል አይችልም፡፡ ስለዚህ መፈለግ ያለበት የምክንያቱ ምክንያት ሳይሆን ቀራቢው ምክንያት ነው፡፡ ቀራቢ ምክንያት ለመሆን ምክንያቱ ወዲያው የደረሰ መሆን አለበት፡፡ “ወዲያው” የሚለው አገላለፅ ለጉዳቱ በጊዜ ቅርብ የሆነው ምክንያት ማለት አይደለም፡፡ “የቅርብ” የሚለው ከውጤታማነት አንፃር መታየት ይኖርበታል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ ላይ መኪናው ቀራቢ ምክንያት የሆነው ከጊዜ አንፃር ቀራቢ በመሆኑ ሳይሆን አደጋውን እንዳይቀር ያደረገው ብቸኛ ምክንያት ከውጤት አንፃርም ቀራቢው እርሱ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ከብዙ ምክንያቶች አንዱ ቀራቢ ምክንያት ተደርጎ ከተመረጠ ውጤቱን በማምጣት ውጤታማ የሆነው እርሱ ነው፡፡ ለዚህም የሰው ልጆች የዕለተ ዕለት እንቅስቃሴ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር አንዱ ሁኔታ ሌላ ሁኔታን በመከተል የሚከሰት መሆኑን

ነው፡፡ የኢንሹራንስ መሰረታዊ መርህም ጉዳቱ የደረሰው ኢንሹራንስ ሽፋን በተሰጠው አደጋ (risk) ቀራቢ ምክንያት (Proximate cause) መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ የአንድ አደጋ መድረስ ምክንያቶች ተከታታይነት ያላቸው (successive cause) ወይም በመክንያቶች ሰንሰለት ጣልቃ የገቡ ምክንያቶች (Intervening factors which obscure the chain of causation) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቅርበት ያለው ምክንያት መርህ ግን ውጤቱ በነዚህ ሰንሰለታማ ምክንያቶች የሚነካ ወይም የሚለወጥ አይደለም የሚል ነው፡፡ ለምሳሌ ፤- አንድ ሰው እግሩ ቢላጥና በዚህ ምክንያት የደም መበከል (septicemia) ብይዘውና ቆይቶ በደም መበከል ምክንያት በሚመጣ የሳንባ ምች(Septicemias pneumonia) ከያዘው በኃላ ቢሞት ለዚህ ሰው መሞት ቀራቢ ምክንያት የእግሩ መላጥ (scratch) ነው ለምን ቢባል ለዚህ ሰው መሞት ምክንያት የሆነው የደሙ መመረዝ እንጂ ከደሙ መመረዝ በኃላ የመጣው ጣልቃ ገቢ (intervening cause) የሆነው በደሙ መመረዝ ምክንያት የመጣው የሳንባ ምች አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ አዲስ ጣልቃ ገብ ጉዳቱን ሊያመጣ የሚችል ቀራቢ ምክንያት ባለመኖሩ በተለያየ ጊዝያት የተከሰቱ ግን ደግሞ ታታቾነት ያላቸው ቀራቢ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ውጤቱን ለማምጣት የገባ አዲስ ምክንያት (intervening afresh cause) መኖር ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን እንደዚህ ያለ ሁኔታ ባለመኖሩ ለሰውየው መሞት እንደ ቀራቢ ምክንያት የሚወስደው በእግሩ ላይ የደረሰበት መላጥ (scratch) ነው፡፡

ሌላው ቅራቢ ምክንያትን መለየት አስቸጋሪ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሁለት ምክንያቶች በአንድነት (concurrently) በሚደርስበት ግዜና አንደኛው ምክንያት የኢንሽራንስ ሽፋን የተሰጠው ሆኖ ሌላኛው ግን የኢንሹራንስ ሽፋን ያልተሰጠው በሚሆንበት ጊዜና ግን ደግሞ አንዳቸው ያለሌላኛው ድጋፍ ውጤቱን ማምጣት የማይችሉ በሚሆንበት ጊዜ የሚከሰት የምክንያት መለየት አስቸጋሪነት ነው፡፡ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የሁለቱን አስተዋፅኦ መሰረት በማድረግ ጉዳዩ መስተናገድ ይኖርበታል፤፤ የሌሎች አገሮች ልምድ ታሳቢ የሚያደርገው የሩቁ ምክንያት ሳይሆን የቅርቡን ነው፡፡ ሌላው መንገድ ደግሞ ከጉዳቱ በመጀመር “ለምን ይህ ሆነ” የሚል ጥያቄ ለራስ ለመጠየቅ በሰንሰለቱ ወደ ኃላ መሄድ ነው፡፡ ሰንሰለቱ ባልተቋረጠ ጊዜ ወደ መጀመርያው ድርጊት መድረስ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ተከተታይ ድርጊቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቀራቢውን ምክንያት በመወሰን ክንውኑ ከተቋረጠ ወይም ያልተቋረጠ መሆኑን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ክስተቱ ያልተቋረጠና በሰንሰለቱ ላይ በመጀመርያውና በመጨረሻው ድርጊቶች መካከል ያለው ግንኙነት ያልተቋረጠ እንደሆነ ለጉዳቱ ቀራቢ የሆነው ምክንያት የመጀመርያው ምክንያት ነው፡፡ የክንውኑ ሰንሰለት አንድ ቦታ ላይ ሲቋረጥ በእያንዳንዱ ድርጊት ምክንያት የመጣውን ጉዳት መለየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ድርጊት በራሱ ለመጣው ጉዳት ምክንያት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ምክንያቶች ሲያጋጥሙና እያንዳንዳቸው ለጉዳቱ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በማዕከል ጊዜ የእሳት አደጋ ሊነሳ ይችላል፡፡ ምክንያቱ ግን ማዕበሉ

ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህም የተወሰነ የማዕበል ጉዳትና የተወሰነ የቃጠሎ ጉዳት ሊኖር ይችላል፡፡ በተመሳሳይ በአመፅ ጊዜ የቃጠሎ አደጋ ሊደርስ ይችላል፡፡ ምክንያቱ ግን አመፅ ላይሆን ይችላል፡፡ በመጨረሻ በመጀመሪያ በደረሰው ቃጠሎ የተወሰነ ጉዳት እንዲሁም በአመፀኞቹ በተነሳ እሳት የተወሰነ ጉዳት ሊደርስ ይችላል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ብዙ ጊዜ ላያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በመጀመርያው ምሳሌ ላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች ተደራርበው ሆኖም እያንዳንዳቸው በራሳቸው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በዚህም የትኛው ጉዳት በቃጠሎ የትኛው ደግሞ በማዕበል እንደመጣ ማወቅ አይቻልም፡፡ በዚህ ወቅት የተገለለ አደጋ ባለሞኖሩ ሁሉም ጉዳት ሽፋን እንደተሰጠው ይቆጠራል፡፡ ጉዳቱ ሊለይ ከቻለ የቃጠሎ ምክንያት የመጣው ጉዳት ብቻ ይሸፈናል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ጉዳቱ ሊለይ ካልቻለ የተለየ አደጋ ያለ በመሆኑ ሁሉም አይሸፈኑም፡፡ ጉዳቱ ሊለይ ከቻለ በኢንሹራንስ ውሉ የሚሸፈነው በቃጠሎ ምክንያት የመጣው ጉዳት ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ቀራቢን ምክንያት በሚመለከት የሚከተሉትን ማስተዋል ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

- ኢንሹራንስ የተገባለት አደጋ የመጀመርያው ምክንያት መሆን አያስፈልግም፡፡
- ኢንሹራንስ የተገባበት አደጋ የተገለለው አደጋ ቀጥተኛ ውጤት መሆን የለበትም፡፡ (ፖሊሲው ይህንን በግልፅ ካልሻረ በቀር)
- ጉዳቱን ያደረሰው የቅርብ አደጋ በፖሊሲው ላይ ባይገለፅም ኢንሹራንስ በተገባለት አደጋ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ይሸፈናል፡፡ (ፖሊሲው በግልፅ ውጤቱን ካላገለለ በቀር)፡፡ በዚህም መሰረት ከቃጠሎ በኃላ በውሃ ወይንም በጭስ የሚመጣ ጉዳት ይሸፈናል፡፡
- በፖሊሲው ላይ የተገለፀው አደጋ እስካልደረሰና በኢንሹራንስ ገቢው ላይ ጉዳት እስካስከተለ ድረስ የተጠቀሰው ጉዳት በእርግጥ ጉዳቱን ባያመጣም ንብረቱ ሽፋን ሊያገኝ ይችላል፡፡ **ለምሳሌ** ከኢንሹራንስ ገቢው ቀጥሎ ያለ ሕንፃ በእሳት ቢያያዝና ኢንሹራንስ ገቢው የደረሰበት ጉዳት በውሃና በጭስ ምክንያት ቢሆን የቃጠሎው ፖሊሲ ይሰራል (ቃጠሎው በፖሊሲው በግልፅ በተገለለ አደጋ ምክንያት ያልመጣ እስከሆነ ድረስ)
- እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ በሚደረግ ሙከራ በንብረት ላይ የሚመጣ ተጨማሪ ጉዳት ይሸፈናል፡፡ በመሆኑም በእሳት ማጥፊያዎች በሚመጣ ውሃ የሚመጣ ጉዳት ይሸፈናል፡፡
- በቀራቢ ምክንያት ትርጓሜ ላይ እላይ እንደተገለፀው ጣልቃ የሚገባ አዲስ ድርጊት(ሃይል) ከመርሁ ውጭ ነው፡፡ በመሆኑም በቃጠሎ ጊዜ ተመልካቾች በአካባቢው ንብረት ላይ ጉዳቱ ቢያደርሱ የጉዳት ምክንያት የተመልካቹ ሕገ ወጥ ድርጊት እንጂ እሳቱ አይደለም፡፡ ስለዚህ በኢንሹራንስ ውል ተፈፃሚነት ላይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣችው እስካሁን ያየናቸው መርሆች ብቻ ናቸው ባይባልም የነዚህ መርሆች ዓላማና አስፈላጊነት ግን እጅግ ክፍተኛ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

4.4. ኣርቦን (premium)

በኢንሹራንስ የኢኮኖሚ ዘርፍ የውሉ ህጋዊነት ከሚወሰኑ ጉዳዮች አንዱ የኣርቦን ክፍያ ነው። የኣርቦን ትርጉም "Premium is the consideration which the insurer receives from the assured in exchange for their undertaking to pay the sum assured in the event insured against" የሚል ፍቺ የሚሰጠው ነው። የኣርቦን ባህሪያት በሁለት ማለትም ከሂወት ኢንሹራንስ ውጭ ባሉ የኢንሹራንስ ውሎችና (non life or indemnity insurance) በሂወት ኢንሹራንስ (life insurance) ተብሎ ሊከፈል የሚቻል ሲሆን የኢንሹራንስ ኩባንያው በጉዳት ካሳ ኢንሹራንስ ውል ን/ህ/ቁ 659(1) እና 666 መሰረት በማድረግ ኣርቦን ሳይከፈለው ሲቀር ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን በሂወት ኢንሹራንስ ግን ን/ህ/ቁ 709 ክስ ማቅረብን ስለማይፈቀድ ቢቀርብም ተቀባይነት ያለው ኣይሆንም። ከእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ከሂወት ኢንሹራንስ ውጭ ባሉ ሌሎች የኢንሹራንስ ዓይነቶች ኣርቦን ያለመክፈል እንደ ኣንድ ግዴታ ተወስዶ የሚገደድበት ሁኔታ ያለ ሲሆን በሂወት ኢንሹራንስ ግን ጉዳዩ በን/ህ/ቁ 709 ስለሚስተናገድና በፖሊሲ ደረጃም የሂወት ኢንሹራንስ እንደ ኢንቨስትመንት ስለሚታይ ኣርቦን እንዲከፍል የማይገደድ መሆኑ ነው።

የኣርቦን ክፍያ የሚወሰነው እንዴት ነው? የሚለውን ኣንስተን በምንመለከትበት ጊዜም የኢንሹራንስ ውል ኣስቀድሞ በተዘጋጀ ፖሊሲ የሚፈጸምና ከፊለግክ ተቀበለው ካላስፈለገህ ተወው ፖሊሲን (take it or leave it policy) የሚከተል ነው ሲባል የኢንሹራንስ ኩባንያው እንደፈለገ የኣርቦኑን መጠን ይወስናል ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል። በመሆኑም የኣርቦን ክፍያ በንግድ ዘርፉ ተቀባይነት ያላቸውን ኣሰራሮች እንደ፡-

1. የኢንሹራንስ ውሉ ከመመስረት በፊት ያሉ ሁኔታዎች ወይም የኣደጋው ዓይነት (Characteristics of the peril)
2. ኣደጋው ስርጭት (risk distribution)
3. የኣደጋው ዓይነት ኣንድ መሆን (homogeneous character of the peril) ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚወሰን ነው።

የኣርቦን ኣለመክፈል ህጋዊ ውጤቶች በንብረትና የሂወት ኢንሹራንስ በንግድ ህጉና በፖሊሲዎች መካከል ያለውን ልዩነትና በፍ/ቤት የሚወሰዱ ኣቋሞችን ስንመለከት ከሂወት ኢንሹራንስ ውጭ ባሉ የኢንሹራንስ ዓይነቶች ኣንድ የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠው ሰው ኣርቦን በወቅቱ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ስለሚኖረው ኣካሄድ በን/ህ/ቁ 666 ላይ

ተደንግጓል፡፡ ን/ህ/ቁ 666(2) ኣርቦን በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት ውሉ ለማፍረስ እንደማይቻልና የኩባንያው መብት እንዲከፈለው መጠየቅ (demand for payment) እንደሆነ ን/ህ/ቁ 666(3) ኣርቦኑ እንደከፈለው ጠይቆ በአንድ ወር ውስጥ ክፍያው ሳይፈፅም ሲቀር ከአንድ ወር በኃላ ለሚኖረው ግዜ ውሉ እንዲታገድ (suspend) ይደረጋል፡፡ ን/ህ/ቁ 666(4) ኣርቦን እንዲከፈለው ከጠየቀ በኃላ አንድ ወር ካለፈና ሳይከፈለው ከቀረ የኢንሹራንስ ሽፈኑ ግንዘቡ እንዲከፈለው ወይም ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ ይችላል፡፡ ን/ህ/ቁ 666(5) በዚህ ሁኔታ ኣርቦን ባለመከፈሉ ታግዶና ክፍያው እንዲከፈል ወይም እንዲቋረጥ ጥያቄ ሲቀርብበት የቆየ የኢንሹራንስ ኣርቦን ከተከፈለበት ግዜ ኣንስቶ ባለ ጊዜ ውሉ የሚፀና ይሆናል፡፡ የህጉ ሐሳብ እስካሁን እያየን እንደመጣነው ቢሆንም ከኣርቦን ኣለመክፈል ውጤት ጋር በተያያዘ በኣገራችን በስራ ላይ የዋሉት የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች የውል ቃል ህጉ የሚሰጣቸውን ኣማራጭ በሚጥስ መንገድ ኣርቦን በማይከፈልበት ግዜ ውሉ ወዲያውኑ እንደሚቋረጥ (automatic termination) የሚገልፁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያመድ|ን ድርጅት የተዘጋጀው የIllness, disease and bodily Injury policy “If any premium is not paid when due the insurance under the policy automatically terminate” በማለት ሲገልፅ በሌሎች የኢንሹራንስ ዘርፎች የኢትዮጵያ መድን ድርጅት፣ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ (ኣ.ማ)፣ ኣፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ (ኣ.ማ) ባወጧቸው ፖሊሲዎች “….the company may at any time cancel the policy up on one month notice …” ሲሉ በኢትዮጲያ መድን ድርጅት ለግል ተሸከርካሪ ባወጣው ፖሊሲ ማስጠንቀቅያ የሚሰጥበትን የአንድ ወር ጊዜ ወደ 15 ቀን ዝቅ በማድረግ ያትታል፡፡ እነዚህ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ህጉ ሲረቀቅ ከነበረው

> *As for the payment of the premium in order to spare the insured from the sudden unforeseen rupture of the contract. I have included a provision as has been done in the French law requiring a mandatory waiting period followed by a period of one month during which the insurance is only suspended. The provision is a matter of public policy and can not be varied by the parties.*

ከሚል የኣርቃቂው ሐሳብ ያፈነገጡ ናቸው፡፡

በን/ህ/ቁ 666 ኣተረጓጎም ዙርያ ፍ/ቤቶች እየያዙት ያለ ኣቋም በምንመለከትበት ግዜም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ኣቶ ጥጋቡ ኣንበርብር ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር በሚከራከሩበት ፍ/ይግ/መ/ቁ 47/87 ኣርቦን የመክፈያ ጊዜው ካለፈ በኃላ አደጋው ለደረሰባቸው ኣቶ ጥጋቡ ኣንበርብር የጉዳት ካሳ ይገባቸዋል ሲል የወሰነ ሲሆን ለዚህ በምክንያትነት የሚሰጠው ኣርቦን ባይከፈልም ን/ህ/ቁ 666(2) የቸሮታ ግዜ ስለሚሰጥ የኣቶ ጥጋቡ ካሳ መብት ኣርቦን ባለመከፈሉ ምክንያት ውድቅ ሊሆን ኣይችልም የሚል ነው፡፡ የፌደራል ጠቅልይ ፍ/ቤት ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ኣቶ እሸቱ አስፋው ከኢትዮጵያ ብሄራዊ

ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) ጋር ብፍ/ይግ/ሙ/ቁ 4452/2000 የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 35/89 የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የአርቦን መክፈያ ጊዜው ኣልፎ ላልከፈሉት ግን ደግሞ የመክፈያ ጊዜው ካለፈ በኃላ ለደረሰ ጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን ጭብጥ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ለዚህ በምክንያትነት የሰጠውም

1. ኣንድ ከውል የመነጨ መብት ኣለኝ የሚል ወገን በኢንሹራንስ ውሉ ለማስገደድ የሚያስችል ውል መኖር ኣለበት፡፡
2. በውል በታወቀ ግዜ የሚከፈል ኣርቦን መኖሩ መረጋገጥ ኣለበት፡፡
3. ኣርቦን ለመክፈል የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር ነው በኣቶ እሸቱ ኣስፋው ጉዳይ ላይ ግን እነዚህ ሁሉ የሉም የሚል ነው፡፡

ከያዝነው ርእሰ ጉዳይ ኣኳያ እነዚህ በህጉና ፖሊሲዎች፣ በፍ/ቤቶች ያሉት የተለያዩ ኣቋሞች የመያዝ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ስንመለከተው በህጉና ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች መካከል ያለው ልዩነት መፈታት ያለበት የህጉን ሃይለ ቃል ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤት ኣካባቢ በን/ህ/ቁ 666 ያለውን ኣረዳድ ማቀራረብ የሚቻለው የኢንሹራንስ ንግድ ዓላማ ትርፍን ማሳደግ (Profit maximization) እስከሆነ ድረስ የኣርቃቂው ሃሳብ ውል ሳይኖር ኩባንያውን ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ እንዲሆን ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው በሚል ሳይሆን መግንዘብ ያለብን ውሉ ወድያውኑ ቢቋረጥ የኢንሹራንስ ተቀባዩ ቀደም ሲል በነበረው የውል ቃልና ኣርቦን የኢንሹራንስ ሽፋን ላያገኝ ስለሚችል እንደዚህ ያለውን መብት ለማስገኘት እንጂ ኩባንያው ከተቋቋመበት ዓላማ ውጪ ባለ እዳ በማድረግ ዘርፉን ለማቀጨጭ እንዳልሆነና የችሮታ ግዜ ስላለ ኣርቦን ባይከፈልም ጉዳት ካሳ እንዲከፈል መጠየቅ ከህግ የመነጨ መብት ነው በሚል መሆን የለበትም፡፡ ከችሮታ ግዜ ኣንፃር እንየው ቢባልም ፍ/ብ/ህ/ቁ 1770(2)፣ 1774(2) 6 ወር የችሮታ ጊዜ የሚሰጠው ግዜ እንዲሆን የተወሰነው በህግ ሲሆን የኣርቡን ይከፈለኝ ጥያቄ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ለኣንድ ወር የተሰጠው የህግ ጥበቃ ግን ጉዳት ካሳ ከመከፈል ውጭ ያሉ ኣንዳንድ ጥቅምችን ያስገኝ እንደሆነ እንጂ ኣንዱን በማክሰር ሌላውን የማበልፀግ ዓላማ ያለው ህግ ነው ብሎ መረዳት ካለው እውነታ ውጭ ማሰብ ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም የኢንሹራንስ ውል ሰጪ ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ሃላፊነት ብቻ መሆን እንዳለበትና ይህም ተፈፃሚነት ማግኘት ያለበት የኣርቦን ኣከፋፈል ስርዓቱ በኣንድ ጊዜ (lump sum payment) ወይም በየጊዜው በሚደረግ የኣርቦን ክፍያ(Installment) ላይም ጭምር ነው፡፡

በሂወት ኢንሹራንስ ኣርቦን በወቅቱ ያለመክፈል ህጋዊ ውጤቶች በምንመለከትበት ጊዜ ከፍ ብለን ካየናቸው ውጤቶች ለየት ባለ መልኩ በን/ህ/ቁ 709 (3) ላይ፤- ሶስት ዓመታዊ ክፍያዎች ከተከፈለ በኃላ የኣርቡን ክፍያ ሳይከፍል ቢቀር የኢንሹራንስ ውል ሰጪው ኣርቦን እንዲከፈለው ከጠየቀበት ጊዜ ጀምሮ በኣንድ ወር ግዜ ውስጥ ሳይከፈለው ቢቀር ውሉ ውድቅ ባይሆንም ያሉት ኣማራጮች

- ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ፖሊሲ መስጠት (paid up policy) ወይም

- በውሉ የተስማማበትን ዋና ገንዘብ ወይም በየጊዜው በሂወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በን/ህ/ቁ 656 በተለከተው መሰረት መቀነስ ብቻ ነው፡፡ (cash or surrender value) ናቸው፡፡

እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ካወጣው የሂወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር ስናነፃፅራቸው የፖሊሲው አንቀፅ 4(a) (b) ከንግድ ህጉን ድንጋጌዎች ጋር በሚስማማ መንገድ የወጣ ቢሆንም አስቀድሞ በተከፈለ አርቦኖች ህጉ ለሶስት ዓመት ሲል ፖሊሲው ለሁለት ዓመት አርቦን ከተከፈለ በማለት የጊዜውን ርዝማኔ በአንድ ዓመት አሳጥሮት ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ልዩነት እምበዛም ለክርክር መንስኤ ሊሆን የሚችል አይደለም ምክንያቱም ኢንሹራንስ ውል ሰጪው ራሱ ያወጣውን ፖሊሲ በመቃወም የሶስት ዓመት አርቦን አልከፈለም ብሎ መከራከር ቅን ልቦና የጎደለው መከራከርያ ስለሚሆንና የዚህ ዓይነት መከራከርያ ያነሳል ተብሎ ስለማይገመት ነው፡፡ ከኢንሹራንስ ውል ተቀባይ አንፃር ልዩነቱን ስንመለከተውም የአርቦን የተከፈለበት ጊዜ ማጠር የሱን ጥቅም የሚያስጠብቅ እስከሆነ ድረስ ጥቅሙን በመፃረር ፍርድ ቤት ይመጣል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ በህጉና በሂወት ፖሊሲው መካከል ልዩነት ቢኖርም እንደመከራከርያ ሊነሳበት የሚችል እድል ዝግ ነው ባይባልም እምብዛ ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርገው ምክንያት ግን አይደለም፡፡

ሶስተኛውና በንግድ ህጉ ሽፋን ያልተሰጠው አማራጭ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሂወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ አንቀፅ 4(c) ላይ የሰፈረው የተራዘመ የኢንሹራንስ ውል (Extended term insurance) ሲሆን አፈፃፀሙም አንድ የሂወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ በመግዛት ለሁለት ዓመት አርቦን ከከፈለ በኃላ መክፈል ያቋረጠ ሰው በከፈለው የገንዘብ መጠን አዲስ የሂወት ፖሊሲ በመስጠት የመክፈያ ጊዜው ሲደርስ በውል የሰፈረውን ገንዘብ ለመክፈል ኩባንያው ውሉን የሚያራዝምበትን አሰራር መሰረት በማድረግ የሚሰጥ አማራጭ ነው፡፡ ፖሊሲው ላይ የሚታየው እጥረት ግን አርቦን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት በአማራጮቹ ሲገለገል የቆየው ሰው በተለይ ደግሞ በተራዘመ ኢንሹራንስ የተገለገለ ሰው አርቦኑን ቢከፍል ስለሚኖረው መብት የሚለው ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 709 ስለዚህ ጉዳይ የሚለው ነገር ባለመኖሩና ን/ህ/ቁ 666(6) በሂወት ኢንሹራንስ ላይ ን/ህ/ቁ 666(5)ን እንዳንገለገል ስለሚከለክል በዚህ ዙርያ የሚነሳ ክርክር እልባት ማግኘት ያለበት በሂወት ኢንሹራንስ ፖሊሲው መሰረትና ሁለቱም በሚያደርጉት ውል ነው፤፤

ስለዚህ ጠቅላላ ባለመልኩ ሲታይ የኢንሹራንስ አርቦን አለ መክፈል በሁሉም የኢንሹራንስ ዓይነቶች ውሉ ወዲያው እንዲቋረጥ እንደማይደረግና የሚኖሩት አማራጮች ወይም አሰራሮች እንዳየ የኢንሹራንስ ውሉ የተለያየ ቢሆንም በህግና ፖሊሲ ልዩነት በሚፈጠርበት ግዜ ህጉን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን ማስተናገድ ያለብን ስለመሆኑ ግንዛቤ ልንይዝበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነገር የሕይወት ኢንሹራንስ

ውል ዓይነቶች ሶስት ሲሆኑ አንደኛው በን/ህ/ቁ 692(1) መሰረት ኢንሹራንስ ገቢው በኢንሹራንስ ውል ውስጥ በተወሰነ ጊዜ በሕይወት ያለ እንደሆነ የተወሰነ ዋና ገንዘብ በሕይወት እስካለ ድረስ ወይም በየጊዜው የሚከፈል ገንዘብ ሊያገኝ የሚችልበት ሲሆን ሁለተኛው በን/ህ/ቁ 692(2) መሰረት ኢንሹራንስ ገቢው በሞተ ጊዜ ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ላላቸው ወይም በኢንሹራንሱ ውል ውስጥ ለተጠቀሰው ተጠቃሚ የተወሰነ ዋና ገንዘብ ወይም በሕይወት እስካለ ድረስ በየጊዜው የሚከፈል ገንዘብ የሚያስገኝ ነው፡፡ ሶስተኛው በን/ህ/ቁ 692 (3) መሰረት ሁለቱ በአንድነት ተጣምረው የሚገኙበት ኢንሹራንስ ዓይነቶች ናቸው፤፤

በዚህ የኢንሹራንስ ዓይነቶች ዙርያ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የተለያየ ትርጉምን እያስከተለ ያለውን ለሞት በሆነ ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚውን አስመልክቶ የሚታዩ ልዩነቶችን መሰረት በማደረግ ስንመለከት ን/ህ/ቁ 701(1) ለሞት የሚዳርግ ኢንሹራንስ ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ጥቅም ሊደረግ ይችላል በማለት ኢንሹራንስ ገቢው ከኢንሹራንሱ ስምምነት ተጠቃሚው ማን መሆን እንዳለበት መወሰን እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ይህን ከን/ህ/ቁ 709(2) ጋር በማዛመድ ያየነው እንደሆነ አወዛጋቢ ጥያቄዎችን ሊያስነሳ ይችላል፡፡ የን/ህ/ቁ 709 (2 ይዘት፤-

ሀ/ ጋብቻው የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ከተፈረመ በኋላም ቢሆን እንኳን የኢንሹራንስ ውል የፈረመው ሰው ባል ወይም ሚስት፣

ለ/ የኢንሹራንስ ውል ሲፈረም የተወለዱት የኢንሹራንሱ ውል ፈራሚ ሰው ልጆች ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ በማለት ስለሚደነግግ ከዚህ ጋር ተያይዘው ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች፡-

1. ተለይቶ በስም የተቀመጠ ሌላ ተጠቃሚ ካለ ይህ ተጠቃሚ ከኢንሹራንስ ፈራሚው ሚስት ወይም ባል እና ልጆች ጋር ጥቅምን መካፈል ይችላልን?
2. ባል ወይም ሚስት እና ልጆች ተጠቃሚ የሚሆኑት የተለየ ተጠቃሚ ያልታወቀ እንደሆነ ነው ማለት ነውን?
3. ባል ወይም ሚስት እና ልጆች በውሉ ውስጥ ጠቅለል ባሉ ቃላት የተገለፁ ከሆነ ስማቸው ባይጠቀስም ተለይተው እንደታወቁ ተጠቃሚዎች ይቆጠራሉ ለማለት ነውን? የሚሉት ናቸው፡፡

የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ ሆኖ የሚከፈለው ብዙውን ጊዜ ከጋራ ሃብት ላይ ሰለሆነ የጋራ ሃብት እኩል ተካፋይ የሆነው ባል ወይም ሚስት ከጥቅሙ ማግለል ወይም ብዙውን ጊዜ በወላጆቻቸው የገንዘብ ምንጭ ላይ ጥገኛ የሆኑትን ልጆች ከጥቅሙ ማግለል አግባብ አይደለም በማለት ባል ወይም ሚስት እና ልጆች በኢንሹራንስ ውሉ ውስጥ ተለይተው ባይጠቀሱም ስሙ ተለይቶ ከተጠቀሰው ሌላ ሰው ጋር ጥቅሙን መካፈል አለባቸው ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ትርጉም የኢንሹራንስ ገቢውን ተጠቃሚን የመወሰን ስልጣን ይገድባል፡፡ ሀጉን ያረቀቁት professor Jauffret በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም ልቅ በሆነ

መንገድ"I have included the most liberal solution for the determination of the beneficiaries of the insured in the case of death" በማለት ኢንሹራንስ ገቢው ተጠቃሚውን ሲወሰን ነፃነቱ በጣም ከፍተኛ እንዲሆን እንደዳረጉ ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም በተጠቃሚነት ጭራሽ ያልተገለፁትን ባል ወይም ሚስት እና ልጆች ተለይቶ ከታወቀው ተጠቃሚ ጋር ጥቅሙን እንዲካፈል በማድረግ የኢንሹራንስ ፈራሚውን ተጠቃሚን የመወሰን ነፃነትን መገደብ አግባብ አይደለም ሊባል ይችላል፡፡ ባል ወይም ሚስት እና ልጆች ተጠቃሚ የሚሆኑት ሌላ የተለየ ተጠቃሚ ያልተጠቀሰ ወይም ያልታወቀ እንደሆነ ነው የሚለው ሓሳብ ደግሞ ከኢንሹራንሱ ውል የሚገኘው ጥቅም ምን እንደሚሆን የን.ሕ.ቁ 705 እና የፍ/ሕ/ቁ. 827/1 በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገኘው ጥቅም በውርሱ አካል ይሆናል፡፡ ስለሆነም በዚህ መልኩ መተርጎም ቁጥር 701/2 ከእነዚህ ድንጋጌዎች ጋር እንዲጋጭ ወይም ጥቅም እንዳይኖረው ማድረግ ነው የሚሆነው፡፡ ሶስተኛውን ሓሳብ በምናይበት ጊዜ ደግሞ ባል ወይም ሚስት እና ልጆች በውሉ ውስጥ ጠቅለል ባሉ ቃላት (General terms) የተገለፁ ከሆነ ስማቸው ባይጠቀስም ተለይተው እንደታወቁ ተጠቃሚዎች ይቆጠራሉ የሚለው አንደኛ ነገር የኢንሹራንስ ፈራሚውን ተጠቃሚን የመወሰን ነፃነት የሚገድብ አይደለም፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ሊገለሉ ይችሉ የነበሩ እንዳይገለሉ በማድረግ ሁሉን አቀፍ እንዲሆን የሚያደርገው ነው፡፡ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ባል ወይም ሚስት እና ልጆች ስማቸው የግዴታ ካልተጠቀሰ ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ አይችሉም የሚባል ከሆነ ውሉ ሲፈረም ያልነበሩ ባል ወይም ሚስት እና ልጆች ከጥቅሙ እንዲገለሉ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን በውሉ ላይ የተጠቀሰው እንደ "ባለቤቴ" ወይም "ልጆቼ" የሚል ጠቅለል ያሉ ቃላት ከሆነ ውሉ ሲፈረም የሌሉትንም ነገር ግን ይህን መስፈርት ማለትም ባልነትን፣ ሚስትነትን ወይም ልጅነትን የሚያሚሉትን ሁሉ የሚያቅፍ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ሶስተኛው ጥያቄ በአውንታ የሚቀበልን ትርጉም መከተሉ አግባብነት ያለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ የን/ህ/ቁ 701(1)እና (2)ን የቃላት አጠቃቀምንም ብናይ ይህንኑ የሚያጠነክር ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 701()1 "... ለአንድ የተለለየ ተጠቃሚ..." ሲል አንድ ሰው የተለየ ተጠቃሚ መሆኑ የሚታወቀው ስሙ በግልፅ የተቀመጠ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ለምሳሌ "ልጆቼ" የሚለው ቃል ሲታይ የትኛው ልጅ እንደሆነ ለይቶ የሚገልፅ አይደለም፡፡ ስለዚህም ን/ህ/ቁ 702(2) "ስማቸው ውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም ... ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ" ብሎ መደምደሙ "ልጆቼ" በሚለው አገላለፅ ወቅት ተለይቶ የታወቀ ሰው የለም ተብሎ ክርክር እንዳይነሳ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ኢንሹራንስ ፈራሚው ሲሞት ተጠቃሚ የሚሆነውን ሰው የመወሰን ሙሉ ነፃነት አለው፤ ሚስት ባል ወይም ልጆች ተጠቃሚነታቸው በውሉ ውስጥ መጠቀስ አለበት፤ ነገር ን ስማቸው ተለይቶ ባይገለፅም ወይም የተጠቀሱት ''ሚስቴ'' ''ባሌ'' ወይም ''ልጆቼ'' በሚሉ ቃላት ቢሆንም ተለይተው እንደታወቁ ይቆጠራል የሚለው ሚዛን የሚደፋ ሓሳብ ነው፡፡ ሌሎች በን/ህ/ቁ 701(2) ላይ ሊነሱ የሚችሉት ጥያቄዎች ውሉ ሲፈረም እና ውል ፈራሚው

ሲሞት የነበሩት ባል ወይም ሚስት የተለያዩ ሲሆኑ ከሁለቱ ተጠቃሚ የትኛው ነው? የኢንሹራንስ ውል ከተፈረመ በኋላ የተወለዱ የፈራሚው ልጆች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጥያቄ ስናይ በግልጽ ለይቶ ባያስቀምጥም "... የኢንሹራንሱ ውል ከተፈረመ በኋላም ..." የሚለውን ሐረግ በመመልከት ተጠቃሚው ኢንሹራንስ ፈራሚው ሲሞት የነበረ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ውል ፈራሚው የነበረው ባል ወይም ሚስት እንዲሆን ፈልጎ ቢሆን ኖሮ ውሉ ላይ ስሙን በግልጽ ለይቶ ማስቀመጥ ይችል ነበር፡፡ ሁለተኛውን ጥያቄ ሰናይ የአማርኛ ቅጂ "የኢንሹራንሱ ውል ሲፈረም የተወለዱት የኢንሹራንሱ ውል ፈራሚ ልጆች ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ" ስለሚል ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተወለዱትን ልጆች የማያካትት ይመስላል፡፡ ነገር ግን ይህ አግባብነት ያለው አይመስልም፡፡ የእንግሊዝኛው ቅጂ "The subscriber's children, whether or not born at the time when the policy is entered into" የሚል በመሆኑ ሲፈርምም ሆነ ከዛ በኋላ የተወለዱትን ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም የእንግሊዝኛውን ቅጂ በመከተል ሁሉንም እንዲጨምር አድርገዉ መውሰዱ ከድንጋጌው ዓላማ ጋር የሚሄድ ነው፡፡ ስለዚህ የአርቦን ክፍያንና የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎችን በመለየት ዙርያ ሊነሱ የሚችሉት አከራካሪ ጉዳዮች እነዚህ ብቻ ናቸው ባይባልም ፈጠው በመውጣት የአተረጓጎም ችግር ለፈጥሩ በመችሉት ርእሰ ጉዳዮች ዙረያ ፍንጭ ሊሰጥ በሚችል መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል

4.5. መሸሸግና የሐሰት መግለጫ

የኢንሹራንስ ውል በከፍተኛ ቅን ልቦና (*uberrima fedes*) ላይ መመስረት ያለበት ለመሆኑ ዓለም የተሰማማበት ጉዳይ ከሆነ ዘመናትን ያስቆጠረ እውነታ ነው፡፡ ለዚህም ነው professor Ivamy በዓፉት መፅሐፍ ላይ፡-

''The reason which underlies utmost good faith is that parties to the contract of insurance are duty bound to assist one another to come into the right conclusion instead of holding "at arms length in defense of their conflicting interest" በማለት የከፍተኛ ቅንልቦናን አስፈላጊነት የሚገልፁት፡፡ በአገራችን የንግድ ህግ መሸሸግንና የሐሰት መግለጫ በማስመልከት የተደነገጉት በን/ህ/ቁ 667 እና 668 ላይ ሲሆን የነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት ከኢንሹራንስ ኣሰራር ዓለም ኣቀፋዊ እድገት ኣንፃር ሲታይ የተሰጠው ሽፋን በእጅጉ ጠበብ መሆኑ ለመገንዘብ አያዳግትም ፡፡ የኢንሹራንስ ውል በከፍተኛ ቅን ልቦና የመመሰረት ዓላማ ከኢንሹራንስ ሽፋን ሰጪው ኣንፃር ስንመለከተው ማስከፈል ያለበትን ኣርቦን (premium) ለማስከፈል ወይም ማስከፈል ያለበትን ባለማስከፈሉ ለመክሰር የሚወስነው ከኢንሹራንስ ሽፋን ተቀባይ በሚሰጠው ፍሬ-ነገር (material fact) በመሆኑ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ከኢንሹራንስ ተቀባይ ኣንፃር ስንመለከተውም ውሉ ከተፈፀመ በኋላ

የተሸሸገ ወይም በሐሰት የቀረበ ፍሬ-ነገር መኖሩ ከታወቀ እንደ የሁኔታው እየታየ በመብቱ ላይ የሚወሰዱ ህጋዊ እርምጃዎች በመኖራቸው ከነዚህ ህጋዊ የፍታብሄር ሃላፊነቶች ለመዳን ገና ከጅምሩ የሚያውቀውን ፍሬ-ነገር በከፍተኛ ቅን ልቦና *(utmost good faith)* መሰጠት ወይም መግለፅ ይኖርበታል ፡፡

መሸሸግና የሐሰት መግለጫ መሰረት በማድረግ በርካታ ጥያቄዎችን በማንሳት ዳሰሳ ማድረግ የሚቻል ቢሆንም ለዚህ ፅሁፍ ዓላማና ወሰን ሲባል ጥቂቶቹን ወስደን የተመለከትን እንደሆነ አንድ የኢንሹራንስ ውል ተዋዋት ወገን እውነታውን በግልፅ የማቅረብ ግዴታ (duty to disclose the fact material) ያለበት ቢሆንም ይህ ፍሬ-ነገሩን ግልፅ የማቅረብ ወሰን የት ነው? በልምድ የሚያውቀውን ወይም ማወቅ ያለበትን ጠቃሚ ፍሬ-ነገር (fact material) መግለፅ ያለበት መሆኑን እንደ አካሄድ የሚከተል ሲሆን የአገራችን ንግድ ህግ በቁጥር 667 በተለይ የእንግሊዝኛው ቅጂ "…. Within his knowledge and which are likely to assist the insurer to appreciate fully the risk…" በማለት ስለሚደነግግ ህጋችን ስለሚያውቀው ፍሬ-ነገር (actual knowledge) መግለፅ የሚደነግግ በመሆኑ ማወቅ ያለበትን ፍሬ-ነገር (presumed to have known) ባለ መግለፁ ሸሽጓል ተብሎ በን/ህ/ቁ 668 ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ ይህ በግልፅ የተደነገገ ባለ መሆኑ በዚህ ዙርያ የሚነሱትን ክርክሮች ማስተናገድ አስቸጋሪ በመሆኑ ተፈፃሚነት ማግኘት ያለበት በን/ህ/ቁ 667 ላይ በግለፅ የሰፈረው የህጉ ሃሳብ ነው፡፡ ሌላው ጉዳይ ተዋዋይ ወገን ጠቃሚ ፍሬ-ነገር (material fact) መግለፅ የሚገባው መቼ ነው? በቅን ልቦና የሚያውቀውን ፍሬ-ነገር እንዲገልፅ የሚጠበቀው በድርድር ግዜ እንጂ ውሉ ከተመሰረተ በኃላ ያወቃቸውን አዳዲስ ጠቃሚ ፍሬ-ነገሮችን እንዲገልፅ አይገደድም፡፡ ይህ ማለት ግን በተራዘመ የኢንሹራንስ ውል ማለትም የኢንሹራንስ ውሉ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው የመጀመርያው አርቦን ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ ነው የሚል የውል ቃል ባለበት የኢንሹራንስ ውል ጠቃሚ ፍሬ ነገር የመግለፅ ግዴታው አርቦን እስከተከፈለበት ቀን ግዴታው ክፍት ሆኖ የሚቆይ በመሆኑ የሸሸገው ወይም በሐሰት መግለጫ የሰጠው ወገን ከሃላፊነት አያመልጥም፡፡ በኢንሹራንስ ውል ጠቃሚ የሚባሉ ፍሬ-ነገሮች ጠቃሚ ካልሆነው ፍሬ-ነገር በምን ይለያል? ብሎ ማየቱ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ጥቅም ያለው በመሆኑ በአገራችን ህግ በግልፅ መልስ ያልተሰጠውን ጉዳይ ፕሮፌደር Invmy, "The general principles of insurance" በሚል መፅሐፋቸው ያሰፈሩትን እንዳለ ወስደን ማየቱ በራሱ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በመሆኑ በሚቀጥለው መልኩ ቀርቧል

1. *All facts suggesting that the subject matter of insurance is exposed to more than ordinary danger for the peril insured against.*
2. *All facts suggesting the proposed assured is actuated by same special motive.*

3. *All facts showing that the liability of the insurer might be greater than would normally be expected.*
4. *All facts relating to the moral hazard.*
5. *All which to the knowledge of the proposed assured are regarded by insurers as material.*

ስለዚህ በአንድ የኢንሹራንስ ውል የመሸሸግ ወይም የሐሰት መግለጫ የመስጠት ሁኔታ ኣለ በሚባልበት ግዜ መከራከርያ ሆኖ የቀረበው ፍሬ-ነገር ጠቃሚ ነው ወይስ ኣይደለም ብሎ ለመለየት ከፍ ብለው የተገለፁ የጠቃሚ ፍሬ-ነገር መለኪያዎችን (test of materiality) ተጠቅመን መለየትና በእነዚህ ስር የማይወድቅ ከሆነ የተሸሸገ ወይም የተሰጠ የሐሰት መግለጫ የለም ብለን ጉዳዩን ማሰናበት ይኖርብናል። የመሸሸግና የሐሰት መግለጫ መስጠት ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው? በን/ህ/ቁ 668 መሰረት የሚኖሩት ውጤቶች በሶስት የተከፈለ ሲሆኑ

1. ውሉ ሲፈፀም ሆኖ ተብሎ ለተደረገ የመሸሸግ ወይም የሐሰት መግለጫ የሚኖርን ህጋዊ ውጤት የሚመለከት፣
2. ውሉ ከተፈፀመ በኃላ ስለሚደረስበት የመሸሸግና የሐሰት ቃል ስለሚኖረው ስነ-ስርዓት የሚደነግግ፣
3. የተሸሸገው ወይም የተሰጠው የሐሰት መግለጫ ለኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሆነው የውሉ ጉዳይ ወይም ሽፋን የተሰጠው አደጋ ከደረሰ በኃላ በሚታወቅበት ግዜ ስለሚኖረው ህጋዊ ውጤት የሚደነግግ ነው። ንግድ ህጉ ከፍ ብሎ በተገለፀው መንገድ ሶስት የተለያዩ ህጋዊ ውጤቶች እንደሚኖሩ የሚደነግግ ቢሆንም በኣገራችን በስራ ላይ ያሉ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች ታትመው የወጡ ፖሊሲዎች ግን የህጉን ይዘት በሚቃረን መልኩ የተሸሸገ ወይም የተሰጠ የሐሰት መግለጫ በሚኖሩበት ግዜ ውሉ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ወድያውኑ ዋጋ ኣልባ መሆኑን በሚገልፅ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው።

<u>ለምሳሌ</u> በኢትዮጵያ መድን ድርጅት የተዘጋጀው የBurglary and house breaking policy condition N<u>o</u>2 “….If there shall by any misstatement in or omission of material fact for the information supplied by the assured where by the said proposal or declaration or otherwise the policy shall be **null** and **void** any premium paid there on shall be **forfeited** ….” በማለት ያትታል። ይህ የሚያስገነዝበን ነገር ቢኖር በህጉና በኢንሹራንስ ፖሊሲዎች መካከል ልዩነት መኖሩን ሲሆን በዚህን ግዜ የመሸሸግ ወይም በሐሰት የተሰጠ መግለጫ መኖሩ ከተረጋገጠ የመሸሸግ ወይም የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ሆነ ተብሎ ነው ወይስ በቸልተኝነት? የታወቀውስ ውሉ ከተፈፀመ በኃላ ሆኖ ግን ደግሞ የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠው አደጋ ከመድረሱ በፊት ወይስ አደጋው ከደረሰ በኃላ? ብሎ

በመለየት ን/ህ/ቁ 668 በሚደነግገው መሰረት መስተናገድ ያለበት መሆኑን ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

4.6 አደጋ ከኢንሹራንስ አንፃር

4.6.1 ስለ አደጋ በጠቅላላ (Risk in general)

ስለ አደጋ እየከበደ መሄድና ስለሚኖረው ሕጋዊ ውጤት የሚደነግገው ን/ህ/ቁ 669 አደጋ ምን እንደሆነ የሚሰጠው ትርጉም የሌለ ቢሆንም በዚህ ርእሰ ጉዳይ የምርምር ስራ ያካሄዱት ፀሃፍት የሰጡትን ትርጉም ወስደን ስንመለከት “Risk is a prediction concerning potential loss partly reasoned from things known and party predicted on guess work, is generally understood as the risk that is the basis of computation of premium that an insured pays to the insurer to acquire insurance.(Keeton and Widiss. P.8) የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አደጋ የሚባል ነገር እርግጠኛ ካለመሆን (uncertainty) ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሆኖ የሰው ልጅ የወደፊት ዕጣ ፈንታውን ለማወቅ እርግጠኛ ባለመሆኑ ምክንያት ራሱን ለመከላከል ሲል አደጋውን ማስቀረት ባይችልም ከአደጋ በኋላ ለሚኖረው ሁኔታ በኢንሹራንስ ወደ በጎ ገፅታው ለመመለስ ሲል የኢንሹራንስ ፖሊሲ የሚገዛ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ኢንሹራንስ አስፈላጊ የሚሆነው ተገማች ያልሆነ አደጋ (Unpredictable risk) በመኖሩ ነው፡፡ የአደጋ ዓይነቶችን (classification of risks) ስንመለከት ፡-

1. በገንዘብ ሊተመን የሚችልና በገንዘብ ሊተመን የማይችል (financial and non-financial risk) ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ በገንዘብ ሊተመን የሚችል አደጋ የሚባለው የገንዘብ ዋጋ (pecuniary value) ባለው ንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ ሲሆን በገንዘብ የማይተመን አደጋ የሚባለው ረቂቅነት ባህሪ (subjective nature) ወይም ስሜታዊ ዋጋ (sentimental value) ያላቸው ሆነው ግን ደግሞ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ዋጋ ያላቸው ለምሳሌ እንደ ህብር መምረጥ (Choice of color) የመዝናኛ ቦታ መምረጥ (selection of recreation area) ሙዚቃን ማድነቅ (appreciation of music) ወዘተ. ያሉትን ያጠቃልላል፡፡
2. ውጤቱ የማይታወቅና ውጤቱ ኣትራፊ ወይም ኣክሳሪ የሆነ ኣደጋ (pure or speculative risk) ውጤቱ በእርግጠኝነት የማይታወቅ ሊሆንም ወይም ላይሆንም ይችላል የሚባል አደጋ (pure risk) የሚከሰተው አንድ በኣውራ መንገድ ላይ ኳስ የሚጫወት ልጅ ኳሷን ተከትሎ መንገዱን ሲያቋርጥ በሚያልፍ መኪና ጉዳት ሊደርስበት ወይም ከአደጋው ሊያመልጥ ይችላል፡፡ አንድ በተበላሸ ማሽን የሚሰራ ሰው በብልሽቱ ምክንያት የኣካል ጉዳት ሊደርስበት ወይም ላይደርስበት ይችላል ሊያሰኝ የሚያስችል ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ሲሆን የመክሰር ወይም ማትረፍ ውጤት ያለው አደጋ የሚባለው ደግሞ አንድ የፋብሪካ ስራ ኣስኪያጅ ገቢውን ከፍ ለማድረግ

በማሰብ የመሸጫ ዋጋ ቢጨመር በተግባር ሊኖር የሚችለው ውጤት እንደታሰበው በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ገቢው ከፍ እንዲል ያደረገዋል ካልሆነም ዋጋው የማይቀመስና ኣዋጪ ባለመሆኑ ምርቱን የሚገዛው ሰው ይጠፋና የማምረቻ ዋጋውን እንኳ መመለስ የማይችልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል ስለዚህም ነው ይሳካል ወይም ኣይሳካም የሚባል ኣደጋ (Speculative Risk) ሊኖር የሚችለው፡፡

3. መሰረታዊና ልዩ ኣደጋ (Fundamental and particular risk) ለዚህ ዓይነት የኣደጋ ክፍፍል መሰረት የሚሆነው ምንጩና (origin) ያለው የኣደጋው ውጤት (consequence of loss) ሲሆን መሰረታዊ ኣደጋ የሚባለው ኣንድ ሰው ወይም ቡድን ሊቆጣጠረው የማይችል ዓይነት ኣደጋ ሆኖ የሚያስከትለው ኣደጋም የኣንድን ቡድን፣ ማህበረሰብ የሂወት ወይም የኢኮኖሚ ውድቀትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለዚህ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት እንደ ማእበል (Storm)፣ የመሬት መንቀጥቀጥ (earth quake) ፣ ጎርፍ (flood)፣ ርሃብ (famine)፣ የትጥቅ ኣመፅ (insurrection) የገንዘብ ግሽበት (inflation)፣ የስራ ማቆም ኣድማ (strike)፣ ጦርነት (war) ወዘተ ናቸው፡፡ ልዩ ኣደጋ (particular risks) የሚባል ኣደጋ በዋናነት በሚፈፀመውም ሆነ ውጤቱ በቀጥታ ጫና የሚያሳድረው በግለሰብ ወይም ቡድን ሆኖ ከግለሰብ ወይም ቡድን ቁጥጥር ውጭ ያልሆነ የኣደጋ ዓይነት ነው፡፡ ለዚህም በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት እንደእሳት ኣደጋ(fire break)፣ ስርቆት (theft)፣ የኣካል ጉዳት (disablement)፣ የመኪና ኣደጋ (car accident) ወ.ዘ.ተ ዓይነት ኣደጋዎች ናቸው፡፡

4.6.2 መግለጫ የመስጠትና የማስታወቅ ግዴታ

ፍፁም የሆነ የቅን ልቦና ተግባር የሚያሳየው ኢንሹራንስ ጠያቂው ዋስትና በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ያሉ መረጃዎች በሙሉ የመግለፅ ግዴታ ያለበት ለመሆኑ የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ ተግባር ተፈፃሚ የሚሆነው ኢንሹራንስ ጠያቂው በሚያውቃቸው ፍሬ-ነገሮች ላይ ብቻ ሳይሆን ሊያውቅ በሚገባው ነገር ላይ ጭምር ነው የሚል ክርክር ሲነሳ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ግን የን/ህ/ቁ 667 “ውሉን በሚዋዋልበት ጊዜ ተጠቃሚው የሚያውቃቸውን ማናቸውን ሁኔታዎች ኢንሹራንስ ሰጪው ሃላፊነት የሚወሰድባቸውን ኣደጋዎች ለማመዛዘን የሚያስችሉትን ማናቸውም ሁኔታዎች በትክክል መግለፅ ኣለበት” ከሚል ውጪ ማወቅ ስላለበት ጉዳይ በግልፅ የሚለው ነገር የለም፡፡ መግለጫ መስጠት ግዴታ የማይሆንባቸው ዋና ፍሬ ነገሮች ኢንሹራንስ ሰጪው በቀጥታ ጥያቄ ያላቀረባቸውን ዋና ፍሬ ነገሮች ኢንሹራንስ ጠያቂው የመግለፅ ግዴታ የለበትም፡፡ ኢንሹራንስ ጠያቂው እንዲያስታውቅ የማይገደድባቸው ፍሬ ነገሮችም፡-

- ኣደጋውን የሚቀንሱ ሁኔታዎችን ለምሳሌ በእሳት ኣደጋ ኢንሹራንስ ጊዜ የእሳት ኣደጋ ማጥፍያ መሳርያ መትከሉን፡፡
- በኢንሹራንስ ሰጪው የሚታወቁና ሊታወቁ የሚገባቸው ነገሮች፡፡ ኢንሹራንስ ሰጪው በተለምዶ የሚታወቁ ነገሮችን እንደሚያውቅ ይገመታል፡፡

- በኢንሹራንስ ጠያቂው ከተሰጡ መግለጫዎች ሊረጋገጡ የሚገባቸው ወይም መረጋገጥ ያለባቸው መረጃዎች ከፕላስቲክ ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙ የእሳት አደጋዎች፡፡
- የህግ ጉዳዮች፡፡
- ኢንሹራንስ ሰጪው በሃሳብ ተለይቷል ተብሎ የማይታይባቸው መረጃዎች ወይም የተዋቸው መረጃዎች፡፡ **ለምሳሌ** በኢንሹራንስ መጠየቅያው ተጠይቀው ተገቢ መልስ ያልተሰጠባቸውና ኢንሹራንስ ሰጪው የተዋቸው ፍሬ ነገሮች፡፡
- በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ነገሮች፡፡ **ለምሳሌ** የኢንሹራንስ ሰርቬየሩ ቅጥር ግቢ ሲመረምር የሚያገኛቸው ነገሮች ኢንሹራንስ ጠያቂው እንዲያስታውቅ ወይም መግለጫ እንዲሰጥ የማይገደድባቸው ፍሬ-ነገሮች ናቸው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የኢንሹራንስ ስምምነት ባህሪያት መካከል አንዱ ከፍተኛ የሆነ ቅን ልቦናን *(utmost good faith)* ከተዋዋዮች የሚጠበቅ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕግም ይህን መርህ ይከተላል፡፡ ኢንሹራንስ ገቢው በሚዋዋልበት ወቅት የሚያውቃቸውን ማናቸውንም ሁኔታዎችና ኢንሹራንስ ሰጪው ሃላፊነት የሚወስድባቸውን አደጋዎች ለማመዛዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ሁኔታዎች በትክክል መግለፅ እንዳለበት ን/ህ/ቁ 667 ይደነግጋል፡፡ ኢንሹራንስ ገቢው መግለጫውን በሚሰጥበት ወቅት እውነትን ነገር መሸሸግ ወይም የሐሰት መግለጫ መስጠት የለበትም፡፡ ሕጉ እውነት መሸሸግንና የሐሰት መግለጫ መስጠትን ዓይነታቸውንና ውጤታቸውን ሁለት ቦታ በመክፈል የሚለያቸው ሲሆን አንደኛው አውቆ እውነትን መሸሸግና ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሆን ተብሎ ያልተደረገና በመጥፎ ልቦና ያልተደረገ ናቸው፡፡

አውቆ የተደረገ ከሆነ እውነተኛው ነገር ተገልያለት ቢሆን ኖር ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ውል አይዋዋልም ነበር ወይም ተጠቃሚው ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያደርግለት ውል ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ከሆነ ለኢንሹራንስ መግቢያ የተከፈለው ገንዘብ ለኢንሹራንስ ሰጪው ይሆንና ውሉ ይፈርሳል፤፤ (ን/ህ/ቁ 668(1)) ሆን ተብሎ እና በመጥፎ ልቦና ያልተደረገ ግን አንደኛ መሸሸጉ ወይም ሐሰት መግለጫ መስጠቱ አደጋው ከመድረሱ በፊት የተገለጸ ከሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኢንሹራንስ ገቢው ማስታወቂያ ከሰጠ ከአንድ ወር በኋላ ውሉን ለማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያው ገንዘብ ተጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል ማድረግ ሲችል ሁለተኛ አደጋው ከደረሰ በኋላ የታወቀ እንደሆነ ሊደርስ የሚችለው አደጋ በሙሉና በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለኢንሹራንስ ሊከፈል ይገባ በነበረውና በአሁኑ ጊዜ በተከፈለው ኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መካከል ያለው ልዩነት ታይቶ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኪሳራ ከሚከፈለውን ገንዘብ በዚሁ ልክ ተቀናሽ ይሆናል፤፤(ን/ህ/ቁ 668(2)(ሀ) እና (ለ)፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በአንድ በኩል ኢንሹራንስ ገቢው እውነተኛ መግለጫን የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ሲያስገነዝቡ በሌላ መልኩ ደግሞ እውነተኛ መግለጫ ስላልተሰጠ ብቻ ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን እንዳያፈርስ ግዴታ ይጥሉበታል፡፡ ውሉ በቀጥታ እንዲፈርስ መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫው በመጀመሪያ ደረጃ ኢንሹራንስ

ገቢው አውቆ የፈጸመው መሆን ሲገባው በሁለተኛ ደረጃና በተጨማሪ ኢንሹራንስ ሰጪው እውነተኛ ነገር ተገለያለት ቢሆን ኖሮ ውሉን አይዋዋልም ነበር ወይም ተጠቃሚው ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያደርግ ውል ይዋዋል ነበር ሊያሰኝ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም በዚህ ነጥብ ላይ ክርክር የሚነሳ እንደሆነ የተሸሸገውን ነገር ወይም የሐሰት መግለጫውን ምንነት፣ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት እና የተሰጠበትን ሁኔታ መመርመርና ለይቶ ማውጣት ጠቃሚ ነው፡፡ የማስታወቅን ግዴታን ስንመለከት ደግሞ ኢንሹራንስ ገቢው በንግድ ሕጉ ስር ሁለት ዓይነት የማስታወቅ ግዴታዎች እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡ እነርሱም ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ ሲሄድ ይህንኑ ማስታወቅ እና አደጋ በደረሰ ጊዜ መድረሱን ማስታወቅ ናቸው፡፡ ን/ህ/ቁ 669(1) ስር እንደተቀመጠው ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ ከሄደ እና ይህ በመሆኑ ውሉ በተደረገ ጊዜ አደጋው በዚህ ሁኔታ እየከበደ የሚሄድ መሆኑ ቢታወቅ ኖሮ ኢንሹራንስ ገቢውን ከፍ ያለ ኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ አስከፍሎ ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ኢንሹራንስ ገቢው ለኢንሹራንስ ሰጪው የማይዋዋል ወይም ቢዋዋልም ኢንሹራንስ ገቢውን ከፍ ያለ ኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ (premium) አስከፍሎ ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ኢንሹራንስ ገቢው ለኢንሹራንስ ሰጪው የአደጋውን እየከበደ መሄድ ማስታወቅ አለበት፡፡ አደጋው እየጨመረ የሄደው በኢንሹራንስ ገቢው ምክንያት ከሆነ አደጋው እንዲጨምር ያደረገው ሁኔታ በተደረገ በ15 ቀን ውስጥ በርሱ ምክንያት ካልሆነ ግን ሁኔታውን ካወቀበት በ15 ቀን ውስጥ ኢንሹራንስ ገቢው ለኢንሹራንስ ሰጪው ማስታወቅ ኣለበት፡፡ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ውሉን ለማፍረስ ወይም ለኢንሹራንስ መግቢያ የሚከፈለውን ገንዘብ ጨምሮ ውሉ እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል (ን/ህ/ቁ 669(2))፡፡ በሕጉ እንደተገለጸው ኢንሹራንስ ገቢው ካላስታወቀ በቁጥር 668 መሰረት ከፍ ብሎ በመግለጫ የመስጠት ግዴታ ስር በተገለጸው ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል (ን/ህ/ቁ 669(3)) ሌላኛው የማስታወቅ ግዴታ በቁ. 670 ስር ያለው አደጋ በደረሰ ጊዜ የሚፈጸመው ነው፡፡ በዚህ ህግ መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ኢንሹራንስ የገባው ሰው ኢንሹራንሰ የተገባበት አደጋ መድረሱን እንዳወቀ እጅግ ቢዘገይ እስከ ኣምስት ቀን ባለ ጊዜ ውስጥ ለኢንሹራንስ ሰጪው ማስታወቅ አለበት፡፡ ማስታወቂያ በጊዜ መደረጉ አደጋው የደረሰበትን ሁኔታና የአደጋውን ምንነት በአግባቡ ለመለየት የሚያግዝ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ግዴታ መኖር አስፈላጊነቱ ግልጽ ነው፡፡ ይሁንና ኢንሹራንስ ገቢው ይህን በአግባቡ ካልተወጣ የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሚሆን በግልጽ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ኢንሹራንስ ሰጪው በዚህ ሰበብ ብቻ ከመክፈል ግዴታው ነጻ ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም፡፡ የንግድ ሕጉ የያዛቸው የኢንሹራንስ ድንጋጌዎች በተለያየ ቦታ ላይ የትርጉም ልዩነቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉ እንደሆኑ ኣይተናል፡፡ የዚህ ሁኔታ መኖር የተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይም ችሎቶች በአንድ ዓይነት ጉዳይ ላይ የተለያየ ውሳኔ እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተግባር ላይ ያሉ አንዳንድ አሰራሮች

ከሕጉ መንፈስ የተለዩ ናቸው፡፡ የተለያዩ ዓይነት አሰራሮችን በማስከተል ልዩነቶችን ሊፈጥር ይችላል፡፡ በእርግጥ አንድን ሕግ ምንም የትርጉም ልዩነት በማያስከትል መልኩ ማውጣት ባይቻልም የትርጉም ልዩነቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉ እንደሆኑ አይተናል፡፡ የዚህ ሁኔታ መኖር የተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይም ችሎቶች በአንድ ዓይነት ጉዳይ ላይ የተለያየ ውሳኔ እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተግባር ላይ ያሉ አንዳንድ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ከሕጉ መንፈስ ያፈነገጡ ናቸው፡፡ ስለሆነም በኢንሹራንስ ርእሰ ጉዳዮች ሊከሰቱ የሚችሉትን የአተረጓጎም ልዩነቶች ለማጥበብ የሚያስችል ስራ መስራትን ይጠይቃል፡፡

<u>የመወያያ ነጥቦች</u>

ሀ. <u>የኢንሹራንስ ውልን በተመለከተ</u>

1. በኢንሹራንስ ውል ግብይት ከሚደረግበት ነገር (subject of sale) አንፃር ከሌሎች የሽያጭ ውሎች የሚለይበት ሁኔታና አደጋ ለመመዘን የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች (Material Facts) መለኪያ በምን መልኩ ይታያል?
2. በንግድ ሕግ ቁጥር 665/2/ ላይ የተገለፀው የኢንሹራንስ ሰጪው የመጨረሻ ሃላፊነት (sum insured) ከንግድ ሕግ ቁጥር 678 ጋር ያለው ልዩነት እንዴት ይታረቃል? አደጋ በደረሰበት ጊዜ ያለው ዋጋ ለኢንሹራንስ ሰጪው የካሳ ክፍያ መሰረት ነው ሲባል በሌላ በኩል ደግሞ በውሉ ላይ የተገለፀው የዋስትና ጣሪያ ለመድን ሰጪው የካሳ ክፍያ መሰረት ሊሆን ይገባል የሚል አቋም ስላለ ይህ እንዴት ይታረቃል?

3. ኢንሹራንስ ሰጪው በንግድ ሕግ ቁ. 683 ላይ ያለው የመዳረግ መብት በፍት/ሕግ ቁ. 2093 ከተገለፀው ጋር እንዴት ተጣጥሞ ይተረጎማል? ኢንሹራንስ ሰጪው በቅሪት ላይ ያለው መብት ከምን ይመነጫል? በጥቅሉ የመዳረግ መብት በንግድ ሕግ ቁጥር 683 ላይ በተገቢው መንገድ ተተርጉሟልን?
4. ለሞት በተደረገ የሕይወት ኢንሹራንስ ጊዜ ተጠቃሚዎች በምን መልኩ ሊወሰኑ ይገባል፣ የንግድ ሕግ ቁጥር 701 በምን መልኩ መተርጎም ይኖርበታል?
5. የኢንሹራስ ውል ኣርቦን አከፋፈልን የሚገዛው የንገድ ሕግ ቁ. 666 አተረጓጎም ምን መልክ ሊይዝ ይገባዋል? የመድን ውሉ በታገደበት ጊዜ አደጋ ቢደርስ ውጤቱ ምን ይሆናል? ውሉ በታገደበት ጊዜ ኣርቦን ሲከፈል ውሉ ከመቼ ጀምሮ ይቀጥላል?
6. የንግድ ሕግ ቁጥር 670 ውጤቱ ምንድነው ኢንሹራንስ ገቢው አደጋ ካላስታወቀ የኢንሹራንስ ሰጪው ሃላፊነት ምን ይሆናል?
7. ከውሉ በሚመነጭ ኪሳራ አተማመን በኣእምሮ ግምት በቂ ነው ተብሎ የሚገመተው ነው፣ ተብሎ በፍ/ህ/ቁ 1799 የተመለከተው እና በፍ/ህ/ቁ 1801 እርግጠኛ ጉዳት (Actual Damage) ተብሎ የተገለፀው የካሳ ልዩነት ምንድነው?
8. በን/ህ/ቁ 597 መሰረት በሰው ሞት ምክንያት አጓዥ ካሳ እንዲከፍል ሲጠየቅ ካሳ ጠያቂ ሊሆኑ የሚገባቸወ ሰዎች እነማን ናቸው? የሚለው ነገር አከራካሪ ነው፡፡ ይኸውም ከፍ/ህ/ቁ 2090 እስከ 2123 ያሉት ድንጋጌዎች በውል አለመፈፀም ምክንያት ለሚጠየቅ ኪሳራ ተፈፃሚ ናቸው ስለሚባልና በዚሁ ውስጥ የፍ/ህ/ቁ 2095 ማለትም ካሳ ጠያቂዎችን መጠን የሚገድበው ሕግ ስለሚገኝ ነው፡፡ በን/ህቁ 597 መሰረት አጓዞች በሰው ሞት ምክንያት ካሳ ጠያቂ ለሆኑ ሰዎች ሊከፍሉት የሚገባው የካሳ መጠን በምን መልኩ ይሰላል? ሟች በመሞቱ ልወርሰው የሚገባ የሀብት መጠን ቀንሷል በሚል ጥያቄ ብቻ የካሳውን መጠን ማጣበብ ይቻላልን?
9. በሰው ሞት ምክንያት የሚጠየቀው ካሳ በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠ ጥቅም መሆኑ በፍ/ህ/ቁ 2095 ላይ ተደንግጓል፡፡ ለዚህ የቀለብ አወሳሰን የፍት/ሕግ ቁ. 812 ኣግባብነት ምን ያህል ነው? በካሳ ጠያቂዎች ላይ በፍ/ህ/ቁ 2096 የተደረገው ገደብ በአብዛኛው ይፈፀማልን?
10. የሞራል ካሳ ጥያቄ መሰረቱ ምንድነው? በፍ/ህ/ቁ 2116(30 ላይ የተገለፀው ገደብ ካሳ ጥያቄዎች በሚበዙበት ጊዜ ወይም አንዱ ጉዳት ለሁለቱ የካሳ ጠያቂዎች መብት በሚሰጥበት ጊዜ ገደቡ የሚኖረው ተፈፃሚነት እንዴት ነው? ለምሳሌ ቤተዘመዶች ሲበዙ፣ አካሏ በመጉዳቱ ሚስት በፍ/ህ/ቁ 2113 መሰረት የሚጠይቀው የሞራል ካሳ ሲኖር የገደቡ ተፈፃሚነት እንዴት ይታያል?

5. <u>የማጓጓዣ ውል ህግ</u>

5.1. ስለማጓጓዣ ውል ህግ በጠቅላላ

የማጓጓዣ አገልግሎት ለአንድ አገር እድገት የደም ስር ነው።።ማጓጓዣ ለንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ሌሎች ማህበረ-ኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን ዓለም አሁን ወዳለበት እጅግ የተራቀቀ የመጓጓዣ አገልግሎት ከመድረሱ በፊት የሰው ልጅ በእግር በመጓዝ በመጫኛነት እንስሳትን ይጠቀም እንደነበረ ብዙ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ የአገራችን ሁኔታ በራሱ ዋቢ ነው።። የኢትዮጵያን የየብስ ማጓጓዣ ታሪክ ወደኃላ መለስ ብለን ስንመለከት ከጣልያን ወረራ በፊት በኢትዮጵያ በጋና ክረምት የሚያገለግል መንገድ ከአዲስ

አበባ እስከ ጅማ፣ ደብረማርቆስና ደሴ ብቻ የነበረ ሲሆን ከጣልያን ወራራ በኃላ ከ1928 – 1933 ዓ.ም ባለ ግዜ 2,770 ማይል ጥርጊያ መንገድ እንደተዘረጋ የታሪክ ድርሳናት ያስነብባሉ፡፡ ይህ በጣልያን ወረራ ጊዜ የተሰራው መንገድ ከኢትዮጵያ ነፃነት በኃላ በጥገና ችግር ብዙ ብልሽት የደረሰበት ቢሆንም ላለው ጥርጊያ መንገድ መስፋፋት በመነሻነት እያገለገለ ይገኛል፡፡

እስካሁን በስራ ላይ ያለው የኢትዮጳያ ንግድ ህግ ረቂቁ የተዘጋጀው ከተሻሻለው የፈረንሳይ ንግድ ህግ፣ ከስዊዝ የውል ህግና ከአውሮፓ የባቡር ህግ እንደሆነና የየብሰ ማጓጓዣ በተመለከተ ከአየር መጓጓዣ ጋር ልዩነት በማይፈጠር መንገድ ረቂቁን እንዳዘጋጁት professor Jaffret እንዲህ በማለት-

> *I have not distinguished between carriage of goods and carriage of passengers or baggage. As in the Warsaw convention relative to carriage by air, believe it is advantageous to have parallel provisions governing the different kinds of carriage, except where it is necessary to treat them differently. Thus the two titles are presented in similar manner- which means that for carriage by land that the presentation is fairly novel. የገለፁ ሲሆን*

አሁን አገራችን የደረሰችበት የእድገት ደረጃን መሰረት ያደረገና የአገራችንን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል የማጓጓዣ ህግ በማሰፈለጉ አዋጅ ቁጥር 468/99 ወጥቶ በየብስ፣ በአየርና በባህር ስለሚኖር የማጓጓዥ አገልግሎትን ህግና ስርዓት ባለው መንገድ ለመምራት ከፍተኛ የሆነ ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡

የአየር መጓጓዣ በአገራችን ከተጀመረ ከሌላው ዓለም ጋር ሲነፃፀር ኣሯጭር እድሜ ያለው ቢሆንም ለመጀመርያ የአየር ማጓጓዣ አገልግሎት የነበራቸው ጅማ፣ ጎሬ፣ ደብረማርቆስና ጎንደር ሲሆኑ ወደ ውጭ ይደረግ የነበረው በረራ 5-De-3/c-47 አውሮፕላን በመጠቀም ወደ ጁቡቲ፣ ኤደንና ካይሮ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የአየር በረራ አገልግሎት አሰጣጥን መሰረት አድርጎ የወጣውን የዋርሶ ኮንቬንሽን በአውሮፓ አቆጣጠር ነሓሴ 1950 በማፅደቅ ህዳር 1950 ዓ.ም በስራ ላይ እንዲውል ያደረገች ሲሆን በአገር ውስጥም መጋቢት 1/47 የአየር መጓጓዣ ደንብን አውጥታ በስራ እንዲውል አድርጋለች፡፡ ከዚያም የንግድ ህጉ በአዋጅ ቁጥር 166/1952 ሲወጣ የአየር መጓጓዣን መሰረት በማድረግ ከን/ህ/ቁ 604 653 ባሉ ድንጋጌዎች የህግ ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ አሁን ካለው የአገልግሎቱ መስፋፋትና አገራችን እየተከተለችው ካለ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ ጋር በተጣጣመ መንገድ ተገቡ የህግ ሽፋንና ጥበቃ እንዲያገኝ በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር

31/1988ና የኢትዮጵያ የኣቬሽን ሴኩሪቲ ኣዋጅ ቁጥር 432/1997 ወጥተው በስራ ላይ ውለዋል፡፡

የባህር መጓጓዣን በሚመለከት ኢትዮጵያ ለመጀመርያ ጊዜ 1945 ዓ/ም ኣዋጅ ቁጥር 136/1945 የኢትዮጵያ የባህር ጠረፍ ጥበቃ (the Ethiopian coast guard) ያወጣች ሲሆን ከአንድ ዓመት በኃላም የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ መቆጣጠርያ ኣዋጅ ቁጥር 137/1946 ኣውጥታለች፡፡ ከዚያም ምንጩ ኣለም ዓቀፍ የባህር ህግ ማለትም የ1924 The Hague Rules የሆነውን የኢትዮጵያ የባህር ህግ በኣዋጅ ቁጥር 137/53 ኣውጥታ በስራ ላይ እንዲውል ኣድራጋለች፡፡ በኣጠቃላይ የየብስ፣ የአየርና የባህር ማጓጓዣን መሰረት በማድረግ በአገራችን የወጡት ህጎች በተለይ ደግሞ ቀደምት ህጎችን በምንመለከትበት ጊዜ የኣየር መጓጓዣ ህጋችን ዓለም ኣቀፍ የኣየር መጓጓዣን መሰረት በማድረግ የወጣው የ1929 ዓ.ም የዋርሶ ኮንቬንሽንን ሲሆን የባህር ህጉም እንደዚሁ ዓለም አቀፍ የባህር ማጓጓዣን መሰረት በማድረግ የወጣውን የ1924 የሄግ ህግን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

5.2. የየብስ ማጓጓዥ ውል (Carriage by Land)

ስለ የብስ ማጓጓዣ ውል ትርጉም የሚሰጠው ን/ህ/ቁ 561 “የማጓጓዥ ውል ማለት አጓጓዡ ዋጋ በመቀበል ሰውን ጓዝ ዕቃዎች በተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ነው፡፡” በማለት የማጓጓዣ ውል ምንነት ያስረዳል፡፡ የማጓጓዣ ስራ በኣዋጅ 468/97 አንቀፅ 12(1) መሰረት “ማንኛውም ግለሰብ ወይም በህግ መሰረት የተቋቋመ ድርጅት በህዝብ የንግድ ማመላለሻ ስራ ለመስራት ይችላል” ሲል የዚህ አንቀፅ ንኡስ ቁጥር 2 “በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ ለመስራት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎችና ድርጅቶች በዚህ ኣዋጅ አንቀፅ 13 መሰረት የሚቋቋም ማህበር ኣባል ሳይሆኑ ስራቸው በግላቸው ሊያካሂዱ ይችላሉ፡፡” በማለት ደነግጓል ይህም የሚያመላክተው የየብስ ማጓጓዥ በግልና በማህበር ሊይዝና የማጓጓዣ ውልም ከግለሰብ ጋር ወይም በማህበር በተደራጀ ህጋዊ ሰውነት ከተሰጠው ድርጅት ጋር ሊፈፀም እንደሚችል ነው፡፡ ይህ ኣዋጅ የተገልጋዬችን ሂወት፣ ንብረትና የኣገር ሃብትን ከአደጋ ለመጠበቅ በኣንቀፅ 22(1) “ማንኛውም ሰው ዓይነቱ ተለይቶ የገለፀ ባለ ሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት በዚህ ኣዋጅ መሰረት የሚወጣ ደንብና መመርያ መሰረት የተሰጠው የፀና የመንጃ ፈቃድ ከሌላው በስተቀር በማንኛውም መንገድ ላይ ማናቸውንም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ኣይችልም፡፡” የሚል በመሆኑ የደህንነት ፖሊሲን መሰረት ያደረገ ድንጋጌ የያዘ ነው፡፡

የማጓጓዣ ውል በኣጓዥና መንገደኛ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚመሰረት ሲሆን ይዘቱም መንገደኛ የጉዞ ትኬቱን ጉዞው ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ይዞ እንዲቆይ የማሳወቅና ቢጠፋ ተጨማሪ ክፍያ ሊያስከትልበት እንደሚችል ለኣጓዥ መብት የሚሰጥና ግዴታም የሚጥል ነው፡፡ የጉዞ ትኬቱ የጉዞው መነሻና መድረሻ ሰዓት መያዝ ይኖርበታል፡፡ በን/ህ/ቁ 567 ተጓዥ የጉዞ ትኬት መያዝ እንዳለበት ሲገልፅ ትኬቱ እንደ ውል ሰነድ

የሚወስድ ነው፡፡ በአዋጅ 468/97 አንቀፅ 2(1) ላይ "መንገደኛ" ማለት በተሽከርካሪ ተሳትፎ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሲሆን ነጂውን ገንዘብ ተቀባዩንና በተሽከርካሪው ላይ የተመደበ ማንኛውም ሌላ ሰራተኛ አይጨምርም" ሲል ይደነግጋል፡፡ የዚህን አዋጅ "....ማንኛውም ሰው ..." የሚለውን አባባል መሰረት አድርገን የጉዞ ትኬቱን የገዛው ሰው ሌላ ሰው በሚሆንበት ጊዜ የውሉ ውጤት ምንድን ነው የሚሆነው? በተጓጉና አጓዡ መካከል የጉዞ ውል እንዳልነበረ ወይስ የአዋጁን ሐሳብ መሰረት በማድረግ የትኬቱን ዋጋ ማንም ይክፈለው ማን ውል አለ ብሎ መተርጎም? እንደ አዘጋጁ ገንዘቤ ከሆነ ን/ህ/ቁ 561 "... አጓጉዥ ዋጋ በመቀበል..." በማለት ስለሚደነግግ የትኬት ዋጋ የከፈለው ተጓጉዥ ወይስ ሌላ ሰው? የሚለው ነገር እስከሌለና ተጓዡ ትኬቱን እስከያዘ ድረስ ውል የለም የሚባልበት ምክንያት አይኖርም የሚል ነው፡፡

ከመንገድ ማመላለሻ ትኬት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ብዙውን ግዜ የሚነሳው አወዛጋቢ ጉዳይ ተጓጉዥ ትኬት በሚገዛበት ግዜ ውል ተገብቷል የሚባለው ከትኬት ቆራጩ ጋር ወይስ ከተሽከርካሪው ባለቤት ጋር? የሚል ሲሆን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙርያ የሚሰጠው አስተያየትም፤-

1. የተሽከርካሪው የባለቤትነት መብት በተሽከርካሪዎች ምዝገባ ህግ መሰረት የተሰጠው ለንብረቱ ባለቤት እንጂ ለትኬት ቆራጩ እስካልሆነ ድረስ ውሉ የተደረገው ከትኬት ቆራጩ ጋር ነው ብሎ ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡
2. ተሽከርካሪውን በንግድ መዝገብ ማስመዝገብ የሚችለው ባለቤቱ እስከሆነ ድረስ ውሉ የተደረገው ከባለቤቱ ጋር ነው፡፡
3. ፈቃዱ የወጣው በባለቤቱ ስም እስከሆነ ድረስ ውሉ ተደረገ መባል ያለበት ከተሽከርካሪው ባለቤት ጋር ነው፡፡
4. ትኬት ቆራጩ የባለቤቱ ወኪል ነው ቢባልም እንኳ ከተሰጠው ስልጣን አልፎና በራሱ ስም እስከልተዋዋለ ድረስ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2189 መሰረት ውሉ ተደረገ የሚባለው ከባለቤቱ ጋር ነው የሚሉ ናቸው፡፡ የአዘጋጁ አስተያየትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ህግ የሰው፣ ሻንጣዎችና እቃዎች ማጓጓዣን በማስመልከት በርካታ ድንጋጌዎች ያሉት ሲሆን እነዚህ እቃዎች በሚጓጓዙበት ጊዜ መጀመርያ የማጓጓዣ ውል ከተዋዋለው ተሽከርካሪ ውጭ ሌላ በመሃል ተቀብሎ ከጫነ ተሽከከርካሪ በጉዞ የነበረው እቃ ቢጠፋ የንብረቱ ባለቤት መክሰስ ያለበት የመጀመርያውን አጓዥ ወይስ የኋለኛውን? በዚህ አከራካሪ ጉዳይ ዙርያ በተለያዩ አገሮች የተለያየ አሰራሮች የሚከተሉ ሲሆኑ ለምሳሌ በእንግሊዝ ህግ የመጀመርያው አጓጓዥ የሁለተኛው አጓጓዝ ወኪል ከሆነ ለአጠቃላይ ጉዞው ሃላፊነት የሚወስደው ሁለተኛው አጓጓዝ ነው፡፡ የመጀመርያው አጓጓዥ ለአጠቃላይ ጉዞ ሃላፊነት የሚኖረው ሁለተኛው አጓጓዥ የሱ ወኪል ከሆነ ነው የሚል ሲሆን በፈረንሳይ አገር

ደግሞ ሃላፊነቱን የሚወሰደው ንብረቱ በእጁ እያለ የጠፋበት አጓጓዥ ነው የሚለው አካሄድ ይከተላሉ፡፡

በኢትዮጵያ ያለው አሰራር ን/ህ/ቁ 600 መሰረት ያደረገ ሲሆን "የማጓዙ ውለታ የተደረገው በአንድ አጓዥ ሳይሆን ከአንድ በላው አጓጓች ጋር የሆነ እንደሆኑ መንገደኛው ወይም ስለመንገደኛው መብት የተሰጠው ሰው በውለታው ላይ መጀመርያው አጓዥ ለመላ ጉዞው አላፊ ይሆናል ተብሎ በግልፅ የተዋዋለ ካልሆነ በቀር በአላፊነት መጠየቅ የሚቻለው አደጋው ወይም መዘግየቱ በደረሰበት ጊዜ አጓዥ የሆነው ሰው ብቻ ነው፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ የመጀመሪያው አጓዥ ሃላፊነት እንዲወስድ ስምምነት ከሌላ ግን ሃላፊነት የሚወስደው አደጋ ወይም መዘግየት በደረሰበት ጊዜ አጓዥ የሆነውን ሰው ነው ስለሚል ሃላፊቱ የሚወድቀው በሁለተኛው አጓዥ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የመጀመርያው አጓዥ አድራሻው ላይታወቅ ይችላል ከሚል ፣ ሁለተኛው አጓዥ ዕቃዎቹን ሲቀበል አስቀድሞ የነበረን ውል ተቀብሏል የሚል ሃሳብ ስላለ ሊሆን ይችላል ወይም በሽግግሩ ወቅት የኃለኛው አጓዥ ሌላ የውል ቃል እስካልጠየቀ ድረስ ንብረቱን ቆጥሮ ተቀብሏል ተብሎ ስለሚገመት ሊሆን ይችላል፡፡ በሰነዱ ላይ ያለው ቃል ስህተት መሆኑ ካላረጋገጠ በስተቀር እቃው የተጎዳ ወይም ግልጋሎቱ የቀነሰ ከሆነ ሁለተኛው አጓዥ ሓላፊ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳቱ የደረሰው በመጀመርያው አጓዥ መሆኑ ከተረጋገጠ ላኪው እና ተቀባዩ በመጀመርያው አጓዥ ላይ ክሳቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ላኪው እና ተቀባዩ ሰፊ አማራጭ ያላቸው ናቸው፡፡ ይሄውም በን/ህ/ቁ 600(3) መሰረት የመጀመርያውንና ቀጣዩን አጓዥ በነጠላና በአንድነት በመክሰስ መብታቸውን ማስከበር ይችላሉ፡፡

የማጓጓዣ ውል ከሌሎቹ ውሎች የሚለይበት መንገድ ለዋጋ ሲባል የሚደረግ ውል መሆኑ ነው፡፡ ለሲህም International encyclopedia የመጓጓዣ ውልን ትርጉም በሚከተለው አግባብ ተርጉሞታል፡፡

> *At law, the carriage of goods and person is the subject matter of an agreement called "contract of carriage" by this contract one party called the carrier, agrees with another party called the consignor to carry certain goods or certain person from one place to another in consideration or the payment of a sum of money, called freight.*

የኢትዮጵያን ንግድ ህግ የእንግሊዝኛውን ቅጅ ትርጉም ስንወስድ ደግሞ ን/ህ/ቁ 561 "A contract of carriage is a contract where by a person called the carrier undertakes for reward to carry person, baggage or goods and to convey them to a specific place." በማለት ይተረጉመዋል፡፡ በእነዚህ የማጓጓዣ ትርጉሞች ያለው ተመሳሳይነት የማጓጓዣ ውል ለጥቅም (consideration) ሲባል የሚደረግ ውል መሆኑ ላይ ሲሆን ልዩነታቸው ግን የመጀመርያው ትርጉም በግልፅ የተወሰነ ገንዘብ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ

ሲገልፅ የን/ህ/ቁ ትርጉም “reward” የሚለው ቃል የማጓጓዣ ውል ክፍያ በገንዘብ ብቻ እንደሚሆን በግልፅ የሚደነግግ አይደለም፡፡ የዚህ ድንጋጌ የአማርኛው ቅጅም ቢሆንም “ዋጋ በመቀበል” ከሚል ውጭ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈል ስለመሆኑ በግልፅ የሚለው ነገር ባመኖሩ ለትርጉም የተጋለጠ ነው፡፡

የየብስ የማጓጓጓዣ ውል በባህሪው በአጓዥ አዘጋጅነት የሚደረግ የውል ስምምነት (adhesive contract) ነው ይህ ማለት ግን ህግ በአጓዥ ላይ የሚጥላቸው ገደቦች (restrictions) የሉም ማለት አይደለም፡፡ ከነዚህም ገደቦች ውስጥ ለምሳሌ አጓዥ በእቃዎችና የተመዘገቡ ሻንጣዎች ለሚደርስ ጉዳት የሚኖርበትን ሃላፊነት ሊወሰን ይችላል ግን ደግሞ የካሳውን መጠን ከንብረቱን ዋጋ ዝቅ በማድረግ ሊያዘጋጀው አይችልም፡፡ ሌላው በራሱ ጥፋት ለደረሰ ጉዳት በውል የተጠቀሰውን የሃላፊነት መጠን (limits of liability) በመከራከርያነት ሊያነሳ አይችልም፡፡ በሰው ላይ ለሚደርስ ጉዳት ብህግ የተቀመጠውን 40,000 ብር የካሳ መጠን በስምምነት መቀነስ አይችሉም፡፡ (ን/ህ/ቁ 594፣ 590፣ 597) የየብስ ጉዞ ውል የሚደረገው ገንዘብ በመክፈልና የጉዞ ትኬት በመቀበል ሲሆን የዚህ ትኬት ህጋዊ ውጤትም እንደማስረጃና የባለቤትነት ማረጋገጫ ያገለግላል ለዚህም ዝርዝር ይዘቱን ከን/ህ/ቁ 576፣ 579(2) እና 581 መገንዘብ ይቻላል፡፡

5.2.1. የአጓዥ ካሳ የመክፈል ሃላፊነት

የአጓዥ ሃላፊነት በመርህ ደረጃ ፍፁም ሃላፊነት (absolute liability) ያለበት ነው፡፡ ለዚህም ህጉ በምክንያትነት የሚወስደው አጓዥ በሰላም ሰው፣ ሻንጣና ዕቃ የማድረስ ዓላማን መሰረት የደረገ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን አጠቀላይ መርሁ (The general principle) ያለ ልዩ ሁኔታ (exception) የተደነገገ ነው ማለት አይደለም፡፡ አንድ ሰው፣ ዕቃ፣ የተመዘገበ ሻንጣ የጠፋው፤ የተጎዳው ወይም የዘገየው ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ ወይም በንብረቱ ውስጣዊ ችግር ከሆነ ፣ በላኪው ወይም በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ከሆነ የሚኖርበት ሃላፊነት በከፊል (partial liability) ሊሆን ይችላል፡፡ (ፍ/ህ/ቁ 2144፣ ን/ህ/ቁ 590፣ 591፣ 595፣ 596 እና ፍ/ብ/ህ/ቁ 1791፣ 1799፣ 1801(1) እና 2091) የአጓዥ ከፍተኛ ጥፋት (Grave fault of the carrier) የአጓዥ ከፍተኛ ጥፋት መኖር በካሳ አከፋፈል ሃላፊነት ላይ ስለሚኖረው ህጋዊ ውጤት ን/ህ/ቁ 599 “ጉዳት የደረሰው አጓዡ በፈፀመው ተግባር ወይም ባደረገው ጉድለትና እንዲሁም ይህ ተግባርና አደጋ ጉዳት ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ እንደሆነ በን/ህ/ቁ 594 እና 597 የተደነገገው ውሳኔ አይፀናም፡፡“ በማለት ይደነግጋል ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አንድ አጓዥ ጉዳቱን ያደረሰው፤-

ሀ. ሆነ ብሎ ድርጊቱን በመፈፀሙ ወይም ማድረግ ያለበትን ባለማድረጉ የመጣ ጉዳት ከሆነ፣

ለ. የድርጊቱ ወይም ያለማድረጉ ውጤት ምን እንደሚሆን እያወቀ ያደረው መሆን፣

ሐ.የጉዳቱ ውጤት በአጓዡ ማድረግ ወይም ኣለማድረግ የመጣ መሆኑን ማረጋገጥ ከተቻለ ያልተወሰነ ሃላፊነት ኣለበት ተብሎ ሊወሰንበት እንደሚችል ነው፡፡

ስለ ሌላ ሰው ሃላፊ ስለመሆን (Vicarious Liability) በመንገደኛ ላይ በሶስተኛ ወገን ለሚደርስ የኣካል ጉዳት ወይም መሞት አጓዥ ሃላፊነት የለበትም፡፡ መንገደኛው ጉዳት ባደረሰበት ሶስተኛ ወገን ላይ ክስ መመስረት ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 599፣ 125(3) እንዲሁም ፍ/ብ/ህ/ቁ 1679 ከ1952 ጋር እና 2027፣ 2028) ይህ ማለት ግን አጓዥ ሃላፊ ለሚሆንባቸው ኣሽከርካሪ እና ረዳት ሰራተኞቹ በመንገደኛው ለሚደርስ ጉዳት ሃላፊ ኣይሆንም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ (ፍ/ብ/ህ/ቁ 2130፣ 2131፣ 1952(1)፣ 1676(1) ከ1952(1) ጋር እና ን/ህ/ቁ 28(2)፣ 33(2)፣ 37(3) ብንመለከት ለዚህ መልስ የሚሰጡ ናቸው፡፡

5.2.2. የሚከፈለው የጉዳት ካሳ (compensatory awards)

ጉዳት መድረሱና ለጉዳቱ ሃላፊ የሚሆን ሰው ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ብዙውን ጊዜ ኣስቸጋሪ የሚሆነውና የዳኞቹ ቀጣይ ስራ የካሳውን መጠን መወሰን ነው፡፡ በካሳ መጠን ኣወሳሰን ዙርያ ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ጉዳዮች፡-

- የውሉ ቃል ምን እንደሚል በሚገባ ማጤንና የዕቃ ማጓጓዣ ውሉ ስለዚህ የሚለው ነገር ካለ በኣግባቡ መገንዘብ፣
- የህጉ ኣስገዳጅ ኣንቀፆች ለይቶ ማወቅና ህጉ በሚለው መሰረት ማስተናገድ፣
- መንገደኛው የኣደጋውን ውጤት ለማምጣት የነበረው ድርሻ(ተሳትፎ) ለይቶ ማወቅ፣
- የዕቃውቹ ባህሪ፣
- አጓዥ የሚያቀርበው መከራከርያና ተኣማኝነቱ፣
- የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ካለ መረዳትና ህግ በሚያዘው መሰረት ማስተናገድ፡፡
- የጉዳቱ ምክንያት ለምሳሌ ጉዳቱ ከኣቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ወይስ ኣይደለም? ብሎ መለየትና እነዚህን ከግምት ውስጥ እያስገቡ የካሳውን መጠን መወሰን ይጠይቃል፡፡ (ን/ህ/ቁ 590፣ 591 እና 596)

በኣገራችን ህግ አንድ ጉዳት የደረሰበት መንገደኛ፣ እቃው ወይም ሻንጣው በመጥፋቱ ወይም መድረስ ካለበት ጊዜ ዘግይቶ በመድረሱ ምክንያት ካሳ የሚከፈልባቸው ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም፡-

- ❖ በእቃ ማጓጓዣ ውሉ ላይ የሰፈረ የውል ቃል ባይኖርም አጓዥ ዕቃው በመጎዳቱ፣ በመጥፋቱ ወይም የመድረሻ ጊዜው በመዘግየቱ ምክንያት መደበኛውን ካሳ (normal damage) የመክፈል ሃላፊነት ኣለበት፡፡
- ❖ ተዋዋይ ወገኖች በኣካል ጉዳትና የሰው ሂወት መጥፋቱ ላይ ካልሆነ በዕቃ ላይ ስልሚኖረው የካሳ መጠን ሊስማሙ ስለሚችሉ የውሉን ቃል መሰረት በማድረግ ካሳ እንዲከፈል ማድረግ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን አጓዥ መንገደኛውን ከእቃው ዋጋ በእጅጉ ዝቅ በማድረግ መስማማት ኣይችልም፡፡ ምክንያት አጓዥ የዚህ ዓይነት ውል እንዲያደርግ ህጉ ፈቀደለት ማለት በመንገደኞች ዕቃ ላይ ቸልተኝነት እንዲያሳይ

በህግ መፍቀድ ሰለሚሆን ይህ በህግም በሞራልም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአንፃሩ ከዋጋው በላይ ለመክፈል እንዳይስማማ ግን አይከለክልም፡፡ (ን/ህ/ቁ 594)

- በዕቃ፣ በተመዘገበ ሻንጣና በሰው አካል ወይም ሂወት ላይ ጉዳት የደረሰው በአጓዥ ጥፋት ከሆነ የሚከፈለው የካሳ መጠን ቅጣትን የሚጨምር ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 594 እና ፍ/ብ/ህ/ቁ 1887)
- ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ወገን ሆኖ ግን ደግሞ ጉዳት አድራሾቹ የአጓዥ ሰራተኞች በሚሆንበት ጊዜ የሚኖረው የካሳ አከፋፈል ስርዓት ጉዳት የደረሰበት ሰው ወይም ወራሾቹ በአጓዥና ሰራተኞቹ ላይ ወይም በተናጠል በመክሰስ ከውል ውጭ በሆነ ሃላፊነት ተጠያቂ ሊያደርጓቸው ይችላሉ፡፡(ፍ/ህ/ቁ/2130)

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የየብስ ማጓጓዣ የንግድ ህዝብ ማመላለሻ መኪና፣ ባቡር ወይም በአዋጅ ቁጥር 468/97 መሰረት ሰረገላና ሌሎች ማጓጓዣዎችን አጠቃቀምና በተዋዋይ ወገኖች ስለሚኖረው መበትና ግዴታ እንዲሁም በዕቃና በተመዘገበ ሻንጣ ላይ ጉዳት፣ መጥፋትና፣ ዘግይቶ መድረስና በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስና ለሞት መዳረግ የካሳ ሃላፊነትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉና ዝርዝር አፈፃፀማቸውን በተመለከተ በንግድ ህጉና አዋጅ ቁጥር 468/97 ላይ ተዘርዝረው የምናገኛቸው የህግ ሽፋን የተሰጠው መብቶች ናቸው፡፡

5.3. የአየር ማጓጓዣ (Air Carriage)

የአየር መጓጓዣ አገልግሎት ዘመናችን ከፈጠረው የመገናኛ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን አገሮችና ህዝቦች ፈጣን ለሆነ የግብይት ስርዓት እንዲውል በማድረጋቸው አገልግሎቱ ከማንኛውም ግዜ በላቀ ሁኔታ እያደገ እንዲሄድ አስችሎታል፡፡ የተለያዩ አገሮች የራሳቸው የሆነ ለአላዊነትና ህግ ያላቸው በመሆኑ የሌላን አገር ህግ ለመቀበል ላይገደዱ ይችላሉ ይሁንና አሁን ባለንበት ዘመን አንድ አገር በሩን ዘግቶ መቀመጥ ስለማይቻል ወደደም ጠላም ከዓለም ጋር አብሮ መኖር፣ መነገድ፣ የባህል ልውውጥ ማድረግ ወዘተ የግድ ወደሚሆንበት ዘመን ደርሰናል፡፡ ለዚህም ነው M.C.Cheshire

> *It is impracticable in the modern civilized world, and nations have long ago found out that they can not, by sheltering behind the principle of territorial sovereignty afford to disregard foreign rules of law merely because they happen to be at variance with their own territorial or internal system of law.*

በማለት ከዓለም ተነጥሎ መኖር እንደማይቻል የሚገልፁት ዓለማችን የ1929 የዋርሶ ኮንቬንሽን ከመውጣቱ በፊት አንድ ወጥ የሆነ (uniform) የአየር ማጓጓዣ ህግ ያልነበራት ሲሆን አገሮች በራሳቸው ይገለገሉበት የነበረ የራሳቸው የአየር ማጓጓዣ ህግ እንደነበራቸውና ይህንን ወደ አንድ ዓለማቀፍ ህግነት ለማምጣት ብዙ ጥረቶች እንደተደረጉ ከአንዳንድ

መጣጥፎች ለመግንዘብ ይቻላል፡፡ ዓለማቀፍ በረራን መሰረት በማድረግ የወጣው የዋርሶ ኮንቬንሽን ለመጀመርያ ግዜ በ23 አገሮች የተመሰረተና የዓለም ዓቀፍ የግል ህግ (International private law) ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ ከፍተኛ ሚናን የተጫወተ ኮንቬንሽን ነበር፡፡ ለዚህም ይመስላል " A good rule with word wide acceptance is better than a better rule opposed by a number of states. One has to pay a price for International Uniformity" በመባል የተሞካሸው፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ለሰፈሩት ድንጋጌዎች በምንጭነት የሚጠቀሰው ኮንቬንሽን ኢትዮጵያ የኮንቬንሽኑን አንቀፅ 2 ክፍል አንድን "the convention should not apply to international air transportation effect directly by Ethiopia" የሚል ቃል በማስፈር የተቀረውን የኮንቬንሽኑን ህግጋት በ1950 ዓ.ም ያፀደቀችው ስለሆነና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 9(4) ደግሞ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ህግ አካል ናቸው፡፡ "በማለት ስለሚደነግግ የዋርሶ ኮንቬንሽን ከህዳር 1987 ዓ.ም ጀምሮ እንደ አገራችን ህግ የሚታይ ነው፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ ከፍ ብሎ የተገለፀውን ቃል በማስቀመጥ የተሰማማች በመሆንዋ ዓለምአቀፍ በረራዎች በዋርሶ ኮንቬንሽን የሚገዙ ሲሆኑ የአገር ውስጥ በራረና በዋርሶ ኮንቬንሽን የማይገዛ ዓለም አቀፍ በረራ የምታደርግ ከሆነ ግንኙነቱ የሚገዛው በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ነው፡፡ በንግድ ህጉ የአየር ጉዞን በማስመልከት ከን/ህ/ቁ 604-653 ባሉ ድንጋጌዎች እንዲሸፈን የተደረገ ሲሆን የአጓዥ ሃላፊነትን በሚመለከት በዋርሶ ኮንቬንሽንና በንግድ ህጉ ያሉት ድንጋጌዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡

5.3.1. የአጓዥ ሃላፊነቶች ከዋርሶ ኮንቬንንና የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንፃር

የሃላፊነቶቹን ይዘት ለመረዳት ያስችለን ዘንድ በሶስት ማለትም፤-

1. በመንገደኞቹ ለደረሰ ጉዳት ስለሚኖረው ሃላፊነት (liability for carriage of passengers)
2. በዕቃዎችና ሻንጣዎች ለደረሰ ጉዳትና፣ መጥፋት ስለሚኖረው ሃላፊነት (liability for the carriage of goods and baggage's)
3. በመዘግየት ምክንያት የሚመጣ ሃላፊነት (liability for delay)

በሚል ከፍለን ልናየው የሚችል ነው፤፤ በመጀመርያው ከአጓዥ ሃላፊነት ብንጀምር አጓዥ ለመንገደኛው የአካል ጉዳት ወይም መሞት ሃላፊ የሚሆነው በአውሮፕላኑ ውስጥ በመጓዝ ላይ ሳለ ወይም በአውሮፕላን ለመጓዝ ሲሳፈር ወይም ሲወርድ አደጋ ከደረሰበት ነው፡፡ ለዚህ የዋርሶ ኮንቬንሽን አንቀፅ 17 በግልፅ "Physical or bodily injury or death are recoverable" በማለት ሲደነግግ የኢትዮጵያ ንግድ ህግም በአንቀፅ 630 ላይ "መንገደኛው በአውሮፕላን ጉዞ ላይ እንዳለ ወይም ለመጓዝ ሲሳፈር ወይም ሲወርድ የሞት አደጋ ወይም ሌላ የአካል ጉዳት ቢደርስበት አጓዥ ሃላፊ ይሆናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ አጓዥ ለደረሰው የአካል ጉዳትም ሆነ ሞት ሃላፊ የሚሆነው ለጉዳቱ መንስኤ የሆነ" አደጋ" (accident) የደረሰ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባና

ሃላፊነቱ ለማንኛውም ጉዳት እንዳልሆነ ነው (ን/ህ/ቁ 630)፡፡ ሁለተኛውን የአጓዥ ሃላፊነት በተመለከተ የዋርሶ ኮንቬንሽን አንቀፅ 18 "The carrier is liable for damages sustained in the event of the destruction or loss of damage to any registered luggage or any good, if the occurrence which caused the damage so sustained took place during the carriage by air." በማለት የአጓዥን ሃላፊነት ሲገልፅ የኢትዮጵያ ንግድ ህግ ቁጥር 631 ላይ "የተመዘገቡ ዓዞች ወይም ዕቃዎች በአየር ጉዞ ጊዜ በሆነ ነገር ቢጠፉ ወይም ቢበላሹ አጓዥ በሃላፊነት ይጠየቅበታል፡፡" ሲል ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ይደነግጋል፡፡ ሶስተኛው ሃላፊነት በሚመለከት የዋርሶ ኮንቬንሽን በአንቀፅ 19 ላይ "The carrier is Liable for damage occasioned by delay in the carriage by air of passengers or goods." ሲል የኢትዮጵያ ንግድ ህግ በቁጥር 633 ላይ "በአየር ጉዞ በሚደረግበት ጊዜ በመንገዶቹ፣ በዓዞቹ ወይም በእቃዎች ዘገይቶ በመድረስ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት አጓዥ ሃላፊ ነው፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡

በእነዚህ ድንጋጌዎች ዙርያ የሚነሱት አከራካሪ ጉዳዮች የዋርሶ ኮንቬንሽን አንቀፅ 17 እና የን/ህ/ቁ 630 "accident" "አደጋ " ሲሉ ቃሉ በራሱ ምን ማለት ነው? ለሚለው ፍች አይሰጡም በመሆኑም ያልተጠበቀ ነገር (Unexpected event) ወይስ ያልተለመደ ከውጭ የሚመጣ ችግር? የሚል ሲሆን የተለያዩ የውጭ አገር ፍ/ቤቶች የተለያየ ትርጉም ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡

ለምሳሌ በ padilla V. Olympia Air Lines ጉዳይ መንገደኛው Padilla በበረራ ላይ እያለ ከ6-7 ቢራ ጠጥቶ ሽንት ቤት (Lavatory) ውስጥ ወድቆ ለደረሰበት የአካል ጉዳት ካሳ አይገባውም ምክንያቱም ይህ አደጋ አይደለም በራሱ ፈቃድ (voluntarily) ያመጣው የአካል ጉዳት ነው በማለት አሰናብቶታል፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር በተያይዞ ሊነሳ የሚችለው አወዛጋቢ ጉዳይ "bodily injury" የሚለው አባባል የአእምሮ ጉዳትን ይጨምራል ወይስ አይጨምርም? የሚል ሲሆን አብዛኞቹ የውጭ አገር ፍ/ቤቶች "bodily injury" is inclusive to mental or psychic injuries በሚል አተረጓጎም ውሳኔ ሲሰጡ ይታያል፡፡

ከእቃዎች ወይም ዓዞች መጥፋትና መበላሸት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ክርክር የዋርሶ ኮንቬንሽን አንቀፅ 18 "... during carriage by air." ከሚለውና የን/ህ/ቁ 631"....whilst such Luggage or goods were carried by air." ከሚሉት አባበሎች ጋር ተያይዞ የሚነሳው ዕቃው ወይም ሻንጣው በአየር ጉዞ ላይ ሳለ የሚለው አባባል መነሻና መድረሻው የት ነው? ወይም ይህ ንብረት በአየር ጉዞ ላይ ነው የሚባለው መቼ ነው? የሚል ሲሆን በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ የአገር ውስጥ የፍ/ቤቶች ጉዳይ የሌለ ቢሆንም በውጪው ዓለም ያለው አተረጓጎም **ለምሳሌ በ** Fovie V.Sabena ጉዳይ Fovie ከስዊዘርላንድ ወደ ብራስለስ ስርዓቶችን ይዛ ለመሄድ ተነስታ አየር መንገድ ውስጥ የጉምሩክ ቀረጥ ለመክፈል አስቀምጣቸው ሳለች ጠፍቶባት ፍ/ቤቱ አየር መንገዱን ሃላፊ አይደለም ብሎ

አሰናብቶታል፡፡ ሌላ ፍ/ቤት በሌላ ጉዳይ Westminster Bank V. Imperial Airways በተከራከሩበት መዝገብ ከሳሽ ባንክ ከፓሪስ ወደ ለንደን ለመጓዝ በዝግጅት ላለ በአየር መንገዱ የደህንነት ሳጥን (security box) ውስጥ ያስቀመጠው ወርቅ ስለጠፋበት ፍ/ቤቱ አየር መንገድ ሃላፊ እንደሆነ ወስኗል፡፡ ከነዚህ ውሳኔዎች ለመገንዘብ የሚቻለው የኮንቬንሽኑም ሆነ የንግድ ህጉ አላባል ለትርጉም የተጋለጠ መሆኑን ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 19 “in the carriage by air” የሚል አባባልና ን/ህ/ቁ 633 “in carriage” የሚል ሐረግ ስለሚጠቀሙ ይህ ሁኔታ አለ የሚባለው መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ እንዲነሳ ምክንያት ሲሆን ይታያል፡፡ ለዚህ አንዳንድ ፀሃፍት የሚሰጡት አስተያየት የኮንቬንሽኑ አንቀፅ መነበብና መተርጎም ያለበት ከኮንቬሽኑ አንቀፅ 17፣ 18፣ 22 እና 24 ጋር ነው በማለት አስተያየት የሚሰጡ ሲሆን ተመሳሳይ ጉዳይ በአገራችን በሚያጋጥምበት የነዚህ የዋርሶ ኮንቬንሽን ድንጋጌ አቻዎች የሆኑትን ህጎች በስራ ላይ ማዋልን የሚጠይቅ ነው፡፡

5.3.2. የአጓዥ የተወሰነ ሃላፊነት (Limited Liabilities of air carrier)

የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን የተወሰነ ሃላፊነትን ከዓለም አቀፍ ኮንቬንሽንና የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንፃር ስንመለከት በዋርሶ ኮንቬንሽን ኋላም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በፈረመይ የ1999 ሞንትሪል ኮንቬንሽን ያለውን ካሳ የመክፈል ሃላፊነት የተወሰነ መሆንን መሰረት በማድረግ ስናየው ኮንቬንሽኑ ካስቀመጠው የካሳ መጠን በላይ ተዋዋይ ወገኖች ለመስማማት እንደሚችሉ ቢፈቅድም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 22(1) ከተደነገገው 125,000 ፍራንክ ወይም 10,000 ዶላር በታች መስማማት ግን አይፈቀድም፡፡ ይህ የካሳ መጠን በመንገደኛ ላይ የደረሰን ጉዳት መሰረት ያደረገ ሲሆን ሻንጣና ዕቃን በተመለከተ የደረሰ ጉዳት በሚኖርበት ጊዜ 250 ፍራንክ ማለትም 20 ዶላር ገደማ በጥቅል እንደሚከፈል የሚደነግግ ነው፡፡ ከፍ ብሎ የተገለፀው ለተመዘገቡ ጓዞች ወይም እቃዎች የሚያገለግል ሆኖ መንገደኛው በእጁ ለያዘው ጓዝ ወይም እቃ ደግሞ 5,000 ፍራንክ ወይም 400 ዶላር ገደማ በካሳ ሊከፈል እንደሚችል የሚወሰን ነው፡፡ ሆኖም ግን የዋርሶ ኮንቬንሽን በሰው ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም መዘግየት ከተጠቀሰው ጣርያ በላይ ሊከፈልበት የሚችልን ሁኔታም ስለሚያካትት ኮንቬንሽኑ በመርህ ደረጃ የተወሰነ ሃላፊነትን የሚከተል ሲሆን በልዩ ሁኔታ (Exception) ደግሞ ያልተወሰነ ሃላፊነትን (unlimited liability) የሚከተል መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

በአገራችን ያለው የጉዳት ካሳ አከፋፈል ኢትዮጵያ አየር መንገድ የ1999 ሞንትሪል ኮንቬንሽን የፈረመ በመሆኑ ይህ ኮንቬንሽን ደግሞ በመንገደኛ ላይ ለሚደርስ የአካል ጉዳት ወይም ሞት የሚከፈለውን የካሳ መጠን ህጋዊ ክፍያዎችን(legal fees) እና ወጪዎችን (costs) የሚጨምር ከሆነ 75,000 የአሜሪካ ዶላር እነዚህን ወጪዎች የማይጨምር ከሆነ ግን 58,000 የአሜሪካን ዶላር እንደሚከፈል ከነበረው በእጅጉ የተሻለ የካሳ ክፍያን የሚደነግግ ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ የአገር ውስጥ በረራን ወደሚገዛውና መሰረቱ የዋርሶ

ኮንቬንሽን ወደ ሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ በምንመጣበት ጊዜ ደግሞ በመንገደኛ ኣካል ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ሞት ን/ህ/ቁ 636(1) ኣጓዥ ለኣንድ መንገደኛ የሚከፍለው የካሳ መጠን ከ40 ሺ ብር መብለጥ እንደሌለበት የሚደግግ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በኣገር ውስጥ በረራና ዓለም ኣቀፍ በረራ የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ለመንገደኞች ያለው ሃላፊነት የተለያየ መሆኑን ነው፡፡ የተለያየ መሆኑ ብቻም ኣይደለም ኣሁን ባለው የውጭ ምንዛሪ በዓለም ኣቀፍ በረራ የሚከፈለው የካሳ መጠን ከግማሽ ሚልዬን ብር በላይ ሲሆን በኣገር ውስጥ በረራ የሚከፈለው 40,000 ብር መሆኑ በእጅጉ የተራራቀ የካሳ ኣከፋፈል ስርዓት ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የዋርሶ 1929 ዓ.ም ኮንቬንሽንን ያሻሻለው የ1955 ሄግ ፕሮቶኮል ኣልፈረመችም ኣላፀደቀችምም እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ይህንን ሰነድ ሳትፈርም ሳታፀድቅ እንዴት ነው ከዓለም ጋር ኣብራ እየሰራች ያለችው? የሚል ጥያቄ ነው፡፡ ዓለም ኣቀፍ በረራን በሚመለከት ኢትዮጵያ ከገበያው ያልወጣችበት ምክንያት የ1955 ሄግ ፕሮቶኮል የኣጓዥ ሃላፊነትን በማስመልከት በዋርሶ ኮንቬንሽን የተደነገጉትን ኣንቀፅ 17፣ 18 እና 19 ሳያሻሽላቸው በማለፉና ኣሁን ድረስ እነዚህ ህጎች በስራ ላይ ስላሉ ነው፡፡ የ1955 ሄግ ፕሮቶኮልን ተከትሎ የመጣው የ1999 ሞንትሪል ኮንቬንሽን ያሻሸለው የካሳ መጠኑን ስለሆነ ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ስለፈረመ ኢትዮጵያን እስካሁን ድረስ በዘርፉ የዓለም ገበያ እንድትቆይ ኣሰችሏታል፡፡

የተወሰነ ሃላፊነት (limited liability) በሚመለከት የኢትዮጵያ ንግድ ህግ የኣጓዥ ሃላፊነት በመወሰን መንገደኛን በሚመለከት በን/ህ/ቁ 636(1) የሚከፈለው ከሳ ከ40,000 ብር መብለጥ እንደሌለበት በን/ህ/ቁ 637(1) ላይ ደግሞ የጓዝ ወይም ዕቃ መጥፋት ወይም መበላሸት ሲኖር የሚከፈለው የካሳ መጠን በኪሎ ግራም ከ40.00 ብር መበለጥ እንደሌለበት የሚደነግግ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደ ኣንድ የተለየ ሁኔታ (exception) የተቀመጠ ነገር ቢኖር መንገደኛው ገና ከመጀመርያው ከኣጓዡ ጋር በዚያ ንብረት ልዩ ጥቅም ኣለኝ በሚል ስምምነት ላይ ደርሰው ከሆነ ኣጓዥ በን/ህ/ቁ 637(2) (3) መሰረት የተስማሙበትን የጉዳት ካሳ መጠን ለመክፈል ሃላፊ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 637(4) በዋርሶ ኮንቬንሽን ለውዝግብ ይዳርግ የነበረውን የጉዳት ካሳው የሚሰላው በጠፋው ጓዝ ወይም ዕቃ ክብደት ነው ወይስ በኣየር ትኬቱ ባለው የክደት መጠን የሚለው ኣከራካሪ ጉዳይ በሚቀርፍ መልኩ የሚሰላው “… የነዚህኑ ጓዞች፣ ዕቃዎች ወይም በውስጣቸው ያሉ እቃዎች ጠቅላላ ክብደት በማሰብ ነው፡፡” በማለት ስለሚደነግግ ከዋርሳ ኮንቬንሽን የተሻለ ግልፅነት ያለው ድንጋጌ ነው፡፡

ከዚህ ጋር የታይዞ የሚነሳው ጉዳይ ኢትዮጵያ የዋርሶ ኮንቬንሽንን ብቻ ተከትላ መሄዷ ወይም ለኣገር ውስጥ በረራ የንግድ ህጉን መሰረት በማድረጓ የቱን ያህል ተቀባይነት ያለው ነው? የሚል ሲሆን የዋርሶ ኮንቬንሽን በወጣበት ጊዜ የነበረው የገንዘብ ምንዛሪና ኣሁን ያለው የዋጋ ገሽበትን መሰረት ኣድርገን ብቻ እንኳን ብናየው በኢትዮጵያ ያለው የኣጓዥ

ሃላፊነት በእጅጉ ዝቅተኛ ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ ዓለም አቀፍ በረራን በተመለከተም ኢትዮጵያ አየር መንገድ የፈረመው የሞንትሪል ኮንቬንሽን በራሱ አሁን በርካታ አየር መንገዶች እሱን ውድቅ እያደረጉ ሌላ "IATA" ውልን ተከትለው የተሻለ የካሳ አከፋፈል ስርዓትን በመከተል ባሉበት ጊዜ የድሮውን ኮንቬንሽንና የሄግ ፕሮቶኮል መሰረት በማድረግ የወጣውን የኢትዮጵያ ንግድ ህግን ብቻ መሰረት በማድረግ የጉዳት ካሳ መክፈል የዘርፉን ተወዳዳሪነት ሊቀንሰው ይችላል፡፡ ስለሆነም ጊዜው የውድድር ነውና አርቆ ማሰብን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የአየር ማጓጓዣን በተመለከተ የዋርሶ ኮንቬንሽን፣ የሄግ ፕሮቶኮል ሞንትሪል ኮንቬንሽንና የንግድ ህጉን መሰረት በማድረግ ከዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን እየሰራች ያለች ስትሆን በነዚህ ህጎች ያለው የመንገደኞቹ መብትና ግዴታ ግን በየጊዜው እየተሻሻሉ ከመጡት 1955 ሄግ ፕሮቶኮል፣ የ1971 ጓቲማላ ሲቲ ፕሮቶኮል፣ የ1978 ጓዳላጃራ ፕሮቶኮል እና የ1999 ሞንትሪል ኮንቬንሽን አንፃር ሲታይ በእጅጉ ዝቅተኛ ትኩረት የተሰጠው ይመስላል፡፡

5.4. የባህር ማጓጓዣ (Carriage by Sea)

5.4.1. አጠቃላይ ገፅታው

የባህር ማጓጓዣ ህግ መቼና የት እንደተጀመረ በውል ባይታወቅም የባህር ንግድ ለዘመናት በልምዳዊ አሰራር የተመራ ስራ ላይ ያውል እንደነበር ግን አንዳንድ የዘርፉ ተመራማሪዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ለዚህም አንድ Professor Edgar Gold የተባሉ ተመራማሪ ፡-

> *The Phoenicians, Judeans, Greeks, and Etruscans, who would become the principal seafaring peoples for the next era, eventually over-shadowed the early Egyptian prominence in commercial shipping. In the last millennium B.C. in particular, the Phoenicians become the true master of the colonized Cyprus by 900 B.C, although they had trade relations with the island long before, By the beginning of the seventh century B.C, Phoenicians had settled in Spain and founded cartage in north Africa, By 600 B.C they had established trading colonies well down the Atlantic coast of Morocco.*

በማለት የአገልግሎቱ ጥንታዊነት ገልፀዋል፡፡ የባህር ጉዞ ውልን ታሪካዊ አመጣጥ በምንቃኝበት ግዜ የባህር አጓጓዥነት ውል ለመጀመርያ ጊዜ በሰነድ መዘጋጀት ሲጀምር "Book of lading" በስራ ላይ የዋለ ሲሆን ይህ አሰራር የተሟላ ይዘት ስላልነበረው ችግሮች በየጊዜው ይከሰቱ ስለነበር አጓጓዦችም ሆኑ ባለንብረቶች ሰነዱን በቅጅ መልክ እንዲዘጋጅና ድንገት አደጋ ሲያጋጥም በማስረጃነት እንዲያገለግል የደርጉ ነበር፡፡ ከ11 ክፍለ ዘመን ጀምሮም ይህን ከ"Book of lading" ጋር የሚያያዝ ሌላ ቅጠል ። "Bill of lading" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ሲገለገሉበት ቆይተዋል፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩ የባህር አጓጓዦችም ሆኑ

ጫኞች “Bill of lading” እንደንብረት ባለቤትና ማስረጃና እንደ የማጓጓጥ ውል አድርገው ሲገለገሉበት ቆይተዋል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው “Bill of lading” ሁለት ባህርያትን ይዞ ወደ የባህር ንግድ ዘርፍ ብቅ ካለ ዘመናት ያስቀጠረ መሆኑን ነው። በልምዳዊ አሰራር ሲመራ የነበረው የባህር ማጓጓጥ ውል በፅሁፍ ወደተዘጋጀ “Book of lading” ከዚያም ወደ “Bill of lading” እያደገ የመጣ ሲሆን በኢትዮጵያ የህግ ማእቀፍ ማግኘት የጀመረው በ1950ዎቹ ሲሆን ለዚህም የኢትዮጵያን የጠረፍ ጥበቃ (Ethiopian coast guard) አዋጅ ቁጥር 136/1953 እና የኢትዮጵያ የንግድ መርከቦች ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 137/1953 ካወጣችና ከዚያም በ1960 የባህር ህግ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ ነው።

5.4.2. ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of lading)

የ”Bill of lading” ትርጉም በ Hague rules፣ Hague-visiby rules ሆነ በኢትዮጵያ የባህር ህግ ኣልተሰጠበትም። የ “Bill of lading” ትርጉም የምናገኘው በ United Nations convention on the carriage of Goods by sea 1978 ወይም በሌላ አጠራር Humberg Rules እየተባለ በሚጠራው ዓለም አቀፍ ሰነድ ሲሆን በዚህ ሰነድ በአንቀፅ 1(7)ላይ፡-

> *Bill of lading” means a document which evidences a contract of carriage by the sea and the taking over or loading of the goods by the carrier, and by which the carrier under takes to deliver the goods against surrender of the document. a provision in the document that the goods are to be delivered to the order of a named person, or to order, or to bearer, constitutes such an undertaking.* በማለት የBill of lading ትርጉም ይሰጣል።

የ”Bill of lading” አገልግሎት (function) ደግሞ ባለጭነት የመርከብ ድርጅትን ይፈልግና በመርከቡ ቦታ እንዲይዝለት ያነጋግረዋል። ከዚያም ባለ መርከቡ የጭነቱን ባለቤት መቼና የት ዕቃውን ማምጣት እንዳለበት ይነግረዋል በተባለው ጊዜና ቦታ ዕቃውን እንዳመጣለት ባለመርከቡ የዕቃውን ዓይነትና ጥራት በሚረከብበት ጊዜ የነበረን የዕቃዎቹ ሁኔታ በመግለፅ ደረሰኝ ይሰጠዋል። የመርከብ ድርጅቱ እነዚህን ዕቃዎች ከተረከበበት ጊዜ ኣንስቶ ለንብረቱ መጫን ሃለፊነት ይወስዳል። በዚህም ግዜ ባለጭነቱ (shipper) ከአንዥር ወኪል የ”Bill of lading” ቅጂ ያገኛል። ከዚህ በኃላ ጫኝ ለገዥ “Bill of lading” ይልክለታል ወይም የሽያጭ ውሉ የአከፋፈል ስርዓት በ letter of credit (L/C) ከሆነ ወደ ከፋይ ባንክ ሊያቀርበውና ገንዘቡ በቀጥታ ወይም የሃዋላ ወረቀት በማውጣት ከከፋይ ባንክ ይወስዳል። ከዚያም ገዢ ወይም ተቀባይ “Bill of lading” በእጁ ከገባ እንደፈለገ እቃውን በመረከብ ወይም ገና በጉዞ ላይ እያለ ፈርሞ ወደ ሌላ ሶስተኛ ወገን ሊያስተላልፈው ይችላል። ስለዚህ የ”Bill of lading” አገልግሎት በንብረቱ ያለህን መብት የሚተካ በመሆኑ ንብረቱ በእጅህ ሳይገባ ገና በጉዞ ላይ እያለ ወደ ገንዘብ በመለወጥ ለትገለገልበት የሚያስችል ሰነድ

በመሆኑ ለፈጣን የግብይት ስርዓት ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ሰነድ የተለያዩ አገልግሎቶች ያሉት ሲሆን የተወሰኑትን ወስደን ስንመለከትም፡-

1. Bill of lading እንደ ደረሰኝ ሲያገለግል

''Bill of lading'' እንደ ደረሰኝ በሚያገለግልበት ጊዜ የዕቃውን ጥራት፣ መግለጫና ኣጓዥ ዕቃዎቹን ሲረከባቸው የነበሩበትን ሁኔታ በመግለፅ ነው፡፡ በመርከቡ ባለቤትና በእቃዎቹ ባለቤት ኣለመግባባት ቢፈጠር Bill of lading እንደ ደረሰኝ በማቅረብ መርታት ይቻላል ይሄውም

- ዕቃው በሚረከብበት ጊዜ ከቀነሰ ወይም ጉዳት ከደረሰበት
- ዕቃዎቹ የተሸጡት በ **C.I.F**.(cost, Insurance and Freight) ከሆነ ክፍያው የሚፈፀመው ሰነዶቹን በማቅረብ ስለሚሆን ገዥው በ ''Bill of lading ''ያለው መግለጫ (description) እና የሽያጭ ደረሰኝ (Sales invoice) ከቀረበው ዕቃ ጋር ኣልተጣጣመም በማለት ሰነዶቹን ውድቅ ሊያደርጋቸው ያስችለዋል፡፡
- በሰነዱና በዕቃው መካከል ልዩነት ከተፈጠረ ገዥ ''Bill of lading'' ፈርሞ ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፍ ስለሚያደርገው ''Bill of lading'' የገዥን መብት በማስጠበቅ ሂደት የበኩሉን ሚና የሚጫወት የመብት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

2. Bill of lading እንደ የማጓጓዣውል Bill of lading የተዋዋይ ወገኖችን የስምምነት ቃል የማይዝ በመሆኑ እንደማስረጃ ሊያገለግል ይችላል፡፡

''Bill of lading'' በራሱ ውል ኣይደለም ይህ የሚባልበት ምክንያትም በመርከቡ ባለቤት ወይም ወኪሉ ብቻ የሚፈረም በመሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው የማጓጓዣ ውሉ የሚደረገው በጫኝ እና መርከብ ድርጅቱ መካከል ነው፡፡ ''Bill of lading'' የሚወጣው (issued) በመርከብ ባለቤት ወይም ወኪሉ ሲሆን ይህም የሚሆነው ዕቃው በመርከብ ከተጫነ በኃላ ነው፡፡ ውሉ የተደረገበትና ''Bill of lading'' የሚወጣበት ወይም ለሻጭ የሚሰጥበት ቀን የተለያየ ሊሆን ይችላል ፡፡ ዕቃው ''Bill of lading'' ለሻጭ ከመስጠቱ በፊት በዕቃው ላይ ጉዳት ቢደርስ ወይም ቢጠፋ ቅድም ባልነው መሰረት የመርከብ ድርጅቱ ንብረቱን ከሻጭ ሲረከብ በሚሰጠው ደረሰኝ መሰረት የጉዳት ካሳ ለመጠየቅ ይችላል፡፡ አንድ ''Bill of lading'' የማጓጓዣ ውሉ ከተፈፀመ በኃላ ዘግይቶ ሊወጣ የሚችልባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም የተወሰኑትን ስንወስድ፡-

1. በመርከቡ የቦታ ጥበት ምክንያት እቃው ወዲያው ሊጫን ስለማይችልና ሳይጫን ደግሞ ''Bill of lading'' ዕቃውን ተቀብያለሁ ብሎ ማስረጃ መስጠት ስለማይቻል፡፡

2. በስራ ብዛት ምክንያት ''Bill of lading'' ላይወጣ ስለሚችልና ዕቃው ተጭኖ ባህር ላይ እያለም ዘገይቶ ሊወጣ የሚችልበት ኣጋጣሚ ያለ በመሆኑ የማጓጓዣ ውሉ (contract of carriage) እና የ''Bill lading'' መውጣት (issuarnce of Bill of lading) በተለያየ ጊዜያት ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ በሌላ አነጋገር ውሉና የውሉ ማስረጃ በተለያየ ጊዜ ሊወጡ ይችላሉ ማለት ''Bill of Lading'' በራሱ ውል አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

3. Bill of lading እንደንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ

የ''Bill of lading'' ዋና ዓላማ በሰነዱ የተወከለውን የንብረት ባለቤትነት መብት ዕቃው ገና በጉዞ ላይ እያለ መብቱን ማስገኘት ነው፡፡ ሰነዱን መያዝ ማለት ብዙውን ጊዜ ንብረቱን እንደመያዝ ይቆጠራል፡፡ ሰነዱን ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ ማለት ዕቃውን እንደማስረከብ የሚቆጠር ነው፡፡ ''Bill of lading'' እንደየሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ከአንዱ ወደ አንዱ የሚተላለፍ ቢሆንም የገንዘብ ሰነድ ግን ኣይደለም፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የተላለፈለት ሰው ካስተላለፈለት ሰው የበለጠ መብት ስለማይኖረው ነው፡፡ ለምሳሌ ሰነዱን ያስተላለፈለት ሰው ይህን ሰነድ በስርቆት ያገኘው ከሆነ ወደ ሌላው ሰው የተላለፈው በስርቆት የተገኘ የንብረት ባለቤትነት መብት ስለሚሆን ይህ ሰው ልክ በሚተላለፉ ሰነዶች እንዳለዉ አሰራር ቼኩን ፈርሞ ያስተላለፈለት ሰው መብት የሌለው ሰው ቢሆንም ይህ ሰው በመጥፎ ልቦና ሰነዱ በስርቆት የተገኘ መሆኑን እያወቀ ካልወሰደው እንደ ቅን ልቦና ሰነድ ያዥ(holder in due course) ሆኖ የመገመት መብት እንዳለው ሁሉ በ''Bill of lading'' የዚህ ዓይነት መብት ማግኘት ኣይቻልም፡፡ ስለዚህ የሰነዱ መተላለፍ የንብረቱ መብት መተላለፍ ነው ስንል Bill of lading እንደ ንብረት መተላለፍ ምልክት (symbol of transfer of possession) የሚታይ እንጂ በአንድ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ከሚኖር ማስተላለፍ ጋር እኩል ይታያል ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

''Bill of lading'' እንደ ሃዋላ ወረቀት "ላምጪው" ወይም "በስም ተለይቶ ለታወቀ ሰው "ወይም "ላዘዘለት" ተብሎ ሊወጣ ይችላል፡፡ ሰነዱ የወጣው "ላዘዘለት" ከሆነ ሊተላለፍ የሚችለው ፈርሞ በመስጠት ሲሆን በሌሎቹ አካሄዶች ያለው የመተላለፊያ መንገድ በመስጠት ብቻ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ግለፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ተለይቶ ለታወቀ ሰው የወጣ ''Bill of lading'' ኣውጪው በመስጠት ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፈው ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የኋለኛው ሰው ፈርሞም ሆነ ሳይፈርም በመስጠት ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፈው የማይችል መሆኑ ነው፡፡ ባ/ህ/ቁ 189 እና 190) በአንድ ''Bill of lading'' ያለ የሚተላለፍ መብት በብዙ ሰዎች በሚያዝበትና ክርክር በሚነሳበት ጊዜ ቅድሚያ የሚሰጠው በቅርብ ተፈርሞ ለተላለፈለት ሰው ይሆናል (ባ/ህ/ቁ 192)፡፡ በዚህ ህግ ላይ ያለው ክፍተት ግን

በአንድ ሰነድ ላይ በተመሳሳይ ጊዝያት የፈረሙ ሰዎች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖረው መብት መልስ የማይሰጥ በመሆኑ ላይ ነው።

ከባህር ማጓጓዣ ውል ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ የባህር ህግ ''Bill of lading'' መሰረት በማድረግ ከቁጥር 180-209 ባሉ ድንጋጌዎች የህግ ሽፋን የሚሰጥ ሲሆን ኢትዮጵያ እስካሁን በ1924 ዓ.ም የወጣውን የሄግ ህግንም ሆነ እሱን ለማሻሻል የወጡትን ሌሎች ህጎች አላፀደቀችም። ይሁንና የ1960 ዓ.ም የኢትዮጵያ የባህር ህግ መርሆች የሄግ ህግን (Hague Rules) መርሆችን መሰረት በማድረግ የወጣ በመሆኑ በተወሰነ ደረጃ ካልሆነ እምብዛም ችግር የሚታይበት አይደለም።

5.4.3. የአጓዥ ሃላፊነቶች

1. መርከቧን ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ

አጓዥ ካሉት ሃላፊነቶች አንዱ በባህር ለመጓዝና ለመጫን ብቁ የሆነች መርከብ የማቅረብ ሃላፊነት ነው። የማጓጓዣ አገልግሎት ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የማድረስና በጉዞ ላይ ጉዳት ሳይደርስበት በሰላም ከተፈለገው ቦታ ማድረስን ይጠይቃል። የ1924 የሄግ ህግ (Hague rules) ከመውጣቱ በፊት የመርከብ ባለቤቶች በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች በቅን ልቦና አገልግሎት ይሰጡ እንዳልነበር ከአንዳንድ መፃሕፍት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የሄግ ህግ (Hague rules) ከወጣ በኃላ ግን በአንቀፅ 19 እና ባ/ህ/ቁ 138 ላይ፡-

The carrier shall be bound before and at the beginning of voyage to exercise due diligence to

a) Make the ship sea worthy

b) Properly man, equip and supply the ship

c) Make the holds, refrigerating and cool Champers, and all other parts of the ship in which goods are carried, fit and safe for their reception, carriage and preservation.

በማለት ስለሚደነግግ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል የህግ ሽፋን እንዲያገኝና የአጓዥ ሃላፊነት በግልፅ እንዲሰፍር ተደርጓል።

2. የማስረዳት ሸክም (Burden of proof)

አንድ የመርከብ ባለቤት መርከቧ ለባህር ጉዞ ብቁ መሆንዋ የማረጋገጥ ግዴታ የራሱ ሲሆን በሃላፊነት ተጠያቂ ላለመሆን በሄግ ህግ (Hague rules) መሰረት መርከቧ Un-worthy የሆነችው በእርሱ ጥንቃቄ ጉድለት አለመሆኑን የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀው በእርሱ ላይ ነው። የኢትዮጵያ የባህር ህግ ይህን በተመለከተ አንቀፅ 139 ላይ፡-

The ship owner shall incur no liability for loss or damage results arising out of or due to, Un-sea worthiness, unless such loss or damage results from his failure to carry out his duties under art. 138. በማለት እና

በአንቀፅ 139(2) ላይ ደግሞ The burden of proof under this article shall rest with the ship owner or with any person pleading the exemption under this article.

በማለት ስለሚደነግግ የመርከብ ባለቤት ጉዳቱ የደረሰው በሱ ጥንቃቄ ጉድለት አለመሆኑን ማስረዳት ካልቻለ የጉዳት ካሳ የመክፈል ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡ የመርከቧ ለጉዞ ብቁ አለመሆን (un sea-worthiness) መሰረት በማድረግ ህብረት ኢንሹራንስ በኢትዮጵያ በመርከብ ድርጅት ላይ የመሰረተው ክስ የፌደራል የመጀመርያ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 32305 የሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት ፍ/ቤቱ በከሳሽ የቀረበውን መርከብ ለ24 ዓመት የሰራች በመሆንዋ ለባህር ጉዞ ብቁ አይደለችም፡፡ በኬሚካል መፍሰስ ምክንያት የተነሳ እሳት ነው ንብረቱን ያወደመው ወዘተ የሚሉ መካከሪያዎችን ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይህን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ለአንድ መርከብ ለባህር ጉዞ ብቁ አለመሆን 24 ዓመት በመስራትዋ ብቻ እንደ በቂ ምክንያት ሊሰውድ አይችልም፡፡ ለተነሳው የእሳት ቃጠሎ መነሻ ኬሚካል ፈሶ ወይስ ከራሷ የተነሳ እሳት የተረጋገጠ አይደለም፡፡ በደረሰው አደጋና ምክንያቱ መካከል ግንኙነት ስለመኖሩ የተረጋገጠ ነገረ የለም በማለት የተሰጠ ውሳኔ ከፍ ብለን ካየናቸው ህጎች አንፃር ከሳሽ በክስ ያነሳቸውን የመከራከርያ ነጥቦች ማስረዳት እስካልቻለ ድረስ የመርከብ ባለቤት ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት አለመኖሩን ነው፡፡

3. ጭነቱን የመንከባከብ ሃላፊነት (Duty of the carrier to take care the cargo)

ይህ ግዴታ የሚመነጨው ከህግ ሲሆን በሄግ ህግና በኢትዮጵያ የባህር ህግ በሚከተለው መልኩ ተደንግጎ የምናገኘው ነው፡፡ የሄግ ህግ አንቀፅ 3(2) “subject to the provision of article 4, the carrier shall properly and carefully load, handle, stow carry, keep care for and discharge the goods delivered.” በማለትና ባ/ህ/ቁ 196(2) ደግሞ ‘’He shall properly and carefully load, handle, stow, keep, care for and discharge the goods carried. The pronoun “he” in this case refers to the carrier.” በማለት ይደነግጋሉ፡፡ ስለዚህ አጓዥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማጓጓዝ የተረከበውን ንብረት በጥንቃቄ ይዞ ወደተፈለገው ቦታ የማድረስ ሕጋዊ ግዴታ አለበት፡፡

4. አጓዥ የማጓጓዣ ሰነድ የማውጣት ግዴታ አለበት (The carrier’s duty to issue bill of lading)

ይህን የአጓዥ ግዴታ በማስመልከት የሄግ ህግ አንቀፅ 3(3) እና ባ/ህ/ቁ 183 አጓዥ የሚጓጓዘውን እቃ በእጁ ካስገባ በኋላ በጫኝ (ሻጭ) ጠያቂነት የማጓጓዣ ሰነድ (Bill of lading) የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በግልፅ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

1. የአጓዥ Bill of lading የማውጣት ግዴታ (The carriers duty to issue a bill of lading)

ይህ የአጓዥ ግዴታ በሄግ ህግ አንቀፅ 3(3) ላይ የተደነገገ ሲሆን ባ/ህ/ቁ 181 እና 183 ላይም መሰረታዊ ልዩነት በሌለው መልኩ የተደነገገ ቢሆንም በመርህ ደረጃ ግን በተጠቀሱት ሕጎች ተካቷል። አጓዥ እቃዎቹን ከተረከበ በኋላ በሻጭ ወይም ባለንብረቱ ወይም ወኪሉ ጠያቂነት የBill of lading መስጠት ይኖርበታል። በሁለቱም ህጎች ያለው ልዩነት Bill of lading በመስጠት ላይ ሳይሆን ልዩነቱ የሚመሰረተው የሄግ ህግ አንቀፅ 3(3) በሻጭ ጠያቂነት (on demand of the shipper) የሚል ሓረግን ሲጠቀም የባ/ህ/ቁ 181 ግን በሻጭ ጠያቂነት Bill of lading የሚወጣ ወይም የሚሰጥ ስለመሆኑ የሚለው ነገር ያለመኖሩ ላይ ነው። በእነዚህ ድንጋጌዎች መካከል የሚስተዋል ሌላው ልዩነታቸው የሄግ ህግ አንቀፅ 3(3) Bill of lading ዝርዝር ሁኔታዎች መያዝ ያለበት ስለመሆኑ የሚለው ነገር የለሌ ሲሆን የባ/ህ/ቁ 182 በ183 ላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ አንድ 'Bill of lading' መያዝ ስላለበት ዝርዝር ነገር ማለትም፡-

- የአጓዥ ስምና አድራሻ
- የሻጭ (ንብረት ባለቤት) ስምና አድራሻ
- የመርከቧ ስምና አድራሻ
- የመድረሻ ቦታና በውል ለታወቀ ሰው የወጣ 'Bill of lading' ከሆነ የተቀባዩ ስም
- አጓዥ የተረከባቸው ዕቃዎች ዝርዝር
- የተጫነበት ቦታና ቀን
- የመጫኛው ግንዘብ ልክ መግለፅ ያለባቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚስተዋል ልዩነት ነው።

የሄግ ህግ አንቀፅ 3(4) (5) ከባ/ህ/ቁ 186 ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ''Bill of lading'' ተሰጠ ማለት በሰነዱ የተዘረዘረውን ንብረት ተረክቤአለሁ ማለት ስለሆነ ሰነዱን መያዝ ብቻውን ያለ ቅድመ ሁኔታ በሰነዱ መሰረት የመረከብ መብትን የሚያስገኝ ነው። በተጫነው ዕቃና ሰነዱ ልዩነት ነበር የሚል ከሆነ የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀው በአጓዥ ላይ ነው። ሻጭ የዕቃዎችን ምልክት፣ ቁጥር፣ ጥራት፣ ተፈጥሮና ክብደት በተገቢው መንገድ ሳይገልፅ በመቅረቱ ምክንያት በዕቃው ላይ መጥፋት ወይም መጎዳት ሲደርስ ግን ሃላፊነቱ የሚወድቀው በሻጭ (shipper) ላይ ነው። ስለዚህ የባህር ማጓጓዣ አገልግሎት በሻጭ፣ አጓዥ ወይም የመርከብ ባለቤት ላይ በርካታ ሃላፊነትን የሚጥል ሲሆን የግንኙነቱ ማስረጃ ተደርጎ የሚወሰደው "Bill of lading" እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። አጓዥ ሃላፊነት ያለበት የመሆኑ ያክል በህግ ከሃላፊነት ነፃ የሚሆንባቸው ሁኔታዎችም በሄግ ህግ አንቀፅ 4(2) እና ባ/ህ/ቁ 197(1) ላይ በዝርዝር ተደንግገዋል። አጓዥ በነዚህ ህጎች ከተዘረዘሩት አንዱን በመከራከርያነት አቅርቦ ማስረዳት ካልቻለ ግን ለንብረቱ ባለቤት ካሳ የመክፈሉ ግዴታ የማይቀር ነው። አጓዥ እቃውን ለተቀባይ ካደረሰለት በኋላ ተቀባይ የመጣው ዕቃ በሰነዱ

መሰረት መሆኑን ማረጋገጥና ችግር ያለበት ነው ካለ በሄግ ቪዝቢ ህግ አንቀፅ 3(6) መሰረት በሶስት ቀን ውስጥ ለአጓዥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህን ካላደረገ ግን እቃው በሰነዱ መሰረት በጥሩ ሁኔታ እንደደረሰ ይገመታል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ካስታወቀው ግን በማስታወቅያው በተገለፀም ሁኔታ ዕቃው እንደደረሰ ይገመታል፡፡ ይህም ማስታወቅያ በሄግ ቪዝቢ ህግ አንቀፅ 3(6) መሰረት በፅሁፍ ተዘጋጅቶ ለአጓዥ ወይም ወኪሉ መስጠት ኣለበት፡፡ በባ/ህ/ቁ 201 መሰረት ማስታወቅያው መስጠት ያለበት ንብረቱ ወደ ሌላ ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ሳይሆን በርክክቡ ጊዜ (upon delivery) መሆን ይኖርበታል፡፡

5.4.4 የሃላፊነት ወሰን (Limitation of liability)

የአጓዥ ሃላፊነት እንዲወሰን የተደረገው ባለመርከቦችን ለማበረታታትና በስራው ላይ እንዲቀጥሉ ለማስቻል ነው፡፡ ይህ አሰራር እስካሁን ድረስ አጓዥን በሁለት መንገዶች እየጠቀመ ያለ አሰራር ነው፡፡ ይሄውም በከፍተኛ ደረጃ ዋጋቸው ለማወቅ የሚያስቸግሩ እቃዎች ቢጎዱ የሚከፈለው የካሳ መጠን ኣስቀድሞ የታወቀ በመሆኑ እንዳይቸገር ያስችለዋል፡፡ በሌላ በኩልም አጓዥን ለመደገፍ ሲባል በህግ እውቅና የተሰጠው አሰራር በመሆኑ አጓዥ በዚህ መንገድ ጥቅሙን እንዲያስጠብቅ የሚያስችለው ነው፡፡ በዚህም መሰረት በባህር ማጓጓዥ ህግ ላይ በርካታ ገደቦች (Limitations) ተጥለው እናገኛለን፡፡

ከሃላፊነት ነፃ መሆንና የጥቅል ወሰን (Exemption from any liability and package limitation) አጓዥ በሄግ ህግ አንቀፅ 4(2) እና ባ/ህ/ቁ 197(1) መሰረት በነዚህ ህጎች በተዘረዘሩ ምክንያቶች ለሚደርስ ጉዳት ሃላፊ ኣይደለም፡፡ እንደዚሁም የኢትዮጵያ የባህር ህግ ስለዚህ ጉዳይ የሚለው ነገር ባይኖርም በሄግ ህግ አንቀፅ 4(4) መሰረት አንድ አጓዥ የሰውን ሂወት ከአደጋ ለመታደግ ሲል ባጋጠመ ጥፋት ምክንያት በንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስ ለደረሰው መጥፋት ወይም መጎዳት ሃላፊ ኣይደለም፡፡ እንደዚሁም አጓዥ በሄግ ህግ 4(5)(4) እና ባ/ህ/ቁ 185 መሰረት ሻጭ (shipper) እያወቀ የጓዙን ምንነት በመደበቅ እንዲጫን አድርጎ በጉዞ ላይ ንብረቱ ቢጎዳ አጓዥ ሃላፊነት የለበትም፡፡ እነዚህ ህጎች በ1978 ዓ.ም Hamburg rules ውስጥ ኣልተካተቱም ያልተካተቱበት ምክንያት አጓዥ ሃላፊ የሚሆነው ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሲኖረው ብቻ በመሆኑ ተዘረዘሩ አልተዘረዘሩ የሚያመጣው ለውጥ የለም በሚል የተተው ናቸው፡፡ አጓዥ ከፍ ብለው በተዘረዘሩት ህጎች ስር በሚወድቅ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ወይም መጥፋት ሃላፊ እንደማይሆን ሁሉ ከነዚህ ሁኔታዎች ውጭ በሆነ ምክንያት በንብረት ላይ ጉዳት ቢደርስ ወይም ቢጠፋ ደግሞ ሃላፊ እንደሚሆን የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም ግን አሁንም አንድ ሃላፊነቱን የሚገድብበት በህግ እውቅና የተሰጠው አሰራር ኣለው፡፡ ይሄውም ለአንድ ጥቅል የሚከፈል ጉዳት ካለ የተወሰነ መሆን (Package limitation) በመባል የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ መብት ያለ ልዩ ሁኔታ (exception) ለአጓዥ የተሰጠ መብት በመሆኑ በሄግ ቪዚቢ ሕግ (Hague visby Rule) አንቀፅ 4(5) (a) እና ባ/ህ/ቁ 198 (3) መሰረት በልዩ ሁኔታ የpackage limitation

መከራከርያ በማንሳት ግዴታውን ውሱን እንዳያደርግ የተገደበ መብት ነው ያለው፡፡ አጓዥ ሃላፊነቱን በጥቅል መወሰን የሚችል መሆኑንና በጥቅልም ስንት መክፈል እንዳለበት በሄግ ህግ አንቀፅ 4(5) መሰረት 100 የእንግሊዝ ፓውንድ ሰተርሊንግ እንደሆነና ባ/ህ/ቁ 198(1) መሰረት 1000 የኢትዮጵያ ብር መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህም በመሆኑ ከፍ ብሎ በተገለፀው ልዩ ምክንያት (exception) ካልሆነ በስተቀር አጓዥ በዚህ መብቱ ተጠቅሞ የሚከፍለውን የጉዳት ካሳ መጠን የተወሰነ (limited) እንዲሆን ለማድረግ ይችላል፡፡

5.4.5 ስለ ይርጋ

በባህር ማጓጓዥ የደረሰን የዕቃ መጥፋት ወይም መጉዳት ምክንያት የሚቀርብ ክስ በሄግ ህግ 6(4) እና ባ/ህ/ቁ 203 መሰረት እቃውን በተረከበ በአንድ ዓመት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ የባህር ህግ የእንግሊዝኛው ቅጂ

1. *The rights arising out of carriage shall be barred after one year from the delivery of the goods and, where the goods have not been delivered, from the day when they should have been delivered.*
2. *In the case of recovery of payment made by mistake, the period shall from the date of payment and, for proceedings by way of recourse from the date of the introduction of the main action.*

በማለት ስለሚደነግግ የይርጋ አቆጣጠር ስርዓቱ ከፍ ብሎ በተገለፀው ድንጋጌ መሰረት የሚመራ ነው፡፡ ይህን ለመወሰን ደግሞ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት መኖሩ የግድ ነው፡፡ የፍ/ቤት ስልጣን በክስ የሚጠየቀውን የገንዘብ መጠን መሰረት ያደረገ ስልጣን (material jurisdiction)፣ የአካባቢ ስልጣን (Local jurisdiction) ሊሆን ይችላል፡፡ በኛ አገር የህግ ማእቀፍ የባህር ማጓጓዣን መሰረት በማድረግ የፍ/ቤት ስልጣን ስንመለከት በኢትዮጵያ የባህር ህግ፣ ፍታብሄር ስነ-ስርዓትና የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት በወጣው Bill of lading ተዘርዝሮ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህም የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 15፣ የባ/ህ/ቁ 208 እና በኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት በወጣው ''Bill of lading'' ላይ ያለውን "the contracts evidenced by this bill of lading shall be governed by the law of Ethiopia and any dispute arising here under shall be determined by the Ethiopia courts according to that law to the exclusion of the jurisdiction of the courts of any other country." በማለት የሚያትተውን መመልከት ይቻላል፡፡ ከፍ/ቤት ስልጣን ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የሚነሳው አከራካሪ ጉዳይ የኢትዮጵያ ባህር ህግ የወጣው በ1960 ዓ.ም በመሆኑና ያኔ ኢትዮጵያ የአሰብና ማሳዋ ወደቦች ባሉት ጊዜ የወጣ በመሆኑ አሁን ምንም ወደብ የሌላት አገር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ሲታይ የባ/ህ/ቁ 208 ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችል ህግ አይደለም የሚል ነው፡፡ የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር 1/1996 ቢሆንም በአንቀፅ 4 ላይ የመርከብ ምዝገባ የሚከናወነው በአዲስ አበባ መሆኑን

ስለሚደነግግ ከባህር መጓጓዣ ውል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዬች መዳኘት ያለባቸው ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 15 በሚደነግገው ሳይሆን በፊደራል ፍ/ቤቶች ብቻ ነው የሚል የመከራከርያ ሃሳብ ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡ እነዚህ መከራከርያዎች መነሳት የሌለባቸው ሓሳቦች ናቸው ባይባልም ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 15(ለ) የሚደነግገው የመዳኘት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/88 የፌደራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ሲዘረዝር ይህን በሚሸር መልኩ የወጣ ህግ እስካልሆነ ድረስ ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 15(ለ) አሁንም በስራ ላይ ያለ ህግ ነው፡፡ የባህር አዋጅ ቁጥር 137/1953 ቢሆንም ከዚህ ጋር የሚቃረን ሃሳብ የለውም፡፡ በመሆኑም ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 15(ለ) በስራ ላይ ያለ ህግ ነው ብሎ መከራከር የተሻለ ተአማኒነት ያለው መከራከርያ እንዲሆን የሚያደርገው ነው፡፡ ባ/ህ/ቁ 208 በሚመለከት ህጉ "The consignee or the shipper may bring proceeding against the carrier at the port of arrival of the goods where such port is in Ethiopia." በማለት ስለሚደነግግና አሁን ደግሞ የራስዋ ወደብ ስለሌላት ይህን ህግ ተፈፃሚ ለማድረግ አይቻልም የሚለው መከራከርያ ከህጉ ተፈፃሚነት አንፃር ብቻ ካየነው የሚያስኬድ መከራከርያ ሊመስል ይችላል፡፡ ሆኖም ህን መታየት ያለበት ከፍ/ቤት የመዳኘት ስልጣንም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች የባህር ማጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ ክስ ሲቀርብ ለመዳኘት ስልጣን የላቸውም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የባህር ማጓጓዣ ውል እንደሁሉም ልዩ ውሎች የራሱ የሆነ ባህርያትና አፈፃፀም ያለው በመሆኑ የራሱ ህግ ወጥቶለት የአገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ፈጣን ዘላቂና ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርገውን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ያለ ህግ በመሆኑ ሰልጣኞች ይህን የማጓጓዣ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመራበትን ህግ በሚገባ ተገንዝበው በስራ ላይ ሊያውሉት ይገባል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በየብስ ለሚደረግ ጉዞ የሚደረግ የማጓጓዣ ውል የሚደረገው ከትኬት ቆራጩ ጋር ነው ወይስ ከህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤት ጋር? ለምን?
2. የላኪውና ተቀባይ መብትና ግዴታዎች ምንድን ናቸው?
3. በየብስ የማጓጓዝ ስራ የአጓዥ ሃላፊነቶች ምንድን ናቸው?
4. አቶ አበበ ከጀርመን ፍራንክፈርት የለፍታንዛን አየር መንገድ ተጠቅመው ዱባይ እንደደረሱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተቀብሎ ቦሌ አውሮፕላን ማረፍያ ሲደርሱ የተመዘገበ ሻንጣቸው ሲፈለግ ጠፍቶ ቢገኝ መክሰስ የሚችሉት ለፍታንዛ አየር መንገድን ወይስ የኢትዮጵያ አየር መንገድን? ለምን?
5. በአየር ማጓጓዣ የላኪና ተቀባይ መብቶች ምንድን ናቸው?

6. በኣየር ማጓጓዥ የኣጓዥ ሃላፊነቶችስ ምንድን ናቸው?
7. አቶ ዘመነ በኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ተሳፍሮ ለጉብኝት ኣክሱም እየሄደ ሳለ ኣውሮፕላኑ ለማረፍ ወደታች ዝቅ ሲል ድንገት ከፍተኛ የሆነ የጀሮ ህመም ኣጋጥሞት ከወረደ በኃላ ታክሞ ሊድን ባለመቻሉ መስማት የተሳነው ቢሆን ኢትዮጵያ ኣየር መንገድን ካሳ እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላልን?ለምን?
8. በ"letter of credit" ግዥና "Bill of lading" መካከል ያለው አሰራር ምንድን ነው?
9. የባህር መጓጓዣ ውል ቀሪ የሚሆነው እንዴት ነው?
10. በንግድ ወረቀቶችና Bill of lading መካከል ያሉት ተመሳሳይነትና ልዩነቶች ምንድን ናቸው?

6. የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች

6.1. ስለሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በጠቅላላ

ንግድ እንደሁሉም የህብረተሰብ እድገቶች(human evolutions) ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመምጣቱን ያህል የሚተላለፉ ገንዘቦችም የግብይት ስርዓቱን ቀልጣፋና አስተማማኝ ለማድረግ አሰራራቸው ጊዜው ከሚጠይቀው የእድገት ደረጃ ጋር እየተሻሻሉና ሞቹ እየሆኑ እንደመጡ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ የሚተላለፉ ገንዘቦች ታሪክ ከሰው ልጆች ማህበር ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ሲሆን ከጋዬሽ ስርዓተ ማህበር ወጥተው የምርት ክፍፍል ስርዓቱና የኣመራረት ስልቱ እየተለወጠ በመምጣቱ መጀመርያ አንድን ዕቃ በዕቃ በመለወጥ ግብይት ያከናውኑ የነበሩ ሰዎች ከኢኮኖምያዊ እድገታቸው ጋር የሚመጥን የኣስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ጥሬ ገንዘብ ተጠቅሞ ወደ መገበያየት ተሸጋግረው ለዘመናት በዚህ መልኩ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ እየተገለገሉ ከቆዩ በኃላ ለመጀመርያ ግዜ የሚተላለፍ ገንዘብ ሰነዶች በጣልያን ነጋዴዎች በስራ ላይ መዋሉና በኣውሮፓ ክፍለ ኣህጉር ይገለገሉበት እንደነበር አንዳንድ የታሪክ ፀሃፍት ያስረዳሉ፡፡ አሁን በውል ከሚታወቁት የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ቀዳሚ ሆኖ የወጣው ከአገር ውጭ የሚያገለግል የሃዋላ ወረቀት (Foreign bill of exchange) እና የተስፋ ሰነድ በሰራ ላይ ሊውሉ ችለዋል፡፡ በ17ኛው ክፍለ ዘመን እነዚህ ሰነዶች በእንግሊዝ አገርም በስፋት ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን በ1882 የሃዋላ ወረቀት ህግን (act) አውጠታለች፡፡ በኣሜሪካ በጠበቆች ማህበር (ABA) አማካይነት

ተመሳሳይ ህግ እንዲያወጣና ከሌሎች አገሮች ጋር የግብይት ስርዓቱን ተከትሎ እንዲሰራበት ሓሳብ ቀርቦ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ታሪክን ስንቃኝ ደግሞ Professor Escarra የ1960 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግድ ህግን ረቂቅ ሲያዘጋጁ የAnglo-Saxon የህግ ስርዓትን ተከትለው Uniform law የማይፈቅደውን የሃዋላ ወረቀት 'ሳምጪው" (Bearer bill of exchange) በኢትዮጵያ ንግድ ህግ በቁጥር 719-721 እና 746(1) ላይ እንዲፈቀድ በሚያስችል መልኩ ያዘጋጁት ሲሆን በኣህጉራዊ ኣውሮፓና ኮመንሎው አገሮች እምብዛም ልዩነት የማይታይበትን የንግድ ወረቀቶች አሰራርን መሰረት በማድረግ በኣሜሪካ ሲሰራበት የነበረውን የተለያየ የኣፈራረም ስርዓት (modes of endorsement) በመከተል የኢትዮጵያ ንግድ ህግም ይህን በን/ህ/ቁ 724-730፣ 746-756 እና 842-852 ባሉ ድንጋጌዎች ስር እንዲካተት ኣድርገዋል፡፡ የህጉ ረቂቅ ሲወጣ በን/ህ/ቁ 731 ሆነ ተብለው በተበላሸ፣ በጠፋ ወይም በተሰረቁ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ምክንያት ሊነሳ የሚችለውን የክርክር ስርዓት በህግ ይወሰናል በማለት ያለፉት ሲሆን በፈረንሳይ የሃዋላ ወረቀት ህግ ላይ የነበረውን አስገድዶ የሃዋላ ወረቀት እንዲቀበል ማድረግንም ከአገራችን ንግድ ህግ እንዲወጣ ኣድርገው ቀርፀውታል፡፡

በዚህ ምትክ በን/ህ/ቁ 766-768 ባሉ ድንጋጌች በባንኮች ተቀባይነት ያገኘን ለመክፈል በዋስትና እሺ የማለት (acceptance for honour) ኣሰራርን በህጋችን ስር እንዲካተት ኣድርገዋል፡፡ ሌላ በህጋችን የተካተተ ክፍት የሃዋላ ወረቀት የማውጣት አሰራር ከጣልያንና እንግሊዝ የሃዋላ ወረቀት ህጎች በመውሰድ በን/ህ/ቁ 744 እና 749(1) እንዲካተት የተደረገ ሲሆን በፈረንሳይ የሃዋላ አገልግሎት ውጤታማ የሆነን በሃዋላ ወረቀት የሚገደዱት ዋሶች የሚንቀሳቀስ ንብረት በጥበቃ ስለመያዝ (sequestration) አሰራርን በን/ህ/ቁ 798 ላይ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በቅን ልቦና ሰነድ የያዘ ሰውን በሚመለከት የረቂቁ ኣዘጋጅ ከእንግሊዝ ህግ የተሻለ ነው ያሉትን የuniform law ሃሳብን ማለትም ሰነዱ የወጣው ለዋጋ (for consideration) መሆኑን ከግምት ውስጥ የማያስገባውን ህግ መሰረት በማድረግ በን/ህ/ቁ 718 እንዲካተት ኣድርገዋል፡፡

የሃዋላ ወረቀትን በተመለከተ በሚወጣበት ግዜ በን/ህ/ቁ 801 እንደተደነገገው በቂ ስንቅ (cover) መኖሩን እንደመስፈርት ሳይወሰድ ማስተላለፍ በሚቻልበት መንገድ በፈረንሳይ ህግ ካለው ኣካሄድ በተለየ መልኩ እንዲቀረፅ ኣድርገዋል፡፡ ሌላው አርቃቂው የተከተሉት ኣካሄድ በሃዋላ ወረቀትና በቼክ መካከል ያለውን አሰራር በእንግሊዝ ህግ ካለው አሰራር በተለየ መልኩ በተለያየ ህግ እንዲገዛ በሚያስችል መልኩ እንዲዘጋጅ በማድረግ ህግ ሆኖ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በእጅጉ ጠቃሚ የሆኑትን ን/ህ/ቁ 735-822፣ 825-826 እና 827-886 ድንጋጌዎች ከዓለም ኣቀፍ የ1930 እና 1931 የሃዋላ ወረቀት ኮንቬንሽን እንዳለ የተወሰዱ ድንጋጌዎች ሲሆኑ

ከን/ህ/ቁ 887-890 እና 891-895 ያሉት ድንጋጌዎች ከጣልያን የፍ/ብሄር ህግ በመውሰድ የተቀረፁና ቀደም ብለን ካየናቸው ድንጋጌዎች በተለየ በProfessor Alfred Jauffret የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ትርጉምና በምንመለከትበት ጊዜም፤-

1. የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ማለት መብቱ ከሰነዱ ተለይቶ ሊሰራበት ወይም ሊተላለፍ የማይችል የአገልግሎት መብት ያለበት ሰነድ ሁሉ ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 715(1)
2. *Negotiable Instruments are documents of a certain type used in commercial transactions and monetary dealings.*
   - ❖ *Negotiable means transferable by delivery and instrument means a written document by which a right is created in favor of some person (Indian commercial act)*
3. *Negotiable Instrument means an unconditional promise or order to pay a fixed amount of money, with or without interest or other charges described in the promise or order. (UCC)* የሚል የተለያየ ትርጉም ተሰጥቶት የምናገኘው ነው

በን/ህ/ቁ 715 (2) መሰረት የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የሚባሉት፤-

ሀ) የንግድ ወረቀቶች

የሃዋላ ወረቀቶች ን/ህ/ቁ 732-822
የተሰፉ ሰነድ ን/ህ/ቁ 823-826
ቼኮች ን/ህ/ቁ 827-895

በዕቃ መጋዘን የተቀመጡ ዕቃዎች የምስክር ወረቀቶች ፍ/ብ/ህ/ቁ 2813-2824

ለ) የግዴታ ምስክር ወረቀቶች

አክስዮኖች ወይም የአክስዮን ሰርተፊኬቶች ን/ህ/ቁ 340, 341
ለሞት ጊዜ የተገባ የመድን ፖሊሲ ን/ህ/ቁ 660, 669 (4)
የግዴታ ወረቀቶች (debentures) ን/ህ/ቁ 429

ሐ) የሸቀጦች ማረጋገጫ ሰነዶች (Documents of title) ን/ህ/ቁ 561- 663

- Bills of Lading
- Air way bills
- Rail way bills
- Truck way bills. የመሳሰሉት ናቸው፡፡

6.2 የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ በቅን ልቦና ስለ መያዝ (Holder in due course)

የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድን በቅን ልቦና የያዘ (holder in due course) **የሚባል ሰው ማን ነው? የሚለውን ለመመለስ ን/ህ/ቁ** 751(2) **ስንመለከት ሰነዱን በእጁ ያስገባው በመጥፎ ልቦና ካልሆነ በስተቀር ወይም ሰነዱን በእጁ ሲያስገባ የሰራው ጥፋት ከሌላ የሰነዱ ባለቤት እሱ መሆኑ የመገመት መብቱን ተጠቅሞ ሰነዱ በሚያስገኘው መብት ሊሰራበት የሚችል ሰው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህ መብት በን/ህ/ቁ** 718 **በህግ እውቅና የተሰጠው መብትም ነው።**

የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ በቅን ልቦና የያዘ ሰው (holder in due course) **ማንነትን ወይም ትርጉምን ስናይ ድግሞ፡-**

A holder in due course is a holder who has taken a bill of exchange complete and regular on the face of it under the following conditions, namely፡-

a) That he becomes the holder before it was over due and with out notice that it had been previously dishonored if such was the fact.

b) That he took the bill in good faith and for value and that at the same time the bill was negotiated to him he had no notice of any defect in the title of the person who negotiated it (Borrie, Gordon J. 1962. P.130) **የሚለው ትርጉም ተሰጥቶት የምናገኘው ሲሆን ሌላ የዘርፉ ተመራማሪም የህንድን ህግ መሰረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ገልፀውታል።**

- *Holder in due course is a particular kind of holder. The holder of a negotiable instrument is called the holder in due course if he satisfies the following conditions.*
    1. *He obtained the instrument for valuable consideration*
    2. *He be came the holder of the instrument before its maturity. That is before the amount mentioned in it be came payable.*
    3. *He had no cause to believe that any defect existed in the title of the person from whom he derived his title.*

  It is clear that a person can not be a holder in due course

    a. *If He has obtained the instrument by gift or for an lawful consideration or by illegal methods.*
    b. *If he has obtained the instrument after its maturity*
    c. *If the circumstances are such that a reasonable person would suspect that the title of the transferor is defective. (Indian commercial act. Sec. 9)*

የአንድ ሰው በቅን ልቦና ሰነዱን የያዘ መሆን የሚያስገኝለት ብቶችም፡-

- ሰነዱን በእጁ ያስገባው በቅን ልቦና መሆኑ የመገመት መብት፣
- ወደ እርሱ ከመተላለፉ በፊት የነበረውን ጥፋት መሰረት በማድረግ በእርሱ መብት ላይ የሚፈጠር ተፅእኖ የሌለ መሆን፣
- በክፍት ሰነድ (blank bill) ላይ ሲሞላ ለተፈጠረው ልዩነት ተጠያቂ ያለመሆንና በዚህ ምክንያት መብቱ የማይነካ መሆኑ፣
- የኣውጪው ወይም ተከፋይ በሀግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት መሆን በእርሱ መበት ላይ የሚፈጥረው ችግር ኣለመኖር
- ከእርሱ የተቀበለ ሰው ከዚያ በፊት በሰነዱ ችግር እንዳለበት እያወቀ ቢወስደውም በቅን ልቦና ሰነድ ያዥ ላይ የሚፈጥረው ችግር ኣለመኖሩ ከሚጠቀሱት ጥቅሞች ጥቂቶቹ ናቸው።።በቅን ልቦና ሰነድ የያዘ ሰው ማነው? በሚለው ረእሰ ጉዳይ ዙርያ በኛ አገር ህግም 868፣ 871 ን/ህ/ቁ 718፣ 751/1/፣ 825/1/ /ሀ/፣ 847 ተደነግጎ የምናገኘው ነው።።

6.3 የሚተላለፍ የግንዘብ ሰነዶች ዋና ገፅታዎች (Basic features)

1. ፊርማ (endorsement)

በሚተላለፉ የግንዘብ ሰነዶች ፊርማ ሲባል ኣውጪው ወይም በሰነዱ ጀርባ የሚሳርፈው ፊርማ (endorsement) ሲሆን ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሰነዱ መፈረም ያለበት ያለሃተታ ነው።። ለዚህን ን/ህ/ቁ 748(1) እና 843(1) በግልፅ የሚደነግጉ ሲሆን ከሚኖራቸው ህጋዊ ውጤት አንፃር ሲታዩም ላምጪው ብሎ መፈረም (endorsement to bearer) እና በባዶ መፈረም (endorsement in blank) ውጤታቸው ተመሳሳይ ነው።። (ን/ህ/ቁ 725(3)፣ 747(3) እና 845(3)

2. ሰነዱን መስጠት (Delivery)

አንድ የሚተላለፍ የግንዘብ ሰነድ በእጁ ያለ ሰው ሰነዱን ወደ ሌላ ለማስተላለፍ የግንዘብ ሰነድ ላይ መፈረም በራሱ በቂ ኣይደለም።። በሰነዱ ያለውን የግንዘብ መበት ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ ከተፈለገ ሰነዱን መስጠት ይጠበቅበታል።።

3. እሽታ (Acceptance)

አንድ የሃዋላ ወረቀት ኣውጪ (drawer) በሰነዱ የተገለፀውን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜው ሲደርስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመክፈል እሺታ ሊሰጥ ይችላል።። ይህ የእሽታ ዋስትና በኣውጪው ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ሊሰጥ ይችላለ።። (ን/ህ/ቁ 764፣ 766 እና 768)

4. ለክፍያ ማቅረብና የእምቢታ ማስታወቅያ (presentment for payment and protest for Recourse)

አንድ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ የመክፈያ ጊዜው በመድረሱ ወይም ለክፍያ ቀርቦ "እምቢታ" ካጋጠመው ሰነዱን በእጁ ያስገባ ሰው የእምቢታ ማስታወቅያ በን/ህ/ቁ 788 እና

870 መሰረት በማሰራት በሰነዱ አስተላላፊዎች ላይ በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሰረት ክስ በማቅረብ መብቱን ማስጠበቅ ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 780-797 እና 825(ሐ)፣ 868፣ 873-875) በዚህ መንገድ ተጠይቆ ክፍያ የፈፀመ ወገን በሌሎች ፈራሚዎች ላይ ክስ በማቅረብ የሚከተሉት ድንጋጌዎች የሚያስገኙለትን ህጋዊ መብቶች ለማስጠበቅ ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 781-791፣ 825(መ)፣ 869-871) ከሃላፊነት ነፃ መሆን (Discharge) በሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች ውል የገቡ ወገኖች ካላቸው ሃላፊነት ነፃ መሆን የሚችሉባቸው በርካታ መንገዶች ያሉ ቢሆንም የተወሰኑትን የወሰድን እንደሆነ፡-

- ሰነዱን በመሰረዝ (By cancellation)
- በሌላ ውል ባለግዴታውን ከግዴታው በማስወጣት (by release)
- በመክፈል (by payment)
- የተረጋገጠ እሺታ በመስጠት (by qualified acceptance)
- የአንድን ቼክ የመክፈያ ጊዜ በማዘግየት (by delaying in presenting the cheque)
- ሰነዱ በመተላለፊያ መንገዶች ተመልሶ ወደ እሺ ባዩ ሲመጣ (by negotiation back) ናቸው፡፡

5. ከሌላ ሰነድ የሚለዩበት ባህሪ

የሸቀጦችና አገልግሎቶች ግዥና ሽያጭ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን ተጠቅሞ ለማከናወን ጅምላ ጮችና ገዥዎች ለዘመናት ሲገለገሉባቸው ቆይተዋል፡፡ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መብት ምንጭ ውል ሲሆን ከጠቅላላው ውል የሚለይባቸው ባህርያት ግን በጠቅላላው ውል ተዋዋይ ወገኖች ሊያነሱዋቸው የሚችሉ የመብት ጥያቄዎች

- ገንዘብ እንዲከፈለው መጠየቅ
- በንብረቱ ያለውን መብት እንዲተላለፍለት መጠየቅ
- ተዋዋዩ ወገን ተገዶ አገልግሎቱን እንዲሰጠው ማስገደድ
- አንድ ነገር ወይም ከዚያ በላይ እንዲፈፀምለት ወይም ከመፈፀም እንዲታገድለት

መጠየቅ ሲሆኑ በሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች እንዲፈፀምለት መጠየቅ የሚችለው አንድና አንድ ብቻ ሆኖ እሱም ገንዘብ (money) እንዲከፈለው መጠየቅ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር የሚተላለፉ ገንዘቦች የራሳቸው ባህሪ ያላቸው በመሆናቸው ከነዚህ ጋር የሚመደቡ እንደ ‘’Bill of lading’’ እና የመጋዘን ወረቀቶች (Ware house receipts) ያሉ ሰነዶች ቢኖሩም እነዚህ የሚያስገኙት መብት ገንዘብ እንዲከፈለው መጠየቅን ሳይሆን የእቃው ማስረከብን (delivery of goods) ስለሆነ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እንደሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች ከሚታዩት የንግድ ወረቀቶች (Commercial papers) የተለየ ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ውል ከጠቅላላ ውል የሚለዩባቸው ሁኔታዎችም፡-

- በጠቅላላ ውል የሚሰጥ የተስፋ ቃል በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ሲችል በሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የሚሰጥ የተስፋ ቃል ወይም ትእዛዝ ግን በሁኔታ ላይ የማይመሰረት (unconditional) ነው፤፤
- በጠቅላላ ውል መሰረት ውሉ የሚፈፀምበት እርግጠኛ በመሆን በተወሰነ ጊዜ (fixed with certainty) ወይም እርግጠኛ ላልሆነ ጊዜ (Uncertainty of time) ሊመሰረት የሚችል ሲሆን የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን መሰረት በማድረግ የሚደረግ ውል ግን ክፍያ የሚፈፀምበት ጊዜ እርግጠኛ (certain) መሆንን የሚጠይቅ ነው፡፡
- በጠቅላላ ውል በውሉ የተገኘውን መብት ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፍበትን መንገድ (assignment of right) የማይገልፅ ሲሆን በሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ግን "ክፍል ለታዘዘለት "ወይም ላምጭው " የሚለ መግለጫዎችን የሚጠቀሙ በመሆናቸው የመተላለፊያ መንገዱን (negotiability) በግልፅ የያዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መብት መሰረቱ ውል ቢሆንም ልዩ ውል እንደመሆኑ የተለዩ የራሱ ባህርያት ያሉትና በልዩ ህግ የሚገዛ የውል ዓይነት ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች አገራችን እየተከየላቸው ያለውን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲና እስትራቴጂ ከግብ ለማድረስ ነጋዴው ማህበረሰብ በእነዚህ ሰነዶች በመገልገል የሚፈጥሩለትን ሞቹ የግብይት ስርዓት ተጠቅሞ ለዘላቂ ልማት በእጅጉ በርትቶ ሊሰራና የአገሪቱን መልካም ገፅታ በመጠበቅ የንግድ ስርዓቱ ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ሁሉ እኛም ተገንዘብ ሰነዶችን የዝውውር ስርዓትና ህጋዊ ውጤት በሚገባ ተገንዝበን ስርዓት የማስከበር ግዴታችንን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ልንወጣ ይገባል፡፡

6.4 በሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች ሊነሱ የሚችሉ መቃወምያዎች

በሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ላይ ሊነሱ የሚችሉ የመቃወሚያ ነጥቦች በን/ህ/ቁ 717 ላይ በዝርዝር ተደንግገው የመናገኛቸው ሲሆኑ የህጉን ይዘት በማፍታታት ስናየው ን/ህ/ቁ 717(1) "ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን በያዘው፣ በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ በተመሰረቱት፣ በሰነዱ አፃፃፍ ፎርምና እንዲሁም በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች ካልሆነ ሌላ መቃወሚያ ሊያቀርብበት አይችልም" በማለት ሰለሚደነግግ በአምጪው ላይ ሊያቀርብ የሚችላቸው መቃወምያዎች፡-

1. በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ በተመሰረቱት
2. በሰነድ አፃፃፍ ፍርምና
3. ሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች ናቸው፡፡

እነዚህ ከ1 እስከ 3 የተዘረዘሩትን ከዚህ በታች አንድ በአንድ የተመለከትናቸው እንደሆነ ደግሞ፡-

1. በሁለቱም የግል ግንኙነቶች

በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ በተመሰረቱት፣ በዚህ መቃወሚያ፣ መከላከያ ወይም የመከራከሪያ ነጥብ መሰረት አንድ ባለዕዳ ማለትም ያንድ ሰነድ አውጪ በርሱ በራሱና በሰነዱ ይከፈለኝ በማለት ሰነዱ ይዞ ቀርቦ ግን ሳይከፈለው ከቀረው አምጪ መካከል ያለውን የግል ግንኙነት ጠቅሶ አምጪውን ሊከራከር ይችላል። ከዚህ የመከራከሪያ፣ የመቃወሚያ ወይም የመከላከያ ነጥብ ጋር በተያያዘ ዋናውና መልስ ሊያገኝ የሚገባው ወሳኝ ጥያቄ "የግል ግንኙነት" ወይም በእንግሊዘኛው "Personal relations" ምንድነው? ምንና ምን ያካትታል? የሚለው ነው። በተራ የዕለት ተዕለት ግንኙነት ውስጥ የግል ግንኙነት ማለት ሌላን ሰው ወይም ሕዝብን የማይጨምር በሁለት ሰዎች መካከል ብቻ የተወሰነ፣ በሌላ ሰው አማካይነት ወይም ጣልቃ ገብነት ሳይሆን በቀጥታ በሁለት ሰዎች መካከል የሚፈጠረውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። የግል ግንኙነት በተራ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ከላይ የተመለከተውን ትርጉም የሚይዝ ከሆነ የህግ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ወይም በሌላ አነጋገር በን/ህ/ቁ 717(1) ስር "በሁለቱ የግል ግንኙነት" ላይ የተመሰረተ መቃወሚያ ወይም መከላከያ ሲል "የግል ግንኙነት" የሚለው ሐረግ ምንና ምን እንዲያካትት ታስቦ የገባ ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት መሞከር ተገቢ ነው። ከህግ አኳያ "የግል ግንኙነቶች" የሚለው ሐረግ ምንና ምን ያካትታል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ተገቢነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረቱ በን/ህ/ቁ 717 (1) ውስጥ "በሁለት የግል ግንኙነቶች" ላይ የተመሰረተ መቃወሚያ ወይም መከራከሪያ ወይም መከላከያ ከላይ ይህ ሐረግ በዕለት ተዕለት ግንኙነቶች ውስጥ የሚይዘውን ትርጉም እንደሚይዝ መገንዘቡ ጥሩ ነው። ይህም ማለት በን/ህ/ቁ 717(1) ስር "በሁለት የግል ግንኙነቶች" ላይ የሚለው ሐረግ በን/ህ/ቁ 790 (1) እና 825(1) (ሐ) እና 872 ስር የተፃፉት እንደተጠበቁ ሆነው ሌላ ማንንም ሳይጨምር በዕዳ ከፋዩ እና በሰነዱ አምጪ መካከል ብቻ ያለውን ግንኙነት የሚመለከት መሆኑን ነው። በዕለት ተዕለት ግንኙነቶች ውስጥ ሐረጉ የሚኖረውን ትርጉም ካየን በሕግ ረገድ የሚኖረውን ወይም የሚያካትተውን ደግሞ ከዚህ በታች ባጭሩ እንመለከታለን።

ከሕግ አኳያ በተለይም ከሚተላለፉ ሰነዶች ሕግ አኳያ በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱ መቃወሚያዎች ማለት ሰነዱን በቅን ልቦና በያዘው ሰው ላይ ሊቀርቡ የማይችሉ መከራከሪያዎች ሲሆን መከራከሪያው ወይም መቃወሚያውን በሚያቀርበው ሰው ማለትም በባለዕዳውና በአምጪው መካከል ባለው እና በሁለቱም በሚታወቀው ሁኔታ፣ ግንኙነት ወይም ዕውነታ የተነሳ ግን ዕዳ ከፋዩ ስለ ሁኔታው፣ ስለ ግንኙነቱ ወይም ስለ እውነታው የሚያውቀው አምጪ ላይ የሚያነሳው መቃወሚያ ነው። ለምሳሌ በዕዳ ከፋዩና በአምጪው መካከል የውል ግንኙነት ኖሮ ሰነዱ ለአምጪው የተሰጠው የውል ግንኙነቱ ላይ ተመስርቶ ከሆነ ዕዳ ከፋዩ በመካከላቸው ያለውን የውል ግንኙነት ጠቅሶ አምጪውን ሊከራከረው ወይም ሊቃወመው ይችላል። የውል ግንኙነት ሲባል በዕዳ ከፋዩና በአምጪው መካከል ተመስርቶ ኖሮ ለሰነዱ መውጣት ምክንያት ወይም መሰረት የሆነውን ውል በተመለከተ ከውሉ ምስረታ

ጋር የተያያዘውን፣ ከውሉ አፈፃፀም ጋር የተያያዘውን ማንኛውንም ነጥብ ማንሳት እና አምጪውን መቃወም ወይም መከራከር እንደሚችል ነው፡፡ የሸጥኩልህን ዕቃ በዚህ ቀን አስረክብሃለሁ ብሎ ሻጩ ግዴታ ስለገባ ገዢው ዕቃውን ትረከባለህ በተባለበት ቀን ቀጥሎ ያለውን ቀን ፅፎበት ቼክ ለሻጭ ሰጥቶ ሻጭ አስረክባለሁ ባለበት ቀን ባለማስረከቡ ገዥ ማለትም የቼኩ አውጪ ቼኩን እንዳይከፈል በን/ህ/ቁ 857 መሰረት ቢያስቆምና ሻጪ በቼኩ ላይ ተንተርሶ በገዥ ላይ ክስ ቢመሰርት ገዥ የበስተጀርባ ውለታቸውና የሻጭን ዕቃውን አስረክባለሁ ባለበት ቀን ግዴታውን ያለመወጣት (ያለማስረከብ) ጠቅሶ ቢከራከር ይህ ክርክር በዕዳ ከፋዩ በገዥ እና በአምጪው በሻጭ መካከል ባለው የግል ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ በን/ህ/ቁ 744 እና 841 መሰረት አንድ አውጪ ፊርማውን ብቻ ያስቀመጠበትን የሐዋላ ወረቀት ወይም ቼክ ሌላ ሌላውን ነገር በመካከላቸው በተደረሰው ስምምነት መሰረት እርሱ ሞልቶ ሰነዱን የተሟላ እንዲያደርገው የተሰጠው ሰው ሰነዱን ሲሞላ ከስምምነታቸው ውጪ ቢሞላው የሰነዱ አውጪ ሰነዱን የሞላውን ገዥ ወይም አምጪ ቢከራከረው መቃወሚያ ይሆናል፡፡ ሰነዱን ከስምምነት ውጪ የሞላው ሰው በእርሱና በአውጪው መካከል ከተደረገው ስምምነት ውጪ መሞላቱን እያወቀ መቀበሉ ካልተረጋገጠ ወይም ሊቀበል ጥፋት ካልፈፀመ በስተቀር አውጪው በርሱና ሰነዱን በሞላው ሰው መካከል ያለውን የግል ግንኙነት ጠቅሶ ሦስተኛውን ሰው (አምጪ) ሊከራከረው አይችልም፡፡ ዕዳ ከፋይ “በግል ግንኙነቶች” ላይ የተመሰረተ መከራከሪያን ወይም መቃወሚያን ማንሳት መቻል አለመቻሉ በን/ህ/ቁ 717(1) ስር ብቻ ሳይሆን በዚሁ ቁጥር በን/ቁ (3) ስር ስለተጠቀሰ ንዑስ ቁጥር (3) ን (1) ስንመለከት

2. በሰነዱ አፃፃ ፎርም

በሰነዱ አፃፃፍ ፎርም ላይ የተመሰረተ መከላከያ ማለት ሕግ ለሰነዱ አፃፃፍ የደነገገው ፎርም አለመሟላቱን የሚያመለክት መከላከያ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ለምሳሌ ሕግ አንድ ሰነድ ቼክ ነው እንዲባል መሟላት አለባቸው በማለት ያስቀመጣቸው የፎርም መስፈርቶች አለመሟላታቸውን ጠቅሶ ከዚህም የተነሳ ሰነዱ በህግ እንደ ቼክ አይቆጠርምና በሰነዱ ላይ በተፃፈው ከሁለም በላይ በቼኩ ላይ የሚታየው ፊርማዬ አያስገድደኝም ብሎ ዕዳ ከፋዩ መከራከር እንደሚችል ለማመልከት የተፃፈ ነጥብ ነው፡፡ አንድ ሰነድ በህግ በኩል ቼክ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችለው በን/ህ/ቁ 827 እና 828 ሥር ተደንግገው ያሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰነድ በቅድሚያ በን/ህ/ቁ 827 ስር የተፃፉትን ማለትም፣

- የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ቅድመ ሁኔታ (ሐተታ) ያልተደረገበት ትዕዛዝ
- የሰነዱን ገንዘብ መክፈል ያለበትን (የሚገባውን) ከፋይ ስም፣
- የሰነዱን ገንዘብ የሚከፈልበትን ቦታ

- ሰነዱ የወጣበት ቦታና ጊዜ
- ሰነዱን ያወጣው ሰው ፊርማ አሚልቶ ካልተገኘ

መፍትሄ ሰጭ በሆነውና ክፍተቶችን በሚሞላው በን/ህ/ቁ 828(ሀ) እና (ለ) ስር በተፃፈው መሰረት መስፈርቶችን እንደሚያሟላ ካልተቆጠረ በስተቀር ሰነዱ እንደ ቼክ ሊቆጠር እንደማይችል በን/ህ/በቁ 828 መጀመሪያ ላይ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም የተነሳ በአንድ ቼክ ላይ በን/ህ/ቁ 827(ለ) መሰረት የከፋዩ ባንክ ስም ካልተፃፈበት በሰነድ በቼክ እንደ ቼክ የማይቆጠር ስለሚሆን ዕዳ ከፋዩ እንደ ቼክ ተደርጎ የቀረበው ሰነድ ላይ የተመለከተውን ግዴታ ለመክፈል አልገደድም፤ ወይም ያልከፈልኩት በዚሁ ምክንያት ነው በማለት ሊከራከር ይችላል፡፡ በሌላም በኩል በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ውስጥ ካሉት ባንኮች ትልቁና ከአንድ መቶ ሰባ በላይ ቅርንጫፎች ያሉትን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ብንወስድ ከፋዩን ለማመልከት በቼኩ ላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚል ብቻ ተፅፎበት ቼኩ ለክፍያ መቅረብ ያለበት በየትኛው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ መሆኑን በን/ህ/ቁ 827(ሐ) መሰረት ካልተገለፀ እንደ ቼኩ መክፈያ ቦታ የሚቆጠረው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት ይሆናል፡፡ የአንድ ቼክ ከፋይ ባንክ ቅርንጫፎች ያሉት ከሆነ የአውጪው ሂሳብ ያለበት ቅርንጫፍ ስም በከፋዩ ስም አጠገብ ይፃፋል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ መፍትሄ ሰጭና ክፍተት ደፋኝ የሆነው የን/ህ/ቁ 828(ሐ) ለአንድ ቼክ ልዩ መክፈያ ቦታ ማመልከት እንደሚቻል ለምሳሌ በን/ህ/ቁ 836 መሠረት ይጠቁምና በከፋዩ ስም አጠገብ ይህ ልዩ የመክፈያ ቦታ ካልተፃፈ ግን በከፋዩ ስም አጠገብ የተፃፈው ቦታ ለምሳሌ ከፋዩ ወጋገን ባንክ ተብሎ ተፅፎ ባጠገቡ ፒያሳ ቅርንጫፍ ተብሎ ቢፃፍ የቼኩ መክፈያ ቦታ ወጋገን ባንክ ፒያሳ ቅርንጫፍ ሆኖ እንደሚቆጠር የን/ህ/ቁ 828(ሐ) ይደነግጋል፡፡ በሌላም በኩል ከፋዩ ወጋገን ባንክ መሆኑ በቼኩ ላይ ተፅፎ በዚሁ ስም አጠገብ ኮልፌ፣ መርካቶ፣ ቂርቆስ ወዘተ... ተብሎ የበርካታ ቦታዎች ስም ተዘርዝሮ ከሆነ የቼኩ መክፈያ ቦታ ተደርጎ የሚወሰደው በከፋዩ ስም አጠገብ በመጀመርያ የተፃፈው ቦታ ማለትም ኮልፌ ቅርንጫፍ እንደ ቼክ መክፈያ ቦታ ተደርጎ እንደሚወሰድ በዚሁ በን/ህ/ቁ 828(ሀ) ስር በሁለተኛው አረፍተ ነገር ላይ ተፅፎ ይገኛል፡፡ እንግዲህ በን/ህ/ቁ 828 በ(ሀ) እና በ(ለ) ስር በመፍትሄነት ከተደነገገው በስተቀር አንድ ቼክ በቅድመ ሁኔታ መፈፀም ላይ የተመሰረተ ግንዘብ ክፈል ትዕዛዝ ቢፃፍበት ለምሳሌ፡- የበልግ ዝናብ የዘነበ እንደሆነ ክፈል ለአቶ በቀለ ወይም ላዘዘበለት ቢባል ይህ የተፃፈበት ሰነድ ህግ ለቼክ የደነገገውን ፎርም ስለማያሟላ እንደ ቼክ አይቶጠርም ብሎ አውጭው በመቃወሚያነት ሊያቀርበው ይችላል፡፡ አውጭው ይህንን በመቃወሚያነት የሚያሳው አንድን ሰነድ ቼክ ለማሰኘት አስፈላጊ የፎርም መስፈርቶች ናቸው በማለት ህግ በን/ህ/ቁ 827 ካስቀመጣቸው ነጥቦች መካከል አንድ በዚሁ በን/ህ/ቁ 827 (ሀ) ስር የተወሰነ ግንዘብ ለመክፈል ሁተታ (ቅድመ ሁኔታ) የሌለበት ትዕዛዝ መያዙ ነውና፡፡ በን/ህ/ቁ 827 ስር የሰፈሩትን ሌሎችን ትተን በ(ሠ) ላይ የተፃፈውን ብንመለከት አንድን ሰነድ ቼክ ከሚያሰኙት አስፈላጊ ፎርማሊቲዎች የአውጭው ፊርማ በሰነዱ ላይ መታየቱ እንደመሆኑ መጠን ይህ ከሌለበት

አንድ ሰነድ ከፎርም አኳያ እንደ ቼክ አይቁጠርም ዕዳ ከፋዩ ይህንን የአውጭው ፊርማ አለመኖሩን ህግ ለሰነድ ፎርም የደነገገው እንደ አለማሚላት ጠቅሶ ሊከራከርበት ይችላል፡፡ በዚሁ ስሜት ለሃዋላ ወረቀቶች በን/ህ/ቁ 735 እና 736 ለተሰፉ ሰነዶች ደግሞ በን/ህ/ቁ 823 እና 824 የተፃፉት ካልተሟሉ አንድ ዕዳ ከፋይ ለሰነዱ አፃፃፍ ፎርም ህግ የደነገገው አልተሟላም በማለት ሊከራከር ይችላል፡፡

3. በሰዱ ላይ በተፃፉት ቃላት (Text) ላይ የተመሰረተ መቃወሚያ

በን/ህ/ቁ 717(1) ስር የተፃፈው ሌላው የመከላከያ፣ የመቃወሚያ ወይም መከራከሪያ በሰነድ ላይ በተፃፉት ቃሎች የተሰኘው መቃወሚያ፣ መከራከሪያ ነጥብ ነው፡፡ ቀደም ሲል በን/ህ/ቁ 735 እና 736፣ 823 እና 824 እንዲሁም 827 መሠረት በሐዋላ ወረቀቶች ለተሰፉ ሰነዶችና በቼኮች ላይ ተፅፈው መታየት የሚገባቸው ነገሮች እንደሉ አይተናል፡፡ እንደ ሰነዱ ዓይነትና መለያ ህግ የሚጠይቃቸው ሁሉ ተሟልተው ካልተፃፉ ወይም ባይሟሉም ህግ እንደተሟሉ ካልቆጠረ ሰነዶች እንደ ሐዋላ ወረቀት ወይም እንደ ቼክ ወይም እንደ ተሰፋ ሰነድ እንደማይቆጠሩም ተመልክተናል፡፡ በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃላት ላይ የሚመሠረቱት መከላከያዎች ን/ህ/ቁ 735፣ 823 እና 827 ድንጋጌዎች በሚያዙት መሰረት መፃፍ ያለባቸውን ቃላትና አገላለፆችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል በቁ 735፣ 823 እና 827 በሦስቱም ስር ሰነድ የወጣበትን ቀን አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን አውጪው በሰነዱ ላይ የፃፈውን ቀን ከርሱ ሰነዱን የተቀበለው ሰው ወይም ሌላ ሰው በመቀየር ወይ ያለፈ ቀን ወይም የወደፊት ቀን ቢፃፍ ዕዳ ከፋዩ ይህንኑ ጠቅሶ አምጪውን ሊከራከርበት ይችላል፡፡ ሰነድ የወጣበትን ቀን መቀየሩ ብዙ ነገሮችን ሊነካ ስለሚችል አውጪው ይህንኑ እንደ ትልቅ የመከራከሪያ ነጥብ ሊያነሳ ይችላል፡፡ አውጪው በሰነዱ ላይ በን/ህ/ቁ 769(1) (ለ) መሠረት ከቀረበ ከ3 ወራት በኋላ ክፈል ለአቶ ሀ ወይም ላዘዘለት ብሎ የፃፈውን አቶ ሀ ወይም ሰነዱን ከአቶ ሀ የተቀበለው ሰው በን/ህ/ቁ 769(1) (ሀ) ስር በተፃፈው ማለትም "ክፈል ለአቶ ሀ ወይም ላዘዘለት" ተብሎ እንዲነበብ ቢያደርገው ይህም ሁኔታ አውጪው በሰነድ ላይ በተፃፉት ቃሎች ላይ የተመሠረተ መቃወሚያ ወይም መከላከያ እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል፡፡ በሰነዱ ላይ የተፃፈውን የገንዘብ መጠን በተመለከተም እንደዚሁ አውጪው ሳያውቀውና ምናልባትም ሳይፈቅድ ከፍና ዝቅ ሊደረግ ስለሚችል ተደርጎ ሲገኝ አውጪው ይህንንም በሰዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች መከላከያት ሊያነሳው ይችላል፡፡ የሐዋላ ወረቀቶችንና ቼኮችን አስመልክቶ የን/ህቁ 740 እና 837 ስር የደነገጋቸው የገንዘቡን መጠን አስመልክቶ በሰነዱ ላይ የተፃፉትን ቃላት የሚመለከቱ ሲሆኑ የገንዘቡን መጠን አስመልክቶ በሰነዱ ላይ የተፃፉትን ቃላት በን/ህ/ቁ 740 ወይም 837 ስር እንደተደነገገው ከሆነ ግን ለሁኔታዎቹ ህግ መፍትሔ ስለሰጣቸው ዕዳ ከፋዩ ይህንን ጠቅሶ እንዲከራከር ሊፈቀድለት አይገባም፡፡ ን/ህ/ቁ 717 (2) እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሰራ፣ ችሎታ፣ ወይም ሥነዱ ሲወጣ የውክልና ስልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው

ተነሱትን መቃወሚያዎች ማቅረብ ይችላል በማለት ሰለሚደነግግ በዚህ በን.ህ.ቁ 717 (2) ስር ለዕዳ ከፋዩ መከላከያት የተፃፉት ነጥቦች አራት ራሳቸውን የቻሉ ነጥቦች ሲሆኑ እንርሱም፡-

- ፊርማን በማስመሰል የተሰራ
- ችሎታ
- ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ስልጣን ያለመኖሩ እና
- ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ያለመሟላታቸው እነዚህን የመከላከያ ነጥቦች ከዚህ በታች አንድ በአንድ እንመለከታለን፡፡

ሀ. ፊርማን በማስመሰል የተሰራ

በሚተላለፉ ሰነዶች ላይ ፊርማ ትልቅ ሚናን ይጫወታል፡፡ የሚተላለፉ ሰነዶች የተፃፉ ሰነዶች ስለሆኑ ተዋዋዮቹ በተለይም ደግሞ ግዴታ ውስጥ የገባው ወገን ፊርማውን በሰነዱ ላይ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል ከሰነዶች አፃፃፍ ፎርም አኳያ በን/ህ/ቁ 735፣ 823፣ እና 827 ስር የተመለከቱትን ስናይ በሰዱ ላይ የአውጪው ፊርማ ከሌለ ሰነዱ በህግ የሐዋላ ወረቀት፣ የተሰፋ ሰነድ፣ ወይም ቼክ ተብሎ ሊወሰድ እንደማይችል ተመልከተናል፡፡ ከዚህም ሌላ የንግድ ወረቀቶች አስመልከቶ በን/ህ/ቁ 734 ስር በንግድ ወረቀቶች ላይ የሚደረጉ ማስታወቂያዎች (የሚፃፉ ነገሮች) እነዚያኑ ነገሮች፣ ማስታወቂያዎች በፃፈው ሰው በእጅ ፅሁፍ መፈረም እንደለበት ተደንግጓል፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 741 እንዲሁም 838 እና 839 ስር የተፃፉትንም ስንመለከት ሰዎችን በንግድ ወረቀቶች ተገዳጅ የሚያደርጋቸው ፊምማቸው በሰነዱ በስተፊት ወይም እንደሁኔታው በጀርባ ላይ መታየቱ ሲሆን ከነዚሁ ቁጥሮች እንደምንረዳው ፊርማው በሰነዱ ፊት ወይም በጀርባ የሚታየው ሁሉ በፊርማው ላይገደድ እንደሚችል እንገነዘባለን፡፡ ታዲያ በፊርማቸው ላይገደዱ ከሚችሉት ሰዎች መካከል በሰነዱ ላይ የሚታየው ፊርማ የኔን ፊርማ በማስመሰል የተቀመጠ እንጂ እውነተኛ የኔ ፊርማ አይደለም በማለት መከራከር ሊኖር እንደሚችል በነዚህ ቁጥሮች ላይ ተደንግጎ ይስተዋላል፡፡ በሰነዱ ዋና ባለዕዳ የሆነው አውጪ ደግሞ እንደ አውጪ ፊርማ የተቀመጠው የኔ ፊርማ አይደለም በማለት መከራከር መቻሉን የን/ህ/ቁ 717(2) በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

ለ. ችሎታ

በን.ህ.ቁ 717 /2/ ስር ዕዳ ከፋዩ በመከላከያነት ሊያነሳ እንደሚችል የተመለከተው ሌላው ነጥብ የችሎታን ነጥብ ነው፡፡ በን/ህ/ቁ 717 የተፃፈው የችሎታ ነጥብ ውጭ የመዋዋል ችሎታን የሚመለከት ነጥብ ነው፡፡ ይህንኑ ተከትለን በን/ህ/ቁ 733 ስር ስለንግድ ወረቀቶች የተፃፈውን ብንመለከት ማንኛውም በውል ለመገደድ ችሎታ ያለው ሰው በንግድ ወረቀትም መገደድ እንደሚችል ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በፍታብሄር ህግ መሰረት አንድ ሰው በውል የማይገደደው ከዕድሜው የተነሳ፣ ከአእመሮው ጤና ማጣት የተነሳ ወይም ከቅጣት የተነሳ ሲሆን ምናልባት የልዩ ችሎታ ጉደይ ከሆነ ደግሞ ከዜግነት ወይም ከሚሰራው ተግባር የተነሳ

መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ እናም በን/ህ/ቁ 717 (2) መሠረት አንድ ዕዳ ከፋይ በሰነዱ ላይ የሚታየውን ፊርማ የኔ ቢሆንም አካለ መጠን ባለመድረሴ ምክንያት በስነድ ውስጥ በተመለከተው እና በኔ በተፈረመው ግዴታ አልገደድም ማለት ይችላል፡፡ በሌላም በኩል የሰነዱ አውጪ የአእምሮ ሕመምተኛ መሆኑንና የፍርድ ክልከላ እንደተደረገበት እና ከዚህም የተነሳ በሰዱ ላይ የሚታየው ፊርማ ችሎታ በሌላው ሰው የተፈረመ ስለሆነ እንደማይገደድበት ጠቅሶ ሊከራከር ይችላል፡፡ በን/ህ/ቁ 741 እና 742 አልፎም 838 እና 839 ስር ተደንግጎ በሚነበበውም መሰረት በችሎታ መጠን ምክንያት ሰዎች በሰነዶች ላይ በሚታዩት ፊርማዎቻቸው ላይገደዱ እንደሚችሉ ተዕፏል፡፡

ሐ. ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሥልጣን ባለመኖሩ

ሌላው በን/ህ/ቁ 717 (2) ስር ለዕዳ ከፋዩ መከላከያነት የተቀመጠው ነጥብ ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ስልጣን ያለመኖሩን ጠቅሶ የመከራከሩ ነው፡፡ ይህ ነጥብ ከራሱ ከአቀማመጡ ግልፅ እንደሆነ ከውክልና ጋር የተያያዘ ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ መሰረት ዕዳ ከፋዩ የሚያነሳው መከላከያ እንደ እኔ ሆኖ፤ እኔን ወክሎ በሰዱ ላይ የፈረመው ሰው ይህን ሲያደርግ የውክልና ስልጣን አልነበረውም፤ ሰነዱ ተፈርሞ ከወጣ በኋላም ቢሆን የፈራሚውን ያለውክልና ስልጣን መስራት ተቀብዬ አላፀደቅሁትም በመሆኑም የውክልና ስልጣን ሳልሰጥ እንደሿሚ ተደርጌ የቀረብኩ እኔ ዕዳ ከፋይ አልገደድም በን/ህ/ቁ 742 እና 839 ስር የተፃፈውን ስንመለከት እንደሿሚ ተደርጎ የቀረበው ባለዕዳ በ717(2) መሰረት ተከላክሎ ከመገደድ ነፃ ቢወጣ የውክልና ስልጣን ሳይኖረው እንደሿሚ ተደርጎ የቀረበው ዕዳ ከፋይ ወኪል ነኝ በማለት በሐዋላ ወረቀት ወይም በቼክ ላይ የፈረመ ሰው እርሱ እራሱ ተገዳጅ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የን/ህ/ቁ 742 እና 839 ድንጋጌ አንድ ወኪል በሐዋላ ወረቀት ወይም በቼክ ላይ ከተሰጠው ስልጣን በላይ ሄዶ ቢፈርምም ሿሚው ድርጊቱን ካልተቀበለለት በስተቀር ከስልጣኑ አልፎ የፈረመው ወኪል በፊርማው እንደሚገደድም ይነግረናል፡፡

መ. ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው

በን/ህ/ቁ 717 (2) ስር ከተነሱት መቃወሚያ ነጥቦች የመጨረሻው ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ያለመሟላታቸውን የሚመለከተው ሲሆን በዚህ የመቃወሚያ ነጥብ ላይ ተመስርቶ ዕዳ ከፋዩ ሊያሳው የሚችለው በዋናነት የዕምቢታ ማስታወቂያ ማሰራት አስፈላጊ ሆኖ እያለ የአምጭውን ያለማሰራት ይሆናል፡፡ በን/ህ/ቁ 780 እና ተከታታዮቹ ላይ በተመለከተው መሰረት የአንድ የሚተላለፊ ሰነድ እምጪ የሰነዱ የመክፈያ ጊዜ ደርሶ ሳይከፈለው ቢቀር ወይም የሰነዱ የመክፈያ ጊዜ ባይደርስም ሰነዱን በእሽታ አቅርቦ እሽታ ቢከለከል እንደ ሁኔታው የመክፈል ወይም እምቢታ ማስታወቂያ (protest) ማሰራት ይኖርበታል፡፡ በን/ህ/ቁ 789 ስር እንደተፃፈው በሰነድ ላይ ያለ እምቢታ ማስታወቂያ ክስ የሚቀርብበት ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ የእምቢታ ማስታወቂያ ማሰራት እንደ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም አምጪው የእምቢታ ማስታወቂያውን ሳያሰራ

ክስ ቢመሠርት ዕዳ ከፋዩ ይህንኑ ጠቅሶ ሊከራከር እንደሚችል የን/ህቁ 717 (2) መብት ይሰጠዋል፡፡

ሌላውና የመጨረሻው ሊቀረበ የሚችለው መቃወምያ ን/ህ/ቁ 717 (3) መሰረት ያደረገ ሲሆን አምጪው ሰነዱን ባገኘበት ጊዜ ዕዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው (የተቀበለው) ካልሆነ በቀር ዕዳ ከፋዩ በራሱና ካሁኑ አምጪ በፊት ሰዱን ይዘው በነበሩት ሰዎች መካከል ያለውን በግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱትን መከራከሪያዎች ጠቅሶ የአሁኑን አምጪ መከራከር (መቃወም) አይችልም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ዕዳ ከፋዩ በእርሱና በአምጪው መካከል ካለው የግል ግንኙነት የተነሳ አምጪው መከራከር ሲችል በን/ግ/ቁ 717(3) ግን የምናየው በመሰረቱ በዕደ ከፋዩ እና ከአሁኑ አምጪ በፊት ሰነዱን ይዘው በነበሩት መካከል የግል ግንኙነት ሊኖር ቢችልም በአምጪው እና በዚያ ሰው መካከል ያለው የግል ግንኙነት ግን ለአሁኑ አምጪ አያገለግልም፡፡ ስለዚህም ዕዳ ከፋዩ በአሁኑ አምጪ ላይ አያንሳ የሚል ክልከላ ሲሆን በዕደ ከፋዩ እና ከአሁኑ አምጪ በፊት ከነበሩት ከማንኛቸውም አምጪ መካከል ያለውን የግል ግንኙነት ጠቅሶ ያሁኑን አምጪ እንደከራከር ግን ለዕዳ ከፋዩ በልዩነት ተፈቅዶለታል፡፡ ይህም የተፈቀደው ያሁኑ አምጪ ሰነዱን ከሰጠው ሰው ሲቀበል መመሳጠር ካለ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ሰነዱን ለመጨረሻው አምጪ የሰጠው ሰው ለዕዳ ከፋዩ መወጣት ያለበትን የውል ግዴታ አለመወጣቱን እና ከዚህም የተነሳ ሰነዱ ለአሁኑ አምጪ ያስተላለፈለት አስመስሎ ዕዳ ከፋዩ ከሰነዱ ሲከፍል የሚገኘውን ገንዘብ ለመካፈል ወይም ኮሚሽን ለማግኘት ተመሳጥሮ ተቀብሎ ከሆነ ዕዳ ከፋዩ በእርሱና ሰነዱን ለመጨረሻው አምጪ በሰጠው ሰው መካከል ያለውን በግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረተውን መከላከያት በአሁኑ አምጪ ላይ ሊያነሳው ይችላል፡፡ የን/ህ/ቁ 717(3) ድንጋጌ በመከላከያነት የሚያገለግለው ቅን ልቦና በጎደለው መልኩ ሆነ ካለው ዕዳ ከፋዩን ለመጉዳት ተመሳጥረው ግን የዋህ ሰነድ አቅራቢ መስለው የሚመጡትንነ ለመቃወም ነው፡፡

6.5 የሰነዶቹ ማስተላለፊያ መንገዶች

የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በተለያዩ መንገዶች ከአንዱ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፉ የሚችሉ ሲሆን ሰነዱ ስሙ ለተጠቀሰ ወይም ላዘዘለት በሚል የሚተላለፉ ሲሆን በን/ህ/ቁ 719 መሰረት ይተላለፋል የሰነዱ ዓይነት ላምጪው (bearer) በሚሆንበት ጊዜ አምጪው የሚኖረው መብት በሚመለከትም በን/ህ/ቁ 721 ላይ በሰነዱ ውስጥ ለተነገረው ግዴታ መብት ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆነው ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የሰነዱ ዓይነት ስሙ ለተጠቀሰ ወይም ለታዘለት በሆነ ጊዜ ስለሚኖረው መብት ደግሞ በንግድ ህግ ቁጥር 722 ተደንግጓል፡፡ በትዕዛዝ የሆነ ሰነድ የሚተላለፈው፡-

- በጀርባው በመፈረምና
- ባለ ጥቅም ለሆነው ሰው በመሰጠት ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙ ን/ህ/ቁ 724ን መሰረትያደረገ ነው፡፡

በጀርባው የሚፈረመውም

- በጀርባው በመፃፍና በመፈረም
- ስም ሳይፃፍ በፊርማ ብቻ ማስተላለፍ
- ለአምጪው ብሎ በመፈረም ሲሆኑ ን/ህ/ቁ 725 748 825 844 መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ናቸው፤፤ ይህም ሲሆን፡-
    - ሃተታ አያስፈልግም፡፡ ን/ህ/ቁ 725 (4)
    - በከፊል መፈረምና ማስተላለፍ አይቻልም ን/ህ/ቁ 725 (5)

በጀርባ የሚደረጉ ፊርማዎች ህጋዊ ውጤትም በ ን/ህ/ቁ 726፣ 749፣ 845፣ 825(1) (ሀ) መሰረት፤-

- በሰነዱ ውስጥ ያሉትን መብቶች ያስተላልፋል
- በሰነድ ጀርባ ስም ያልተሞላበት ሲሆን ደግሞ
    - ባዶውን ቦታ በራሱ ስም ወይም በሌላ ሰው የመሙላት መብትን
    - በሰነዱ ላይ ስም ሳይፃፍ ወይም በሌላ ሰው ስም የማስተላለፍን
    - ባዶ ቦታውን ሳይሞላና ሳይፈርም ለሌላ ሦስተኛ ወገን በመስጠት ማስተላለፍ መብትን ያስገኛል፡፡

ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመወከል ተብለው በጀርባቸው የተፈረሙ ሰነዶች የሚያስገኙት መብትም በን/ህ/ቁ 728፣ 753፣ 851 መሰረት፤-

- አምጪው በሰነዱ ውስጥ ያሉትን መብቶች ሊሰራባቸው ይችላል፡፡
- በጀርባ በመፈረም ሊያስተላልፈው ይችላል ሆኖም ፈራሚው ወኪል ሆኖ እንደፈፀመው ይቆጠራል፡፡
- አውጪው የሚኖረው የመቃወሚያ መብት በሰነዱ ጀርባ በፈረመው ሰው ላይ ከሚያቀርበው መቃወሚያ በስተቀር በመወከል ባለ ጥቅም በሆነው ሰው ላይ መቃወምያ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

በዋስትና ስም በሰነዱ መፃፈ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ስናየው ደግሞ ን/ህ/ቁ 729, 754, 825 (1) መሰረት በመድረግ የሚፈፀመ ነው የሚሆነው፤፤ ይሄውም፤-

- አምጪው በሰነዱ ላሉት መብቶች ሁሉ ሊሰራባቸው ይችላል፡፡
- በጀርባው በመፈረም ወደ ሌላ ሰው ሲያስተላልፍ ህጋዊ ውጤቱ በውክልና እንደተፈፀመ ይቆጠራል
- በዋስትና ስም በተላለፈለት ሰው ላይ መቃወሚያ ማቅረብ የሚቻለው
- ከፋዩን ሆነ ብሎ ለመጉዳት አስቦ ያደረገው ከሆነ ወይም (ን/ህ/ቁ 850)
- በአውጪውና በፊራሚው መካከል ባለ የግል ግንኙነት ካልሆነ በስተቀር እንደ መቃወሚያ ሊያነሳበት አይችልም፡፡ ን/ህ/ቁ 717(1) ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የኢኮኖሚ ዘርፉ ዋና መሳርያዎች

እንደመሆናቸው መጠን የአጠቃቀም ስርዓታቸውን ጠነቅቆ ማወቅና ህጋዊ በሆነ አገባብ መገለገልን የሚጠይቁ ናቸው።

6.6 የንግድ ወረቀቶች

6.6.1 የሃዋላ ወረቀት ትርጉም

የሃዋላ ወረቀት ትርጉም በንግድ ህጉ ያልተሰጠ በመሆኑ ቀጥሎ ያለውን ትርጉም ወስደን የሃዋላ ወረቀት ምንነት በህንድ ህግና ሌላ የዘርፉ ተመራማሪ የተሰጠውን ፍቺ ስንመለከት፡-

'A bill of exchange is an instrument in writing Containing an unconditional order signed by the maker direction a certain person to pay a certain sum of money only to or to the order of a certain person or to the bearer of the instrument.' (Indian commercial act sec.5)

'A bill of exchange is unconditional order in writing, addressed by one person to another, signed by the person giving it, requiring the person to whom it is addressed to pay on demand or at a fixed or determinable future time a sum certain in money to or to the order of a specified person or to bearer.' (David A.L.Smout, 1964, P.11)

የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል በን/ህ/ቁ 735 የሃዋላ ወረቀት መግለፅ ስለሚገባቸው ነገሮች ከሚዘረዝር ውጪ ትርጉምን ስለማይሰጥ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ትርጉም ከንግድ ህጉ አንፃር በሚከተለው መልኩ መረዳት ይቻላል፡፡

- በፅሁፍ መሆኑን ግን ደግሞ ሰነዱ የወጣበት ቀን ወደ ኃላ በመመለስ ወይም ወደፊት በማስቀደም በመፃፉ ሰነዱ ዋጋ አልባ የማይሆን ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 745 መታየት ያለበት ነው፡፡
- ሲጠየቅ የሚከፈልና በን/ህ/ቁ 769-770 መሰረት የሚስተናገድ መሆኑ፣
- የሰነዱ መፈረም እንደ መስፈርት የሚከተል መሆኑ ከን/ህ/ቁ 735(ሸ) ጋር ተመሳሳይ ነት ያለው መሆኑ፣
- በውል ለታወቀ ግዜ የሚለው አገላለፅ ከን/ህ/ቁ 769 ላይ የሚመሳሰል መሆኑ፣
- የታወቀ የገንዘብ መጠን (a sum certain) የሚለው የትርጉም አባባል ከን/ህ/ቁ 735 (ለ) እና 740(2) ጋር ብሮ የሚሄድ መሆኑ፣
- ለራሱ ወይም ላዘዘለት የሚለው ሃሳብ ከን/ህ/ቁ 735 (ረ) ጋር የሚሰማማ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ን/ህ/ቁ 825 በተስፋ ሰነድ ላይ የሃዋላ ወረቀት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ይደነግጋል፡፡ የሃዋላ ወረቀት የሚተላለፈው በን/ህ/ቁ 746 መሰረት ሆኖ፡-

- ለአምጪው የሚል ሲሆን ሰነዱን በመሰጠት፡፡

- ❖ በትእዛዝ የሚል ሆኖ ባይወጣም እንኳን በጀርባው በመፈረም ይተላለፋል፤፤
- ❖ በትእዛዝ ያልሆነ ወይም ይህን የመሰለ ቃል የያዘ እንደሆነ ከመደበኛ የመተላለፊያ መንገድ ውጭ አይተላለፍም፤፤ ቢተላለፍም ውጤት አይኖረውም፤፤
- ❖ ለከፋዩ፣ ለአምጪው ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በጀርባው በመፈረም ሊተላለፍ ይችላል፤፤
- ❖ እነዚህ ሰዎች እንደገና በጀርባው በመፈረም ሊያስተላልፉት ይችላሉ፡፡

በጀርባ የመፈረም ሁኔታዎች ን/ህ/ቁ 747ን መሰረተ በማደረግ የሚፈፀሙ ሲሆኑ፤-

- ያለ ሃተታ መሆን አለበት::
- በከፊል በጀርባው በመፈረም ማስተላለፍ አይቻልም::
- ለአምጪው ተብሎ በጀርባው ከተፈረመ ስም እንዳልተፃፈበት ይቆጠራል፡፡
- በጀርባው የሚደረግ ፊርማ በሰነዱ ላይ ወይም ከሱ ጋር በተያያዘ ቅጠል ላይ ማድረግ ይቻላል:: (ን/ህ/ቁ 748) በጀርባ የመፈረም ህጋዊ ውጤትም፤-

✓ በሃዋላ ወረቀት የሚገኘውን መብት ሁሉ ያስተላልፋል

✓ በጀርባው ፅሑፍ ስም ያልተሞላበት ሲሆን

- ስም ያልተሞላበትን በሰሙ ወይም በሌላ ሰው ስም በመሙላት
- በሌላ ሰው ስም ወይም ስም ሳይሞላ በጀርባው በመፈረም
- ስም ሳይሞላና በጀርባው ሳይፈርም ለሌላ 3ኛ ወገን በመሰጠት ብቻ ሊያስተላልፈው ይችላል፡፡

የመክፈያ ግዜ ካለፈ በኃላ ወይም የእምቢታ ማስታወቅያ ከተደረገ በኋላ በጀርባ ፈርሞ ማስተላለፍ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት በሚመለከትም፤-

- ❖ ግዜ ከማለፉ በፊት የመፈረምን ውጤት ያመጣል፡፡
- ❖ የተደረገው መተላለፍ የመደበኛ መተላለፍ (Assignment) ውጤት ይኖረዋል፡፡
- ❖ ቀን የሌለበት በጀርባ ፈርሞ ማስተላለፍ የእምቢታ ማስታወቅያ መስጪያው ቀን ከማለፉ በፊት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡
- ❖ በቁጥር 781(2) መሰረት በከፋዩ ማስታወቅያ የተገለፀ እንደሆነ ቀን የሌለበት በጀርባ መፈረም የመክፈል እምቢታ ከመነገሩ በፊት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

አንድ የሃዋላ ወረቀት የሚኖረው የአከፋፈል ስርዓትም ን/ህ/ቁ 769 መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ሲሆን፤-

- እንደቀረበ
- ከቀረበ በኃላ በተወሰነ ግዜ
- ከተፃፈበት ቀን አንስቶ በተወሰነ ግዜ
- ቁርጥ ባለ ቀን ተብሎ ሊወጣ ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 770 ፣771 ፣772፣ 773)

የሃዋላ ወረቀት እሺ ባልተባለና ባልተከፈለ ግዜ የሚኖረው ሁኔታ በን/ህ/ቁ 780 መሰረት፤-

- ❖ አምጪው በጀርባ ፈራሚዎች በአውጪውና ሌሎች ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው

የገንዘብ መክፈያ ግዜ ደርሶ ገንዘቡ ያልተከፈለ እንደሆን፣

- ❖ የመክፈያ ግዜ ባይደርስም የሃዋላ ወረቀት ያልተከፈለው እሺታው በሙሉ ወይም በከፊል እምቢ የተባለ እንደሆነ፣
- ❖ እሺ ቢልም ባይልም ከፋዩ የከሰረ እንደሆነ በፍርድ ቤት ባይረጋገጥም እንኳን እዳውን መክፈል ያቋረጠ እንደሆነ ወይም ንብረቱ እንዲያዝ ተደርጐ ፍሬ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ፡፡
- ❖ እሺታ የማይሰጥበትን የሃዋላ ወረቀት ያወጣው የከሰረ እንደሆነ ናቸው፡፡

በሃዋላ ወረቀት ያለ የይርጋ አቆጣጠር በተመለከተም፡- (ን/ህ/ቁ 817)

በእሺ ባይ ላይ በ3 ዓመት ውስጥ ክስ መቅረብ አለበት

በአውጪውና በጀርባ ፈራሚዎች ላይ ከሆነ ደግሞ

- የእምቢታ ማስታወቅያ ከተደረገበት
- ያለ ኪሳራ የሚመለስ የሚል ቃል ባለበት ግዜ በአንድ ዓመት ግዜ ክስ መቅረብ አለበት፡፡

በጀርባ ፈራሚዎች መካከልና በጀርባ ፈራሚና በአውጪው መካከል የሚቀርብ ክስ በጀርባ የፈረመው ሰው የወረቀቱን ዋጋ ከከፈለበት ግዜ ጀምሮ ወይም በሱ ላይ ክስ ከቀረበበት ግዜ ጀምሮ በስድስት ወር ግዜ፣

ክስ በፍርድ ቤት በቀረበ ግዜ የይርጋ ዘመን መቁጠር የሚጀምረው የመጨረሻ ክስ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ነው፡፡ ፍርድ ተሰጥቶ እንደሆነ ወይም ዕዳው በተለይ በሌላ ሰነድ ታምኖ ከሆነ ከዚህ በላይ የተፃፉበት የይርጋ ዘመኖች አይፀድቁም፡፡ (ን/ህ/ቁ 818)

በሃዋላ ወረቀት የችሮታ ግዜ መስጠት አይቻልም (ን/ህ/ቁ 822) ይህ ማለት ግን የተስፋ ሰነድ ከሃዋላ ወረቀት የሚለዩት ባህርያት የሉትም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ ለምሳሌ በሃዋላ ወቀት ያሉት ተዋዋዮች (parties) አውጪው፣ ተከፋይና ከፋይ ሲሆኑ በተስፋ ላይ ሰነድ የሚኖሩት ተዋዋይ ወገኖች ግን አውጪውና (maker) እና ተከፋዩ (payee) ብቻ ናቸው፡፡ የሃዋላ ወረቀት በባለ ሃብቱ ለባለ እዳው የሚወጣ ሲሆን የተስፋ ሰነድ ግን ባለ ዕዳው (debtor) ለባለ ሃብት (creditor) የሚሰጠው ሰነድ ነው፡፡ በሃዋላ ወረቀት እሽታ (acceptance) የሚጠይቅ ሲሆን የተሰፋ ሰነድ ግን ለመክፈሉ እሽታን (acceptance for honour) የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ስለዚህ እነዚህና ሌሎች ልዩነቶች በሁለቱም ሰነዶች መካከል ያለ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

6.6.2 የተስፋ ሰነድ

6.6.2.1 የተስፋ ሰነድ ትርጉምና ዓይነቶች

‘A promissory note is an instrument in writing (not being a bank note or currency note) containing an unconditional undertaking signal by the maker to pay a certain

sum of money only to or to order of a certain person to the bearer of the instrument' (Indian commercial act sec. 4)

"A Promissory note is an unconditional promise in writing made by one person to another signed by the maker, engaging to pay, on demand or at a fixed determinable future time, a sum certain in money to the order of, a specified person or to bearer." (Bill of exchange Act sec. 65(1)) የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል። የተስፋ ሰነድዓይነቶች በርካታ ሲሆኑ፤-

- **ተራ የተስፋ ሰነድ** (ordinary promissory note) የዚህ ዓይነት የተስፋ ሰነድ በአስመጪና ላኪዎች፣ ጀምላ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች እየወጣ ለንግድ አገልግሎት የሚያውል የተስፋ ሰነድ ሲሆን ለምሳሌ ኣሜቼ ያስመጣቸውን መኪናዎች በብድር በሚሸጥበት ጊዜ የሚጠቀምበት የተስፋ ሰነድ እንደ ተራ የተስፋ ሰነድ የሚታይ ነው።
- **የባንክ ተስፋ ሰነድ** (Bank notes)

በባንክ የተዘጋጁ ሰነዶች እንደ የተስፋ ሰነድ ላምጪው ወይም የታዘዘለት ክፍያ የሚፈፀምባቸውና ለመተላለፋቸው ዋስትና ያላቸው ሰነዶች ናቸው። የባንክ ሰነዶች (Bank notes) እንደ ገንዘብ ስለሚቆጠሩ በአገሪቱ የገንዘብ ዝውውር ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው።

- **የመንግስት ግምጥ ቤት ሰነድ** (Bonds and treasury bills)

የመንግስት ግምጥ ቤት ሰነዶች የተስፋ ሰነድ ዓይነት ሲሆኑ Bond የሚለውን ቃል "a long term promissory note with stipulated interest issued by a government or a corporation) የሚል ትርጉም ሲሰጠው treasury bill ለሚለው ደግሞ "A short term promissory note with stipulated interest " የሚል ትርጉም ተሰጥቶት የምናገኘው ነው።

- **የአደራ ሰርቲፊኬት** (certificate of deposit)

ይህ ዓይነት የተስፋ ሰነድ ሃተታ የሌለው ተስፋ በመስጠት በግልፅ በታወቀ የመክፈያ ጊዜ ክፍያ የሚፈፀምበት ሆኖ ኣፈፃፀሙም አንድ ሰው በባንክ ሒሳብ ገንዘብ በማስቀመጥ ሰዎች ሰርቲፊኬቱን ይዘው በመሄድ ሲጠየቅ ክፍያ የሚፈፀምበት የሰነድ ዓይነት ነው። ይህ ማለት ግን ወዲያው እንደቀረበ የሚከፈለን ክፍያ የሚያስተናግድ ወይም በዚሁ መንገድ ክፍያ ለመፈፀም የሚያስችል ዓይነት ሰነድ ኣይደለም። እንደማንኛውም የተስፋ ሰነድ ሲጠየቅ የሚከፈል (payable on demand) ዓይነት ሰርቲፊኬት ነው። ከዚህ ውጭ የተስፋ ሰነድ በሚመራባቸው ህጐች የሚመራ ስለሆነ ከን/ህ/ቁ 823-826 ያሉትን ድንጋጌዎች መሰረተ በማደረግ ልነመለከተው የገባል።

6.6.3. ቼክ (cheque)

6.6.3.1. ስለ ቼክ በጠቅላላ

ቼክ እንደ ሁሉም የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ለፈጣን የንግድ ልውውጥ ገንዘብን ተክቶ በመስራት የግብይት ስርዓትን ቀልጣፋ በማድረግ ለአንድ አገር ኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያበረክት የገንዘብ ሰነድ ነው፡፡ ቼክ በን/ህ/ቁ 732፣ 827፣ 828 እና 829 መሰረት እንዳቀረበ የሚከፈል በባንክ ተቀማጭ ሒሳብ ያለው ሰው ገንዘቡ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሃተታ የሌለው ትእዛዝ የሚሰጥበትና ክፍያ የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ነው፡፡

Dr. Hart የተባሉ የዘርፉ ተመራመሪ"Law of Banking, 4th ed. P.327) ላይ በሰጡት የቼክ ትርጉም በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ከተሰጠው ፍች ባልተለየ መልኩ

> *"A cheque is unconditional order in writing drawn on a banker signed by the drawer, requiring the banker to pay on demand a sum certain in money to or to the order of a specified person or bearer, and which does not order any act to be done in addition to the payment of money.* በማለት የተረጎሙት ሲሆን፤-

የህንድ ንግድ ህግም 'A cheque is a bill of exchange drawn up on a special field banker and payee on demand (Indian commercial act Sec.6)

በማለት የቼክን ትርጉም የሰጡ ሲሆን የቼክ አስፈላጊነትም ፤-

- ❖ የንግድ ልውውጥን ያሳድጋል፡፡
- ❖ የገንዘብ ዝውውርን ይቀንሳል፡፡
- ❖ ሽያጭና ግዢን ያቀላጥፋል፡፡
- ❖ ዝርፍያንና ስርቆትን ይከላከላል፡፡
- ❖ በስራ ላይ ያልዋለን ገንዘብ ይሰበስባል፡፡
- ❖ አውጪው ሂሳቡን በቀላሉ እንዲቆጣጠር የሚያስችል ሲሆን

ቼክ ከሌሎች የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ጋር ሲነፃፀር የራሱ የተለየ ባህሪያት ያሉት ነው፡፡ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን የወሰድን እንደሆነ፡-

- በቼክ ዝውውር ከፋዩ ሁል ጊዜ በባንክ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 829
- ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል የንንድ ሰነድ መሆኑ፡፡ (ን/ህ/ቁ 854)
- በቼክ ላይ የስርዝ ምልክት ሊደረግበት ይችላል፡፡ ((ን/ህ/ቁ 863-869)
- ቼክ ለመከፈሉ እሽታ የማያስፈልገው ሰነድ ነው፡፡(ን/ህ/ቁ 831)
- አውጪው ገንዘቡን በባንክ ያስቀመጠ ከሆነና ሰነዱን በትክክል እስከ ፃፈና እስከፈረመ ድረስ በሀግ ካልታገደበት በስተቀር አውጪውን በየደረጃው ላሉት አስተላላፊዎችም ሆነ ለአምጪው ዋቢ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 832፣ 831፣ 855፣ 839፣ 853 እና 766 – 768) ከሌሎች የንግድ ወረቀቶች ጋር የሚጋራቸው የጋራ ባህሪያትም፡-

- በሰነዱ ያለውን የገንዘብ መብት ቀጥታ በመስጠት በጀርባው በመፈረም ወይም በጀርባው በመፈረምና በመስጠት ከአንዱ ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችል ሰነድ መሆኑና፤-
- ቼክን በቅን ልቦና የያዘ ሰው (holder in due course)
  - ለእርሱ ካስተላለፈለት ሰው የተሻለ የባለቤትነት መብት መኖር፣
  - ከእርሱ በፊት በነበረው ሁኔታ ተጠያቂ (ሃላፊ) ያለመሆን መብት፣
  - ሰነዱን በእጁ ካስገባ በራሱ ስም ክስ የማቅረብ መብት፣
  - አምጪው ይዞታውን ከምን እንደመነጨ የማስረዳት ግዴታ የሌለበት መሆንን እንደመብት የሚያስገኝ መሆኑ ናቸው፡፡

6.6.3.2 የቼክ ዓይነቶች

1. Bearer cheque አምጪው እንደቀረበ ን/ህ/ቁ/833 (1) እና719 ወዲያውኑ ክፍያ የሚፈጸምበት ቼክ (ን/ህ/ቁ/ 848)
2. Blank cheque (ባዶ ቼክ) የአምጪው ስም ያልተፃፈበት ነገር ግን በአግባቡ የተፈረመና አውጪው ገንዘብ እንዲከፍል ትዕዛዝ የሰጠበት ቼክ፡፡ ን/ህ/ቁ 843 ፣ 844
3. Open cheque (ግልፅ ቼክ) የሰርዝ ምልክት የሌለበት ሆኖ እንደ ቀረበ የሚከፈል፡፡
4. Crossed cheque (የሰርዝ ምልክት ያለበት ቼክ) ሰርዙ በሌሎች አገሮች የቼክን የዝውውር ጠበይ የሚገድብ ሲሆን በኛ አገር ህግ ሰርዙ የመተላለፍ ባህሪውን አይገድበውም (ን/ህ/ቁ 863-865)
5. Antedated cheque የመክፍያ ግዜው ያለፈበት ቼክ
6. Marked cheque (ምልክት ያለው ቼክ) ሲቀርብ እንደሚከፈል በአውጪው የተረጋገጠ ቼክ ነው፡፡
7. Order Cheque (የትእዛዝ ቼክ) ለተወሰነ ሰው ወይም እሱ ለሚያዝበት የሚከፈል የትእዛዝ ቼክ ነው፡፡(ን/ህ/ቁ 842)
8. stopped cheque (እንዳይከፈል የተዘዘበት ቼክ) እንዳይከፈል ለከፋዩ ትእዛዝ የተሰጠበት ቼክ፡፡(ን/ህ/ቁ 857)
9. Certified cheque (የተረጋገጠ ቼክ) ከፋዩ አውጪው በቂ ጥረት ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ የሰጠበት ቼክ፡፡ (ን/ህ/ቁ 832)
10. Travellers cheque (የመንገደኛ ቼክ) ለመንገደኞች የሚሰጥ ቼክ ሲሆን ቼኩን ሲመነዝር የሚፈርምበት ቦታ ያለው ሆኖ፡፡ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ያለ ምንም ችግር መተከት የሚቻል ቼክ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 887)
11. Cashiers cheque አንድ ባንክ ወደ ቅርንጫፍ ባንኩ ገንዘብ የሚያዘዋውርበት ወይም በአንድ ባንክ ውስጥ ከካዝና ወደ ሌላ ከዝና ገንዘብ የሚያዘዋውርበት ቼክ ነው፡፡
12. Teller's cheque በባንክ የወጣ ከፋዩ ሌላ ባንክ የሆነ ቼክ ናቸው፡፡

6.6.3.3 በቼክ አሰራር ያሉ መብትና ግዴታዎች

1.የአውጪው መብቶችና ግዴታዎች

1.1 መብቶች

- አስቀማጭ በዓይነት ለይቶ እንዲመለስለት ከባንኩ ጋር ውል የገባውን ጥሬ ገንዘብ ወይም ሌላ ምልክት ያለባቸውን ገንዘቦች ባለሀብትነት የባንክ እንዳይሆን የማዘዝ መብት አለው፡፡ (ን/ህ/ቁ/ 896)
- በአደራ የሚቀመጠውን ሂሳብ በተመለከተ አንዳንድ ሁኔታዎችን በስምምነት መገደብ ይችላል፡፡
- የሂሣብ መግለጫ በወር አንድ ግዜ መጠየቅ ይችላል፡
- ካለው ሂሣብ እስካልበለጠ ድረስ በሚያዘው ገንዘብ ላይ ገደብ አይኖርበትም
- ተከፋዩን ማመልከት ይችላል (ን/ህ/ቁ 833)
- አውጪው ለራሱ ወይም ለአንድ 3ኛ ወገን ቼክ ሊያዝ ይችላል፡፡ ባለባንኩ በራሱ ላይ የሚያዝበት ቼክ ላይ ግን ለአምጪው እንዲከፈል ለማለት አይችልም፡፡ ን/ህ/ቁ 834
- አውጪው በቼኩ በፊርማ ማስተላለፍ ሊገታ ይችላልን (ን/ህ/ቁ/ 842 (2))
- አምጪው ወይም ቼክ የታዘዘለት ሰው (ተከፋዩ) ቼኩን በአቀረበ ጊዜ ክፍያ እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብት አለው ፡፡ (ን/ህ/ቁ/ 854 እና 855)
- አውጪው አንድ ቀደም ሲል አውጥቶት የነበረ ቼክ እንዳይከፈል ባንኩን (ከፋዩን) ማዘዝ ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 857)
- አውጪው ቼክ ሰጥቶ ይህ ቼክ ከመከፈሉ በፊት ቢሞት ወይም ችሎታ ቢያጣ ቀደም ሲል የሰጠው ትዕዛዝ አይሻርም (ን/ህ/ቁ 858)
- በቼክ ላይ የስርዝ ምልክት በማድረግና "የማይተላለፍ " የሚል ጽሁፍ በመጨመር የቼኩን በፊርማ የማስተላለፍ ባህሪ መገደብ ይችላል፡፡

1.2 ግዴታዎች

- በባንክ የተንቀሳቃሽ ሂሣብ መክፈት ይኖርበታል፡
- በከፈተው የተንቀሳቃሽ ሂሣብ ከሚያዝበት ገንዘብ ያላነሰ ተቀማጭ ሊኖረው ይገባል ፡፡(ን/ህ/ቁ 830 እና 899)
- የቼኩን ሰነድ በትክክል ማውጣት ይኖርበታል ፡፡(ን/ህ/ቁ 827 እና 828)
- አውጪው ከፋይ በጠየቀ ጊዜ ገንዘብ በሂሣብ መኖሩን ማጋገጥ አለበት፡፡ የሚከፈልበትን ቦታና የመክፈያውን መደበኛ ቦታ መወሰንና ስለአከፋፈሉ ዋስትና መሰጠት አለበት፡፡ (ን/ህ/ቁ 832፣ 836፣ 840)
- በአንድ ቼክ አውጪዎች ብዙ ሲሆኑ ለአምጪው (ተከፋዩ) በአንድነት ሳይከፋፈሉ ሃላፊ ይሆናሉ፡፡ይህ ግዴታ ከን/ህ/ቁ 827 እና ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1896 እና 1897 ጋር ሲገናዘብ አውጪዎች የማይከፋፈል ግዴታ ይኖራቸዋል፡፡

2. የከፋይ መብትና ግዴታዎች

2.1 መብቶች

1. አውጪው በባንክ ለአስቀመጠው ገንዘብ ባንኩ (ከፋይ) ባለሃብት ነው። አስፈላጊ ለሆኑት ስራዎች ሊገለገልበት ይችላል ።(ን/ህ/ቁ 896)
2. በእነዚህ ምክንያቶች ባንክ ቼክን ላይከፍል ይችላል ።
   - ✓ ቼኩ በስተጀርባ ፊርማ ሳይኖረው በመቅረቱ ።
   - ✓ የተቀዳሚ ተከፋይ ፊርማ በመቅረቱ ።
   - ✓ የተቀዳሚ ከፋይ ፊርማ በትክክል ሳይፈረም ሲቀር።
   - ✓ የባለሂሣቡ ፊርማ ከሰጠው የፊርማ ናሙና ሲለይ።
   - ✓ እርምት ተደርጐ ነገር ግን ለዚህ የአውጪው ማረጋገጫ ፊርማ ሳይደረግበት የቀረ እንደሆነ።
   - ✓ ከተሰጠበት ቀን ወደፊት ተደርጐ ከተጻፈ።
   - ✓ የክፍያ ቀኑ ያለፈበት ከሆነ።
   - ✓ በአሀዝና በፊደል ያልተጻፈበት ከሆነ።
   - ✓ ክፍያው በባለ ሂሣቡ ሲታገድ ።
   - ✓ ባልተጣሩ ገቢዎች የተሰጠ ሲሆን።
   - ✓ ፅሑፉ የማይነበብ ሲሆን ።
   - ✓ ቼኩ በአውጪው ሳይፈረም ሲቀር።
   - ✓ ተጨማሪ ፊርማ አስፈላጊ ሲሆንና ሳይደረግ ሲቀር።
   - ✓ ሂሣብ የተዘጋ ሲሆን።
   - ✓ ሂሣቡ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ የተዛወረ ሲሆን።
   - ✓ በሂሣቡ በቂ ገንዘብ የሌለ እንደሆነ ።
3. ሂሣቡ እንዲዛወር በአውጪው ትዕዛዝ ሲሰጥ በቂ ስንቅ ከሌለው አላዛውርም ማለት ይችላል። (ን/ህ/ቁ 903 እና 908)
4. በሙሉም ይሁን ለከፊል ክፍያ ደረሰኝ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።
5. የአውጪውንና የመጨረሻውን የጀርባ ፊራሚዎች ፊርማ መርምሮ ለማጣራት መብት አለው። (ን/ህ/ቁ 860)

2.2 ግዴታዎች

- ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ባንኩ በአስቀማጩ ገንዘብ እንዲከፈል ሲጠይቅ መክፈል አለበት።
- የሂሣብ መግለጫ በየጊዜው አዘጋጅቶ መሰጠት አለበት (ን/ህ/ቁ 900)
- ከአስቀማጩ ጋር ከተዋዋለው ውጪ ወይም አስቀማጩ ካዘዘው ውጪ ሌላ ዓይነት አሰራር ሊፈጸም አይችልም። (ን/ህ/ቁ 897)

- አውጪው አንድ ቼክ ሰጥቶ ከመከፈሉ በፊት ቢሞት ወይም ችሎታ ቢያጣ ባንኩ ይህንን ምክንያት በማድረግ ክፍያን መከልከል አይችልም።(ን/ህ/ቁ 858)
- ቼክ አውጪው ክፍያውን ለአስቆመበት ምክንያት ዋቢ መሆኑን ይገልጻል። (ን/ህ/ቁ 857)
- ከመክፈሉ በፊት ፊርማውን ከናሙናው ጋር ማገናዘብ አለበት። (ን/ህ/ቁ 860)

6.6.3.4 በቼክ ላይ የሚነሱ አከራካሪ ነጥቦች

ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው ከሆነ በባንክ የተቀመጠ በቂ ስንቅ ሳይኖራቸው አንዳንድ ሰዎች ቼክ አዘው ሳይከፈል ተመላሽ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የወንጀል ክስ ሲቀርብ የአውጭው መከላከያ ቼኩን የሰጠሁት በመያዣነት በዕዳ ማረጋገጫነት ነው የሚል ነው። የመያዣ ሰነዶችና የቼክ አጠቃቀምና ዓላማ ግን የተለያየ ነው። የን/ህ/ቁ 842-852 ስለቼክ ሰነድ መተላለፍ ይደነግጋሉ። በዚህ ርዕስ ስለቼክ በመያዣነት መስጠት የሚገልፅ ነገር የለም። ከዚህም ሌላ ቼክ ከሐዋላ ወረቀት ጋር በተመሳሳይ ድንጋጌዎች ይመራል ሲል የሚደነግገው ን/ህ/ቁ 886 ቼክ በመያዣነት ወይም በዕዳ ማረጋገጫነት ሊያዘ እንደማይችል ያረጋግጣል። ከቼክ በተለየ ሁኔታ የተሰፋ ወረቀቶችንና ሃዋላን ስለ ዋስትና ዋጋ (መያዣ) መያዝ እንደሚቻል በን/ህ/ቁ 825 (1) (ሀ) እና 754 በግልፃ ተደንግጓል። ለተስፋና ለሃዋላ ወረቀቶች የጋራ ድንጋጌዎች ለሆኑት አንዱ የተሰፋ ሰነድን በመያዣ መስጠት ይቻላል የሚለው ነው። በቼክ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑትን የሐዋላ ወረቀት ድንጋጌዎችን የሚዘረዝረው የን/ህ/ቁ 886 የሃዋላ ወረቀትን በመያዣነት መስጠት ይቻላል የሚለውን ድንጋጌ ለቼክ ተፈፃሚ እንዲሆን ያላደረገው ያለ ምክንያት አይደለም። የቼክ ሰነድ ዓላማው፣ አሰራሩና ጥቅሙ ለመያዣ ያለ መሆኑን ነው።

በቼክ ላይ የሚፃፈው ቀን ቼኩ የወጣበት ወይም የተሰጠበት ቀን ሲሆን የሚከፈለው ከዚሁ ቀን ጀምሮ ነው። የሐዋላ ወረቀትን ወይም የተሰፋ ሰነድን ግን በወጣበት ቀን ሳይሆን ወደፊት እንዲከፈል አድርጐ መፃፍ በንግድ ህግ ስለሚፈቀድ ተከፋዩ ሰነዱን አስይዞ ሊበደርበት ወይም ወደፊት ለሚከፈል ዕዳ ክፍያ መያዣ ወይም ዋስትና ሊያደርገው ይችላል። የን/ህ/ቁ 754ም ይህንኑ ይፈቅዳል። ቼክን በተመለከተ ግን የነ/ህ/ቁ 754 ተፈፃሚ ያልተደረገ ስለሆነ በዋስትና ወይም መያዣነት መጠቀም አይችልም ማለት ነው። ምክንያቱም በቼክ ላይ የሚፃፈው ቀን ቼክ የወጣበት ወይም የተሰጠበት ቀን መሆን ስላለበት፣ ቼኩም እንደቀረበ መክፈል ስላለበት፣ ለብድር ወይም ወደፊት ለሚከፈል እዳ በዋስትና ወይም በመያዣነት እንዲያገለግል ለማድረግ የሰነዱ ጠባይ የማይፈቅድ ከመሆኑም በላይ የንግድ ሕጉም አይፈቅድም። (ቁ. 827፣ 828፣ 854 እና 856)

ቼክን በመያዣነት ወይም በዋስትና መስጠት ከአገራችን ህጐች እና ከአጠቃላይ መርሆች አንፃር ሲታይ አንድ ሰው ቼክ ሲፈርም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚበቃ ገንዘብ መኖሩን በማረጋገጥ ነው። ቼክ ፈራሚው እና ተቀባዩ በቼክ አጠቃቀም ላይ ህግ

ከሚፈቅደው ውጭ ሊዋዋሉ አይችሉም፡፡ተዋውለው ቢገኙም የሚፀና አይሆንም፡፡ ይህ የቼክ አጠቃቀም መርህ መሆኑ ቢታወቅም ባገራችን ካለው የተሳሳተ የቼክ አጠቃቀም በርካታ ሰዎች ተከሰው ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ ቼክ ፈረመው መስጠታቸው በማመን በመከላከያት እኔ ይህንን ቼክ ለተቀባዩ ፈርሜ የሰጠሁት በዋስትናነት (በመያዣነት) እንዲያገለግለው እንጂ ወደ ባንክ ሂዶ ገንዘብ እንዲጠይቅበት አይደለም ብለው ሲከራከሩ ይስተዋላል ፍርድ ቤቶች ቼኩ የተሰጠው በዋስትናነት በመያዣነት እንዲያገለግል ብቻ ነው የሚለው ክርክር እንዳለ ቢቀበለውም እንኳ ክርክሩ የሚቀጥሉትን ሌሎች ጥያቄዎች ማንሳቱ አይቀርም፡፡

- ቼኩ በህግ በተፈቀደው ጊዜ ክልል ውስጥ ባንክ ቀርቦ ገንዘብ የማያስገኝ ከሆነ የዋስትና (የመያዣነት) አገልግሎቱ የት ላይ ነው?
- በዚህ መልክ የቆየ ግልፅ የሆነ ስምምነት ካስ ግል ተበዳዮች ወደ ባንክ ለምን ይሄዳሉ? ለምንስ ክስ ያቀርባሉ?
- ቼኩ ወደ ባንክ ቀርቦ ገንዘብ የማያስገኝ ከሆነ ለመብቱና ለግዴታው መንስዔ የሆነውን ውል ለምን በሌላ ፅሁፍ አያደርጉም? ቼክስ ይህንን የፅሁፍ ውል በመተካት ሊያገለግል ይችላልን?
- ቼክ ተፈርሞ የተሰጠው ለዋስትና ለመያዣነት እንዲያለግል መሆኑ በሌላ ማስረጃ ቢረጋገጥ ቼኩ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ የባንክ መረጋገጫ ከተሰጠበት በኋላ በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚኖረው ህጋዊ ውጤትስ ምንድን ነው?
- በአንድ ተዋዋይ ወገን በሚገባው ውል መተማመኛ የሚሆን የማይመነዘር ቀንና የገንዘብ መጠን ያልተፃፈበት ባዶ ቼክ ፈርሞ ምስክሮች ባሉበት ለአንድ ተዋዋይ ወገን ቢሰጠው እና ይህንን ባዶ ቼክ ሌላኛው ወገን ይህንን ቼክ ቀኑንና የገንዘቡን መጠን ሞልቶ ባንክ ድረስ በመውሰድ በቂ ስንቅ የለውም የሚል ማረጋገጫ በመያዝ ቼክ ፈራሚው በማጭበርበር ወንጀል ቢከሰው ተከሳሹ ፍርድ ቤት ቀርቦ እኔ ይህንን ቼክ የሰጠሁት በመተማመኛነት ነው ቼኩም እንዳይመነዘር ቀኑን እና የገንዘቡን መጠን ሳልሞላ የሰጠሁት ስለሆነ በወንጀል እኔን አይስጠይቀኝ ያውም መከሰስ ያለበት ግል ተበዳይ ነኝ ባይው ነው ብሎ ቢከራከር በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው? በፍትሀብሔርስ በቼኩ ላይ ለተጠቀሰው ገንዘብ ተጠያቂ መሆን አለበትን?
- ቼክን በከፊል መክፈል ከወንጀል ተጠያቂነት ሊያድን ይችላልን? ን/ህ/ቁ/859
- በቼክ ላይ የሚደረግ እርቅ ከወንጀል ተጠያቂነት ይከላከላልን?
- ከአቅም በላይ የሆነ እክል ከወንጀል ተጠያቂነት ያድናልን?
- አንድ ቼክ ወደ ባንክ ቀርቦ በቂ ስንቅ የለውም ከተባለ በኋላ ለአውጪው ቢመለስለት ከጅምሩ እንዳልተሰጠ ሊቆጠር ይችላልን?
- የመክፈል ትዕዛዝ የተሰጠበትን በን/ህ/ቁ/ 857 መከልከል የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላልን?

- ❖ የማታለል ወንጀል ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ሊፈጸም የሚችል ወንጀል ነውን? አይደለም ከተባለ ወ/ህ/ቁ/693(2) ለምን አስፈለገ? የሚሉ ጥያቄዎችን እንድናነሳ የሚያደርገን ነው።።

ስለዚህ በቼክ የመጠቀም ልምድ በሀገራችን ከምን ጊዜም በበለጠ ሁኔታ እያደገ የመምጣቱን ያህል ችግሮችን በተለያዩ ምክንያቶች እየበዙ መሄዳቸው ውሎ ያደረ የፍርድ ቤቶች ችግር ሆኖዋል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በባንኮችና ደንበኞቻቸው መሃከል ቅን የሆነ አስተሳሰብና ሀጋዊ አጠቃጠም እንዲከተሉ የሚያስችል ትምህርትና ከዚያም አልፎ ቼክን ያለ አግባብ የሚጠቀሙት ደንበኞች ላይ የባንክ አገልግሎት እንዳያገኙ እስከ መከልከል ድረስ የሚዘልቅ ጠንከር ያለ እርምጃ ባንኮች እንዲወስዱ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን በቼክ የመጠቀምን አላማ እጅጉን ከመጉዳቱ በተጨማሪ ሰዎች በወንጀል አየተከሰሱ መቅረብንና ተጨማሪ ወጭን መጠየቁ የማይቀር ነው።

6.4.4 የመንገድ ቼክ (Travelers cheque)

የመንገድ ቼክ ምንነት በን/ህ/ቁ 887 ላይ "የመንገድ ቼክ ማለት ገንዘብ ተከፋይ የአውጪው ባንክ ቅርንጫፍ በሆነ ባንክ ወይም ከዚህ ከአውጪ ባንክ ጋር ግንኙነት ባለው በማንኛውም ባንክ ገንዘብ እንዲቀበል በሰነዱ ውስጥ የሚቀበለውን ገንዘብ ልክ ፅፎ አንድ ባንክ ለደንበኛው የሚሰጠው ሰነድ ነው" በማለት ትርጉም የተሰጠው የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ሲሆን በመንገድ ቼክና ሌላው ዓይነት ቼክ መካከል ያለውን ልዩነት ስንመለከት በሌላው ቼክ ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች በመንገድ ቼክ ተፈፃሚነት እንደማይኖራቸው ን/ህ/ቁ 890 ሲደነግግ። አንድ የመንገድ ቼክ ቢጠፋ በቀላሉ መተካት የሚቻል ሲሆን ሌላው ቼክ ቢጠፋ ግን ክፍያ እንደዳይፈፀምበት ትእዛዝ በን/ህ/ቁ 857 መሰረት ይሰጥበት እንደሆነ እንጂ መተካት ኣይቻልም። በመንገድ ቼክ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ህጎች ን/ህ/ቁ 715-734 እና ወ/ህ/ቁ 693 ናቸው። ስለዚህ የመንገድ ቼክ ደንበኞቹ በቀላሉ የገንዘብ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ከባንክ ወደ ባንክ የሚደረግ የገንዘብ ዝውውር መሳሪያ ነው።

6.4.5 በሰነዶቹ መካከል ያለ ልዩነትና ተመሳሳይነት

የቼክና የሐዋላ ወረቀት ተመሳሳይነት

- የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መሆናቸው
- ለአምጪው ወይም አምጪው ላዘዘለት ሶስተኛ ወገን ወይም አውጪው ለራሱ የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፈለው ትእዛዝ የሚሰጥባቸው በመሆናቸው የሚያመሳስል ባህሪ ያላቸው ሲሆኑ ልዩነታቸውም፤-
  - ➢ በሐዋላ ወረቀት ክፍያን ወደፊት ማድረግ የሚቻል ሲሆን በቼክ ግን ይህ አሰራር ተቀባይነት የለውም። (ን/ህ/ቁ 855 እና 848)

- በሐዋላ ሰነድ ወለድ ተከፋይ መሰጠት ይቻላል የሚል ትእዛዝ ሊኖር ሲችል በቼክ ግን ይህ አሰራር አይኖርም፡፡ (ን/ህ/ቁ 835 እና 739)
- በቼክ ገንዘብ ለመክፈል አውጪው በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ ሊኖረው ይገባል፡፡ በሐዋላ ግን ይህ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ (ን/ህ/ቁ 830)
- በቼክ ከፋይ ሁል ጊዜም ባንክ ነው፡፡ በሃዋላ ግን ከፋይ ባንክ ላይሆን ይችለል፡፡
- በሐዋላ ወረቀት ጀርባ የሚፈርም ሰው ሰነዱን ለመቀበልና ለመክፈል ዋስ ሲሆን በቼክ ጀርባ ሚፈርም ሰው ደግሞ ለአከፋፈሉ ዋስ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 750 እና 846)
- የሃሐዋላ ወረቀት በእሽታ መረጋገጥ አለበት ቼክ ግን እሽታ አያስፈልገውም፡፡ (ን/ህ/ቁ 854) በቼክና የተሰፋ ሰነድ መከከል የለው ተመሳሳይነት ሁለቱም የሚተላለፉ እና እንደቀረቡ የሚከፈሉ ሰነዶች መሆናቸው ሲሆን ልዩነታቸውም
- ❖ ቼክ ገንዘብን ተክቶ የሚሰራ እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ ሲሆን የተሰፋ ሰነድ ግን ከወደፊት ግዴታ ጋር የተያያዘ የእዳ ክፍያን የማረጋገጥ ዓላማ ያለው ነው፡፡
- ❖ በተስፋ ሰነድ የወለድ ውል መግባት የሚቻል ሲሆን በቼክ ግን የዚህ ዓይነት ውል ማድረግ አይቻልም በሌላ አነጋገር በቼክ ላይ የዚህ ዓይነት ውል ቢደረግም ህጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡ (ን/ህ/ቁ 835፣ 739 እና 825) በቼክና በመንገድ ቼክ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ስናይ ደግሞ፤-
- የመንገድ ቼክ ቢሰረቅም ቢጠፋም ያለምንም ችግር ሊተካ ይችላል፡፡
- በን/ህ/ቁ 890 መሰረት በቼክ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት ደንቦች በመንገድ ቼክ ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡ በመንግድ ቼክ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት ህጎች ወ/ህ/ቁ 693

  ን/ህ/ቁ 715 – 731 እና ን/ህ/ቁ 732 – 734 ያሉት ብቻ ናቸው
- ቼክ ሰነዱ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ በ6 ወር ውስጥ መከፈል ሲኖርበት የመንገድ ቼክ ግን ከተፃፈበት ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ያገለግላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 855 እና 888 (7))
- በመንገድ ቼክ ላይ "ላዘዘለት" የሚል ቃል ወይም ይህ ቃል ከሌላ “የማይተላለፍ” የሚል ቃል እንዲኖርበት የሚያስፈልግ ሲሆን ይህ ሁኔታ በመደበኛው ቼክ አስፈጊ አይደለም፡፡ (ን/ህ/ቁ/888(5))
- የመንገድ ቼክ አውጪ (drawer) ባንክ ሲሆን የመንገደኛ ቼክ አውጪ (drawer) በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሣብ ያለው ሰው ነው፡፡

ስለዚህ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የሚተላለፉ ገንዘቦች ጠቀሜታ ከፍተኛ የመሆኑ ያህል በርካታ ጥያቄዎች ሊያስነሱ እና በፍ/ቤቶች የተለያየ ግንዛቤ ሊያዝባቸው እንደሚቻል ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት ይቻላል ። ስለሆነም በዚህ ርዕስ ጉዳይ የሚደረግ ውይይት በዚህ አጭር ማብራርያ የሚያልቅና ይበቃዋል የሚባል ባለመሆኑ ይህን ፅሁፍ በመነሻነት ተጠቅመን በዕለተ ተዕለት ስራችን ልናሰፋውና እርስ በርሳችን በመናደርገው ውይይት ያለውን የግንዛቤ ክፍተት ማጥበብ ይጠበቅብናል።

<u>የመወያያ ነጥቦች</u>

1. አንድ በሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ የተከሰሰ ሰው የሚኖሩት መከራከርያዎች ምንድን ናቸው? በሁለ አቀፍ (universal) መቃወምያና ግላዊ ግንኙነት (personal relation) መቃወምያ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
2. ቼክ በመያዣ ሊሰጥ የሚችል የገንዘብ ሰነድ ነውን? ለምን?
3. በሃዋላ ወረቀትና ቼክ መካከል ያለው ተመሳሳይነትና ልየነት ምንድን ነው? በተስፋ ሰነድና ቼክ ያለው ልዩነትስ?
4. በጀርባ ፊር የገንዘብ ሰነድ የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤቶች ምንድን ናቸው?
5. የሃዋላ ወረቀት የሚተላለፈው እንዴት ነው?
6. አንድ ቼክ ለክፍያ ቀርቦ ክፍያ የማይፈፀምባቸው ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?
7. አንድ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ጀርባ ላይ ፊርሞ በማስተላለፉ ምክንያት ሌሎች በጀርባ ፊርመው አስተላላፊዎችን ከሃላፊነት ነፃ ሊያዳርጋቸው ይችላልን?
8. በዋስትና ስም በሰነዱ መፃፍ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው?
9. የባንክ ደንበኛ መብቶችና ግዴታዎች ምንድን ናቸው? የባንክ መበትና ግዴታዎችስ?
10. የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ በቁጥር 693 ላይ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክን ማውጣት በወንጀል ሃላፊነት እንደሚያስጠይቅ ይደነግጋል። ን/ህ/ቁ 859 ደግሞ በከፊል ክፍያ መፈፀምን ይፈቅዳል። ከነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት አንድ በወጣው ቼክ ላይ በከፊል ክፍያ የፈፀመ ሰው ከወንጀል ሃላፊነት ሊያመልጥ ይችላልን? ለምን?

7. የመክሰር ህግ

7.1. የመክሰር ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጥ

የመክሰር ህግ ታሪካዊ አመጣጥን እድገቱ ከሰው ልጆች የግብይት ስርዓት ማደግ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደሆነና ከጥንት ሮማውያን ጀምሮ ቀስ በቀስ የሃቀኛ ተበዳሪ መክሰርንና ለሌላ ቅጣት ከመዳረግ ይልቅ ዕዳው በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም የማድረግና በሌላ በኩል ደግሞ የገንዘብ ጠያቂዎችን የንብረት መብት ለማስጠበቅ ታስቦ የመጣ የህግ ማእቀፍ መሆኑን የዘርፉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ የዚህ በዘገምታዊ እድገት ኣሁን ወደ ደረሰንበት ዘመነ ግሎባላይዘሽን የዘለቀው የመክሰር ሕግ ከዘመናዊው ዓለም ኣንፃር ያለው ዓላማን መሰረት በማድረግ አንድ ፀሃፊ “Bankruptcy laws are no longer used primarily to punish an insolvent, but more often to release (discharge) and Rehabilitate him.” በማለት ገልያታል፡፡ ስለዚህ የመክሰር ህግ የራሱ የሆነ ጤናማ የኢኮኖሚ ግንኙነት የመፍጠርና ግንኙነቱ ሲደፈርስም ስርዓት ባለው መንገድ አንዱ የሌላውን ሃብት በመውሰድ እንዳይበለፅግና ሁሉም በሃብት ላይ ያለውን የተጠቃሚነት መብቱን እንዲሰራበት ለማስቻል የሚወጣ ህግ ነው፡፡ የመክሰር ህግ ለመጀመርያ ጊዜ የወጣው በጣልያን አገር ሲሆን በኛ አገር ህግ ሆኖ የወጣው በ1933 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ህግ የቱን ያህል በስራ ላይ እንደዋለ ባይታወቅም አሁን በ1960 ዓ.ም በወጣው የንግድ ሀጉ አምስተኛ መፅሃፍ እስከታወጀበት ጊዜ የአገራቱ ህግ የ1933 ዓ.ም የመክሰር ህግ (Bankruptcy law) እንደነበር ይታወቃል፡፡

የመክሰር ትርጉምን በሚመለከት የተለያዩ ፀሃፍት የተቀራረበ ግን ደግሞ የመስፋትና መጥበብ ሁኔታ በሚስተዋልበት ኣግባብ እየተጎሙት የመጡ ሲሆን ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ እነዚህ ቀጥሎ ያሉትን ትርጓሜዎች ለማስፈር ተሞክሯል፡፡

> *Bankruptcy can be defined as both a collective and universal mode of execution, collective in the sense that it puts secured and unsecured creditors more or less on an equal footing, universal is a sense it applies to the total estate of the bankrupt person. The goal of this procedure is either to save the enterprise by a composition with creditors or to liquidate it, which may bring into play different loses of right or penalties for the debtor in bade faith in particular.*

Bankruptcy is a situation where, one who by his acts and conducts affords evidence of his inability to pay or his intention to avoid payment of his debt.”

ን/ህ/ቁ 969 ስለመክሰር የሚያስፈልግ ሁኔታ በሚል ስር “ማንኛውም ከንግድ የተያያዘውን ዕዳውን መክፈል ያቋረጠና መክስሩ በፍርድ የተወሰነ ሁሉ የከሰረ ሆኖ የሚቆጠር ነው” በማለት ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ መክሰርን መሰረት በማድረግ የተሰጡ ትርጓሜዎች መገንዘብ እንደሚቻለው መክሰር ዕዳን ለመክፈል ካለመቻልና ይሄውም በፍርድ ቤት ከሰሯል የሚል ውሳኔ ሲሰጥበት አንድ ሰው ከስሯል ሊባል እንደሚችል ነው፡፡ በሌላ ኣባባል አንድ ሰው ዕዳውን መክፈል ኣለመቻሉ ብቻ እንደከሰረ እንደማያስቆጥረውና ከስሯል ብሎ የመወሰን

ስልጣን ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ እንጂ ሁሉም በያላበት እከሌ ከስሯል ስላለ ብቻ በንግድ ህጉ እይታ ከስሯል እንደማይባል የሚያስረዱ መሆናቸውን ነው።

አሁን በስራ ላይ ባለው የንግድ ህግ መክሰርን መሰረት በማድረግ የተደነገጉት ህጎች በዋናነት የአምስተኛው መፅሃፍ አንቀፅ 1-5 ያሉት ሲሆኑ ከ1-4 የተደነገጉት የህጉ አርቃቂ የነበሩት Professor Escarra ህጎቹን የወሰዱዋቸው በ1955 ዓ.ም ከተሻሻለው የፈረንሳይ ህግ ሲሆን ከሳቸው መሞት በኋላ የንግድ ህጉን የማርቀት ስራ የተረከቡት Professor Janffret በንግድ ህጉ አንቀፅ 5 ላይ ማለትም ከን/ህ/ቁ 1119-1166 ያሉትን ድንጋጌዎች በዋናነት የወሰዱት ከ1942 ዓ.ም የጣልያን ህግ ነው።

የአምስተኛው መፅሓፍ አደረጃጀት በአምስት አንቀፆች የተከፈለ ሲሆን

አንቀፅ አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌዎች
አንቀፅ ሁለት - ስለመክሰር
አንቀፅ ሶስት - የመጠበቅያ ስምምነት
አንቀፅ አራት - ስለማህበሮች መክሰርናተመጠበቅያ ስምምነቶች የሚፀኑ ልዩ ውሳኔዎች
አንቀፅ አምስት- ኣጭር ስነ-ስርዓት

በሚል የተደራጀ ነው። ኣካሄዱ የባለ ዕዳ ንብረት ማጣራትን (Liquidation) ከባለ ዕዳው ንግድ እንዲያገግም ከማድረግ (rehabilitation) የሚመርጥ ነው። ይህንን ከንግድ ህጉ ለማጣራት የሰጠው የህግ ሽፋን መገንዘብ ይቻላል። ህጉ የባለ ዕዳው ንብረት እንዳይነጣጠል (dismemberment) የሚሰጠው ግምት በጣም ውሱን መሆኑ ሌላው የትኛውን ኣካሄድ እንደመረጠ ማሳያ ነው። ህጉ በሌላ በኩል የገንዘብ እጥረት የገጠማቸው ባለዕዳዎችና ባለገንዘቦች ሁለት አማራጭ መንገድ ማለትም የመክሰር ማስታወቅያ እንዲሰጥ የመጠየቅ ወይም የመጠበቅያ ስምምንት (Schema of arrangement) ተጠቅመው ጉዳያቸውን ማስኬድ እንደሚችሉ የሚፈቅድ ነው። የኢትዮጵያ ንግድ ህግ የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ኮሚሽን ንግድ ህግ (UNCITRAL) ከሚከተለው ኣሃዳዊ ኣካሄድ (Unitary approach) አንፃር ሲታይ የተለያዩ መነሻዎችን ወይም አማራጮችን የሚጠቀም በመሆኑ ኣሃዳዊ ኣካሄድ ከሚከተለው የገንዘብ እጥረት ያለበትን የንግድ መደብር እንደገና እንዲደራጅ (Reorganization) መጀመርያ ማካሄድና ዕዳውን እንዲከፍል ማስቻል፤ ይህ ሳይሳካ ሲቀር ብቻ ወደ ሃብት ማጣራት (liquidation) መሄድ ከሚለው ጋር የሚፃረር ነው። በሌላ በኩል አሁን በዓለም እየተስፋፉ ካለው ረጋ በልና ተመልከት(wait and see period) አንፃር ሲታይም አንድ ንግድ (Business) ከስሯል ብሎ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ቶሎ የመክሰር ውሳኔ ይሰጥልኝ ወደሚለው መግባት ተመራጭ ኣይደለም የሚለውን ኣካሄድ የሚከተል ባለመሆኑ የማስተዋል (observation period) ጉዳይ ለወደፊቱ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ሌላው በንግድ ህጉ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የህጉ አቀራረፅ ሁለት (dual) አካሄዶችን ማለትም መክሰርና የመጠበቅያ ስምምነትን በጠቅላላ በሚል ከን/ህ/ቁ 974-1118 ባሉ ድንጋጌዎች እንደገና ደግሞ በአንቀፅ አራት ስለማህበራት በሚል ለሁለት ከፍሎ መደንገጉ የመጀመርያዎቹ ድንጋጌዎች በማህበራትም ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በመሆኑ ስለማህበራት የተለየ ህግ የሚያስፈልግ ቢሆንም እነዚህ ህጎችም እዚያው እንዲካተቱ ቢደረግ የተሻለ በመሆኑ ሌላው የትኩረት የሚያሻው ጉዳይ እንዲሆን የሚያደርገው ነው።

መክሰር የሚለውን ቃል የንንድ ህጉ በእንግሊዝኛ (Bankruptcy) የሚለውን ቃልና በን/ህ/ቁ 542(3) 'Insolvency' ለሚለው ቃል ከሚጠቀም ውጭ በሌሎቹ ድንጋጌዎች ወጥነት ባለው መልኩ ''Bankruptcy'' የሚል ቃል የሚጠቀም ቢሆንም በነዚህ ሁለት ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት ያክል አንድ ፀሃፊ በመጣጠፋቸው ያስፈሩትን ብንመለከት፤-

> *The leading distinction between a bankruptcy law and an insolvency law in the proper technical sense of the words consists in the character of the persons upon whom it is designed to operate the former contemplating as to objects traders of a certain description, the later insolvents in general, or persons unable to pay their debts.*

በማለት በሁለቱም መካከል ያለው ልዩነት "Bankruptcy" በዋናነት ከንግድ ጋር የተያያዘን መክሰር ሲያመለክት "insolvency" ግን ማንኛውንም ዕዳውን ለመክፈል ያልቻለን ሰው እንደሚመለከት አብራርተዋል። ሆኖም ግን መክሰር የሚለውን አባባል ከንግድ ጋር ብቻ የተያያዘ የመሆኑ ጉዳይ አሁን ባለንበት ዘመነ ግሎባላይዘሽን ብዙ አገሮች መክሰር "Bankruptcy" ከንግድ ጋር ብቻ ተያይዞ መታየት የለበትም ከሚል አመለካከት በመነሳት መክሰር በማንኛውም ዕዳውን ለመክፈል ባልቻለ ግለሰብም ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚያስችል ህግ በማውጣት ላይ ናቸው። ን/ህ/ቁ 968 ከዚህ አኳያ ሲታይ ዓለም አቀፍ ተቀባይነቱ እምብዛም የጎላ አይደለም።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የ1952 ዓ.ም ንግድ ህግ ከወጣ ወዲህ የተለያዩ መንግስታትንና በነዚህ መንግስታት በየግዜው ከንግድ ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በርካታ አዋጆች አስተናግዳለች። አሁን ካለው ህገ-መንግስታዊ ስርዓት አንፃር እንኳን ብንመለከት ን/ህ/ቁ 968 እና 1155 ከሚደነግጉት ውጭ ናቸው ብሎ ለመደምደም የሚያስቸግር ቢሆንም መንግስት የባንኮችን መክሰር (Bankruptcy of banks) በተለየ ሁኔታ ስለ ባንክ ስራ የወጣ አዋጅ ቁጥር 592/2008ዓ.ም እንዲገዛ ያደረገበት ሁኔታ ያለ ስለመሆኑ ከዚህ አዋጅ ይዘት ለመረዳት ይቻላል። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ያለው የአገሮች አሰረራር ጥቂት አገሮች እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች የተለየ የባንኮች የመክሰር ህግ በማውጣት የሚተዳደሩ ሲሆን ከእንግሊዝ በስተቀር አብዛኛዎቹ የአውሮፓ አገሮች የሚከተሉት አሰራር የባንኮች የመክሰር አሰራር በዋናነት በንግድ ህጉ ባለ የመክሰር ህግ እንዲገዛ ግን ደግሞ ከባንክ ልዩ ስራና ባህሪ ጋር

የሚሄድ ሌላ የንግድ ህጉ ደጋፊ ህግ (supplementary law) በማውጣት የመክሰር ስርዓቱ እንዲመራ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ በኢትዮጵያ ያለው የባንኮች የመክሰር ህግ ከአሜሪካው የህግ ስርዓት ጋር ማለትም የተለየ ህግ በማውጣቱ ረገድ የሚመሳሰል ነው ሊባል ይችላል፡፡

የስለ ባንክ ስራ የወጣ አዋጅ ቁጥር 592/2000 ይዘት በምንመለከትበት ጊዜ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን ፈቃድ መሻርን (revocation of license) ሞግዚትነት (receivership) እና ማጣራትን (Liquidation) ከንግድ ህጉ በተለየ መልኩ በአዋጅ አንቀፅ 33 እና 34 (1) ከአሁን ቀደም የከሰረ ሰው ንብረት ጠባቂ (trustee) ለሚለው ሞግዚት እና ኮሚሽነር በሚለው ምትክ ብሄራዊ ባንክን የሚገለገል በመሆኑ ከንግድ ህጉ አሳባል የተለየ አገላለፅን የሚጠቀም ህግ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በንግድ ህጉ የተደነገጉትን ን/ህ/ቁ 1071፣ 1072፣ 1081፣1119 የባንክ መክሰርን በሚመለከት ሂደቱ የተለየ እንዲሆን በሚያደርግ መልኩ የተደነገገ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 39-46 ያሉት ድንጋጌዎች ስለ ሞግዚት ስልጣንና ተግባርና ሌሎች የሞግዚት አገልግሎቶች ፣ በሞግዚት የሚቀርብ ክርክርና (receivership proceeding) የሞግዚት አገልግሎት መጠናቀቅ በማስመልከት የሚደነግጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በንግድ ህጉ ከን/ህ/ቁ 989-1003 ያሉት ድንጋጌዎች በባንክ መክሰር ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 48 የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች በባንክ መክሰር ጉዳይ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ከአዋጁ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ነው የሚል ድንጋጌ የያዘ በመሆኑ ይህ አዋጅ የንግድ ህጉ በባንክ መክሰር ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆን ባይከለክልም አዋጁን እንደ ዋና ህግ የሚወስድ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ህግ በመንግስት ልማት ድርጅቶች (public enterprises) ያለውን ተፈፃሚነት በምንመለከትበት ጊዜም እነዚህ የልማት ድርጅቶች ምዝገባቸው በዋናነት በልዩ የምዝገባ ህግ ማለትም በሽግግር መንግስት ቻርተር መሰረት በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1992 ሲሆን ከዚያም በንግድ ህጉ መሰረት በንግድ መዝገብ የሚመዘገቡ ናቸው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 25/92 አንቀፅ 40 የልማት ድርጅቶች መፍረስና ማጣራት በንግድ ህጉ አምስተኛ መፅሓፍ ድንጋጌዎች እንደሚገዙ ስለሚደነግግና ለመፍረስና ለማጣራት እንደምክንያት የሚወስዱት ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀፅ 29(6) የሚዘረዝር በመሆኑ የንግድ ህጉ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚያስችል ነው፡፡ በዚህ አዋጅ የተለየ ነገር ቢኖር በአንቀፅ 40(2) የተደነገገው ኣሮር ስነ-ስርዓት የመከተሉ ጉዳይ በን/ህ/ቁ 1076(1) (2) የተደነገገው የገንዘብ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በልማት ድርጅቶች ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚደነግግ መሆኑ ላይ ነው፡፡ የነዚህ ድርጅቶች መፈረስና ሂሳብ ማጣራት ጉዳይ የሚዳኘው በአዋጁ አንቀፅ 39-44 ባሉ ድንጋጌዎች ሲሆን አንድ የልማት ድርጅት የሚፈርሰው በአንቀፅ 39 መሰረት፡-

- በማቋቋሚያው ደንብ የተመለከተው የድርጅቱ የመቆያ ጊዜ ሲያልቅ፣
- ድርጅቱ የተቋቋመበት ስራ ሲያልቅ፣
- ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ ሲከሽፍ ወይምሊፈሸመ የማይችለ ሲሆን፣

- ከመቶ ሰባአምስት(75 በመቶ) የሚሆነው የተከፈለው የድርጅቱ ካፒታል ሲጠፋ፣
- የሚኒሰተሮች ምክርቤተ የድርጅቱን ህልውና የሚነካ ውሳኔ ሲሰጥ
- የድርጅቱ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን እንደሆነ ይደገማል።።

ይህ የሚያሳየው የልማት ድርጅቶች መክሰር ከንግድ ህጉ በዙም ያልተለየ ቢሆንም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ የሚፈርሱበት አሰራር መኖሩ ግን የአዋጁ የተለየ ገፅታ ነው።። **ለምሳሌ፤-** መንግስት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በደንብ ቁጥር 124/1993 የተቋቋመውን ''Engineering Design and Tool Enterprise'' በደንብ ቁጥር 15/19997 እና በደንብ ቁጥር 38/1998 የተቋቋመውን ''Addis Metal Pressing Enterprise'' በደንብ ቁጥር 102/2004 እንዲፈርሱ ማድረጉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በፍ/ቤት ከስረዋል የሚል ውሳኔ ሊተላለፍባቸው የሚችሉ ቢሆንም የመንግስት ንብረት በመሆናቸው በራሱ ውሳኔ ሊያፈርሳቸው እንደሚችል ግልፅ ነው።። ስለዚህ የኢትዮጵያ የመክሰር ህግ በዋናነት ከአህጉራዊ አውሮፓ የተወሰደና በሁለት የተለያዩ አርቃቂዎች የተዘጋጀ ሆኖ አሁን ዓለም ከደረሰበት እድገት ጋር በመራመዱ ሂደት የራሱ ውሱንነት ያለውና ከህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ህግ እንዲኖረን አዲስ የንግድ ህግ የማርቀቁ ስራ በሂደት ያለ መሆኑና የባንክ መክሰር ሁኔታ በሌላ ህግ እንዲገዛና የልማት ድርጅቶችን የመፍረስና የማጣራት ሂደት የንግድ ህጉን በማመሳሰል (*Mutatis mutandis)* መገልገልን የሚፈቅድ ግን ደግሞ የራሳቸው ህግ እንዲኖራቸው የተደረገበት የህግ ስርዓት ያለን መሆኑ ልንገነዘብ ይገባል።።

7.2. የመክሰር ህግ ተፈፃሚነት

የተለያዩ አገሮች የተለያዩ የመክሰር ህግ (Bankruptcy Law) ያላቸው ሲሆን እንደ ኣካሄድም የተለያየ ኣሰራርን የሚከተሉ ናቸው።። **ለምሳሌ፤-** የእንግሊዝ፣ ጀርመን፣ አሜሪካ የመክሰር ህግን ያየን እንደሆነ የህጉ ተፈፃሚነት እስከ ግለሰብ የሚዘልቅ ነው።። ብእንግሊዝ ህግ በሽርካ ማህበር የተደራጀ በሚሆንበት ጊዜም በሃላፊነቱ የተወሰነ የሽርካ ማህበር ሕግ 1907 ዓ.ም መሰረት በመክሰር ሕግ ስር የሚወድቅ ነው።። ኩባንያዎች በተመለከተ በ1948 ዓ.ም የኩባንያዎች ህግ የሚገዙ ሽርካ ማህበራት ደግሞ የሚዳኙት በመክሰር ህግ (Bankruptcy law) ሳይሆን በኩባንያው ሂሳብ ማጣራት (liquidation of company) ነው።። በኣሜሪካ አገር የህግ ማእቀፍ ደግሞ የተወሰኑ ልዩነቶችን ብቻ በመፍጠር የመክሰር ህግን በግለሰቦች፣ ነጋዴዎችም ሆኑ ነጋዴ ባልሆኑ ላይ ተፈፃሚነት ያለው ነው።። ከዚህ ኣንፃር የኛ አገር ህግስ ምን ይላል? ብለን ወደ ንግድ ህጉ ስንመጣ ን/ህ/ቁ 969(1) "በዚህ *መፅሓፍ ድንጋጌዎች፣ በዚህ ህግ አንደኛ መፅሓፍ* በቁጥር 5 *መሰረት ነጋዴ* በሆኑ ሰዎችና በዚህ ህግ አንደኛ *መፅሓፍ* በቁጥር 10 *መሰረት* የኣሽሙር ማህበር ከሆኑት በቀር በንግድ ማህበሮች ሁሉ ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ።።" በማለት ስለሚደነግግ ከአርጀንቲና፣ ቤልጂም፣ ብራዚል፣ ፈረንሳይ፣ ጣልያንና ስፔን ህግ ባልተለየ መልኩ ግለሰቦች ሆነው በን/ህ/ቁ 5 የተዘረዘሩ ተግባራትን

የሚያከናውኑ ከሆነና በን/ህ/ቁ 10 መሰረት ከእሽሙር ማህበር በስተቀር ሌሎች የንግድ ማግበራት በመክሰር ህግ የሚዳኙ መሆናቸውን የሚደነግግ ነው፡፡

7.3 የሽርካ ማህበር መክሰር

አንድ የሽርካ ማህበር በን/ህ/ቁ 968(1) ስር የሚወድቅ የንግድ ማህበር ነው ብሎ ለማስተናገድ የንግድ ማህበሩ በን/ህ/ቁ 5 እና 10(1) የተዘረዘሩትን ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡፡ የሽርካ ማህበር መክሰር ለገንዘብ ጠያቂዎች ህጉ የሚሰጣቸው ጥበቃ ቢኖር የሽርካ ማህበሩ አባላት ሃላፊነት ያልተወሰነ ሃለፊነት (Unlimited liability) ከመሆኑ የሚመነጭ መብት ነው፡፡ ለዚህም ን/ህ/ቁ 255 (2) ከ32280(1) ጋር አያይዘን ማየት ይኖርብናል፡፡ ከሽርካ ማህበር መክሰር ጋር ተያይዘው የሚመጡ ሁለት የመክሰር ውጤቶች ያሉ ሲሆን አንደኛው የሽርካ ማህበሩ አባል በመክሰሩ ምክንያት የሚመጣ የሽርካ ማህበሩ መፍረስ (dissolution) ሲሆን ሁለተኛው የመክሰር ውጤት ደግሞ ሽርካ ማህበሩ ከስሯል የሚል ውሳኔ በፍ/ቤት በመስጠቱ ምክንያት የሚመጣ የማህበሩ መፍረስ ወይም በሽርካ ማህበሩ መክሰር ምክንያት የሚመጣ የአባላቱ መክሰር ናቸው፡፡ እነዚህን የን/ህ/ቁ 260(2) ከ1158 (2) እና 1163(1) ጋር አያይዘን ብናያቸው የሽርካ ማህበሩ አባል መክሰር የሽርካ ማህበሩ ከሰረ የማያሰኝ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ የሽርካ ማህበር በሚከስርበት ጊዜ የአባላቱ ሃላፊነት (Liability of partners) ያልተወሰነ ሃላፊነት (Unlimited liability) ስለሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች ገንዘባቸውን ከአባላቱ የግል ሃብት በመጠየቅ መብታቸው ማስከበር የሚችሉበት መርህ የሚከተል በመሆኑ ለገንዘብ ጠያቂዎች የሚሰጠው ዋስትና በእጅጉ አስተማማኝ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ የህም ነው አንዳንድ ሰዎች የሽርካ ማህበር መክሰር በገንዘብ ጠያቂዎች ላይ የሚያመጣው ለውጥ እስከሌለ ከሰሯል (bankrupt) ብሎ ውሳኔ መስጠቱ ሁኔታውን አይገልፀውም ወይም ‘it is a misnomer’ ሲሉ የሚስተዋሉት፡፡ ስለዚህ የሽርካ ማህበር አባላት በን/ህ/ቁ 255(2) መሰረት በአንድነት ሳይከፋፈል ሃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ገንዘብ ጠያቂዎች ያለስጋት በመብታቸው ሊሰሩበት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ በህግ የተፈጠረላቸው ናቸው፡፡

7.3.1. የሽርካ ማህበር መክሰር ክርክር

የሽርካ ማህበር መክሰርን መሰረት በማድረግ የሚነሳ ክርክር የሚመራበትን ስነ-ስርዓት በማስመልከት የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህጉም ሆነ የመክሰር ህግ በግልፅ የተባለ ነገር ባይኖርም ከን/ህ/ቁ 1158(2) እና 1163(1) ድንጋጌዎች ይዘት ግን ክሱን በሽርካ አባላቱ ብቻ ወይም ሽርካ ማህበሩንና አባላቱን በአንድነት ለመክሰስ እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ን/ህ/ቁ 1158(2) “ሳይከፋፈል የአንድነትና ያልተወሰነ ሃላፊነት ያለባቸው ማህበርተኞች ያሉበት ማህበር መክሰር ወድያውኑ የነዚህን ማህበርተኞች መክሰር ያስከትላል፡፡” ስለሚል ይህ ድንጋጌ የሽርካ ማህበሩ አባላት ገንዘብ ጠያቂዎች ገንዘባቸውን ከአባላቱ ለመጠየቅ እንዲችሉ

የማድረግ ወይም እያንዳንዱን አባል ያለበትን ዕዳ በመክፈል ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆን ዕድል የሚሰጥ ድንጋጌ ነው፡፡ የመክሰር ክርክር በሽርካ ማህበሩ አባላት ላይ በሚቀርብበት ጊዜ ስለሚኖር አካሄድ ን/ህ/ቁ 1163(1) "የማህበሩንና ሳይከፋፈል በአንድነት ሃላፊዎች የሆኑትን ማህበርተኞች መክሰር ፍ/ቤ/ቱ በአንድ ፍርድ ይገልፃል…" በማለት ስለሚደነግግ የሚኖረው የክርክር ሂደት፣ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትና ውጤቱን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት እንችላለን፡፡

አንድ የሽርካ ማህበር በመክሰሩ ምክንያት ህልውናውን እንዲያጣ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ቀዳሚዎቹ የሚሆኑት የግል ገንዘብ ጠያቂዎች (Personal creditors) እና የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች (firm's creditors) ናቸው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ከነዚህ ገንዘብ ጠያቂዎች ቅድሚያ የሚሰጠው ለማን ነው? የሚለው ጥያቄ ሲሆን ን/ህ/ቁ 1163(3) 'መክፈል ከሚገባቸው በላይ ስለ ከፈሉትገንዘብ የያንዳንዱ ማህበርተኛ መክሰር በሌላው ማህበርተኛ መክሰር ላይ ክስ ለማቅረብ የተሰጠው መብት ሳይነካ ከማህበሩ ያይ ገንዘብ ጠያቂ የሆነው ሰው ገንዘቡ በሙሉ እስኪከፈላው ድረስ ቢደረጉ ክፍያዎች ሁሉ ተካፋይ ለመሆን መብት አለው፤፤' በማለት የሚደነግግ ሲሆን ን/ህ/ቁ 256(1) በበኩሉ "ከማሕበርተኞቹ ላይ በግል ገንዘብ የሚፈልጉት ሰዎች ለባለዕዳቸው የሚደርሱትን ትርፍና ማስያዝ ይችላሉ፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ እንደዚህ ባለሁኔታ ህጉ እንዴት የሁለቱን ገንዘብ ጠያቂዎች መብት አጣጥሞ ማስተናገድ እንደሚቻል እንደ አሰራር አንድ *"the jingle rule"* የሚባል አሰራር የሚከተሉ የአገሮች ልምድ መሰረት በማድረግ ያየነው እንደሆነ የሽርካ ማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ከማህበሩ የጋራ ሃብት የመክፈል ቀዳምትነት ያላቸው ሲሆኑ በማህበሩ አባላት የግል ሃብት ደግሞ የግል ገንዘብ ጠያቂዎች ቅድሚያ እንዲያገኙ የሚያደርግ አሰራርን ተከትሎ ችግሩን መፍታት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን *"the jingle rule"* የሚፈፀመው በሁሉም ሁኔታዎች አይደለም፡፡ ይሄውም የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች

- የማህበር የሚባል ሃብት እስከነጭራሹ የሌለ ወይም ሃብት ያለው የማህበር አባል በማይኖርበት ጊዜና
- የጋራ ገንዘብ ጠያቂዎች የሽርካ ማህበር አባላቱን ገንዘብ ጠያቂዎች ገንዘብ በሙሉ በሚከፍሉበት ጊዜ የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የይከፈለን ጥያቄ ሊያነሱ ወይም ጨረታ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉበትን አሰራር የሚከተል ነው፡፡

ይህን አሰራር ወደኛ አገር አምጥተን ለማሰራት ን/ህ/ቁ 1163(5) አባባል በአንድ የሽርካ ማህበር አባል በግል ገንዘብ ጠያቂዎች አንዱ ሌላኛውን የቀዳምትነት መበት አለኝ በማለት ሊከራከረው ይችላል፡፡ እንዲሁም የአንድ የሽርካ ማህበር የጋራ ገንዘብ ጠያቂዎች በሌሎች የጋራ የገንዘብ ጠያቂዎች ላይ መቃወምያ ሊያቀርቡ ይችላሉ በሚል ካልተረጎምነው የዚህን ድንጋጌ ቀጥተኛ ይዘት "እያንዳንዱ የገንዘብ ጠያቂ ከእርሱ ጋር ገንዘብ ተካፋይ የሆኑትን ገንዘብ ጠያቂዎች መብት ለመቃወም ይችላል፡፡" የሚለውን ብቻ ወስደን የቀዳምትነት መበት ለምን መሆን አለበት? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ

በዚህ አዘጋጅ አስተያየት *"the jingle rule"* በኛም አገር የህግ ስርዓትም ብናሰራው የበለጠ ሂደቱን ውጤታማ ያደርገዋል የሚል ነው፡፡

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የሽርካ ማህበር አባል መክሰር የማህበሩን መክሰርና መፍረስ የሚያስከትል ሲሆን የማህበሩ መክሰር ደግሞ የአባላቱን በሙሉ መክሰር የሚያስከትል ሲሆን የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ወደ ማህበሩ የግል ሃብት በመሄድ መብታቸው ሊያስከብሩ የሚችሉበትን አካሄድ የሚከተል የንግድ ህግ ነው ያለን፡፡

7.4. የአክስዬንና ሃላፊነቱ የተ.የግ. ማህበር መክሰር

አክስዬንና ሃላፊነቱ የተ.የግ. ማህበር በን/ህ/ቁ 10(2) መሰረት በን/ህ/ቁ 5 የተዘረዘሩትን ተግባራት አከናወነ አላከናወነ ሁሌ ነጋዴ እንደመሆኑ መጠን የመክሰር አደጋም ሊያጋጥመው የሚችል ነው፡፡ ይሁንና የአክስዬን ማህበር አባላት ሃላፊነት የተወሰነ በመሆኑ የመክሰር ውጤት የሆነው የኩባንያው ገንዘብ ጠያቂዎች ልክ እንደ ሽርካ ማህበር አባላት ወደ ግል ሃብታቸው መሄድ አይችሉም፡፡ (ን/ህ/ቁ 310 እና 510) አንድ አክስዬን ማህበር ከሰረ የሚባለው እዳው ከኩባንያው ሃብት ሲበልጥ፣ የተቋቋመበትን የንግድ ስራ ማከናወን ሲሳነው ወይም በረጅም ጊዜም ቢሆን ሊወጣው ወደማይችል የኢኮኖሚ ቀውስ የገባ ሲሆን ነው፡፡ በአባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ መሆንና የኩባንያው ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው መሆን የኩባንያው መክሰር ውጤት ወደ አክስዬን ማህበሩ አባላት የግል ንብረት በገንዘብ ጠያቂነት ክስ ማቅረብ አይቻልም ማለት ግን አባላቱ ያልከፈሉት የአክስዬን ዋጋ ካለ አይጠየቁም ማለት እንዳልሆነና አባላቱ ከኩባንያው የሚጠይቁት የግል ገንዘብ ካለ እንደማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ የኩባንያው ሃብት ለእዳ መክፈያነት ሲውል እንዳይጠይቁ የሚከለክል አሰራር አለ ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ የአክስዬን ማህበሩ መክሰር በዳሬክተሮች የግል ሃብት ላይ የሚያስከትልም ሃላፊነት የለም፡፡ ሆኖም ግን የኩባንያው ወኪሎች እንደመሆናቸው መጠን የፈፀሙት የአሰራር ጉድለት ወይም ጥፋት ካለ ግን ተጠያቂ የማይሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ (ን/ህ/ቁ 364-366) የአንድ አክስዬን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዳሬክተር በማህበሩ ስም ለራሱ ጥቅም ሲሰራ ከቆየና ማህበሩ መክሰሩ ፍ/ቤት ካስታወቀ እርሱም አብሮ መክሰሩ እንደተፈረደበት ሊታሰብ ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 1060(1) ስለዚህ ጠቅለል ባለመልኩ ስንመለከተው የአክስዬን ማህበር መክሰር የአባላቱን መክሰር እንደማያስከትልና ክስ የሚቀርብ ከሆነም በንግድ ማህበሩ ላይ እንጂ በአባላቱ የግል ሃብት ላይ ክስ ማቅረብ እንደማይቻልና በአባላቱ ላይ ክስ ሊቀርብበት የሚችል ሁኔታ የአባላት መዋጮውን ሳያዋጣ የቀረ ያልተከፈለ ገንዘብ ካለ ብቻ መሆኑንና ይህ የሚሆንበትም ምክንያት የአክስዬኑ ዋጋ የንግድ ማህበሩ ገንዘብ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

7.4.1. የክስዬን ማህበር ላይ የሚቀርብ ክስ

እንደ አሜሪካና እንግሊዝ ባሉ አገሮች የመክሰር ክስ የሚቀርበውና የሚታየው ራሱን ችሎ ለዚህ ጉዳይ ስልጣን በተሰጠው የመክሰር ፍ/ቤት ሲሆን በአገራችን ግን የኣክስዬን ማህበር ክስ የሚቀርበው ወደ መደበኛው የገንዘቡ መጠን ለማየት ስልጣን (Material jurisdiction) ወዳለው ፍ/ቤት ነው፡፡ የመክሰር ክስ የሚቀርበው በኩባንያው አንጥሮ ሃብት (assets) ላይ ሲሆን ገንዘብ ጠያቂዎች የሚያቀርቡት ክስ የኣክስዬን ማህበሩ ሃብትና የዚህ ሃብት ፍሬ ተለይቶ እንዲታወቅና በገንዘብ ጠያቂዎች መካከል እንዲከፋፈል እንዲደረግላቸው ነው፡፡

የመክሰር ውሳኔ እንዲሰጥ በን/ህ/ቁ 975 መሰረት ክስ ማቅረብ የሚችሉት ባለእዳው (debtor) ወይም ኣንድና ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች (Creditors) ናቸው፡፡ በባለእዳ የሚቀርብ የከሰሯል ውሳኔ ይሰጥልኝ ጥያቄ የሚቀርበው በገዛ ፈቃዱ (Voluntary Proceeding) ሲሆን በምክንያትነት የሚገልፀውም እዳየን መክፈል ኣልቻልኩም የሚል ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ክስ የሚቀርበው በዳሬክተሮች ሲሆን ይህንን ስልጣን የሚያገኙትም በን/ህ/ቁ 362(ሰ) ነው፡፡ አንድ ኣክስዬን ማህበር ከሰረ ለማለት በን/ህ/ቁ 969 እና 971 መሰረት ዕዳውን ለመክፈል ያልቻለ መሆኑን የሚያሳዩ ነገሮች መኖር ያለባቸው ሲሆን ፍ/ቤትም ከሰሯል የሚል ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እነዚህን ሁኔታዎች ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት አንድ ዕዳውን መክፈል ያለቻለ ነጋዴ ይህን በማስመልከት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት ማስተወቅ ይጠበቅበታል፡፡ (ን/ህ/ቁ 972 እና 973 (1) የዕዳ ሳይከፈል ማራዘም ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ኣባላቱ አንድን ሰው በመወከል ወይም የኣክስዬን ማህበሩ ሂሳብ በማጣራት (Liquidation) ሂደት ካለ አጣረው በን/ህ/ቁ 1156 መሰረት ለፍ/ቤት ማሳወቅ ይችላል፡፡ በኣክስዬን ማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የሚቀርብ ክስ ወይም የዕዳ የመክፈል ሂደት መራዘም ን/ህ/ቁ 975(ለ) መሰረት ያደረገ ሲሆን ኣቅራቢዎቹ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ገንዘብ ጠያቂዎች ያላቸውን መበት በገንዘብ በመጥቀስ ፍ/ብ/ሰ//ህ/ቁ 226(1) በሚያዘው መሰረት ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ይህን ማድረግ የሚችሉት የሚጠይቁት ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ የደረሰ (debts due) ሲሆን ወይም በን/ህ/ቁ 971 መሰረት ባለእዳው ዕዳውን ለመክፈል የማይችል መሆኑ አስቀድመው ካወቁ የመክፈያ ጊዜውን መጠበቅ ሳያስፈልጋቸው ሁኔታው መኖሩን ማረጋገጥ ከቻሉ ክስ ከማቅረብ የሚያግዳቸው ነገር የለም፡፡ የመክሰር ውሳኔ ይሰጥልንና የኣክስዬን ማህበሩ ንብረት ተጣርቶ ለእዳ መክፈያ እንዲውል ይወሰንልን ክስ ከተመሰረተ በኃላ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በጣልቃ ገብነት ገብተው ሊከራከሩ የሚችሉ ሲሆን እነዚህ ገንዘብ ጠያቂዎች ከመጀመርያውም ክሳቸውን ኣጣምረው እንዳያቀርቡ የሚከለክላቸው ነገር የለም፡፡

7.4.2. የመክሰር ጉዳይን መዳኘትና መፍረድ

ፍ/ቤት የመክሰር ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የኣክስዬን ማህበሩ በእርግጠኛነት ዕዳውን ለመክፈል ያልቻለ መሆኑን ማረጋገጥ ኣለበት፡፡ አክስዬን ማህበሩ ዕዳውን መክፈል ባለመቻሉ ጊዜውን ያስተላለፈ (suspension of payment) ካለና ይህ በእርግጠኛነት

መክፈል ያልቻለው ጥሪት ስለሌለው መሆኑ የሚያስረዱ ሁኔታዎች መኖራቸው ከተረጋገጠ ከሰሯል የሚል ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የመክሰር ውሳኔ እንዲሰጥለት ያመለከተ ባለዕዳም ሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች አክስዬን ማህበሩ የከሰረ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀው በአመልካቶች ላይ ነው፡፡ የማስረጃ የመስማቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኃላ ፍ/ቤቱ ከሰሯል የሚል ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ሂደቱ የሚመራው በን/ህ/ቁ 976 እና 977 ይሆናል፡፡
መክፈሉ ከተቋረጠበት ቀን ጀመሮ የፍርድ ማስታወቅያ በተሰጠበት ቀን መካከል ባሉ 15 ቀናት ውስጥ ባለዕዳው በን/ህ/ቁ 1029 የተዘረዘሩትን ተግባራት ሰርቶ ቢገኝ እነዚህ ድርጊቶች በህግ ፊት የሚፀኑ ተግባራት ተደርገው ስለሚወሰዱ ህግ በአንድ በኩል የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ሲያስጠብቅ በሌላ በኩል ህጋዊ ባልሆነ መንገድ መብት ገንዘባችን አገኘን ብለው ለሚያስቡ ገንዘብ ጠያቂዎችም ሆነ ከአክስዬን ማህበሩ ዳሬክተሮች በመመሳጠር ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ገንዘባቸውን በማስመለስ ሂደት ላለስፈላጊ ወጪ እንዳይደረጉ ጥበቃ የሚሰጥ ነው፡፡ የዚህ ፍርድ ህጋዊ ውጤትም በባለ ዕዳው ላይ ከሰሯል የሚል ማንነት(status) መስጠት ነው፡፡ ከፍርድ በኃላ የአክስዬን ማህበሩን ንብረት (assets) የሚያስተዳድሩ ኮሚሽነር ወይም የከሰረው ሰው ንብረት ጠባቂዎች (trustees) በማድረግ ከፍርድ በፊት የነበረን ንብረት ሆነ ከፍርድ በኃላ የሚመጡ የማህበሩ ገንዘብም ሆነ ንብረት በማህበሩ አስተዳደሪዎች እንዳይስተዳደር ያደርጋል፡፡ የአክስዬን ማህበሩ ንብረት ተጣርቶ ከተጠናቀቀ በኃላ ለገንዘብ ጠያቂዎች የሚከፋፈልበት ስርዓት መሰረት የሚያደርገው የገንዘብ ጠያቂዎች ማንነት ይወስነዋል፡፡ ይሄውም የገንዘብ ጠያቂዎች (secured creditors)

- ዋስትና ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች እንደ የማየነቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል (Mortgage)፣ የሚንሰሳቀስ ንብረት ዋስተና (pledge) ወይም ሊን (lien) መብት ያላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች ሲሆኑ
- ዋስትና ያልተሰጣቸው ገንዘብ ጠያቂዎች (unsecured creditors) የዚህ ዓይነት ገንዘብ ጠያቂዎች ማንኛውም ዓይነት ንብረት በባለ እዳው ያለተሰጣቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ናቸው፡፡
- የበለጠ መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች (preferential creditors) የዚህ ዓይነት ገንዘብ ጠያቂዎች ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች የቀደምትነት መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት ፍ/ቤት የሚሰጠው የመክሰር ፍርድ (Bankruptcy Judgment) በነዚህ የተለያየ ማንነት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ገንዘብ ጠያቂው ዋስትና የተሰጠው ከሆነና አክስዬን ማህበሩ በፍ/ቤት የመክሰር ፍርድ ከተሰጠ የዕዳው መክፈያ ጊዜው ባይደርስም ፍርዱ እንደተሰጠ የዕዳው የመክፈያ ጊዜው እንደደረሰ ተቆጥሮ በዋስትና የያዘውን ንብረት ይወስዳል፡፡ ለምሳሌ ባንክ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 97/98 መሰረት በመብቱ ይሰራበታል፡፡ ግለሰብ ከሆነም እንደዚሁ ዋስትናውን የያዘው ዕዳው ለመከፈሉ ዋስ እንዲሆነው እስከሆነ ድረስ በመብቱ ይሰራበታል ማለት ነው፡፡ የመክሰር ፍርድ ዋስትና

ባልተሰጠው ገንዘብ ጠያቂ (unsecured creditor) ላይ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ዋስትናያልተሰጣቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ፍርድ እንደተሰጠ በአንድነት ክሳቸውን ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ሳያደርጉ ጊዜ የወሰደ ዋስትና ያልተሰጠው ገንዘብ ጠያቂ እስከወድያኛው ገንዘቡን የማያገኝበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

የመክሰር ፍርድ በተሰጠበት ወቅት የቀደምትነት መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚኖረው መብት ቅድሚያ ገንዘቡን የማግኘት መብት ነው፡፡ ይሄውም የመክሰር ፍርድ ተሰጠ ማለት ለዚህ ገንዘብ ጠያቂ ኣፈፃፀም ፋይል ተከፍቶ የንብረት ክፍፍል ሲዳረግ የሚኖረው መብቱ በዚህም ሁኔታ ሊሰራበት ይችላል ማለት ነው፡፡ ገንዘብ ጠያቂዎች በኣክስዬን ማህበሩ ያላቸውን መብት የማስረዳት የነርሱ እንደመሆኑ መጠን ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀውና የሚገዛው በን/ህ/ቁ 1041 መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ የመክሰር ፍርድ በተለያዩ ገንዘብ ጠያቂዎች የራሱ የሆነ ህጋዊ ውጤት ያለው ሲሆን ዋናው ቁምነገሩ ደግሞ የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት በማስጠበቅ የንግድ ግንኙነቱን ስርዓት ባለው መንገድ በማስኬድ ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር ማስቻልና ከዘርፉ በሚገኝ የልማት ውጤት ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

የመወያያ ነጥቦች

1. ን/ህ/ቁ 968(1) “የዚህ መፅሓፍ ድንጋጌዎች በዚህ ህግ አንደኛ መፅሓፍ በቁጥር 5 መሰረት ነጋዴ በሆኑ ሰዎችና በዚህ ህግ አንደኛ መፅሓፍ በቁጥር 10 መሰረት የአሸሙር ማህበሮች ከሆኑት በቀር በንግድ ማህበሮች ሁሉ ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡” ሲል በመደንገጉ በተራ ሽርካ ማህበር ላይ የመክሰር ፍርድ (Bankruptcy judgment) ሊሰጥ ይቻላል ማለት ነውን?
2. የን/ህ/ቁ 1155(1) አባባል በማንኛውም በማጣራት ላይ ያለ ሽርካ ማህበር ተፈፃሚነት ሊኖረው ይችላል ማለት ነውን? ለምን?
3. ን/ህ/ቁ 1155(3) በህግ የሌለ ግን ደግሞ በሐሳብ (factually) ያለን የንግድ ማህበር ከስሯል የሚል ፍርድ ሊሰጥበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ያልተወለደ እንደማይሞት እየታወቀ እንዲህ ሲል የመደንገጉ እንድምታ ምንድን ነው?
4. ሃላፊነታቸው ባልተወሰነ የሽርካ ማህበር አባላት መካከል ከዋናው ባለዕዳ ጋር ተከራክር (benefit of discussion) ሊነሳ ይችላልን? ለምን?
5. የአንድ የሽርካ ማህበር መክሰር የማህበሩን መክሰር የሚያስከትለው ለምንድን ነው?
6. የይግባኝ መብት የማይፈቅደው ን/ህ/ቁ 987 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 20(6) አንፃር ሲታይ በአንቀፅ 9(1) መሰረት ተቀባይነት የሌለው ድንጋጌ ነው ሊባል ይችላልን?
7. መክሰርን የማስታወቅ ፍርድ በባለ ዕዳው ላይ የሚኖራቸው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው?
8. የመክሰር ንብረት አስተዳዳሪዎች ተግባርና ሃላፊነቶች ምንድን ናቸው? ያላቸው መብትስ?
9. በመፋለም የመጠየቅ መብቶች መሰረቶች ምንድን ናቸው?
10. የመክሰርን ስራን የሚያስፈፅሙ ሰዎች ሃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

ማጠቃለያ

የአገራችን የንግድ ስርዓት ከዓለም የንግድ ስርዓት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ ኋላ ቀር ቢሆንም ይህን ዘርፍ ዘመናዊ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ይህን ስርዓት ባለው መንገድ ለማስኬድና በአገራችን የተነደፉ የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከግብ ለማድረስ ያስችላሉ የተባሉ ከንግድ ህጉ በተጨማሪ በርካታ ህጎች ወጥተው በስራ ላይ እንዲውሉም ተደርጓል፡፡ ሰልጣኞች ይህን ሞጁል በመነሻነት ተጠቅመው በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙርያ ያላቸው እውቀት፣ ክህሎትና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የማስፋቱ ሂደት እንደተጠበቀ በስልጠናው ያገኙትን የአስተሳሰብ ለውጥ በስራ ላይ በማዋልና የህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በነጋዴው ማህበረሰብም ሆነ በሸማቹ ህብረተሰብ አመኔታ እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ የሁሉም ዜጎች መሆኑን በመገንዘብ ሙያዊና ዜግነታዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች ይህን በበርካታ ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ በመነሻነት እንዲያገለግል የተዘጋጀን ሞጁል ይዘቱን ለማወቅም ሆነ የመወያያ ጥያቄዎችን በሚገባ በማጤን የእውቀት፣ ክህሎትና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አድማሳቸው ለማስፋት በላቀ ተነሳሽነት ሊሰሩና እራሳቸው ማነፅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ሲናደርግ ነው የህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ የፍትህ ለሰላም፣ ልማትና መልካም አስተዳደር ባለሙያ መሆን የምንችለው፡፡ በመሆኑም በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግምባታ ሂደቱ ፍትህ በተገቢው መንገድ በመስጠት ህዝባዊ ተአማኒነት ለማግኘት አበክረን ልንሰራ ይገባል፡፡

አመሰግናለሁ!!

ማገናዘቢያዎች (References)

1. ሕጎች (Laws)

- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ኣዋጅ ቁጥር 1/1987
- የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ኣዋጅ ቁጥር 166/1952
- የኢትዮጵያ ባህር ሕግ 137/1953
- የኢትዮጵያ ፍታብሄር ሕግ በተለየ የወጣ ቁጥር 165/1952
- የኢትዮጵያ ፍታብሄር ስነ-ስርዓት ድንጋጌ ቁጥር 52/1958
- የወንጀል ሕግ ኣዋጅ ቁጥር 410/1997
- የፈጠራ፣ ኣነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪ ንድፍ ኣዋጅ ቁጥር 123/1987
- የንግድ ፈቃድ ምዝገባና ጥበቃ ኣዋጅ ቁጥር 501/1998
- የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ኣዋጅ ቁጥር 410/1996
- የንግድ ኣሰራር ኣዋጅ ቁጥር 329/1995
- ስለ የንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣ ኣዋጅ ቁጥር 98/1990
- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ኣዋጅ ቁጥር 67/1989 እና ማሻሻያ ኣዋጅ ቁጥር171/1991፣328/1995 እና376/1996
- በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ ኣዋጅ ቁጥር 97/1990 እና ማሻሻያው 126/1991
- ትራንስፖርትን ስለመቆጣጠር የወጣ ኣዋጅ ቁጥር 468/1997
- የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር 1/1996
- ስለባንክ ስራ የወጣ ኣዋጅ ቁጥር 592/2000
- የመንግስት ልማት ድርጅቶች ኣዋጅ ቁጥር 25/1992
- የመርከብ ምዝገባ ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቆጥር 1/1996

2. መፃህፍት (Books)

1. Arun Kumar sen and Jitendra Kumar mitra, ***Commercial Law***, (including company law), The world press private Limited, Reprinted 1998.
2. Colinvaux Raul, ***The Law of Insurance***, London, sweet and Maxwell, 5th ed.,1984.
3. Hailu Zeleke, ***Insurance in Ethiopia***, Historical Development, present status and future challenges, Master printing press, 2007
4. Harka Haroye, ***Competition policy and Law***, Mizan Law review,2008

5. Ivamy E.R.Hardy, ***General Principles of Insurance Law***, London, Butter worths, 6th ed., 1986.
6. Jain D.P, ***Company law***, Koare publishers, PVT LTD, Revised ed., 2004.
7. Keeton Robert E. and Widiss ALan I, ***Insurance Law***, St. Paul, Minn, West publisheing Co.1988.
8. MC Kuchhal, ***Business Law***, Vikas Publishing House PVT LTD, 4th ed., 2005.
9. Raoul Colinvaux, ***The Law of Insurance***, London,Sweet and Maxwell,5th ed.1984
10. Singh Avtar***, Law of Insurance***, East Book Company, Lucknow, India, 2004.
11. Singh Avtar, ***Introduction to Negotiable Instruments***, East Book Company, Lucknow, India, 2002.
12. Taddese Lencho, ***Ethiopian Bankruptcy Law***, A commentary (part I)
13. Vance William R., Hand Book on the Law of insurance, Sc.Paul.Minn, west publishing company, 3rd ed. 1951.
14. WE Astle, ***Bill of Lading Law***, Fair play Publications, 1982.
15. Wilson John F., ***Carriage of goods by sea***, Parson Longman, 4th ed., 2001.
16. Win ship Peter, ***Background Documents of the Ethiopian Commercial code of 1966***, Addis Ababa University (Published) 1996.

3. International Conventions

1. Convention for the unification of certain Rules Relating to international carriage by Air. Signed at Warsaw on 12 October 1929.
2. Convention for unification of certain Rules for International carriage by Air, Mont real, 28 May 1999.
3. Protocol to amend the Convention for the unification of certain Rules relating to International carriage by Air, signed at Warsaw on 12 October 1929, done at the Hague on 28 September, 1955.
4. Protocol to amend the convention for the unification of certain Rules Relating to International carriage by Air signed at Warsaw on 12 October 1929. As a mended by the protocol done by the Hague on 28 September 1955, signed at Guatemala city, on 8 March 1971.
5. International convention for the unification of certain Rules of law relating to Bill of Lading signed at Brussels, on 25 August 1924.

6. The Hague Visibly Rules, The Hague Rules as amended by Brussels protocol 1968.
7. The United Nations convention on the carriage of Goods by sea. 1978 (The Hamburg Rules)

4. Insurance Policies

1. Commercial Vehicle Policy issued by Nile Insurance Company (S.C)
2. Burglary and Housebreaking policy issued by Ethiopian Insurance corporation
3. Life Insurance policy issued by Ethiopian Insurance Corporation
4. Illness, diseases and bodily injury policy issued by Ethiopian Insurance Corporation

5. ጥናታዊ ፅሑፎች (Research Papers)

1. Berhane Assefa, ***The Discrepancy of Insurance policies with the 1960 Ethiopian commercial law***, LL.M Dissertation, Amsterdam University, 2007. (Unpublished)
2. Berhane Assefa, ***The International Air carrier Liability Regime under the Warsaw and Montreal conventions,*** LL.M, Term paper, Amsterdam University, 2005, (Unpublished)
3. Gebru Zenebe, ***Carriers Liability under contract of carriage supported by a Bill of Lading, The Ethiopian Law and practice***, LL.M Dissertation, Amsterdam University, 2007 (Unpublished)
4. አሕመድ ጀማል በኢንሹራንስ ላይ ለዳኞች ስልጠና ፕሮግራም የተዘጋጀ ፅሑፍ 19993 ዓ/ም
5. ብርሃነ አሰፋ በባንክ ህጎችና ፎርክሎዠር ለዳኞች ስልጠና ፕሮግራም የተዘጋጀ ፅሑፍ 1993 ዓ/ም
6. ብርሃነ አሰፋ በሚተላለፉ የገንዘበ ሰነዶች ለጋምቤላ ክልል ዳኞችና ዓ/ህጎች ስልጠና የተዘጋጀ ፅሑፍ 1998 ዓ/ም
7. ጥላሁን ተሾመ ለዳኞች ስልጠና ፕሮግራም በኢንሹራንስና የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ላይ የተዘጋጀ አጭር ፅሑፍ 1993 ዓ/ም

6. **የፍ/ቤት ጉዳዬች**

1. አቶ ጥጋቡ አንበርብር V. ኢትዮጵያ መድን ድርጅት (ፍ/ይግ/መ/ቁ 47/87)

2. አቶ እሸቱ አስፋው V. የኢትዮጵያ ብሄራዊ የኢንሹራንስ ኩባንያ ፍ/ይግ/መ/ቁ 4452)
3. ሆርን ኢንተርናሽናል ባንክ V. ብሄራዊ ባንክ ፌ/ክ/ፍ/ቤ (ፍ/መ/ቁ 58/92)
4. ዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያ V. ብሄራዊ ባንክ (ፍ/መ/ቁ 812/88)
5. ጣሂር ሐጂ እና አቶ ዓብደል መልክ (ፍ/መ/ቁ 2869/87)
6. አልፋ የጉዞ ወኪል V. አባላቱ (ፍ/መ/ቁ 97/90)
7. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. ከድር ዓለም አቀፍና አባላቱ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፍ/መ/ቁ 70/89
8. ህብረት ኢንሹራንስ V. የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት (ፍ/መ/ቁ 323051)
9. ሳሊኒ ሌክስ Joint Venture V. አዋሽ ኢንራንስ (ሰ/መ/ቁ 23703/99)
10. ህብረት ኢንሹራንስ V. የኢትዮጲያ መርከብ ድርጅት(ፍ/ብ/መ/ቁ 32305)

7. ድህረ ገፅ (website)

- Copy rights, Wikipedia, the free encyclopedia, 2008
- (http://en.Wikipedia.org/w/index.php?title=Copyright and printable=yes)
- Industrial Design Rights, Wikipedia, the free Encyclopedia,2008
- (http://en.Wikipedia.org/w/index.php? Title=Industrial design and printable +yes)
- Patent, Wikipedia, the free Encyclopedia 2008.
- (http://en.Wikipedia.org/w/index.php? Title + patent and printable =yes)
- Trade Mark, Wikipedia, the free Encyclopedia, 2008 (http://en.Wikipedia.org/w/index.php? Title=Trademark and printable =yes)